
# አንድ እረኛ አንድ መንጋ

From the Library of
STEPHEN J. STRAUSS

ከ (ቀደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ደረሰ

ከሁሉም ሁሉን ይወቅ የሚቀጥል፤ ክርስቲያን እርስ በርሱ የሚጣላበትን ምክንያት የሚገልጥና ልዩነቱን ለማስወገድ የሚሞክር።

መስከረም 1989 ዓ.ም.





ደራሲው በ35 ዓመቱ ።



ደራሲው በ74 ዓመቱ ።

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነት እግዚአብሔርን እንዳመልክ፥ እውነትን እንድከተል፥ ችግርን ሸሽቼ፥ ወደ ስርብትና ተጠግቼ ፈጣሪዬን እንዳላስቀይም እስተምረው ለአሳደጉኝ ወላጆቼ መሪጌታ፥ ቄስ ምገስ ደረሶ፥ (ወልደ ማርያም) እማሆይ ወርቅነሽ ደስታ (ወለተ ማርያም) ነው።

<u>ለዚህ መጽሐፍ አንባቢ አጠቃላይ ምክር ወይም መመሪያ</u>

ብዙ ሰዎች ለፖለቲካ ጥቅም ሲሉ በሃይማኖትና በተማረው ታማኙ ላይ ይቀሻሉ፥ ይህ መጽሐፍ ግን ከምን ይሉኝና ከስርብትና ነጻ ስለሆነ ብትወድ አንበህ እውነትን አስተውልበት፣ ከዚህ በፊት የበማሁትን ውሸትም ይሁን ተረት ያጽድቅልኝ፥ እኔንም ቅዱስ ይበሉኝ የምትል እንደሆነ ግን ከወዲሁ ራስህን መርምር፥ ያለበለዚያ ግን 4 ነገር፣ ገንዘብህን፥ ጊዜህን፥ እውቀህን፥ ዐይንህን በከንቱ ታፈዛለህ። ታሪክን እውነትነቱን መርምረህ እንጂ በጊዜው ወይም በነገርህ ሰው ምክንያት አትመነው፣ አትቀበለው። <u>በጊዜ፥ በፊት፥</u> ከሁሉ በፊት የነበረ ሃይማኖት አረመኔነት ነው፣ አሉ የኖረ ነው። በፊት የመጣ ሁሉ እውነተኛ ሃይማኖት አለመሆኑን ያስረዳል። <u>በኋላ ደግሞ፥</u> ከክርስቶስ በኋላ የመጡ ብዙ የውሸት ሃይማኖት ድርጅቶች አሉና በኋላ መምጣትም የሐቀኛ ምልክት አይደለም ውሸታምና እውነተኛ በጊዜ አመጣጥ ሲለዩ አይቻልምና በፊት የበማሁት ነው እውነት ብለህ፥ አትማበቅ። ለምን ብትል፥ በእኛ ዘመን እንኳ

ሀ/ ፀሐይ ትዞራለች፥

ለ/ አእርጥባን የሚበረው ጋኔን፥ ጥቁር ሰው (ወይም) ባሪያ ታርዶ ለት ነው ይዞት የሚሄደው፥

ሐ/ መኪና አሑድ ቅዳሜ በአየመንገዱ የሚበዛው ሰንበትን ለማሻር ጋኔን እያሽከረከረው ነው እየተባለ ይወራ ነበር። ከዚህ እምነቴ ፍንከች አልልም ብለው እስኪሞቱ ድረስ የቆዩ ብዙዎች ናቸው።

መ/ ሃይማኖት በእግዚአብሔር መንፈስ በተጻፉ መጻሕፍት የተገለጠ አምላካዊ ክሥተት እንጂ በዘር የሚወረስ ርስት፥ በመመራመር የሚገኝ ፍልስፍና አይደለምና፥ መጻሕፍትን አንብበህ፣ ሊቃውንትን ጠይቀህ ሃይማኖትህን ተረዳ እንጂ፥ በዘርህ አትኩራ፥ በፍልስፍናህ አትምቦጥረር።

ሠ/ ትልቅ ሰው ስለነገርህም አትመን፥ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ የምድራዊ ትልቅነት የሚገኘው በውሸት ስርብትና ነውና። ስለዚህ

ውድ አንባቢ ሆይ! አንድ ነገር በፊት ስለበማሸው እውነት አይሆንም ሌላው ደግሞ በኋላ ስለመጣ ውሸት አይደለም። ውሸት ወይም እውነት የሚያሰኘው እውነተኛ ጠባዩ ነው እንጂ ዘመኑ አይደለም። ስለዚህ ከዚህ በፊት የያዝሁትን አልለቅም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንም፣ አላጠናም፣ አልመረምርም የምትል ከሆነ፣ ከልማድህ ጋራ ተጣብቀህ እውነትን ሳታውቅ እንደምትሞት የተረጋገጠ ነው።

ደራሲው ይህን ምክር የሚያቀርብልህ መጽሐፉን የጻፈበት ዓላማ

አንበቢን ለመጥቀም እንጂ ለምድራዊ ትርፍ አይደለምና ነው። በሃይማኖት ብዙ ትሩፋትና ታምራት ይሠራሉ፤ ተሠርተዋል፤ ለምሳሌ በጥንተ ተፈጥሮ ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር የመጣው በተአምር ነው። ጌታችን በተዘጋ ቤት የገባው፣ በባሕር ላይ የሄደው በተአምር ነው። የቃናው ውሃ ወይን የሆነው፣ አለአዛር ከሞተ በኋላ የተነሣው በተአምር ነው። ግን በዚህ ቀዳዳ መግቢያ ብዙ ተረቶች ተጽፈዋልና ከመቀበልህ በፊት አስተውል።

ረ/ ሀገርህን፣ ባህልህን፣ ሃይማኖትህን የሚነቅፍ ሰው ሲያጋጥምህ ተቆጥተህ መልስ ከመስጠትህ በፊት በነገሩ ተመራመር።

ሰ/ የያዝኸው ሃይማኖት ተረት መሳይ ከሆነ ግን አሽቀንጥረህ ለመጣል አትጠራጠር።

ቀ/ ቅዱሳት መጻሕፍትን የምትቀበል ከሆንህ ግን የሃይማኖትህ ችግር ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በሁሉን ሁሉን ይወቅ፣ በዚህ መጽሐፍ በደምብ ተብራርቶልሃልና ሌላ አወናባጅ አያስፈልግህም፤ አሜን።

<u>ከመቅድሙ በፊት የሚጠቀሱ፤</u>

(ፊል: 2፤ 2-5) በአንድ ሐሳብ ተስማሙ። አንድ ፍቅር፣ አንድ ልብ፣ አንድም ሐሳብ ይኑራቸው። ለወገን ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ አንድ እንኳን አታድርጉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንደሚበልጥ በትሕትና ይቁጠር። እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፤ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ። (ብዙ ክርስቲያኖች ይህን መልእክት ቢረዱ ኑሮ መለያየት አይኖርም ነበር)። (ሮሜ: 16: 17-18) ነገር ግን ወንድሞቼ ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና መሰናከል የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ (ከሚያደርጉት ሰዎች እንድትጠነቀቁ) እለምናችኋለሁ። ከእነሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ። እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለእየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፤ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌላቸውን ሰዎች ያታልላሉ። ለዚህ ተጨማሪ፣ (2ቆሮ.11:13፤ ኤፌ. 4:14፤ 2ጢሞ. 3:13፤ ቲቶ.1:10 2ዮሐ.2:7-11) ጌታም ማቴ. 5:9 የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዜአብሔር ልጆች ይባላሉና ክርስቲያን ሁሉ ከማጣላት ማፋቀርን፣ ማስታረቅን መምረጥ አለበት። ክርስቲያን ቢፋቀሩ ይህን ጊዜ ዓለም በሞላ ክርስቲያን ነበር። (ኢሳ.5:20) ክፉውን መልካም መልካሙን ክፉ ለሚሉ፣ ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ፣ ጣፋጩን መራራ፣ መራራውን ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው።

## ማውጫ

ገጽ


| | |
|---|---|
| ማውጫ | 7 |
| ከመቅድም በፊት የሚጠቀሱ | 4 |
| መቅድም | 12 |
| መግቢያ | 16 |
| ምስጋናና ሂስ | 18 |
| ምዕራፍ አንድ | 19 |
| ምስጢረ ሥጋዌ፤ በልደት ሦስቱም ሥላሴ ተባብረዋል፤ | " |
| ምዕራፍ ሁለት | 23 |
| መቼና የት ነው የተዋሐደው? | " |
| ልደታትስ ስንት ናቸው? ለሚል ጠያቂ፤ | " |
| ምዕራፍ ሦስት | 24 |
| የካራ የቅባት፤ የጸጋ አጭር መግለጫ | " |
| ምዕራፍ አራት | 25 |
| የቅባት ዐይነቶች | " |
| መወድስ በአንተ ልደታቲሁ ለወልድ | 28 |
| ምዕራፍ አምስት | 30 |
| ቤተ ክርስቲያን | " |
| ቤተ ክርስቲያን አንድ ነበረች | " |
| የቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና ልዩነት በሹመት | " |
| ምዕራፍ ስድስት | 38 |
| ቤተ ክርስቲያንን ያለያዩአት አውጣኪስና ተከታዮቹ | " |
| ምዕራፍ ሰባት | 43 |
| የኬልቄደን ጉባኤ ተሳታፊዎችም እንደ እነዚህ ነበሩ | " |
| የጉባኤ ሊቃውንትና የአቡነ ጳውሎስ አምባጓሮ | " |
| በዚህ ርእስ የሊቃውንቱ ችሎታ ተገልጧል | " |
| ለዚህ ምዕራፍ የተነበቡ መጻሕፍት | 56 |
| ምዕራፍ ስምንት | 57 |
| ለሹመትና ክብር ሲሉ በትዕቢት የተለያዩ ክርስቲያን | " |
| ምዕራፍ ዘጠኝ | 58 |
| የክርስቲያን ስንደቅ ዓላማ ምንድር ነው? | " |
| ምዕራፍ ዐሥር | 60 |
| ማስታረቅና ማግለድ | " |

11. የቤተ ክርስቲያን ትምህርት 138
12. የዓለም ቤተ ክርስቲያን "
13. የክርስቶስ አካል አንድነት "
14. ጥምቀት 139
15. ቅዱስ ቁርባን "
16. መንፈሳዊ አገልግሎትና ተሰጥዎ "
17. ሀብተ ትንቢት "
18. የክርስቲያን ሕይወት 140
19. ሰንበት "
20. መጋቢነት (አስተዳዳሪነት) "
21. ክርስቲያናዊ ምግባር "
22. ጋብቻና ቤተሰብ 141
23. የክርስቶስ ሥራ በሰማያዊ መቅደስ "
24. ዳግም ምጽአት "
25. ሞትና ትንሣኤ 142
26. ከምጽአት በፊት የዘመነ ብፁዓንና የኀጢአት ፍጻሜ "
27. ሐዲሲቱ መሬት "
<u>ምዕራፍ ሃያ ሦስት</u> 143
1. የአደበንቲስቶች ኢክርስቲያናዊ ትምህርት "
ቀዳሚትና ሐዋርያት 145
2. ስለቀዳሚት ወይም ሰንበተ አይሁድ ትምህርት 147
ስለ ሥጋውና ደሙ 148
ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን "
ዘለዓለም ሕያውነት 151
3. መደምደሚያ 152
4. ሽው ዘላዓለማዊ ነው 154
Books consulted 155
<u>ምዕራፍ ሃያ አራት</u> 157
ሰባልሳውያንና አርዮሳውያን "
የስብከት ዘዴያቸው 166
የተጠቀሱ መጻሕፍት "

## አርእስት


| | |
|---|---|
| ምዕራፍ ሃያ አምስት | 167 |
| አርዮስ | ” |
| ምዕራፍ ሃያ ስድስት | 169 |
| በእየጊዜው የተነሡ መናፍቃን | ” |
| 1. ረበናተ አይሁድ | ” |
| 2. ናዝራውያን | 170 |
| 3. ኤቢዮሳውያን | ” |
| 4. ዶኪቲስታውያን | ” |
| 5. ግኖስቲስዝም | ” |
| 6. ሌው ግርኪዮን | 172 |
| 7. ሞንታኖስ | 173 |
| 8. አፅራረ ሥላሴ | 174 |
| 9. ፒላጊዮስ | ” |
| 10. አውሳብዮስ | 175 |
| 11. ኦርጌኒስ | ” |
| 12. አንቲፊቆግርያጦስ | 176 |
| 13. ሳዊሮስ | ” |
| 14. መንክዮስ | ” |
| 15. አፍትኪስ | ” |
| 16. አርስላን | 177 |
| 17. ፍላብያኖስ | ” |
| 18. ክርታርዮስ | ” |
| 19. ሰዱቃውያን | ” |
| 20. የተጠቀሱ መጻሕፍት | ” |
| ምዕራፍ ሃያ ሰባት | 178 |
| አጠቃላይ ምኞት | ” |
| መፍትሔ ቃላት | 182 |
| በጠቅላላ የተጠቀሱ የመጻሕፍት ዝርዝር | 184 |
| (መጀመሪያ ያግርኛ) | ” |
| Consulted Foreign Books | 186 |

<u>መቅድም</u>

ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው የዓለም መድኅኒት ወልደ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ እርስ በርሳችሁ እንድትፋቀሩ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንዳፈቅረኋችሁ፥ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ፤ እርስ በርሳችሁ ከተፋቀራችሁ፥ የኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ሁሉም ያውቃል። (ዮሐ.13:34) <u>ተፋቀሩ</u> የክርስቶስ አዲስ ትእዛዝ ናት። የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ (14:15) ትእዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያውለው ይወደኛል (21) የሚወደኝ ቃሌን ይጠብቃል፥ የማይወደኝ ግን ቃሌን (እርስበርሳችሁ ተፋቀሩን) አይጠብቅም። የኔ ትእዛዝ እኔ እንደወደድኋችሁ እናንተም ርእሰበርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው። (15:12) ከዚህ በላይ እንዳየነው የጌታችን ትእዛዝ ርእሰበርሳችሁ ተፋቀሩ፤ በዚህም ዓለም ያውቃችኋል ነው። ክርስቲያኖች ግን የዓለም አብያተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየውና እንደሚገልጥልን ከርደተ መንፈስ ቅዱስ ከጰራቅሊጦስ ጀምሮ እስካሁን ይፋጃሉ። ጀጀባውን ያኘው ቢላት ስለልክ አረፋውን ብላ እንደሰጠመችው ሴትዮ ተረት፤ ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ተፋቀሩ ካልኸንስ ስለልክህ ርእሰበርሳችን እንጋደላለን ብለው የሚፋጁ ይመስላሉ። ስለምን? ለምን? እንደምን? ወይንም በማን? ምክንያቱስ? ለሚል ጠያቂ ከሁሉም ሁሉን ይወቅ የተረፈው ዝርዝር ሁሉ በዚህ መጽሐፍ ተዘርዝሯልና አንባቢ ሆይ! በንቁሕ ኅሊና አንብበህ እንድታስተውለው አደራ ትባላለህ። ክርስቲያኖች የሚጣሉበት ሁሉ በሚከተሉት ምዕራፎች በግልጥ በሰፊው ተዘርዝሯል። ይህ መጽሐፍ የሁሉም ሁሉን ይወቅ ሁለተኛ መጽሐፍ ወይም ቅጽ ነው ለማለት ይቻላል። ከሁሉም ሁሉን ይወቅ በመጻፍ ምክንያት ብዙ ጥያቄና ገምቢ ሂስ ስለደረሰ የዚያ ማስተካከያ፥ ማሟያ፥ ማብራሪያ ይህ ተከትሏል ይህን መጽሐፍ ለመረዳት ሦስት መጻሕፍት፤

1. ሁሉም ሁሉን ይወቅ፥
2. መጽሐፍ ቅዱስ፥
3. ይህ ራሱ ያስፈልጋሉ።

እያንዳንዱ የሃይማኖት ድርጅት ወይም ቤተ ክርስቲያን አዕማደ ምስጢር በሁሉም ሁሉን ይወቅ የታወቀ ካልሆነ በቀር በዝርዝር ይሰማል። በዚያኛው መጽሐፍ የተብራራ ከሆነ ግን ተጠቅሶ ይታለፋል። የደራሲው እምነት በሁሉም ሁሉን ይወቅ የተዘረዘረው ነው። በዚህ ግን እገሌ ወይም

እንዲህ ያለው የሃይማኖት ድርጅት እንዲህ ይላል እያለ በንጽጽር (በማነጻጸር) ያሳያል እንጂ የደራሲውን እምነት አይናገርም። ስለዚህ በዚህ የዓለማየሁ እምነት እንዲህ ነበር፥ ነው ሊባል አይቻልም፥ ከዚህ መጽሐፍ የተነገረውን አንድ ምዕራፍ ይዞ፣ ለምሳሌ ስለ ምስጢረ ሥጋዌ ብዙ የተለያዩ አስተያየቶች ተጽፈዋል፣ ከእነዚያ አንዱን ደራሲው ይከተላል ማለት ከግምት አልፎ የሚያሳየው ነገር የለም።

ለዚህ መጽሐፍ የሚከተሉት አርእስት በማግረጥ ቀርበውለት ነበር፣

ሀ/ ክርስቲያን እርስ በርሱ ለምን ይሳደዳል?

ለ/ ክርስቲያን አንዱ ሌላውን ለምን ይገላል?

ሐ/ ክርስቲያን ወንድሙን ገድሎ ጠላቱን ለምን ይረዳል?

መ/ ክርስቲያን በሐሰት የወንድሙን ስም ለምን ያጠፋል?

ሠ/ የክርስቲያን መስተሳልም

ረ/ የክርስቲያን መስተፋቅር

ሰ/ አንድ እረኛ፥ አንድ መንጋ

ከሀ እስከ ረ ያሉት አርእስት ሁሉ ለዚህ መጽሐፍ ይስማማሉ። ሁሉም እንደሚያሳዩት ክርስትና ከተመሠረተችበት ቀን ከጰራቅሊጦስ ጀምሮ ለዘለዓለም ክርስቲያን ሲጋደል እርስ በርሱ ሲፋጅ ኑሯል፣ አሁንም ለሹመት፣ ለፍቅረ ንዋይ፥ ለትዕቢት ሲል ለብዙ ዘመን በዚህ የሚቀጥል ይመስላል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተገልጦ እንደምናየው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን፣ የእንጸኪያ፣ የአርመን፣ የግሪክ፣ የካቶሊክ፣ የአንግሊካን እብያተ ክርስቲያን፣ ከወንጌላውያንም (ፕሮቴስታንት) ጥምተትንና ሥርዓተ ቁርባንን የሚቀበሉ አንዱ የሌላውን ስም በፈጠራ ወሬ ከማጥፋት ይልቅ ልዩነታቸውን ተነጋግረው ቢገናኙ በጣም ጥሩ ነበር።

ርግጥ ሃይማኖት ስለፍቅር አይለወጥም፣ ለሹመት ለክብር ለገንዘብ ተብሎ ግን የሌለ ነገር ፈጥሮ እያወሩ ከሃይማኖት ወንድም ጋር እያጣሉም፣ አያስያይም። በመካከለኛው ዘመንና በመካከለኛው ምሥራቅ ይደረግ እንደነበረው ለሹመት ብሎ ሰላምን እየመሩ፣ ከሰላም ጋር ሁኖ ክርስቲያንን እያቀጋም፣ በሀገራችንና በዘመናችንም ከአረሚ መንግሥት ጋር ሁኖ በአባቱ ላይ ውሸት አመላልሶ ንጽሑን አባት እያስገድልም። ስለዚህ ከሀ እስከ መ ያሉት አርእስት ሁሉም መጋደልን መጣፋትን ስለሚያሳዩ በሠና በረ የተገሩት አርእስት ተመረጡ። ከእነሱም መስተሳልም

የሚለው ቃል ለተራ አንባቢ ትንሽ ራቅ ስለሚል፣ የክርስቲያን መስተፋቅር ተመረጠ። ሰውን ሲወዱ ከነንፍጡ የሚለው ተረት ዘመኑ አልፏል፣ ዘመናችን የሳይንስና የጽዳት ዘመን ስለሆነ ለመቃረብ፣ ለመሳሳም፣ ለመዋደድ፣ ወደ ሰው ከመጠጋት በፊት የፊትን አድፍ መክላት፣ ቆሻሻን ማጽዳት ያስፈልጋል። እንደዚሁም ከሌላው የሃይማኖት ድርጅት ለመገናኘት እያንዳንዱ የሃይማኖት ድርጅት ሌላውን ከመንቀፍ በፊት መጀመሪያ በራሱ ማኅበር ውስጥ ያለውን ከቅዱሳት መጻሕፍት ያልተገለጠ ጊዜ ወይም የታሪክ ሂደት ያመጣውን ጉድለት መተው አለበት። እንደዚሁም በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረውን ደግሞ እጣም አለመተርጎም ወይም እኛ እንደዚህ አንልም ብሎ አለመደርገም፣ ለምሳሌ የሮም ቤተ ክርስቲያን ከተገናኘን ዘሥረፀ እምአብ ወእምወልድ ብላ በጸሎተ ሃይማኖት በ9ኛው መቶ ዘመን የጨመረችውን ወእምወልድ (ከልጅም) የሚለውንና ሥርዓተ ቁርባንን እናገናኝ እንጂ እነማለሁ፣ ሥርዓተ ቁርባንንም አስማማለሁ ብላለች። ስለ ክርስቶስ ባሕሪያትም እንነጋገር ብላለች። ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሉት በሃይማኖት ከተስማማን፥ ሥርዓት አያጣላም፣ በሥርዓት የሚጣላ ያልተማረና ቂል ነው። ለምሳሌ አንዱ ግልጾ፣ ሌላው ደግሞ ግታ ቢቀድስ፣ አንዱ በአርባ ወይም በስማኒያ ቢያጠምቅ ቢጠመቅ አያጣላም።

ይህ መጽሐፍ ብዙኃን አብያተ ክርስቲያንን ያገናኛል፣ አገናኝቶም ክርስቲያንን እርስ በርሱ ያረዳዳል፣ የክርስትናን ጠላት ያሳፍራል ተብሎ ይታመናል።

ስለዚህም የመጨረሻው አንድ እረኛ፥ አንድ መንጋ የሚለው ርእስ ተመረጠ።

ለዚህም የልዑል እግዚአብሔር ፍቃድ ይሁንልን፣ አሜን።

ከዚህ በፊት ያሉትን መጻሕፍቴን ይልቁንም ሁሉም ሁሉን ይወቅን ያነበቡ ሰዎች ኀይለ ቃል አብዝተሃል፥ ተሳድበሃል፥ የሚል ሂስ አቅርበውልኛል። ሂሱ ግን በእነሱ በኩል እንጂ በእኔ በኩል ልክ አልነበረም። በእነሱ በኩል ልክ የሚሆነው በሐቅነቱ ሳይሆን በልምዳቸው ነው። የንግግር ነጻነት በሌለበት ዘመንና ሀገር የተወለዱና በአሽሟጣጭና ስም አጥፊ አካባቢ አድገው የኖሩ ስለሆነ በአጋጣሚ የደርግና ከዚያ በፊት የነበረው መንግሥት ሴንሰር ያላየው፥ ፍርጥ አድርጎ እውነቷን የሚናገር መጽሐፍ በመውጣቱ ደንግጠው ነው። እውነታቸውን ነው፣ ምን ያድርጉ

ሌባ ሰርቆ ሲሮጥ ሌባ! ሌባ! ብሎ ቢጮሁ ሰደብሽን ብሎ የሚጣላ ከተማና ሀገር ውስጥ ነው ያለሁ።
እኔ ግን በስድብ አላምንም፣ ስድብ ውሸት ወይም እውነት ነው፣ እውነት ከሆነ ታሪክ ነው፣ ውሸትም ከሆነ ለሚና ዐይታ ይፈርደዋል፣ ለምሳሌ ዓለማየሁ ሞገስ አፍንጫው ቅስር ነው ማለት ታሪክ ነው፣ ጉራዳ ነው ማለት ውሸት ነው፣ የሚያይ ስለሚፈርደው አያጣላም። እንደገና ደግሞ ዓለማየሁ ሌባ ነው ማለት ግን ስም ማጥፋት ነው፣ ወዳጅ ዘመድ ስለሚያርቅ ያጣላል፣ በሐሰት እንደሆነ የሚወራው፣ እውነት ከሆነ፣ መድኀኒቱ ተጠጥቶ መተው ነው። እንጂ አትስደበኝ ማለት አይደለም።

በዚሁ! መሠረት በሀገር ምንድር ናት ጊዜ እንደተደረገው ሌባ! ሌባ! በማለቴ ብዙ ሌቦች እንደተቆጡ፣ ሌባን ይጣላሉ፤ ሕግ ያስከብራሉ ያልኳቸው ንጉሡና መኳንንቱ እንኳ ሳይቀሩ ደራሲውን አስረው፤ መጽሐፉን አቃጥለው አንዳሉ፣ አሁንም መስሎቻቸው በስም ሊቃውንት፤ በትምህርት ደናቁርት፤ በውዳሴ ከንቱ ቅዱሳን፤ በግብር ርኩሳን፤ በዘር ክርስቲያን፤ በዕውቀት መሃይምናን ቢቆጡ አያስገርምም። እኔ ግን የሚከተለውን የቅዱስ መጽሐፍ ቃል ለመፈጸም እታገላለሁ፣ 2ጢሞ.4:1-8፣ ....፣ ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም ያለጊዜውም ጽና፣ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፤ ገሥጽ፤ ዝለፍና ምከረም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የሚታገሡበት ዘመን ይመጣልና፣ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ፣ እንደገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ፣ አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፣ መከራን ተቀበል፣ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፣ አገልግሎትህን ፈጽም።

ይህ መጽሐፍ ብዙኃን አብያተ ክርስቲያንን ያዋሕዳል፣ አዋሕዶም ክርስቲያንን። ርእስ በርሱ ያረዳዳል፣ የክርስትናን ጠላት ያሳፍራል ተብሎ ይታመናል፣ ለዚህም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ልዑል እግዚአብሔርን እንለምናለን፣ አሜን ዮሐ.14:13-14፣ 15:16።

<u>መግቢያ</u>

በመቅድሙ እንደ ተገለጠው ይህ መጽሐፍ የክርስቲያን መስተፋቅር የሁሉም ሁሉን ይወቅ ቀጣይ ወይም ሁለተኛ መጽሐፍ ነው ማለት ይቻላል፤ በመሆኑም ቃላቱና ሂደቱ አንድ ነው። በዚያ መጽሐፍ አጻጻፍህ ለተራ አንባቢ አይገባም የሚል ሂስ ስለደረሰ፥ ደራሲው ደግሞ ላንባብያን የሚከተለውን ምክር ያቀርባል። በርግጥ ደራሲ ተደራሲውን ማሰብ አለበት። ጌታም ሲያስተምር ቋንቋውንና ምሳሌውን እንደ አዳማጩ አያደረገ ነበር። ገበሬ ሲያይ ምሳሌ ዘርን፥ ዓሣ አሥጋሪ (ዓሣ አጥማጅ) ሲያይ መረብን፥ ሴት ሲያይ ርሾን፥ ቀለበትን የመሳሰሉትን ምሳሌዎች ይናገር፤ ይሰጥ ነበር።

ስለዚህ ደራሲውም ሂሱን ሰምቶ፥ ጌታን ተቀብሎ ሸብረክ ብሎ ከመካከል ለመገናኘት ለክቡር አንባቢ የሚከተለውን ሲያቀርብ በታላቅ ትሕትና ነው።

ሀ/ በትምህርተ መለኮት የተለመዱ ውሳኔዎች (ድንጋጌዎች) ካልሆኑ በቀር በቀላል አማርኛ ለመግለጥ ተሞክሯል።

ለ/ የትምህርተ መለኮት ሐሳቦችን ለመግለጥ ከጥንት የተለመዱ ቃላት ቢሆኑ ደግሞ በእየደጁ ይተረጎማሉ።

ሐ/ አሁንም ለተራ አንባቢ የሚያስቸግሩ መሰለው የሚታዩት ቃላትና ሐረጎች ደግሞ በመፍትሔ ቃላት ይሰጣሉና፥ ስለዚህ የተሰጠውን ምዕራፍ ማየት ያሻል።

ተደራሲው፥ አንባቢው ደግሞ የትምህርተ መለኮት መጻሕፍትን የማንበብ ልምድ እንደሌለው በትዕግሥት እንዲያነብ ይጠየቃል። ማንኛቸውም ትምህርት በመግቢያው ያስቸግራልና።

ይህን መጽሐፍ ለመረዳት ከቃላትና ከዘይቤ፤ ከሐረግም ሌላ ሦስት ነገር ያስፈልገዋል፤ ራሱ መጽሐፉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ፥ (የሚጠቅሱት መጻሕፍተ ሊቃውንት)፥ ሁሉም ሁሉን ይወቅ። ስለምን ቢሉ በዘመነ ውድ ወረቀት የሚጠቀሰው ሰው ሁሉ ከዚህ አይጻፍምና ነው።

አቀራረቡም በመጀመሪያ በምዕራፉ መግቢያ የሃይማኖቱ ድርጅት ታሪክና ትምህርት፥ ተከታዮቹ እንደሚሉት ቁልጭ ብሎ በትክክል ይጻፋል፤ በመጨረሻ በቅዱሳት መጻሕፍት የተለየ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚያ ትምህርት የሚሉትን ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ ተናግሮ ስለዚያ ምዕራፍ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ዘርዝሮ ይዘጋል።

ይህም የተደረገበት ምክንያቱ ይህ መጽሐፍ፣ የክርስቲያን መስተፋቅርም ቢሆን ክርስቲያንን ተፋቀሩ ከማለት ባሻገርም እንደ ሁሉም ሁሉን ይወቅ ትምህርትህን ዐውቀህ፥ ሃይማኖትህን ተረድተህ፥ የመረጥኸውን እውነተኛውን ያዝ ብሎ ለመጠቆምም ስለሆነ ነው።

በራስህም ሆነ በሃይማኖትህ ድርጅት ከቅዱሳት መጻሕፍት የማይስማማ ጉድለት ካለ በምን ይሉኝ ገመድ ታስረህ፥ በጥቅም ሰንሰለት ተተብትበህ፥ በእልክ ቀምበር ተጠምደህ፥ በልማድ ጠፍር ተጠፍረህ፥ በጥቅም ማነቆ ታንቀህ፥ በኀሊናህ ባላንጋራነት፥ ለመጭው ዓለም ስደተኛ እንዳትሆን፥ ከመናገርህ በፊት አስተውለህ እንድታነብ ሰፊ መግለጫ ቀርቦልሃል። ለዚህም የሚጠቀሱት ሁሉ ከመጀመሪያው በኩል የቀረ እንዳለ... እንዲህ ባለ ነጠብጣብ ይቀጥላል። ተጀምሮ የቆመ እንደሆነ ደግሞ የሚፈልገውን ጥቅስ ከጨረስ በኋላ...። እንዲህ ያለውን ነጠብጣብ በአራት ነጥብ ይዘጋል። ደራሲውና ምዕራፉ ካልተለወጠ ደራሲውም ሆነ ምዕራፉ ሳይደገም ቁጥሩ ብቻ ይጠቀሳል። ብዙ ጊዜ የሚደጋገሙት ቃላት ደግሞ ከብዙ ስም አንዱ ተመርጦ ይሠራበታል፣ በብዛት ብቻም ሳይሆን የዚህ መጽሐፍ ዓላማ መስተፋቅርና መስተሳልም ስለሆነ ከማይወደድ ወይንም ነቀፌታ ካለው ስም ተወዳጁና ለሰላሳው ይመረጣል።

<u>ተዋሕዶ</u>፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣

<u>ቅብጥ</u>፣ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን

<u>ኦርቶዶክስ</u>፣ ለግሪክ ቤተ ክርስቲያንና ተከታዮችዋ።

ሮም፥ የሮም፥ ሮማዊት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ፣ ወንጌላውያን፣ ወንጌላውያት ለፕሮቴስታት አብያተ ክርስቲያን ወይም ድርጅት (Denomination)።

በሀገራችን መጽሐፍ ቅዱስን ተሸክመው፥ እጣመው እየተረጎሙ ዐውቀውም ሳያውቁም ጎጋውን ሕዝብ ለሚያስቱ ረሲአን ይህ መጽሐፍ በተቃሕዋ ሕግ መልስ ይሰጣል። ክርስቶስ በኋላ የመጡ ክሓድያን ግን ክርስቲያን ስላልሆኑ በሁሉም ሁሉን ይወቅ ምዕራፍ 20: ገጽ 126-134 የተጻፈውን ጠቁሞ ያልፋል። ሲያነቡም ለስርብትና ተብሎ የተዘለለውን ወይም የጠየመውን አትኩሮ ያነቧል።

በመጨረሻ የተጠቀሱት መጻሕፍት ሁሉ ለተሰጠው ሐሳብ ማስረጃ እንጂ ቅዱስ ወይም ልክ ነው ለማለት አለመሆኑ ለአንባቢ ግልጥ እንዲሆን ያስፈልጋል።

<u>ምስጋናና ሂስ</u>

ይህን መጽሐፍ ለብዙኃን ሊቃውንት አሳይቻቸው፤ በሐሳብም ደግፈውኛል ለሥራም ረድተውኛል። ስለዚህም በምስጋና ላስታውሳችሁ ብላቸው ግን ጥብዓት የላቸውምና አልተስማሙም። ይህም የሆነው የሚከተለው ጥቅስ ደርሶባቸውና ተፈጽሞባቸው ነው። (ዮሐ.12:42-43) ግን ካለቆች ደግሞ ብዙዎች በእሱ አመኑ፤ ነገር ግን ከምኩራብ እንዳያስወጧቸው፥ በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም፤ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።

በሁሉም ሁሉን ይወቅና በዚህ መጽሐፍ ሊቃውንቱ ሁሉ ተስማምተዋል፤ ይስማማሉ፤ ስለክርስቶስ መስከረው ከኀጓው ሕዝብ ጋራ መጣላቷን ግን አልደፈሯትም። ከዚህም አልፎ ተርፎ በምቀኝነት፥ በቅንዓት፥ ባለማወቅ ብዙ ጠማሞችና ውሸታሞች የሊቃውንትን ስም ለማጥፋት በሐሰት ሊቀደዱ ዝም ይላሉ፤ ከዚያም አልፈው የውሸት ወሬ ያስተጋባሉ፤ ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ይግራቸው ከማለት በቀር ምን ይደረጋል?

ሁለተኛም ቅዱስ ጳውሎስ (2ጢሞ.4:2-4) በጊዜውም ያለ ጊዜውም (ቢመችም ባይመችም) ቃሉን ስበክ፥ ጽና፥ ፈጽመህ፥ እየታገሥህና እያስተማረህ፤ ዝለፍና ገሥጽ፥ ምከርም፥ ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት ለመስማት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፥ ነገር ግን ጆሮአቸውን ለሚያሳክክ እንደገዛ ምኞታቸው ላለ፥ ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ፥ እውነትንም ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፥ ተረትንም መስማት ይወዳሉ ያለው ደርሶባቸው፤

## ምዕራፍ አንድ

### ምስጢረ ሥጋዌ

ከአምስቱ አዕማድ ምስጢር፤ (ምስጢረ ሥላሴ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ቁርባን፣ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን) አንዱ በአቆጣጠር ሁለተኛው ምስጢረ ሥጋዌ ነው። በሁሉም ሁሉን ይወቅ አራቱ ሁሉ ሲገለጡ፤ ምስጢረ ሥጋዌ ግን አልተነካም። ምክንያቱም አንባቢው ለዚህ አካሄድ የተዘጋጀ ስላልመሰለ ተዘሎ ነበር። አሁን ግን በሁሉን ሁሉን ይወቅ መንገዱ ስለተጠረገ፣ ከዚህ ቀጥለን እንጽፈዋለን። ይህም ሲሆን በዘመናችንና በአማርኛ ስለአምስቱ አዕማደ ምስጢር ብዙ መጻሕፍት ስለተጻፉና የደራሲውም ዓላማ ሌሎች በፍርሃት ወይም ምስጢር ነው በማለት ወይንም ኀጋውን በመፍራት አያድበሰበሱ የተውትን በጥበዓት ለማግለጥ ስለሆነ ለሕዝብ በደምብ ያልተገለጠውን አብራርተን እናልፈዋለን።

ወደ ምስጢረ ሥጋዌ ርእስ ከመግባታችን በፊት በምስጢረ ሥጋዌ ዓለምን ሲያጨቃጭቁ የኖሩትን፣ ለወደፊቱም የሚኖሩትን ቃላት ከዚህ ቀጥለን እንዘረዝራለን፤ እነሱም፤ ህላዌ፣ ህሉና፣ ባሕርይ፣ ጠባዕይ፣ አካል፣ ገጽ፣ ባሕርየ ሥጋ፣ ትስብእት፣ መለኮት፣ ባሕርይ መለኮት፣ ሀልዎት፣ ክዋኔ፣ ኩነት፣ ፍጥረት፣ ተፈጥሮ ናቸው። በእንግሊዘኛ Ousia, Hypostasis, Person, (Prosopon) nature, substance, essence, being። ይልቁንም በገጽና በባሕርይ መካከል ያለውን ልዩነት ከክፍል መሳልሶ አስተምሮ በምሳሌ ማስረዳት ካልሆነ በቀላሉ ለማስረዳት አስቸጋሪ ስለሆነ አንባቢ በአማርኛ የኪዳነ ወልድ ክፍሌን መዝገበ ቃላት በእንግሊዘኛም ሰፋ ያለ መዝገበ ቃላት ፈልጎ እንዲመለከት ይጠቀማል። እነዚህን ቃላት አተረጉማለሁ፣ አገልጣለሁ ብሎ መጀመር ሁሉም እንደ መቀናጆ በሬ በእያቅጣጫው ስለሚስብ የመለያየት ጫጫታ እንጂ የመመካከር መንፈስ ስለማይመጣ ለፊ ጥናታቸውን ለሚቀጥለው መጽሐፋችን አስከዚያም ለትጉህ አንባቢ ትተነው አልፈናል።

ይልቁንም ባሕርይ ፊሲስ (nature) ከክርስቶስ ልደት በፊት ጥንታውያን ግሪኮች፤ ቀጥሎም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከሁለተኛው መቶ ዘመን ጀምሮ ግኖስቲኮች፤ ከዚያም አስከ ቅዱስ ቄርሎስ ድረስ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በተቃራቢ ትርጉም ሲሠሩበት ኑረዋል። ቅዱስ ቄርሎስም ንስጥሮስን በ431 ገዝቶ፣ አውጣኪስን ሳይገዝት በ444 ስለሞተ ፍጹም ውሳኔ ሳይሰጠው ቀርቷል። ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ እንዲያው ዝም ብሎ ሁለት ባሕርይ ቢል ወደ ንስጥሮስ ስለሚቀርብ፣

አንድ ባሕርይ ቢል ደግሞ እንደ አውጣኪስ ስለሚሆን መለኮትና ትስብእት በተፀቅቦ ያለመደባለቅ፥ ያለመለወጥ፥ ያለመከፋፈል፥ ያለመለያየት ተዋሕደው ይኖራሉ፥ አንድ አካል ናቸው ለማለት ውሑድ ባሕርይ (የተዋሐደ ባሕርይ) ወይም መለትበ (መለኮትና ትስብእት) አያለ ጂኋል። እንባቢም እንደ ንስጥሮስ ሁለት አካል፤ ሁለት ባሕርይ ብሎ ከተዋሐደ በኋላ ባሕርያት ተለያይተው መለኮት የመለኮትን፥ ትስብእት የትስብእትን ሥራ ይሠራሉ፤ ወይንም እንደ አውጣኪስ መለኮት ትስብእትን አቅልጦ አንድ ባሕርይ ብቻ ነው ብሎ ተዋሕዶን እይካድ እንጂ ከሦስት ቃላት መለስት፥ ውሑድ ባሕርይ፥ አንድ ባሕርይ (እንደልማዱ) ቢል አይወቀሥም፥ በዚህም በፊት የለመድነውን ቃል እንለቅም በማለት ካልሆነ ጭቅጭቅ መነሣት የለበትም። እንባቢው ምስጢሩን ከተረዳው ወሳኙ ትምህርቱ እንጂ ቃሉ አይደለምና ነው።

እነዚህ ቃላት በመለዋወጥ አንዱ በሌላው እየተተኩ፤ መዘበራረቅ ሲያስከትሉ ሊቃውንቱን ሲያፋጁ ኑረዋል። ስለዚህ ሊቃውንቱ ተሰብስበው የተወሰነ ትርጉም እስኪሰጧቸው ድረስ በዚህ መጽሐፍ ከዚህ በላይ በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት በሚከተሉት ምሕጻረ ቃላት እንሠራለን። በባሕርይ ፈንታ የመለኮትንና የትስብእትን በተዋሕዶ አንድ አካልነትን፤ በሥምረት አንድ ፈቃጅነት፤ አንድ ገባሪነትን በኅብረት መናርን ለማሳየት <u>መለትበ</u> ይህም የመለኮትና የትስብእት የመጀመሪያዎቹ ቀለማት በምሕጻር መሆናቸው ነው። እንዲሁም ፈቃድና ግብር የሚሉት ቃላት ከተዋሐዱ በኋላ ትስብእትና መለኮት በአንድ ፈቃድና ሥምረት ነው የሚሠሩ የሚናሩ ለማለት፥ አንድ ፈቃጅ፥ አንድ ገባሪ ተብለው ተተክተዋል። ለጊዜው አንድ መለትበና አንድ ውሑድ ባሕርይ በተለዋዋጭነት በዚህ መጽሐፍ ይሠረሉ። በዚህ መሠረት መለኮትና ትስብእት በተዋሕዶ ከሁለት አካል፥ አንድ አካል፥ ከሁለት ባሕርይ አንድ መለትበ ሁነዋል ይባላሉ። ስለዚህ ሰው የሆነው አምላክ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ወልደ ማርያም ሥገው፤ ወልደ አብ በመለኮቱ፥ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ይባላል፥ ተብኋል። ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ (በመለኮቱ ከአብ ጋራ እኩል የሆነ) እንዳሉት ሠለስቱ ምእት በጸሎተ ሃይማኖት በመለኮቱ እንደ አብ ፍጹም አምላክ፥ በትስብእቱ ደግሞ ከኀጢአት በቀር እንደኛ ፍጹም ሰው፥ ሥጋ ለበሸ ሰው የሚያደርገውን ያደረገ፥ የሚያደርግ፥ በመለኮቱ ከአባቱ ጋራ፥

እንደ አባቱ ዓለምን የፈጠረ፣ ፈጣሪ፣ እምላክም ሰውም መለኮትንና ትስብእትን አዋሕዶ በአንድ አካል፤ በእንድ መለትስ ይዞ ወይም ውሑድ ባሕርይ ሁኖ የሚኖር ወልደ እግዚአብሔር በመለኮቱ፣ ወልደ ማርያም በትስብእቱ አሁንም እንደገና ለአጽንዖተ ነገር።

ውድ እንባቢ ሆይ! ይህ እንዴት እንደሆነ ከዚህ በታች እናየዋለንና እስኪ አትቸኩል። የፈጣሪውን ትእዛዝ በመተላለፉ አዳም ከገነት ወጥቶ፣ እሱ ብቻ ሳይሆን በመላ ዘሩም በሕይወተ ሥጋ ሳለ፣ ሲኖር፣ በሦስት እካላት ሲመሰገን የሚኖር እግዚአብሔር በዳዩን አዳምን ይቅር ለማለት ወሰነ። (ዘፍ.3:1-24) ለዚህም መሥዋዕት አስፈለገ፤ በደሉ ትልቅ ስለሆነ ለመሥዋዕቱ የእንስሳና የሰው ደም የማይበቃ ሆነ። ስለዚህ (ዘፍ.3:15) በእንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፣ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ ባለው መሠረት፣ በዳይም ተበዳይም ልጁ ልጃቸውን እዋጡና የአምላክ ልጅ አግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ፣ ትስብእትን ተዋሕዶ፣ የሰውን ልጅ ጠላት ሰይጣንን ድል ነሥቶ፣ ከዲያብሎስ ባርነት ከሲኦልና ከገሃነም ሥቃይና ኩነኔ አዳነ። የተበዳይና የበዳይ ልጅ (ዘር) በተዋሕዶ ተሰቅሎ ዓለምን አዳነ። (ከሦስቱ ሥላሴ፤ ከሠለስቱ አካላት እንዱ በተለየ እካሉ፣ ሥጋ ለብሶ፣ ተሠቃይቶ፣ ተገፎ፣ ተገርፎ፣ ተሰቅሎ ዓለምን እንዲያድን በወልድ እንዴት ተፈረደ፣ ተወሰነ? ለሚል ጠያቂ፣ ሃይማኖት በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠ በመሆኑ፣ ስለዚህም የሚናገር ከቅዱሳት መጻሕፍት ሰለሌለ፣ ደራሲው ስለዚህ የሚያውቀው ነገር የለም።) ተበዳዩ አምላክ በዳዩን እዳምን ይቅር የሚልበት ጊዜ ሲደርስ በመበሥሩ በቅዱስ ገብርኤል እማካይነት፣ የቅድስት ድንግል ማርያምን ፈቃድ እንዳገኘ፣ አንድያ፣ ተቀዳሚ፣ ተከታይ የሌለው ልጁን ሳከ። በልደት ሦስቱም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይተባበራሉ፣ ተባብረዋል። አብ መርጧል፣ አጽንቷል፣ መንፈስ ቅዱስ በላይዋ ላይ አድሮ ቀድሷታል፤ ከጥንተ አብሶ እንጽቶ፤ ማኅደረ መለኮት እንድትሆን አዘጋጅቷታል፤ ትስብእትንም (ሥጋን) እግዚአብሔር ወልድ እንዲለብሰው እድርጎ አመቻችቶታል። አግዚአብሔር አብም ትስብእትን በመንፈስ ቅዱስ አከብሮታል፣ ይህን ግብር ብዙዎች ቅብዓት ይሉታል። ቅብዓት (መክበር) የሚያየው ትስብእትን እንጂ መለኮትን አይደለም። እግዚአብሔር ወልድ በመለኮቱ ከአባቱ ጋራ እኩል ስለሆነ

የመንፈስ ቅዱስን ክብር አይፈልግም ትስብእት ግን ከተዋሕዶ በፊት ፍጡር ስለነበረ ከአካለ ቃል ተዋሕዶ ከአብ ጋራ እኩል ለመሆን ቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ፥ ግብረ መንፈስ ቅዱስ= የሦስቱም ኀይል፥ ኀይለ መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገው ነበር። የማርያምን ሥጋ አብ በመንፈስ ቅዱስ ቅብዐትነት ካከበረው በኋላ ወልድ ለበሰው፣ ተዋሐደው። በዚህም ትስብእት የባሕርይ አምላክነትን ወረሰ፣ መለኮትም ሰው ሆነ። ሰው አምላክ፥ አምላክ ሰው ሆነ የሚያሰኘውም ይህ ነው። በመለኮቱ አምላክ አማልክት፥ ፈጣሬ ዓላማት ሲሆን በትስብእቱ ደግሞ ንጉሠ ነገሥት፥ ሊቀ ነቢያት፥ ሊቀ ሰማዕት፥ ሊቀ ካህናት ነው። እንደ ሰውነት፥ ሰው መሆኑን ለማጠየቅ ትንሽ በትንሽ አድጓል፣ እንደ ሕፃናት አልቅሷል፥ ደክሟል፥ ተርቧል፥ ተጠምቷል፥ ምራቅ፥ ደም ወጥቶታል፥ ሙቷል። አምላክ እንደመሆኑ አምላክነቱን ለመጠየቅ፣ በድንግልና ተወልዷል፣ በተዘጋ ቤት ገብቷል፣ በባሕር ላይ ያለጀልባ ሂዷል፣ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ መቃብር ክፈቱልኝ፥ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ተነሥቷል። በዚህም አንድ መለትስነቱን ወይም አንድ ውሑድ ባሕርይነቱን እንረዳለን። መለትስ መሆኑን ያልተረዱ ብዙ ሰዎች ትስብእትን ሲያዩ የተነገሩትን ቃላት፥ ጥቅሶች፥ ዐረፍተ ነገር ባነበቡ ቁጥር ለማረም ወይንም ለማጣመም ይሞክራሉ። ይህ ግን ካለማወቅ የመጣ ነው፣ ልኩ መለኮቱን ቢያዩ የተነገሩትን ለመለኮቱ ሰጥቶ በመለኮት ባሕርይ መተርጎም፥ ለትስብእት የተነገሩትን ደግሞ ለትስብእት ሰጥቶ ካነበቡ በኋላ አንድ አካል አንድ መለትስ ብሎ አስታርቆ አስማምቶ መፍታት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ፥ የአብና የማርያም ልጅ በአንድ መለትስ መሆኑን ለመረዳት በሰፊው የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ሁሉን ይወቅ ገጽ 47-67 ያለውን መግለጫ ከጥቅሶቹ ጋራ እያገናዘበ እንዲያነብ ይነገራል። ከዚህ ግን ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው፥ አንድ መለትስ መሆኑን ለማስረዳት የሚከተሉት ተጠቅሰዋል፣ (ዮሐ.1:1-14፣ 3:16-18፣ መዝ.2:6-8፣ 109:4፣ ሉቃ. 23:34 ዮሐ.10:30፣ 14:6፣ 20: 17፣ ኢሳ.61:13፣ ሉቃ.4:18-19፣ 53:11-12፣ ዮሐ.14:28፣ 31፣ መዝ.21:1፣ ማቴ.27:46፣ ሉቃ.13:32፣ 2ቆሮ.1:3፣ 11:31፣ ኤፌ.1:3፣ 17፣ ፊል.2: 6-10፣ 1ጴጥ.1:3፣ 2ጴጥ.1:17-18፣ ግብ.2.24፣ ራእ.1:6፣ 3:2፣ 3:12፣ ዮሐ. 6:37-39፣ 7:29፣ 1:36፣ 8:42፣ 9:4፣ ሉቃ.4:43፣ገላ.4:4፣ዮሐ.4:9፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህን የመሳሰሉ ለቁጥር የሚያዳግቱ ጥቅሶች ሞልተዋል።

## ምዕራፍ ሁለት

### መቼና የት ነው የተዋሐደው?

ኧረ! የሆነስ ሆነና መቼና የት ነው የተዋሐደው? ለሚል ጠያቂ ኦርቶዶክሳዊ መልስ እነሆ! ከማርያም ሲወለድና በፈለገ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ ነው የሚሉ አሉ፣ ልክ አይደለም፣ አይሰድም፣ ለምን? ቢሉ፣ መቼው፣ እመቤታችን ለቅዱስ ገብርኤል ብሥራትና ጥያቄ፣ እነሆ የእግዚአብሔርን ባርያ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ብላ ፈቃደኛነትዋን (እግዚአብሔር ያዝዛል እንጂ ብዙ ጊዜ ታዛዡ ካልፈቀደ አያስገድድምና) በገለጠች ጊዜ ነው።

የት ነው? የሚለው ደግሞ በማሕፀነ ድንግል (በከርሥ) ነው፣ ይህስ ለምን ሆነ ቢሉ በማሕፀን ሳይዋሐድና አንድ መለትስ ሳይሆን፣ ትስብእት የመለኮትን ርቀት፲ መለኮት የትስብእትን ግዘፍ ሳይነሡ በዕሩቅ ብእሲነት (በተራ ሰውነት) ቢወለድ ኑሮ ድንግልናዋ ይጠፋና ትንቢተ ነቢያት ሁሉ ተበላሽቶ፣ መስናዶው ሁሉ ከንቱ ሁኖ ይቀር ነበር። መለኮትም ከማርያም ተወለደ አይባልም ነበር፲ ማርያምም ወላዲተ አምላክ ባልተባለችም ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋን የነሣው ትስብእትን የተወሐደው ከማሕፀን ውጭ ቢሆን ኑሮ፲ በአንድ ጎረምሳ አደረ እንጂ ተወልደ አያሰኝም ነበር። ይህም ለጥስጥሮስ ባመቸ። ተዋሕዶ በማሕፀን እንደሆነ ከሚያስረዱት ትንቢታትም፣ እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና፲ ተዘግቶ ይኖራል። (ሕዝ.44:1-2፲) ስለዚህ ጌታ ራሱ ምል ክት ይሰጣችኋል፲ እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፲ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች። (ኢሳ.7:14)። እንቱ ሙሽሪት የተቆ ለፈ ገነት (ተጋን) የተዘጋ ምንጭ፣ (የታተመ) ነቅዕ (መሐ.4:12)። ተዋሕ ዶው ከማሕፀን ውጭ ከሆነ እንደዚህ ያለው ትንቢት ሁሉ ከንቱ ይሆንና የነቢያትም የሐዋርያት ትምህርትና ስብከት የልጆች ተረት ሁኖ ያርፋል።

ልደታትስ ስንት ናቸው? ለሚል ጠያቂ ደግሞ፲ እሞቅድመ ዓለም ከእብ ያለ እናት፣ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያላበት፣ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ፣ ነአምን ክልኤተ ልደታተ እንዳሉ ሠለስቱ ምእት፲ ልደት ወይም ልደታት ሁለት ብቻ ናቸው። ለመለኮቱ እናት፣ ለትስብእቱ አባት የለውም። ምንም ቅባቶችና ጸጎች ሦስት ልደት ቢሉም ከልጆች ተረትና ከመጽሐፉ ባልቴት አልፎ ከቁም ነገር አይገባም። መንፈስ ቅዱስ ከኔ ይነሣል፲ እኔ እልከዋለሁ እያለ (ዮሐ.16:8-14) ይወልደዋል ቢባል የልጆች፣ የሚዜዎች የጫጉላ ጨዋታ ይሆንና ያርፋል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የሦስቱ የሃይማኖት ክፍላት፤ ካራ፤ ቅባት ጸጋ አጭር መግለጫ፤

በኢትዮጵያ ሦስት የሃይማኖት ክፍላት፡ ካራ፡ ቅባት፡ ጸጋ የሚባሉ ነበሩ፤ ከጥላቻቸው ብዛት የተነሣ አንዱ ሌላውን እንደ ክርስቲያን አያየውም ነበረ። በመካካላቸው የቃል ክርክር ብቻ ሳይሆን በመሣሪያ ጦርነትም ብዙ ደም ፈሷል።

ጸጎችና ቅባቶች ሦስት ልደቶች፡ ሦስት ልደት በመባል ይታወቁሉ። ሦስት ልደት ማለትም ወልድ ከአብ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ተወልዷል ማለት ነው። ይህም ቅባቶችንና ጸጎችን ያሻማል። ጸጎች በማሕፀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የጸጋ ልጅ ሆነ ሲሉ፡ ቅባቶች ደግሞ ልክ እንደ ጸጎች በማሕፀን በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ የባሕርይ አምላክ ሆነ ይላሉ። ለተራ አንባቢ ነገሩ ጭፍንና ስውር ረቂቀም ስለሆነ ወይም ለደራሲው መስሎ ስለታየ በሌላ አነጋገር ግልጽ ለማድረግ ተሞክሯል፤ እምቅድመ ዓለም ካአብ፡ ያለ እናት አንድ ልደት፡ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት ሁለት ልደት (ሁለተኛ ልደት) ወልደ አብ፡ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ ከሚሉት ከካሮች ጋራ ሁለቱም ይመሳሰሉና በዚህ ላይ ሁለቱም የእየራሳቸውን ቁሪት ጨምረው፡ ቅባቶች በማሕፀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብቶ፡ የባሕርይ ልጅ ሆነ ሲሉ፡ ጓደኞቻቸው ጸጎች ደግሞ ይህንኑ የእነሱን ፀረፍተ ነገር፡ በማሕፀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብቶ፡ በመቀባት የጸጋ ልጅ ተባለ፡ ተብሏል፡ ሁኗል ይላሉ። ስለዚህ ሁሉም መለያያ ምክንያት ነውና የሚፈልጉ ቅባትና ጸጋ እየተባሉ ይኖራሉ።

ካሮች (ተዋሕዶዎች) ደግሞ የክርስቶስን ሰውነትና መለኮት አይለያዩም፡ አንዳንዶቹስ እንደ መለትስ ያለ ውሳኔም የሚገባቸው አይደሉም። ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋና (ትስብእት) መለኮት የተለያዩበት ጊዜ ነበር አይባልም፡ አይሉም (ልክ)። ስለዚህም ይህን የሠራው ሥጋው ነው፡ ይህን ደግሞ መለኮቱ ነው የሚሉበት ጊዜ የለም። ለዚህስ ሌላ አባባል አላቸው፡ ይህን በሥጋው፡ ይህን ደግሞ በመለኮቱ ነው ይላሉ። ሥጋው (ትስብእቱ) ማለትና በሥጋው በመለኮቱ ማለት ልዩነት አላቸው።

ካሮች ከቅባቶችና ከጸጎች የሚለያዩበት ለሌላ አነጋገር ባጭሩ፤ ክርስቶስ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ ነው። ተዋሕዶ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ወልድ በትስብእት ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ዐማኑኤል ተብሎ፡ የተባለው የእኛን ሥጋ ከቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን በተለይ አካሉ ከፍሎ ቢዋሐደው በሰውነቱ እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ያለ ፍጹም አምላክ ሆነ።

ወልድ ራሱ ቅብዕ፥ ራሱ ቅቡዕ፤ ራሱ ቀባዒ፥ ቅባቱም ቀቢውም ራሱ ነው እንጂ ከእሱ የሚበልጥ ለሌላ ቀቢም፥ ቅባትም አይፈልግም። በመለኮቱ ይህ ርግጥ ነው፥ ለሥጋ ለትስብእት ግን ከዚህ በፊት የተሰጠውን ሐተታ ያስፈልጋል።

## ምዕራፍ አራት

### የቅባት ዐይነቶች

እስተውሎ ለሚያነብ እንባቢ ከዚህ በላይ የተነገረው ለለቅባትና ጸጋ ይበቃ ነበር። ነገር ግን በአነጋገሩ ምክንያት አንዳንድ ጭፍን ነጥቦች ስለማይጠፉ ለማብራራት የቅባት ልዩነቶች ተጨምረው ከዚህ በታች ከሞላ ጎደል ተደግሟል።

ለማብራራት እንዲመች የንስጥሮስን እባባል የእኛ ሊቃውንት እንዴት እንደሚያትቱት ከዚህ ቀጥለን እንገልጣለን፤ ንስጥሮስ የኮነን ጠባይ ስልቱን አፈታቱን ፈጽሞ ሳያውቀው፥ ሳያውቅ፥ የፈጣሪ ባሕርይ እንደ ፍጡር ባሕርይ የሚለውጥ መስሎት "ኮነ" ማለት እንደሎጥ ምሽትና እንደ ሙሴ ብትር፤ እንደ ግብጽና እንደ ቃና ውሃ ተለወጠ ያሰኛል በማለት፤ ቃል ሥጋ ኮነን ነቅፎ፥ አጸይፎ፥ ቃል በሰው አደረ እንጂ፥ ሰው አልሆነም፥ አልተዋሐደም፥ መሲሕም ይባል ዘንድ ሰው ሁኖ አልተቀባም፥ አብ የወለደውን ማርያም አልወለደችም፥ እሷም ወላዲተ ሰብእ እንጂ ወላዲተ አምላክ አትባልም ቢል፥ ቅዱስ ቄርሎስ፥ እንዳንተ ሐሰብ ኮነ ማለት በውላጤ ሳይሆን በተለይ አካሉ የእኛን በሕርይ ነሥቶ በመወለድ ሥጋ ለብሶ፥ በመዋሐድ ተዋሕዶ ከኀጢአት በቀር እኛን በመምሰል፥ እንደኛ በመሆን ነው እንጂ በኀድረት አይደለም ሰላለ የባህሉ ስም ተዋሕዶ ሁኗል። (ሃ.እ.ዘቀ.ወዘደ.189፡ገ.19)

ይህንን ለማራቅ በጎንደር በሰውነቱ የእብ የባሕርይ ልጅ የሚል ኑፋቄ ተነሥቶ እንድ ዘመን ለተወሰነ ጊዜ ያጨቃጭቅ ነበር ይባላል። የዚህ ተከታዮች ግን በ1954 በዜና ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔር ወልድ በሥጋው የባሕርይ እባቱ ነው የሚለው ስሕተት ቢተበተነ ወዲሀ፤ እንዳሉ ይታመናል። (ዜና፡ቤ.ክ. 16፡ መጋቢት)

አንዲህ አድርጎ ንስጥሮስ ለሚከተሉት መናፍቃን ስአውጣኢስና ስመስሎቹ በር ከፍቶ ሄደ። ከዚህ ላይ ሌሎቹን ለሌላ ጥናት ትተን ቅባቶቹንና ጸጎቹን እናስከትላለን፤

በዘመነ ፋሲል የተነሡት የእነዘኢየሱስ መጽሐፍ አንደየ ርእሰ (ራሱን አራቆተ፥ አደኸየ) (ፊል.2:7) ይላልና ቃል በተዋሕዶ ዜገ፥ ደኸየ፥ ከሥጋ ሲዋሐድ የባሕርይ ክብሩን አጣ፥ ለቀቀ፥ ሲቀባ ግን ወደ ጥንተ ክብሩ ተመለሰ፥ በሰውነቱም በእምላክነቱም አንድ ወገን ሁኖ (በዚህ መጽ ሐፍ አባባል መለትስ ማለት ነው) በቅባት የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል።

በአንደኛው ዮሐንስ ዘመን የተነሡት እነ አካለ ክርስቶስ ደግሞ ዜገ ማለትን ነቅፈው፥ አጸይፈው፥ እስመ ተዋሕዶ አእተታ ስምንታዌ ይላልና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል ሆነ እንጂ የአምላክነትን ክብር አላገኘም፥ ሲቀባ ግን ክብር ተላልፎለት፥ ተፈጥሮ፥ ተገብሮ ጠፍቶለት፥ በቅባት፥ ሲቀባ የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ ሆነ ብለዋል። ምስጢሩም መቀባትና መለወጥን ለሥጋ ብቻ መስጠት ነው።

በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን የነበሩ እነ አራት ዐይና ጎሹ ደግሞ በቅባት ብቻ ማለትን ነቅፈው፥ መጽሐፍ በሁለቱም ሁሉ በተዋሕዶ ከበረ፥ በቅባት ከበረ ይላልና ቅባት ያለተዋሕዶ፥ ተዋሕዶ ያለቅባት ብቻ ብቻውን አያከብርም፥ ስለዚህ በተዋሕዶና በቅባት አንድነት (በአንድነት) የአምላክ ክብር ከብሮ የባሕርይ ልጅ ሆነ ብለዋል።

ወመለከቱሰ ኢይትቀባዕ (መለኮቱስ አይቀባም) በሚለው በቄርሎስና በዮሐንስ አፈወርቅ ድጅኖ ተቀደሰ ምስሌነ በሥጋሁ ይላልና በሥጋው ሞተ እንደሚባለው፥ የተቀባ ግን ከተዋሕዶ በፊት ትስብእት እንጂ መለኮት አይደለም።

ስለዚህ ካሮች ደግሞ ወልድ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ልጅ፥ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ሁኖ፥ በመሆኑ በቀባዒነት ከአብ ጋራ አንድነት ሰላለው፥ ቀባዒ አና ቅቡዕ ቢባል እንጂ አንድ አብ ቀባዒ፥ እንደ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ አይደለም ይላሉ።

ቅባቶች የወልድ ልደታት ሦስት እነደሆኑ ያስተምራሉ፤ እምቅድመ ዓለም ከአብ ያለእናት የተወለደው አንድ ልደት፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ከመንፈስ ቅዱስ የተወለደው ሁለተኛ ልደት፤ ከእመቤታችን ሥጋን ለብሶ በኢየሩሳሌም የተወለደው ሦስተኛ ልደት ብለው፥ አምነው ያስተምራሉ።

በዚህም ሦስት ልደት በማለታቸው ከካራ እምነት ይለያያሉ። እንዴት? ቢሉ፤ ካሮች እምቅድመ ዓለም ካብ ያለእናት፤ አንድ ልደት፤ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያላባት ሁለት ልደት፤ ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ ሲሉ፤ ቅባቶች ግን ከካሮች ሁለት ልደት ላይ ሦስተኛ ልደት ጨምረው ከመንፈስ ቅዱስ በማሕፀነ ማርያም ተወልዷል ይላሉ። እኛ በጥምቀት በመንፈስ ቅዱስ መደበኛነት የሥላሴን ልጅነት እንደምናገኝ፤ የእኛ በኩር ለመሆን ሲል የባሕርይ ልጅነቱን በማሕፀን የጸጋ (የስጦታ) አድርጎ ተቀበለው። በማሕፀን መንፈስ ቅዱስን በመቀባቱ የባሕርይ ልደቱን፤ የጸጋ አድርጎ ሲቀበል ከበረ ስለሚሉም ቅባት ማለት ክብር ማለት ነው ብለው ያስተምራሉ። በእነሱ አባባል አብ ቀባዒ፥ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ፥ ወልድ ተቀባዒ፥ እንደሆኑ ያስተምራሉ።

ቅብዐት ለትስብእት በትስብእት እንደሆነ ደጋፊ አያጡም። ቅባቶች ከካሮች የሚለዩበትን እምነት ባጭሩ ስንመለከተው ፍሬ ነገሩ እንደሚከተለው ይሆናል፤ የሥጋና የቃል መዋሐድ ምንታዌን (ሁለትነትን) አጠፉ እንጂ፤ ቃል ለለበሰው ሥጋ የባሕርይ አምላክነትን ክብር ሰጥቶ ያከበረ መንፈስ ቅዱስ ነው። በዚህም አብ ቀባዒ ወልድ ተቀባዒ፥ መንፈስ ቅዱስ ቅብ ናቸው። ምንም መንፈስ ቅዱስን በመቀባት ወልደ ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል ቢባልም ልደቱ የባሕርይ እንጂ የጸጋ ልደት አይደለም ብለው ያስተምራሉ።

ጸጎችም እንደ ቅባቶች አብ ቀባዒ ወልድ ተቀባዒ፤ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ብለው ያምናሉ፤ ያስተምራሉ።

ጸጎችን ከካሮች የሚለያቸው አባባል ይህ ነው፥ ቃል በለበሰው ሥጋ እንደኛ በመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ክብር አግኝቶ ክርስቶስ ተባለ። ክርስቶስ ማለትም ቅቡዕ ማለት ነው። አብ ቀቢ፤ መንፈስ ቅዱስ ቅብ፤ ወልድ ተቀቢ ናቸው። ወልድ መንፈስ ቅዱስን ሲቀባ የጸጋ ልጅ ሆነ፤ እኛም እሱ ወዶ የተቀበለውን ሰውነት (ሰው መሆን) ለማስወገድ አንጥርም ይላሉ። የካሮች ግን አሁንም ከላይ እንዳየነው ነው።

ከአብ በመንፈስ ቅዱስ የከበረ የተቀባ ሥጋ ከመለኮት ጋር ከመዋሐዱ በፊት ከሆነ በጥንታውያን ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም፥ አለው፥ መለኮትን ካየና ከጨመረ ግን የቅባቶችና የጸጎች አንጡራ ገንዘብ ሁኖ ኑሯል፥ ይኖራል። ሦስት ልደት ማለት ግን የሁለቱ የቅባትና የጸጎች ፍልስፍናዊ የግል ገንዘብ

ናት፤ ከእነሱ በቀር ሌላ ቤተ ክርስቲያን አያውቃትም።

በቅኔስ ምንም እነሱም ባይበገሩ አንድ ከተዋሕዶ ወገን የተሰጣቸው ቅኔ ከዚህ ቀጥሎ ተጽፏል።

__ሞዜማ__

መንበረ ኪሩባዊ
ለእመ በቅብዐት ወረሰ ፍሬ ክርሥኪ ዕፁብ
ዘቤተ ድንጋሌ ማርያም ርግብ
እስመ ከማሁ ኩልነ ሉቱፋነ ቅብዐት ሕዝብ
እስፍንተ ያገምር መንበሩ ለእብ
ወእስፍንተ ይጸውር ኪሩብ።

ከእነዚህም ሌላ ከመቃብር ተወለደ፥ እንደ አርጌንስም የወደቁትን መላእክት፤ እጋንንት ለማስታረቅ ተወልዷል ወይም ይወለዳል የሚሉም ስላሉ፥ ልደትን በሙሉ ቁጥር በሰባት የመወድስን ስምንት ቤት ደግሞ ባሥር ለመደምደም በፍና ተሣልቆ የሚቀጠለው መወድስ ተጽፏል፤

__መወድስ በእንተ ልደታቲሁ ለወልድ፤__

ብሉየ ዘመን ወልድ መፍቀሬ ተወልዶ
ከመ ዕፀ ቆላ ራምኖን ዘትትወለድ በበዓመት
እምቅድመ ዓለም እምአብ ወእማርያም ቅድስት
ለእድኅኖተ ዓለም ድኅረ ዓለም
ተወለድከ በከመ ይቤሉ ዘከልኤ ልደት
ወሣልስ ከመ ቅብዐት
ወጸጋ ይቤሉ እመንፈስ ቅዱስ በፅንስት፤
ወራብዐ በትንሣኤ እምገ መቅበርት
ወማእዜ ለተዐርቶ ትትወለድ እመላእክት
እስመ ኮንከ እንተ መድኅነ ኩሉ ፍጥረት
ለምንት ኢትወለድ እምነ እንስሳ ወዕፀዋት?
ወተወለድ ሰብዐ እምነ ዘባሕር ዓሣት
ፍጹም ከመ ይኩን ታሪክከ በትሰብእት።

በቅድሳት መጻሕፍት የተገለጡት ልደታት፤ ከእግዚአብሔር አብ በመለኮቱ ያለ እናት እምቅድመ ዓለም፥ በዚህ ዓለም ደግሞ ከቅድስት ጽንግል ወላዲተ አምላክ ማርያም ያለ አባት በሥጋ በትሰብእት ናቸው። በዚህም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ መለትስ ሁኖ

## የቅባት ፀይነቶች

በተዋሕዶ ያስመክፋፈል፥ ያስመስያየት፥ ያስመጠፋፋት፥ ያስመደባለቅ ይኖራል።

መቀባትን፥ መወለድን፥ ልደትን በጠቅላላ የሚያሳዩ ጥቅሶች፤ ኢሳ.7:14፤ 11:1-2፤ 42:1፤ 61:1፤ ሉቃ.4:14-19፤ ግብ.ሐ.4:27፤ 3:13፤ 27፤ 30፤ ሮሜ.8:15-17፤ 29፤ 10:38፤ በተዋሕዶ መሳተፍና መገናዘብ እንጂ፤ መጣፋትና መሳሳብ መቀላቀል መስያየት የለም። ባዕሉ፥ ብዕሉን ሳይለቅ ነዳይ ሆነ፥ ነዳዩንም ንዴቱን ሳይለቅ ባዕል አደረገው። እንደየ ርእሶ እንዘ ባዕል ከመ ትብፀሉ እንትሙ በንዴት ዚአሁ ወእብፀሎ ስሥጋ ዚአት በትድምርት። እሩ ኢያብዕል ቃል ሥጋ ዚአሁ በትድምርት (ቄር) ሥጋ ረከበ ዕበየ ወብዝኀ ፍድፍድና በተሳትፎቱ ምስለ ቃል (አትና)

አንዳንድ ሰዎች ግን ንባብ ጥሰው፥ ምስጢር አፍርሰው፥ በስውነቱ የአብ የባሕርይ ልጅ፥ በስውነቱ የባሕርይ አምላክ፥ በስውነቱ ዕሩይ ምስለ አብ ይሉታል፤ በስውነቱ ሳይሆን በተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ፤ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ስለሆነ ከተዋሐደ በኋላ፥ በተዋሕዶ ትስብእትም ፍጹም አምላክ ሁኗል። ቃል ሰው መባልን ሲወርስ ስሥጋም አምላክ መባል ተሰጥቶታልና። በስድስተኛው ክፍለ ዘመን አቡሲዲስ፥ ወከመዝ ንብል ከመ ዕሩይ ወእቱ ምስለ እግዚአብሔር አብ፤ ወሥጋሂ ይትዌከፍ ዘንተ አሐደ ስመ፤ እስመ ዋሕድ ውእቱ ምስለ ዘይትዔረዮ ለእብ፥ ወከማሁ ንብል ምስለ ዕጓለ መሕያው፤ መስኮትሂ ይትዌከፍ ስመ፤ ዕጓለ ማሕየዊ፤ እስመ ተፀርየ ምስሌነ በለቢሰ ሥጋነ ወረሰዮ አሐደ ምስሌሁ ወኢተወለጠ ምንተኒ እምህላዌ ሥጋ በተዋሕዶ። (ኪዳነ ወልድ አ.ዝ.ገ.183)

## ምዕራፍ አምስት

### ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን በግሪኩ አቅሌስያ= ጉባኤ፥ ሸንጎ ማለት ነው። በነጠላ ጉባኤ እንጂ ጉባኤያት በብዙም አይደለችም። የመሠረታትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የምታሳየውም በውስጧ የሚኖሩ ሁሉ በክርስቶስ የሚያምኑ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ተከታዮች ስለሆኑ በግዕዝ ቤተ ክርስቲያን ትባላለች። ከዚህ በላይ በተጻፈው አንቀጽ እንደተገለጠው የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ እሱን ያመኑና የተቀበሉ፥ የሚከተሉ፥ ፍቅር ስንደቅ ዓለማቸው፥ ክርስቶስ መሪያቸው፥ እግዚአብሔር አምላካቸው የሆኑ የምእመናን ማኅበር ማለት ነው። ክርስቶስ የመሠረተ አንድ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ እሷም አካሉ ናት። ጥንታውያን ቅዱሳን አበውም በጸሎት ሃይማኖት እንደ ተገለጠው ከሁሉ በላይ በምትሆን በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ጉባኤ፥ ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ብለው በኒቅያ ጉባኤ ወስነዋል። ማቴ.16:18: አንተ ጴጥሮስ (አለት) ነህ በዚችም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም ብሎ አንድና መሠረቷም የማይነቃነቅ ጽኑ አለት እንደሆነ በማያሻማ ቃል ተናግሯል።

እንደገናም ማቴ.18:17: እነሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። አሁንም ነጠላ ናት። ሐዋርያትም በአጠቃላይ ሲናገሩ በነጠላ፤ በእየስፍሩ ሲናገሩ ግን በብዙ፥ በዚህ ቃል ይጠቀሙ ነበር። ይኸውም የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን፥ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን፥ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን፥ እንደማለት እንጂ በትምህርት ይለያያሉ ማለት አልነበረም፤ ይህም በዘመናችን፤ የአክሱም ጽዮን፥ የጣና ቂርቆስ፥ የመረጡስ ማርያም፥ የአዲስ ዓለም፥ የደብረ ሊባኖስ አብያተ ክርስቲያን ወይም አድባራትና ገዳማት እንደማለት እንጂ የተለያዩ እምነት ያላቸው ምእመናን ማለት አይደለም፤ አልነበረም። እሷም አንድ፥ ቅድስት፥ ሐዋርያዊት፥ ከሁሉ በላይ ናት። ቤተ ክርስቲያን እርሱ ራስዋ፥ አስታዋ የሆነ የክርስቶስ አካል ናት።

(ኤፍ.1:22-23፤ 4:15፤ ቆላ.1:18) ርግጥ፥ መንቆራቆስ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ መበባል በሐዋርያት መካከልም ነበረ። አብዛኞቹ ክርስቶስን የተከተሉት፥ ትንቢት የተነገረለት፥ ሉባኤ የተቆጠረለት መሲሕ ሲመጣ፥ እየሩሳሌም ከሮማውያን ቀምበር ነጻ ስትወጣ፥ ራስ፥ ቢትወደድ፥ ጀኔራል ተብለው፥ ሚኒስቴር ሁነው ለመሰፈን ነበረና የክርስቶስኝ መልእክት

የመረዳታቸው መንፈስ ቅዱስ እስከ ወረደባቸው ድረስ ሐዋርያትም ይጨቃጨቁ ነበር። ጰራቅሊጦስ ከወረደ በኋላም፣ ለጊዜው በቀጥተኛ ተከታዮቹ መካከል የፍቅረ ሢመቱ እንቁርቁሽ (ጠብ) ገብ ቢልም በአስተዳደርና በትምህርት መከራከራቸው አልቀረም፤ ባይቀርም እስከ 4ኛው መቶ ዘመን ድረስ ክርስቲያንን የሚለያይ ጠንካራ ልዩነት አልነበረም። (ማቴ.18:1-5፤ 20:20-28፤ ግብ.ሐ.6:1-5፤ 15:1...።)
ከዚህ በኋላ ግን በብዙ ሰዎች ክርስቶስ የመጣው ለምድራው መንግሥት፣ ለሥጋ ተድላ ሳይሆን ለሰማያዊ መንግሥትና ጽድቅ መሆኑ ስለታወቀና ስለ ታመነ ለሦስት መቶ ዘመን ብዙ ምእመናን በተጋድሎ እየሰበኩ በአላውያን አደባባይ በሰማዕትነት ሲሠው ኖሩ።

4ኛው መቶ ዘመን እንደገባ ቆስጠንጢኖስ መጀመሪያ በ313 ለክርስትና ሃይማኖት ነጻ ሰጠ። ቀጥሎም አብያተ ክርስቲያናት ይከፈቱ፣ አብያተ ጣዖታት ይዘጉ ብሎ ዐወጀ። ካህናትም ዲያቆን፣ ቄስ፣ ጳጳስ እየተባሉ ተሹመው ደመወዝ ይቀበሉ፣ ከላይ ይቀመጡ ጀመር፣ ምስፍና ቅስና፣ መንግሥት በጽጽስና ተገኘ። በዚህ ምክንያት ቀድሞ በቤተ መቅደስና በአብያተ ጣዖት የነበረች ስርብትና ቅናት ዘውዷን ደፍታ፣ ተንኮል ካባዋን ደርባ ስተት ብላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገባችና ጳጳሳቱን ታፍኗቸው ካህናቱን ታበጣብጣቸው ጀመር።

ከቆስጠንጢኖስ በፊት ብዙ መናፍቃን ተነሥተው ነበር፤ ይህን መናፍቃን በሚለው ምዕራፍ ይመለከቷል። ከአርዮስ በፊት ያሉት [illegible]ኞቹ መናፍቃን ግን ብዙዎቹ ከሹመትና ከገንዘብ ከክብር ይልቅ ለትምህርት ለዕውቀት የጓጉ ይመስላሉ።

እስከ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በአየስበካው፤ የኢየሩሳሌም፣ የአንጾኪያ፣ የእስክንድርያ፣ የኤፌሶን፣ የኒቅያ፣ የቁስጥንጥንያ የሮም ቤተ ክርስቲያን እየተባለች አንደዛሬው የአንድ ቤተ ክርስቲያን አድባራትን፤ የደብረ ብርሃን፣ የዲማ፣ የተድባበ ማርያም እየተባለች በሰበካው ስም ከላይ እንደተባለው ይጠሩ ነበር እንጂ በአዕማደ ምስጢር ልዩነት አልነበረም።

ከቆስጠንጢኖስ በኋላ ግን ሃይማኖትን ተጠልሎ ሥጋዊ ሥልጣንን ማመቻቸት ሆነ፤ በዚያን ዘመን በነበረው የሮም መንግሥት ያሉት አብያተ ክርስቲያን ተጠቃለው ባራት ፓትርያርኮች፤ የእስክንድርያ፣ የአንጾኪያ፣ የሮማ፣ የቁስጥንጥንያ ተብለው ተከፈሉ። ተከፈሉ ሲባልም

በትምህርት ሳይሆን በሥጋዊ አስተዳደር ብቻ ነው። በአንዱ ክፍል ፓትርያርክ የተበደለ ወደ ሌላው ሂዶ አቤት ይል፥ ይግባኝ ይጠይቅ ነበር። ስላሞች በ7ኛው መቶ ዘመን ባቃጠሏት ቤተ መጻሕፍት ምክንያት በሊቃውንት አንደኛዋ እስክንድርያ ነበረች። በዚህ ምክንያት በ325 አርዮስን ስመዝዘት በኒቅያ ጉባኤ ሲደረግ አፈ ጉባኤው የእስክንድርያው ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ፥ የጉባኤውን ሂደት ያዘጋጀው ደግሞ የሉው ያን ጊዜ ሊቀ ዲያቆን በኋላ ፓትርያርክ ትልቁ አትናቴዎስ ነበሩ።

በሁለተኛው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ በ381 መቅዶንዮስና አቡሊናርዮስ ሲወገዙ ደግሞ ሊቀ መንበሩ አሁንም የእስክንድርያው ፓትርያርክ ጢሞቴዎስ ዘአልቦ ጥሪት ነበረ።

በሦስተኛው የዓለም ጉባኤ በኤፌሶን በ431 ላይ የቁስጥንያው ፓትርያርክ ንስጥሮስ ሲገዘት፥ ሊቀ መንበሩ አሁንም የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር።

ሦስት ጊዜ በተከታታይ ሊቃነ መናብርቱ የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት ስለሆኑ፥ በይርጋ ሂዶ ይቀራል እሉና ሦስቱም መናብርተ ፓትርያርክ ይልቁንም የሮምና የቁስጥንጥንያ በተጠንቀቅ ይጠብቁ ጀመር። የሮም ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም ሊቃነ ሐዋርያት ጴጥሮስና ጳውሎስ የሞቱ ሮም ስለሆነና የጥንትም የሮም መንግሥት መዲና ሮም ስለሆነው የቤተ ክርስቲያን መሪ፥ የክርስቶስ በምድር እንደራሴ፥ የሮም ጳጳስ መሆን አለበት ባይ ናት። ቁስጥንጥንያ ደግሞ የጊዜው የሮም መንግሥት ዋና ከተማ እኔ ስለሆንሁ የፓትርያርኮች መሪ የአዲሷ ሮም መዲና ቁስጥንጥንያ መሆን አለብኝ ባይ ናትና በዚህ ምክንያት ከሌሎች ከእስክንድርያና ከአንጾኪያ ይልቅ ሮምና ቁስጥንጥንያ ይቃረባሉ፥ ይግባባሉ፥ በብዙ ነገር ይስማማሉ። ይህ በዚህ እንዳለ ከ448-451 ቤተ ክርስቲያንን የአውጣኪስ ኑፋቄ፥ አንድ ባሕሪ (መስኮተ ትስብእትን አቀሰጠው) አተራመሳት፤ በ449 አውጣኪስ በዲዮስቆሮስ ሊቀ መንበርነት ተወገዘ፤ እንደገናም ንስሓ ገባሁ በማለቱ በተነሣው ጭቅጭቅ የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ፍላብያኖስ ሞተ። በዚህ ጊዜ ዲዮስቆሮስ የልዮንን ጦማር አላስነበብም በማለቱ በጉባኤው ላይ ጉንጭ አልፋ ክርክር ተነሥቶ ሁሉም ከኪሉ እያወጣ በሁለቱ ባሕርያት ላይ የሚመስለውን ግምት ያወራ ጀመር። ዲዮስቆሮስም አባቶቼ ይዘውት የኖሩትን ሊቀ መንበርነት ይገር ገብቼ እኔ ልምራ ቢል የልዮን መልእክተኞችና

የፍላብያኖስ ወዳጆች ወግነው እንደኛ እስክንድርያ የበላይ ሁና በይደር እንዳትቀር፥ ሁለተኛ የልዮንን ጦማር አላስነብብም ስላለ፥ ሦስተኛ ፍላብያኖስ በእሱ ምክንያት ነው የሞተው እየተባለ ስለተወራ በቁም እስረኝነት ከጉባኤ እንዲገባ ቢፈቀድለት በዚህ አልስማማም በማለቱ፥ ተገዘቱ። የተሰበሰቡበት ጉባኤም ቃለ እግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ ሁላቸውም የየበኩላቸውን እያወሩ ተበታተኑ በዚህ ጉባኤ ላይ ሮም ከብዙ ጊዜ ጀምራ ትመኘው የነበረን የዓለም አብያተ ክርስቲያን አፈ ጉባኤነት ለመጀመርያ ጊዜ ከእስክንድርያ ወስዳ በልዮን ወኪል ሊቀ ጳጳሳት መሪነት የኬልቄዶንን ጉባኤ መራች።

ዲዮስቆሮስን የሚደግፉ ምዕራብያውያንን ንስጥሮሳውያን ናቸው፥ ሁለት ባሕርይ፥ ሁለት አካል፥ ይላሉ ባሕርያቱ እንደጠባያቸው መለኮት የመለኮትን፥ ትስብእት የትስብእትን በተለያየ እንደ ሁለት አካል ይሠራሉ። ምዕራባውያን ደግሞ ምሥራቃውያንን የአውጣኪስ ተከታዮች ናቸው፤ አንድ ባሕርይ ይላሉ። በዚህም እግዚአብሔር ውልድ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ትስብእትን በነሣ ጊዜ፥ አምላክነቱ ትስብእቱን ስለዋጠው (አቀለጠው) ረቀቀ ይላሉ እያሉ አወሩ። ይህም የሁለቱ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ (ስርብትና) ብዙ ቋንቋ አጥንተን ነገሩን እስከ መረመርንበት እስከ ዘመናችን ድረስ ደረሰ።

ከ1950 ዓ.ም. ወዲህ ግን ንጉሠ ነገሥቱ ለያይተህ ግዛ ፖለቲካቸው አባቶቻችን እንዳቆዩን ይቆይ ስላሉና ለዘመኑም የንግግርና የጽሑፍ ነጻ ነት ስላልነበረ፥ ይልቁንም በአግራው ሕዝብ ላይ፥ እስከ ዛሬ ሳይነካ ቆየ።

የአራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ የተካሄደው በግሪክ ነው፤ ቃለ ጉባኤውም አለ። የልዮን ጦማርም የተጻፈው በላቲን ነው፤ እሱም አለ። በኋላ የተወራው ግን የለም። ሁለቱም ወገኖች ንስጥሮስንም ሆነ አውጣኪስን ይገዝታሉ፥ ያወግዛሉ። ሁለቱም እምቅድመ ዓለም ካብ ያለ እናት ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያላባት ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ፤ በሰማይ እናት፥ በምድር አባት የለውም ይላሉ። የክርስቶስ መዋሐድ መግለጫም "መለኮትና ትስብእት <u>ያለመለያየት፥ ያለመከፋፈል፥ ያለመቀላቀል ያለመለዋወጥ</u>" ተዋሕደው በአንድ አካል እንዳንድ መለትስ፥ እንዳንድ ፊቃጅ እንዳንድ ገባሪ ይኖራሉ ይላሉ። ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር በመለኮቱ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ እንደሚለው፥ ፍጹም አምላክ፥ ከአባቱ ጋራ እኩል በመለኮቱ፥ በትስብእቱ ደግሞ

ከኀጢአት በቀር ፍጹም እንደኛ ሰው ነው ይላሉ። አንዳንድ የሚናገሩትን የማያውቁ ዘላባጆች <u>ወልድ ዋሕድ</u> (አንድ ልጅ) ብቻ ብላ የምታምን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት እያሉ የሚዘባርቁትም በፍጹም ሐሰት ነው። ለምን ቢሉ? ክርስቶስን የሚቀበል ክርስቲያን ሁሉ እግዚአብሔር አብ በባሕርዩ ሁለት ልጅ አለው የሚል የለምና፥ አይልምና።

ምዕራብያውያን ሁለት ባሕርያት የሚሉ ሁሉ የተማሩ ከሆኑ ባሕርያት ከተዋሐዱ በኋላ አይለያዩም ይላሉ። ምሳሌ ዘየሐጽጽም (ጎዶሎ) አይቀበሉም። ለምሳሌ ዘመኑ ያለፈበት ምሳሌ የሚሰጡ የጌታ መዋሐድ እንደ እሳትና ብረት ነው ይላሉ፤ ይህ ግን መጀመሪያውንም ያላስተዋይ ምሳሌ ነው፤ ምክንያቱስ? ቢሉ እሳቱ ሲጠፋ ሙቀት ብረትን ጥሎ ይሄዳልና። ሁለተኛም እንደ ነፍስና ሥጋ ብለው ይመስላሉ፤ ይህም ከዚያው ያልተሻለ የቂል ምሳሌ ነው። ምክንያቱም ነፍስና ሥጋ በሞት ይለያያሉና። መለኮትና ትስብእት ተዋሕደዋል፤ አንድ አካል አንድ ገጽ አንድ መለትለ ናቸው ብሎ ሲያበቃ ከምስጢረ ሥጋዌ ላይ ልዩነት አለኝ የሚል ሁሉ ምድራዊና ሥጋዊ ጥቅም ፈላጊ ስርባች እንጂ ቅዱስ፥ ንጹሕ ሰባኪ ያይደለ ፈሪሳዊ ነው። ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ምዕራባዊትና ምሥራቃዊት ተብላ ተከፈለች። ያለምንም በቂ ሃይማኖታዊ መረጃ ርእሰበርሳቸው ሲገዘቱ፥ ሲወነጃጀሉ ኑረዋል።

አሁንም ክርስቶስን የሚወዱ ደጋግ መሪዎች ካልተነሡ በቀር ለብዙ ጊዜ ይኸው ብጥብጥ የሚቆይ ይመስላል። በግራ ቀኙም በኩል የኬልቄዶን ጉባኤ በሃይማኖት ልክ ነበረ የሚል ማስረጃ ያለው ሊቅ ቢመጣ፤ እንዴት ጥሩ ነበር። ምሥራቃውያን እውጣኪስን፥ ምዕራባውያን ንስጥሮስን የማይከተሉ ከሆነ፥ ለመከተላቸውም ጠላት ያወራው፥ ባላንጋራ የነዛው እንጂ የራሳቸው ጸሐፊ ወይም ደራሲ ከሌለ፥ ፍቅርን የሚፈልግ እውነተኛ ክርስቲያን ሁሉ ዛሬውኑ የተዋሕዶን መንገድ መመልከትና መያዝ አለበት።

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ምሥራቃውያንና ምዕራብያውያን ወይም ምሥራቃዊትና ምዕራባዊት ተብላ ከሁለት ተከፈለች። ምሥራቃዊት እምስት ቅርንጫፍ አበጅታ ስትኖር እንዲያውም ይህ በዝቶባት ስልምና መጣና ወረራት። ምዕራባዊት ደግሞ በአለቅነት፥ በትዕቢት፥ በአስተዳደር ምክንያት ተጣልታ፥ የካቶሊክና

የግሪክ ኦርቶዶክስ በሚል ስያሜ ከሁለት ተከፈለች። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በ16ኛው መቶ ዘመን የትምህርት አሰጣጡንና አስተዳደሩን እናሻሽላለን በሚሉ ሉተራውያን ምክንያት ከሁለት ተከፈለች።

ከዚህ በኋላ በጠላቶቻቸው ፕሮቴስታንት (ተቃዋሚ) በራሳቸው ወንጌላውያን የሚባሉት ደግሞ ስመለያ ምክንያት እየፈጠሩ ተለያዩ።

የወንጌላውያንን የሃይማኖት ድርጅቶች በአሁኑ ዘመን አቆጥራስሁ ግለት በጣም አስቸጋሪ ነው። በቂ ልዩነት ግን የላቸውም። ፍቅረ ሢመት ባይዛቸው በአንድ ዓመት ውስጥ ጉባኤ አድርገው መገናኘት ይችላሉ።

በዚህም ምክንያት ግንም የበሽር ልጅ እንደወለደ ሁሉ አዳዲስ ስም እያወጣ፥ በእየጎጡና በእንዳንድ ራሱን ወዳድ ስም ልክ እንደ ስርበታ ይጠሩ ጀመር። ስለዚህ መጀመሪያ በሃይማኖትና በሰብዓቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን፥ በእምስቱ አዕማደ ምስጢር፤ ምስጢረ ሥላሴ፥ ምስጢረ ሥጋዌ፥ ምስጢረ ጥምቀት፥ ምስጢረ ቁርባን፥ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን (በእምነት) ሀብተ ጥምቀት፥ ሚሮን፥ ቁርባን፥ ንስሐ፥ ክህነት፥ አውሰቦ (ጋብቻ) ቀንዲል፥ (በሥርዓት) በእነዚህ የሚያምኑ፤ የኢትዮጵያ የግብጽ፥ የእንጾኪያ፥ የአርመን፥ የሕንድ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት፥ የግሪክ ኦርቶዶክስ የሮም ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያናት የአገልግሎት ልዩነታቸውን በእየራሳቸው እንደያዙ አብረው ቀድሰው ቆርበው፥ የጋራ ጠላታቸውን ሥጋዊነትንና ሰይጣንን መዋጋት አለባቸው።

የቀረው ይቅርና የካቶሊክና የእንግሊዝ አብያተ ክርስቲያናትስ ተለያይቶ መኖር አይገርምም ወይ? ሁስቱም ካቶሊኮች ነን ይላሉ። ግን ለሥራትና በሥልጣን በገንዘብ ምክንያት ጎን ለጎን ሲሄዱ ይኖራሉ። ለዚህም የሁለቱንም የጸሎትና የአዕማደ ምስጢር መጻሕፍት ማየት ይበቃል። እሉም ለመረጃ በተጠቀሱት መጻሕፍት ተዘርዝረዋልና አንብቦ መረዳቱን ለአስተዋይ አንባቢ ፈንታ ነው ተብሎ ታልፏል።

በምስጢረ ጥምቀትና በምስጢረ ቁርባን የሚያምኑትን ከተንታውያን አብያተ ክርስቲያን ጋራ ምን ለያቸው? በእነሉተር መሪነት ከሮም ቤተ ክርስቲያን የተለዩት ወንጌላውያን ደግሞ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋራ የተጣሉት በሃይማኖት ሳይሆን በአገልግሎት ሥርዓትና በአስተዳደር፥ ቤተ ክርስቲያንን ከክርስቶስ ጋራ ለማገናኘት ብለው ሰሆነ፥ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያንን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ በእነዚህ

በሁለቱ መጻሕፍት መሪነት አገናዝበው አንድ ቢሆኑ ፍጹም የክርስቶስ ተከታዮች ይሆናሉ፥ ሁነው፥ አንድ ክርስቲያን ይባላሉ።
እንድነታቸውም ጠሳታቸውን ሁሉ ባሸነፈ። ይህ ካልሆነ ግን፥ ከመ ደርከብ ሰብእ ሢመተ ብዙኅ ኀሠሣ፥ ካህን ለቅንዓቱ ሃይማኖተ ያለብሳ። በሰው ዘንድ የምትፈለግ ሹመትን ለማግኘት ካህን ቅናቱን ሃይማኖት ያለብሳታል የሚለው ቅኔ ይደርስና የሹመት ባሪያ፥ የጥቅም ተገዥ፥ የገንዘብ ሰባኪ ሁና ኑሮ ማለፍን ያስከትላል።

<u>ማስጠንቀቂያና ማስታወቂያ፤</u>

የኬልቄዶን ጉባኤ ሃይማኖታዊ ልዩነት ነበረው፥ ምዕራባውያን እንደሚወራው እንደ ንስጥሮስ ሁለት ባሕርይ ሁለት አካል ብለው ከተዋሐዱ በኋላ ተለያይተው መለኮት ግብረ መለኮት፥ ትስብእት ግብረ ትስብእትን ይሠራሉ፥ ምሥራቃውያን ደግሞ እንደ አውጣኪስ መለኮት ትስብእትን አጥፍቶታል፥ አቅልጦታል፥ ከዚያም አልፎ እንደ ኀድረት ነው የሚል ነቃፊ ወይም ህያሲ ጉባኤ በተካሄደበት ቋንቋ ቢሆን ፀግሪክ ያለዚያም በሳቲን መረጃ ሰነድ ካሳመጣ በጋዜጣም ሆነ በመጽሐፍ ጉንጭ አልፋ ተቃውሞ እንደነ አባ መሸ በከንቱው ያለ የመጽሐፉ ባልቴት ጥቅስ ቢያቀርብ መልስ የማይሰጥ መሆኑ በቅድሚያ ይገለጣል።

<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ለዚህ ምዕራፍ አስተዋፅኦ ያደረጉ መጻሕፍት</u>

1. ሉሌ መልአኩ፥ <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥</u> ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1986 ዓ.ም. ገች 45-48
2. ዐሥራት ገብረ ማርያም፥ <u>ትምህርተ መለኮት፥</u> አርቲስቲክ ማ/ቤት፥ 1983 ዓ.ም.ገች 58-84።
3. <u>The Book of Common Prayer and Administration of the Sacraments and other Rites and Ceremonies of the Church according to the use of the Church of England.</u> Oxford University Press.
4. <u>The Catechism of the Catholic Church.</u> Poulines Publications, Africa 1994, pp.213-224.
5. <u>The Christian Faith.</u> Ed. Neuners, J., 2nd Edition, The Merciers Press, Dublin and Corks, 1976,pp. 138-146.

Messale Dell, Assemblea Cristiana, Festivo, Ed. Elle Di Ci-Esprienze, Torino-Leumann, 1979.

6. Messale Dell' Assemblea Crstiana, Feriale, Ed, Elle Di Ci- Esperienze, 1979.

7. O'Mahnney, Kevin, M. Afr., The Sprit and the Bridge, A Manual of Church History, Book one, United Printers, Addis Ababa, 1994.pp. 109-130.

8. Pope John Sanday Missal, A Treasury of Catholic Spirituality, Ed. Mgr. Buckley, Michall, Kevin Mayhew LTO. 55 LEIGH Road. pp. 11-53.

9. The Scotish Book of common Prayer and Administration of the Sacraments and other Rites and Ceremonies of the Church, Cambrige University Press, Londnn, 1929,pp.326-516.

10. Stephanidis, Basil Church History from the Beginning to the Present (in Greek), Aster, Athen, 1948, pp.191-227.

11. The Vienna Dialogue, Five Pro Oriente Consultations, with Oriental Orthodoxy Communque's and Common Declarations, Booklet Nr.1.

## ምዕራፍ ስድስት

### ቤተ ክርስቲያንን ያለያዩዋት አውጣኪስና ተከታዮቹ

አውጣኪስ በቁስጥንጥንያ አንድ ቤተ ክርስቲያን የነበረ ቆምስ ነው። የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ንስጥሮስ ወልድ በመለኮቱ አንድ አካል አንድ ባሕርይ፥ በትስብእቱ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አለው፥ በፍጹም የተለያዩ፥ ያልተዋሐዱ በአየራሳቸው የቆሙ ሁለት ባሕርያትና አካላት አሉት በማለቱ ከላይ እንዳየነው በኤፌሶን ጉባኤ ስለተገዘተ ይህን እርሞ ለማስታረቅ ይመስላል፤ አውጣኪስ ደግሞ የእግዚአብሔር አብ ልጅ መለኮት ከድንግል ማርያም ሲወለድ ትስብእትን (ሥጋን) አቀለጠውና መለኮት ብቻውን ተወለደ፥ በዚህ ዐይነት በመወለዱም አንድ ባሕርይ ሆነ አለና ዐረፈ። ይህም ያለምንም የተዋሕዶ ችግር አንድ ባሕርይ አንድ አካል ለማለት አመቸ። በዚህ ትርጉም ዛሬ አንድ ባሕርይ የሚል ማንም የለ። የዲዮስቆሮስ ተከታዮችም ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሲሉ መለኮትና ትስብእት ተዋሕደው አንድ መለትስ (አንድ ገጽ) ሆኑ ለማለት እንጂ በኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ አንድ መለትስ መሆኑን ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ብለው ያረጋግጣሉ።

ከዚህ ላይ ለማንኛቸውም አንባቢ ፀረ መቄዶንያውያንና መቄዶናውያን የተጣሉበትን መግለጥ ያስፈልጋል፤ መጀመሪያ ባሕርይ ግሪክ ፊሲስ፥ ላቲን፥ ናቱራ፥ እንግሊዝ ኔቸር) የግሪክ ፈላስፎች ውሳኔ ስለሆነ ለምሥራቃውያን በጣም አስቸጋሪ ነው። ባሕርይ ጠባዕይ፥ አመል፥ ተፈጥሮ ይሆናል፤ በምዕራብያውያን ዘንድ ባሕርይ የጠባይና የተፈጥሮ ትርጉም ነው ያለው። ስለዚህ ሁለት ባሕርይ ሲሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አካል፥ (ሰውነት፥ ገጽ) መለኮትና ተስብእት <u>ያለመለያየት፥ ያለመከፋፈል፥ ያለመቀላቀል ያለመለወጥ</u> ተዋሕደው በአንድነት በአንድ አካል ይኖራሉ ይላሉ። ይህም ለመለትስ የተሰጠው ትርጓሜ ነው። በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካል፥ ገጽ body ና person ህላዌ፥ ህሉና፥ ተቋዋም፥ ጠባዕይ ማለት ይሆናል። ለዚህም ለአብ ፍጹም አካል ፍጹም መልክ፥ ለወልድ ፍጹም አካል ፍጹም መልክ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል ፍጹም መልክ አለው ትላለች። ምዕራባውያን ግን አካልን የሚሰጡት ለሚታይና ለሚዳሰስ ብቻ ነው።

(body) እንደኛ እንደ አካል ሁለት ነገር በአንዱ ቃል አያይም። ስለዚህ አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋ ባለመልበሳቸው የማይዳሰሱ መንፈሳውያን ስለሆነ ገጽ (person, prosopon) ህላዌ፥ ህሉና፥ ኩነት እንጂ አካል

የላቸውም ይላሉ፤ በእነሱ አስተሳሰብ ለሥላሴ አካል የላቸውም ይላሉ፤ በእነሱ አስተሳሰብ ከሥላሴ አካል ያለው ወልድ ብቻ ነው። ይኸውም የሚታይንና የሚዳሰስን ትስብእት ስለለበሰ፥ የሚዳሰስ አካል የሌለው መንፈስ፥ ረቂቅ መለኮት አካል ያለውን ግዙፍ ሥጋ (ትስብእት) ስለለበሰ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ መለትስ ይላሉ። የመለኮትና የትስብእት ጠባዕያት ተዋሕደው በአንድ በክርስቶስ አካል ሰላሉ። መለኮትና ትስብእት በመዋሐዳቸውም አባቱ አብም እናቱ ማርያምም ልጄ! ልጄ! ይሉታል፤ መርያምም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ተዋሕዶ የተወለደ መለኮትን ስለወለደች ወላዲተ አምላክ ትባላለች፥ አብም በተዋሕዶ አንድ አካል ከልጁ ጋራ የሆነ ትስብእትን የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር መስክሯል።

በዚህ ላይ ምሳሌ ዘየሐጽጽ ሊሰጥ ይችላል፤ ማንኛቸውም ሰው ከእናትና ከአባት ይወለዳል፤ በአባቱ ግብጻዊ በእናቱ ኢትዮጵያዊ ሲሆን ይችላል፥ በአካሉና በሕርዩ አንድ ሳለ፥ ሲሆን ከግብጻዊ አባት ከኢትዮጵያዊት እናት በመወለዱ ሁለት ሰው አይባልም፥ የወላጆቹ ደም ተዋሕዷልና፥ ስለዚህም ሁለቱ ወላጆቹ ልጄ! ልጄ! ይሉታል። በዚህ ምሳሌ አንጻር ክርስቶስም የአባቱን መለኮትና የእናቱን ትስብእት ያለመለወጥ፥ ያለመከፋፈል፥ ያለመለያየት ያለመቀላቀል አዋሕዶ የያዘ አንድ አካል አንድ መለትስ ነው።

የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከንስጥሮስ ክሕደት ሁለት ሁለት የሚለው ለመሸሽ ነው እንጂ ትስብእትና መለኮት (መለትስ) ተዋሕደው በአካለ ኢየሱስ ክርስቶስ መኖራቸውን፥ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን፥ መለትስም (መለኮትና ትስብእትም) ያለመለያየት፥ ያለመከፋፈል፥ ያለመቀላቀል፥ ያለመለዋወጥ ስለተዋሕዱ (ልብ አድርጎ ይመለከቷል፤ ተዋሐዱ እንጂ አልተጠፋፉም) አንድ አካል አንድ ባሕርይ አንድ ፈቃድ፥ አንድ ግብር መሆኑን ታምናለች። አሁንም ለመለያየት የሚችሉት ሁለት አካላትና ሁለት ባሕርይ ለመሸሽ እንጂ ወልድ በመለኮቱ እንደ አብ አምላክ እንደ እናቱ ደግሞ እንደኛ ሰው አይደለም ማለት አይደለም። (መ.ቅ.ገ. 132፡ ቁ.100)

እንደዚህ ጉባኤ የሰካራም ጥርቅም ይመስል፥ አንዱ ጓደኛው የሚለውን ሳይለማ ወይም ሰምቶ ለማጭበርበር ሌላውን የገዘተበት፥ የረገመበት፥ ያወገዘበት ሌላ የዓለም ጉባኤ የለም ቢባል ከእውነት አይርቅም።

ዲዮስቆሮስ የልዮንን ተከታዮች ኬልቄዶናውያን እንደ ንስጥሮስ ያልተዋሐዱ ሁለት ባሕርያት ክርስቶስ አሉት ያሉ አስመስሎ ገዘተ። ኬልቄዶናውያን ደግሞ ዲዮስቆሮስን የአውጣኪስ ተከታይ አስመስለው ያላላውን፥ ያላሰበውን ይላል፥ አምኗል ብለው ገዘቱ። ከዚህ በኋላ ዲዮስቆሮሳውያን ኬልቄዶናውያንን መለኮት ይገብር ግብረ መለኮት፥ ወትስብእት ይገብር ግብረ ትስብእት (መለኮት የመለኮትን፥ ሥጋም የሥጋን ሥራ (በእየራሳቸው) ይሠራሉ ይላሉ ብለው አወሩ፤ ማውራት ብቻም ሳይሆን ይህን ወሬ የሚያምኑ ብዙዎች አሁንም አሉ።
(Kevin O. Mohoney. Op. Cit. pp. 109-130)
ይህ የሐሰት ወሬ እውነት መሆኑን ግን ከቃለ ጉባኤው ጠቅሶ የመያስረዳ ወይም የሚያሳይ የለም። እምቅድመ ዓለም ከአብ ያለእናት፥ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያላባት ተወለደ፤ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ሳይቀላቀል፥ ሳይለያይ፥ በተዐቅቦ ከበረ የሚል ሁሉ ፍጹም እርቶዶክስ ነው። ይህንም ወረስዮ አሐደ ምስለ መለኮቱ ዘእንበል ቱስሕት ወኢትድምርት ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ= ያለ ትጽምርት ያለመቀላቀልና ያለትድሞርት (መጨመር) ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋራ አንድ ያደረገው ብሎ አረጋግጧል። (መ.ቅ.ገ.132፤ ቁ.100) ከላይ እንደተገለጠው ሁለቱ ባሕርያት መለትለ (መለኮትና ትስብእት) በእየሉለ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር አካል እንዳሉ ያምናሉ፤ አምነውም ያስተምራሉ፤ ይህን የሚከዱ ሁሉ፥ ዜማና ቅኔ ብቻ ተምረው መጽሐፍ መማሩ ይቅርና ሳያነቡ እናውቃለን የሚሉ፥ ያልተማሩ እነደርሰ ሊቅ፥ መሆን አለባቸው። በቃል፥ በባሕርይ ልዩነት አለን የሚሉ ሹመት፥ ገንዘብ የሚፈልጉ፥ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፥ እርስበርሳችሁ ተፋቀሩ፥ እርስ በርሳችሁ ብትፋቀሩ ዓለም የኔ ደቀ መዛሙርት መሆናችሁን ያውቃል ያለውን የካዱ፥ በሰው መሃል ጥላቻ የሚዘራውን እኩይ የሚከተሉ ናቸው። (ዮሐ.13:35-36) ከላይ እንደተገለጠው ንስጥሮስን በኤፌሶን በ431 ዓ.ም. 200 ሊቃነ ጳጳሳት እንደገዘቱ አውጣኪስን ደግሞ ለማውገዘ ከቁስጥንጥንያ አጠገብ በምትገኝ ኬልቄደን ትንሽ ከተማ 650 ጳጳሳት ተሰብስበው በ451 ዓ.ም. በቅድሚያ (ሹመት) ምክንያት እሉን በማውገዝ ፋንታ እርበርሳቸው ተወጋግዘው ተለያዩ። ታድያ በአውጣኪስ ምክንያት የተጣሉት ክርስቲያን፥ በብዙ ቋንቋ መግባባት በተቻለበት በአሁኑ ዘመን፥ የተጣሉት በቃል እንጂ በትምህርት (በዶክትሪን፥ በምስጢር) ካልሆነ ለምን ችግራቸውን በዙሪያ

ጠረጴዛ ፈትተው በኅብረት እየተረዳዱ አይኖሩም? ስሚል ጠያቂ፥ መልሱን የያዙት ቀድሞ አስማወቅ ስርብትና፥ እሁን ደግሞ ጥመት፥ ቅናት፥ ምቀኝነት፥ ሥልጣን፥ ፍቀረ ንዋይ፥ ሹመት፥ ትዕቢት፥ ጸሊአ ቢጽ (ወንድምን መጥላት) ሁነው ይገኛሉ። የሚያውቁት ይፈራሉ፤ የማያውቁት ደግሞ ከኪሳቸው እያወጡ በሮማና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን፥ ሊኖር ይገባው የነበረን ግንኙነት ዐውቆ አፍራሾች (ስባኪዎች) እኔ ጴጥሮስ ፓኤዝ ባለሰለሱት መሬት ጠብ ዘርቶ፥ እሜካላ እብቅሎ እስካ ሁን ካዘገየው አንዱ ክሮማ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ተብሎ ተሹሞ የመጣ ው የሚጎዶዝ አልፎንስ ስሕተት ነው። ሜንደዝ እልፎምሱ ኢትዮጵያ የአ ውጣኪስ ተከታይ በኀድረት የምታምን፥ እንድ ባሕርይ ባይ ናት ብሎ ስለ ሚያምንና የስብከት ዘዴ ስለሚጎድለው፥ እሥመራ እንደ ደረሰ ከዛሬ ጀም ሮ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በካቶሊክ ሥርዓት መጠመቀ እለባቸው ብሎ ዐወጀ። ኢትዮጵያውያንም ሃይማኖታችንም ርትዕት ናት፥ ሥርዐታችንም ልክ ነው፥ ስለዚህ እንደገና እንጠመቅም፥ እንካንም፥ ቤተ ክርስቲያናችንንም በካቶሊክ ቄስ እናስባርክም፥ እናስቀድስም አሉና በንጉሡ ላይ ዐመፁ፤ በዚህም ለብዙ ዓመት ጦርነት ተደረገና ብዙ ደም ፈሰሰ። የስርብትና ወሬ ተነዛ፥ የፕሮፓጋንዳ ጽሑፍ ተበተነ፤ በእየገዳሙና ደብሩ ካቶሊክ ጠላታችን ነው እየተባለ ለሕዝብ ሁሉ ተስፈፈ። ይህም እስከ ጊዜያችን የደረሰ ስብከት ነው። የሁለቱን ቤተ ክርስቲያን ሰላምም ከሦስት መቶ ዓመት በላይ አደፍርሶ ኑሯል። የአንድ መሪ አካሄድ ኅብረተ ሰቡን እንዴት እንደሚጎዳ በአልፎሱ ለመረዳት ይቻላል። እሁን ደግሞ የእልፎንሱው ስሕተት መሆኑ ሲታወቅ፥ በእኛ ቤተ ክርስቲያን በኩል ስክርክራቸው አንድም መረጃ ሳይዙ የተጀመረውን የሰላም ጉዞ፥ የዕርቅ ጎዳና ለመበጥበጥ ስለጀመሩ እነዚህ ሰዎች ምን እንደሆኑ ስምእመናኑ ለማስጥ ተገደድን። ምክንያቱም ውስጡን ያላወቀ ጎጋ የተናገሩት ዐዋቂ ሰዎች መስለውት እንዲህ ብለዋል እያለ ሲበጠብጥ እንዳይኖር ነው።

በእለፈው ያላጠፉ ወገን የለም፥ የኛ አባቶች ልክ ናቸው የእናንተዎች ተሳስተዋል፥ ተሳስተው ነበር ለማለት አይቻልም። ያለፉት ብለውም ይሆናል፥ ሳይሉ ለስርብትና ተወርቶባቸውም ይሆናል። እሁን ሁላችንም የምናምነው እንድ ከሆነ፥ ጉባኤ ሊቃውንት እድርገን፥ ችግራችንን ተወያይተን ፈትተን እንገናኝ።

—

ከላይ እንዳየነው በ16ኛው መቶ ዘመን በተደረገው በሚንደዝ እልፎንሱ ስሕተት ብዙ ደም ፈሷል። ግን ይህ ያንድ ሰው ስሕተት ለዘለዓለም የጥል ግድግዳ ሁኖ ሊቀር አይገባም፥ መሆንም የለበት። በዘመናችን ምዕራባውያን ለመገናኘት እየጣሩ ነው።

I. በI054: የተለያዩ ሁለቱ የቆስጥንጥንያ ፓትርያርክና የሮም ፖፕ ሮም ቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል ውስጥ የጴጥሮስንና የጳውሎስን በዓል በሚያከብሩበት ዕለት ሰኔ 29 1987 በአንድነት ጸለዩ፥ ቀደሱ። (The Ethiopian Herald Saturday 1 July 1995, P.7)

2. ከግብጽ፥ ከእንጾኪያ፥ ከአርመን እብያተ ክርስቲያን ጋራ አንድ መሆናቸውን አረጋግጠው ተፈራረሙ። (ጦማር ሐምሌ I0 1988፥ገጽ 4) ተዋሕዶዎቹ ግን፥ የሚገባቸው የተማሩትም ስርብትና ፈርተው ኀጋዎቹም ስለማያውቁት፥ እናጥናው ቀን ስጡን ብለው እያኮተመተሙ ናቸው።

3. የሮም ቤተ ክርስቲያን በአጠገባችሁ ምስጢረ ቁርባንን ከሚቀበሉ እብያተ ክርስቲያን ሂዳችሁ ተቀበሉ ብላ ለተከታዮዎችዋ ፈቃድ ሰጥታለች።

4. የራስዋ እብያተ ክርስቲያንም በእየሀገሩ ሥርዓትና ቋንቋ እንዲያገለግሉ አዝዛለች። ትእዛዙም እየተፈጸመ ነው።

5. Joint Declaration on the Church Unity by his H.H, Pope Paul II and H.H. Sheroda III Pope of Alexandria and Patriarch of the See of St. Mark of Alexandria (10 May 1973) Acta Apostolica Sedis (AAS) 65 (1973) PP.299-301.

6. Joint Decharation of the Unity of the Church by H.H. Pope VI and his Beatitude Mar Ignatius Jacob III. Patriarch of the Church of Antioch of the Syrians (27 October 1971) pp. 814-815

7. Common Christological Declaration between the Catholic Church and the Assyrian Church of the East, by H.H. John Paul II with the Patriarch of Assira. L' Ossorvatore Romano, 12 November 1994, p.1

በዚህ መሃል እንዲህ ባለው ዘመን የሃይማኖትን መስፋፋት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን እድገት የማይፈልጉ፥ መረዳዳትን የማይፈቅዱ፥ ትምህርተ መለኮትን የማያውቁ፥ በቅኔና በዜማ የሚራቀቁ፥ ቀጥተኛውን ትምህርት

በአንድም ሰም ሲያጣምሙ የናሩ አነ ደርሶ ሊቀ፥ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ሊቃውንት ሰም ተቀምጠው ወፍራም ደመወዝ የሚበሉ፥ አባታችን ፓትርያርኩ ግሪክን፥ ቁስጥንጥንያን፥ ሮምን፥ ሌሎችንም መሰሎቻችንን እኅቶቻችንን አብያተ ክርስቲያናት ጎብኝተው፥ ተባብሮ ለመሥራት ተነጋገሩ ብለው፥ ካህናት እንዲነሡባቸው ጳጳሳት እንዲያወግዟቸው፥ አምና በጥቅምት 17: 1987 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና ቅዱስ ፓትርያርክ የሚል ርእስ በተኑ። ያ የተበተነው ምንም ሳይሠራ ጊዜ ዘንድሮ ደግሞ ሊቃውንቱና ጳጳሳቱ በተሰበሰቡበት፥ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያን ጋራ ተነጋግረዋልና ፓትራያኩ ይገዘቱ ብለው ረጅም ንግግር አደረጉ። ለዚህ ለመቻ መሪም አለቃ አያሌው ታምሩ የቅኔውና የዜማው ሊቅ የትምህርት መስኮቱና የመጽሐፉ ግን ዕንግዳ ይመስላሉ ናቸው፤ ለምን እንዲህ ትላለህ? የሚል ሰው መልሱን በሚከተለው ምዕራፍ ይመልከት።

## ምዕራፍ ሰባት

### የኬልቄዶን ጉባኤ ተሳታፊያንም እንደነዚህ ነበሩ፤

ፍቅረ ሢመት፥ ፍቅረ ንያዋይ፥ ጸሊአ ቢድ፥ ተዝኅሮ (ትዕቢት፥ ኩራት) በአሉበት ሐቅና ሃይማኖት አይዞሩም። ኬልቄዶናውያንን ያፋጀዋቸው እነዚህ ነበሩ። አሁን በአለቃ አያሌውና በፓትርያርኩ መካከል እንደ ተደረገው፥ አለቃ ሳይነሡ መታለፍ ተፈልጎ ነበር። አሁን ግን የማያውቁትን የሥነ መለኮት ትምህርት አርግለሁ ብለው ሁሉም ሁሉን ይወቅን ሊነቀፉ ሰስተነሡ ዐቅማቸውንና ምንነታቸውን ከዚህ ቀጥሩ ገልጠው በጋዜጣ ደግሞ ለመተንተን ተገደድሁ። ምንም እንዲህ ያለው መጽሐፍ እንደ ጋዜጣ የግለ ሰብእ ስም ማንሣት ደግ ባይሆንም የመጽሐፉ ዓላማ ክርስቲያን በክርስቶስ የምታምን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በቀጥታ አተረጓጎም የምትቀበል ሁሉ፥ አንድ ነህ፥ አንድ ሁን፥ እንደ መጀመሪያዎች ክርስቲያኖች፤ አንድ ሁነህ ወገንህን አስተምር፥ አለቃህን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከተል፥ አንድ ሁነህ ሃይማኖትህን ስበክ፥ ወገንህን ርዳ፥ ጠላትህን በትዕግሥት ተከላከል የሚል በመሆኑ የአለቃ አያሌው ተአምሩን ምንነትና ትምህርት ለመግለጥ ግዴታ ሆነ። ከሁሉ አስቀድሞም

---

ደራሲው በሹመትም ሆነ በዘር የማይወግን መሆኑ ለክቡር ውድ አንባበ ይገለጣል። ዓላማውም መሪዎችህ ነን የሚሉ ካህናት አብዛኞቹ ስብርትና (ፖለቲካ፥ ፕሮፓጋንዳ) እንጂ ሃይማኖቱን አያውቁትም አውቀውም አያስተምሩትምና ራስህን አውጣ፥ ነፍስህን አድን፥ መጻሕፍትን በራስህ ተመራምረህ፥ ሲጠንህም ሥጋዊ ጥቅም ካማርካቸው፥ ከንቱ ረብሕ ካላወራቸው ጠይቀህ ተረዳ ለማለት ነው። ለዚህም መጀመሪያ የአለቃ አያሌውንና የመሰሎቻቸውን፥ ከዚያ በቅዱስ ሲኖዶሱ ስም በእየጊዜው የሚበተኑ ልክ ያልሆኑ ጽሑፎችን እንገልጣለን።

ክርስትያን እርስ በርሱ ቢረዳዳና የጠላቱ ሰላይና መንገድ መሪ ባይሆን ኑሮ፥ መካከለኛውን ምሥራቅ ስልምና በመቶ ዘመን ባልወረረውም ነበር። አሁንስ በዚህ ዓመት በአቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያና በአለቃ አያሌው መካከል ያለው እንኪያስላንቲያ ምን ያሳያል? ምን ያስረዳል? ምን ያስተምራል? ሃይማኖት ወይስ ሹመትና ጥቅም? እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሱ ነው ወይስ እያነጹ? ወገናቸውን ምእመኑን ነው? ወይስ የቤተ ክርስቲያኒቱን ጠላቶች? ወንጌል እንዳትሰበክ መሰናክሉን ሁሉ ሲፈጥሩ የሚያድሩት አወናባጆች በስመ ክርስቲያን፥ በግብረ ረበናት የሚኖሩት ሁሉሳ? ያስተምራሉ ወይስ ይዘጋሉ?

አለቃ በእሳቸው ስብሳቢነት ከሚሰበሰበው ጉባኤ ሊቃውንት ተባባሪዎቻቸው ጋራ የአባቶቻችን ተረት ነፋስ ዐይቶ ምን አይል ጓደኛውን ያስቀድማል እንደሚለው፥ ይህን ብንል ሰው ይቀበለናል፥ ይህን ብናወጣ ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ ያልተማረ ስለሆነ ይቆጣናል፥ ሕዝቡ ከሚቆጣነስ ውሸት ነግሣ፥ ድንቁርና ስፍና ትኑር ብለው፥ ከሥነ ጽሑፍ ፈረስ ላይ ተቀምጠው በሴንሰር ልጓም ለጉመው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለ34 ዓመት ወደኋላ የነዱ ሰው ናቸው።

1. በ1975 ዓ.ም. በሀገራችንና በዘመናችን ለመጀመሪያ ጊዜ ምስጢረ ቁርባንን ጌታ የሰጠው ለስርየተ ኀጢአት ስለሆነ ሳትበቁ በቅታችሁ፤ ሳትነቁ ነቅታችሁ ብትቀበሉት ሥጋው እሳት ሁኖ ይፈጃችኋል፥ ደሙ ባሕረ እሳት ሁኖ ያስጥማችቀል የሚለው ዐዋጅ ኢክርስቲያናዊ ስለሆነ፥ እምናችሁ፥ ከኀጢአታችሁ ንስሓ ገብታችሁ፥ ከኀጢአታችሁ ለመንጻት ተቀበሉ፥ የሚል ክታብ ቢበተን፥ ስለተበተነ፥

ቁጡ ሰው ቆረበ፥ የቀረውም እንዲህ ከሆነስ እንቆርባለን ብሎ ሲሰናዳ ጊዜ አጅሬም፥ ተከታዮቻቸውን ይዘው፥ ሥጋውና ደሙ መቀበጃ አይደለም፤ ስለዚህ በሕይወት ሦስት ጊዜ ብቻ ነው የሚቆረበው፤ ይኸውም፥ ሲወለዱ፥ ሲጋቡ፥ ሲሞቱ ነው ብለው ፀረ ክርስቶስ ሰብከት ሲሰብኩ ከረሙ፤

2. በዘመነ ደርግ ክርስቲያኖች ይጨቆኑ ስለነበረ፥ የተወሰኑ ቅዱሳት እንስት እኒህን ሰው ይጠይቋቸው ነበር፥ ከእነዚህ አንዷ ባሌን መንግሥት አሜሪካ ለሥራ ልኮት ሂዷል፥ እኔም እሱም ንጹሕ ነን፥ መቁረብ እፈልጋለሁ ብትላቸው ባልሽ ካጠገብሽ ከሌለ አትቆርቢም ብለው ከለከሏት። አዎ! በዘመኑ የቀበሌ ዳቦም በድርጅት ነበር የሚሰጠውና ከዘመኑ ተስፈንጣሪ ላለመሆን።

3. ከቦታው ለሰማርያም ስንናገር እንደምናየው ማርያምን ከጥንተ አብሶ ያነጻት መንፈስ ቅዱስ ነው እያሉ በ1953 በወጣው መጻፋቸው ሊያስተምሩና ሲሸጡ ኑረው አሁን እንአተ ዐሥራት ሐሳባቸውን ደግፈው መጽሐፍ ቢጽፉ፥ ለስተሸጠ ቀንተውም ይሁን ወይም ሐሳባቸውን ለውጠው አይታወቅም፥ የዐሥራትን መጽሐፍ አትግዙ እያሉ ዐወጁ።

4. እራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስንና ሰብከት የተማሩ ስዊድን ሚሽን ሲሆኑ ሰውን ግን ከመካነ ኢየሱሶች ጋራ አይነጋገር ይላሉ።

5. ሰብዓቱን ሀብታተ ቤተ ክርስቲያንን (ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያንን) ከእምስቱ አዕማደ ምስጢር ጋራ አማትተው፥ አምስት እንጂ ሰባት አይደሉም ይላሉ። በዚህም ሀብተ ክህነትንና ሀብተ ተክሊልን ይክዳሉ።

6. ከእሳቸው ተረትና መጽሐፈ ባልቴት ጋራ የማይስማማውን የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ሁሉ እንዲስማማቸው ለማድረግ ሲሉ አበላሽተውታል።

ይህም በ1975 በእሳቸው መሪነትና ሰብሳቢነት ተተርጉሞ ቤተ ክርስቲያን አሳትማ ዛሬ በአየቤተ ክርስቲያኑ ለአገልግሎት በሚነበበው ሐዲስ ኪዳን ይታወቃል። ለምሳሌም የሚከተሉትን ቁጥሮች ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ጋራ ማስተያየት ይበቃል። ሮሜ.8:34፤ ዕብ.7:25፤ 9:15) እነዚህንና ሌሎችንም ጥቅሶች አንደኛ ከ1840 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን ከተተረጎሙት ልዩ ልዩ የአማርኛ ትርጉሞችና ከምታውቃቸው ባዕዳን ቋንቋዎች ትርጉሞች ጋራ አነጻጽረህ እኒህ ሰው በቤተ ክርስቲያንና ሃይማኖት ላይ ስንት ነገር እንዳጠፉ ትረዳ ዘንድ

ትጠቆማለህ። ይህ ትርጉም በመጽሐፈ ባልቴት የሚመራ ተረት አዘል ስለሆነ መሰብሰብ አለበት።

7. አለቃ በቅድስት ማርያም ምዕራፍ ይህንም እንደምናየው፥ ማርያምን ከጥንተ አብሶ ያነጻት መንፈስ ቅዱስ ነው እያሉ ሲሰብኩ ሲያስተምሩ ሲጽፉ ኑረው፥ ከኖሩ፥ ከጻፉ በኋላ አሁን ተመልሰው ጥንተ አብሶ አልበረባትም፥ ከዚያም አልፈው እነ እገሌ እንዲህ ስላሉ ፀረ ማርያም ናቸው እያሉ ሰውን ከሰው ሰማጣላት ይሰብካሉ። ከስሕተታቸው አይመለሱ አይባልም፥ ግን ብዙ ሕዝብ ያጠፉበትን ስሕተታቸውን በይፋ ለቤተ ክርስቲያን ተሳስቻለሁ ብለው ነግረው ንስሓ ገብተው ነው መመለስ ያሰባቸው።

8. ለጦማር ቃለ ምልልስ መጋቢት 18:1988 ዓ.ም. በሰጡት መሠረት ከ53 ዓ.ም. እስከዛሬ ጉባኤ ሲቃውንትን ሲመሩ የኖሩ እሳቸው ናቸው፤ ይህም ማለት በቤተ ክርስቲያን ስም የሚታተመው ሁሉ የሚያለፈው በእሳቸው ተቈጣጣሪነት ነው። በተሾሙ በዓመቱ በዜና ቤተ ክርስቲያን፥ ለካቶሊኩ ዶክተር አባእየለ መልስና ማስፈራሪያ ተብሎ "<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ እናታችን፥ ከማርቆስ አባታችን በተቀበለችው መሠረት እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔር ወልድ በሥጋው የባሕርይ አባቱ</u> ነው ብላ ታምናለች" ብለው በተኑ። በተዋሕዶ፥ በተፀቅቦ ከሁለት አካል አንድ አካል፤ ከሁለት ባሕርይ (አንድ መለትስ) ነው ካልተባለ፥ ከማርያም ማሕፀን ከእግዚአብሔር አብ ቢወለድም አብን ሥጋ ያለብሰዋል እንጂ የእግዚአብሔር ወልድን፥ በምንም ሁኔታ፥ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰውነት? አያስቀርበትም። አይሰውጥበትም። ይህ ክርክር በጊዜው እንዴት እንደቆመ ለማወቅ ሁሉም ሁሉን ይወቅን: ገጽ:14 ቁጥር 10ን ያይዋል።

የዚህ ስሕተት ጓደኛ የሰውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ክርስቶስን ከማርያም ወለደው ከሚለው ክሕደት ጋራ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያገናኛታልና ነው። እሳቸውም መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ከክርስቲያን ሳይንስ መሥራች ከወይዘሮ ሚሪ ቤከር ጋራ ይስማማሉ። (መለስ ወጉ እምነ ዝኩር ገጽ.63) አሁን ደግሞ ስሕተቴ ለምን ታወቀብኝ ብለው የንግግር ነጻነት ተሰጠና አብና ማርያም ሲጋቡ ተብሎ ተጻፈ እያሉ፥ መነሻውን ለማጥፋት ያድበሰብሳሉ። ይህ የሚያሳየው ሃይማኖቱን አለማወቃቸውን ስለሆነ ወይ ይማሩ፥ በተቀር በቤተ

ክርስቲያኒቱ ስም መዘባረቃቸውን ያቁሙ፤ ያለዚያም ሃይማኖታቸው ሌላ ሆነ አቋማቸውን ይለዩ።

9. ከዚህ በታች በተጻፈው ማመልከቻ በተራ ቁጥር 3 እንደተጻፈው፤ አለቃ ከኔ በላይ ዐዋቂ ለው ሆነ ፈጣሪ የሰም ስለሚሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ፥ ሥጋ ለብሶ ያስተማረውን፥ ሐዋርያት ተቀብለው ለዓለም የሰበኩትን ሐዲስ ኪዳን እንኳ እኛ እንዲህ አንልም እያሉ ቃለ እግዚአብሔሩን ትተው የራሳቸውን መጽሐፈ ባልቴት ምልተው ቤተ ክርስቲያኒቱን፤ ያውም በቅዳሴ ጊዜ መጽሐፈ ባልቴት እንድታነብ አድርገዋታል። ስሕተቱ ቢሰበሰብ ራሱን የቻለ አንድ ወደላ ቅጽ መጽሐፍ ይወጣዋል፤ ከዚህ ግን አንባቢ እንዲረዳው ያህል ወረቀት ስለተወደደ በጥቂቱ ጠቅሰን እናልፋለን።

10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ፥ መዋረዱን፥ ከአባቱ ጋራ ማስታረቁን፥ ማማለዱን የሚናገሩ ዐረፍተ ነገር በመላ ተዘለዋል ወይም በሌላ አወናባጅ ቃል ተተክተዋል። ለምሳሌ ሥጋ መልበሱን የሚያጠይቁ በሐዋርያት ሲደገሙ ተዘለዋል፤ ዮሐ.20:17 ኢየሱስም ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፥ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ፥ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና አምላካችሁ አርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት። ይህ አነጋገር በሐዋሪያት መልእክታት ሁሉ ተዘሏል፤ (2ቆሮ.1:3፤ 11:31፤ ኤፌ.1:3፤ 17፤ 1ጴጥ.1:3፤)። ምልጃን የሚያሳዩት የሚከተሉት ደግሞ ይፈርዳል፥ ይበይናል፥ ያስታርቃል እየተባሉ ባልዋሉበት ተተርጉመዋል፤ የግዕዙ ቃል ተንበለ (ለመነ) እንኳ ምንም አሻሚ ቃል ሳይኖረው ይፈርዳል ተብሎ ተጣሟል። (ሮሜ: 8:34፤ ዕብ.7:25፤ 9:15) አለቃ እያሌው ታምሩ መጻሕፍትን በማጣመምና በመዝለል በኩል የጀሀባ ምስክሮች ተከታይ ወይም ደቀ መዝሙር ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም፥ (መለስ ወጉ፥ ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ ገቾ 14-35)

11. ከዚህ በፊት እንዳየነው ከክርስቶስ ልደትም በፊት ኢትዮጵያ ጣዖት አላመለከችም እታመልክም ነበር ይላሉ፤ ለዚህ ግን ሌላ መጥቀስ ሳያስፈልግ የዛሬዎቹን ኢትዮጵያውያን እጠቃሉ ማጥናት ይበቃል። ለዚህም የሚጠቅሱት ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ነው፤ አለቃ በጦማር ምልልስ ላይ ሁሉን እውቃለሁ ብለው ነበር፤ ይህ መዝሙር ግን እለማወቃቸውን ያስረዳል። ይህ ጥቅስ የሚገኘው መዝሙር

67 ቁጥር 31 ነው። እሱም ዳዊት ስለትሩፋት የተናገረው መዝሙር ነው። የተፈጸመውም ናቡከደንጾር እየሩሳሌምን ወርሮ፥ ጎያላንን ማርኮ፥ ደካማ ደካማውን ትቶ ከሄደ በኋላ በስድስተኛው መቶ ዘመን ከክርስቶስ በፊት ነው። ትሩፋን የተባሉትም ቹምሮከ ተንቀው የቀሩ ርትፋኖች ናቸው። ኢትዮጵያ እጅዎችዋን ትዘረጋለች ማለትም በኋላ ዘመን ኢትዮጵያ ወደ አምላክ እስራኤል ትመጣለች፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብላ ክርስቲያን ትሆናለች ማለት እንጂ እስቃ እንደሚሉት አይደለም፥ ምክንያቱም የዳዊትን ልጅ ሰሎሞንን ለመጎብኘት የሄደችው ንግሥተ ሳባ እንኳ አረማዊት እንጂ እስራኤላዊት አልነበረችምና። ይህንም ለማረጋገጥ ሲፈልጉ ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ያሳተሙትን መዝሙረ ዳዊት ይመልከቱ።

12. ከዚህም በላይ እልፈው ተርፈው የውጭ ቋንቋ የተማሩ ለላዋቂዎች ናቸው ይላሉ። ከገደላገድሉ በቀር የሃይማኖታችን መጻሕፍት ሁሉ የተተረጎሙት ከውጭ ቋንቋዎች መሆኑ እየታወቀ እንዲህ ማለት እንኳ ሳይቀድመኝ ልቅደመው ብሎ ለድብ ማዛወር ነው።

13. ከዚህም ሌላ ጎጋውን ሕዝብ ለማስነሣት ሲሉ ወልድ ዋሕድ (አንድ ልጅ ብቻ) የምትል ኢትዮጵያ ብቻ ናት ብለው ያወራሉ።

እግዚአብሔር አብ በባሕርዩ ሁለት፥ ሦስት፥ አራት ልጆች አሉት የሚል ክርስቲያን ማነው? እስቃ እንኳንስ አዋልድንና ሐዲስ ኪዳንንም ለራሳቸው እንዲመቻች አጣመው ስለሚተረጉሙ (ወሪድየ ብሔረ ሮሜ ስቤተ ክርስቲያን ርኢክዋአ እመርክዋ እፍቀርክዋ ብለው ጠቅሰው ሲያበቁ ወደድኋት የሚል የለም ብለዋል፥ በሐዲስ ኪዳን ልክ ይተነብል ይፈርዳል ብለው እንደተረጎሙት። (ጦማር ግንቦት 28 1988 ዓ.ም. 7.4)

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእኃት አብያተ ክርስቲያን ጋራ ግንኙነት ማድረግ የጀመረችው በታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች፥ ቆስጠንጢኖስ ተብለው የሃይማኖት ጠባቂ ሁነው በተሰየሙት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት፥ በዘመኑ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፊታጅነትና ባራኪነት በኋላው ቅዱስ ወሰማዕት ቴዎፍሎስ መሪነት በ1941 ዓ.ም. ነው። ለዚህም ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የ4ኛ ዓመት በዓለ ሢመት የወጣውን መጽሔት ከገጽ 43-51 ያነቧል። ይኸውም ከልጆችዋ የውጭ ቋንቋ የሚያውቁ እንደ ደረሱላት ማለት ነው። ከዚህ ወዲህ በእየጉባኤው ስትሳተፍ ኑራለች። በዚህም ብዙ የመግባባት መንገድ ተሂዷል። ታዲያ

አሰቃ በቀደም ዕለት በጦማር በሰጡት ቃለ ምልልስ ሰውን ለማስበርገግ ካቶሊኮች አይገዙንም ብለው የወገኙ ለምን ይሆን? ይህም ጠቅላላ ግብራቸውን ይገልጣል።

ከዚህ ሁሉም በላይ፥ በቀደም ሠኔ 27 ቀን 1988 ዓ.ም. ለመብሩቅ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ፥ ሲኖዶስ ቀኖና ከሠራ፥ መተዳደሪያ ሕግ ካወጣ አትቀበሉት፥ አትከተሉት፥ ተፈታችሁ አትቀበሩ፥ ልጆቻችሁን አታስጠምቁ ብለው ገዘቱ። እውነት ነው ሃይማኖትን የሚክድ፥ ከሓዲና መናፍቅ ሲነሣ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንም መከራ፥ ዘከራ፥ ቢያንስ የሰብከተ ሀገሩ ሊቀ ጳጳስ የአካባቢውን ካህናትና ሊቃውንት ሰብስቦ፥ በተቀረም ፓትርያርኩ ጳጳሳቱንና ኤጲስ ቆጶሳቱን ሰብስቦ ይገዝታል። በመጀመሪያ ደረጃ እርዮስም የተገዘተው በዚህ አኳኋን ነው። በቅስና ደረጃ ብቻቸውን ሁነው ካልሾማችሁኝ ብለው የገዘቱ ግን፥ የመጀመሪያውም ሆነ የመጨረሻው ብቸኛው አሰቃ ናቸው። በዚህም ብዙ ደጋፊ ሰላሳቸው አየ! ሊቁ! ይባሉ ይሆናል። በዚህም ሊቁ! መምህር ኤስድሮስ ደቀ መዝሙራቸውን መምህር ወልደ ኢየሱስን ሲመርቁ፥ ልጄ ሆይ! ከደንቆሮ (ያልተማረ ማለታቸው ነው) ጋራ እንዳትጣላ፥ ለምን ብትል፥ ደጋፊው ብዙ ነው ያሸንፍሃል! ያሉት ሊደርስ ይችል ይሆናል። ግን ያውቃል?

የሆነስ ሆነና አሰቃ እንዲህ ያለውን የያፌ ገዝት ልማድ ከምን አመጡት? ወይም ማን አስተማራቸው? ለሚል ጠያቂ፥ ከአየአገር ቤቱ ግብረ ዲቁና አንኳ በደምብ ሳይማሩ ይቀሉና በሆነ ባልሆነው፥ ባል ሻርህ፥ ከምሽትህ ጋራ ዐርብ ረቡዕ ወይም በወር በዓል አደርህ እያሉ ከሚገዝቱት ናዝራውያን ነው። የሚታገሉበትን ሥጋዊ ስርብትናቸውን ሃይማኖት አልብሰው. ክርስቲያን ሁኖ፥ ከክርስቲያን ጋራ ከተነጋገረ፥ ሲኖዶሱ ቀኖና ከሠራ፥ ሕግ ከደነገገ፥ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበትን ሥርዓት ካወጣ ገዝቻለሁ አትተባበሩት ሲሉ የገዘቱበት ምክንያት ይህ ነው። ይህን ግን ለእውነተኛ አንባቢ መተው ይሻላል።

1. ጦማር መጋቢት 28:1988 ዓ.ም.ገጽ.4
2. The Vienna Dialogue, Op. Cit P.132.
3. Wort und Wahrheit, Op. Cit.pp. 49-50

ይህም አሁን ብቻ ሳይሆን ቀደም ብዬ የጀመርሁት ትግል መሆኑን ለማስረዳት የሚቀጥለውን ሰነድ አቀርባለሁ። ኅዳር: 3:1988 ዓ.ም.

# አንድ እረኛ፤ አንድ መንጋ

ለቅዱስ አባታችን አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ፣
ቅዱስ አባታችን ሆይ!

በጉባኤ ሊቃውንት ይልቁንም በሰብሳቢው በአለቃ አያሌው ታምሩ ብዙ የሃይማኖት ስሕተት በባልቴት ተረት ተሸፍኖ እንደሚካሄድ ቅዱስነትዎ ግጥም አድርጎ እንደሚያውቀው በፍጹም ልቤ አምናለሁ። ግን ቅዱስነትዎ ዐዋቂ ብቻም ሳይሆን አስተዳዳሪም ስለሆነ፤ ዐይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ ይመስላል።

ቅዱስነትዎ እንደሚያውቀው በኀይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን የንግግር ነጻነት ስላልነበረ እነ አለቃ እንዲህ እንበለው እያሉ ኖሩ፣ አሁን ግን ዕድሜ ለኢኅዴግ መናገር ተፈቅዷል፣ የንግግር ነጻነትም ተሰጥቷል፣ መረጃ ያለው ዐዋቂም ይጽፋል፣ ይናገራል።

ስለዚህ ጉባኤ ሊቃውንት ሲያደርገው የኖረገና የሚያደርገውን ስሕተት በቅዱስነትዎ በኩል ቢቻል እንዲታረም በተቀር ግን ስሕተቱን ልገልጥ ነውና ቅዱስ አባታችን እንዳይቆጡ በትሕትና አመለክታለሁ፣

<u>የሚታረሙ ስሕተቶችም፣</u>

1. የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ትምህርት፣ እምቅድመ ዓለም ካብ ያለ እናት፤ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት ተወለደ፤ ወልደ አብ በመለኮቱ፤ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ፣ በሰማይ እናት፤ በምድር አባት የለውም ነው። እነሱ ግን አንድ ባሕርይን እናጠናክራለን ብለው፤ ከማርቆስ አባታችን ከእስክድርያ ቤተ ክርስቲያን እናታችን በተማርነው መሠረት እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔር ወልድ በሥጋው የባሕርይ አባቱ ነው ብለን እናምናለን ብለው በ1954 በዜና ቤተ ክርስቲያን በተኑ፤ ለዚህም ግዙፍ ስሕተት፤ ለቅሶ፤ ንዴት፤ ቀልድ የያዘ ክታብ (ሳርር እሥቃለሁ እንደማሽላ ነገር በሆዴ እየተብላላ ሆነና ነገሩ) በተንሁና ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ፤ የተረዱት ስለመሰለኝ ጋዜጣውን በጋዜጣ አርሙ ብል ነገሩን ተረድተነዋል ብለው ሳያርሙ ዝም ብለው ቆዩና አሁን ደግሞ አብና ማርያም ሲጋቡ እያሉ መንደር ለመንደር ያወራሉ። ቀልዱን ይተውና የጋዜጣውን ቁጥሩን፤ ጠቅሰው ዕለቱን ጠርተው፤ ስሕተቱን ጽፈው፤ እርማቱን አስተካክለው ይጻፉ፤ ያርሙ፤ ራሳቸውም ከስሕተታቸው ይታረሙ።

2. ሥጋውና ደሙ የሚሰጠው በሕይወት ሦስት ጊዜ ብቻ ነው፥ እሱም ሲወለዱ፥ ሲጋቡ፥ ሲሞቱ ነው፥ እያሉ የራሳቸውን ቅጀት ያወራሉ፤ እንዲህ ያለውን መረጃ የለሽ ቅጀታቸውን ያቁሙ።

3. በግዕዝና በአማርኛ በሐዲስ ኪዳን ስም፥ 1975 ዓ.ም. በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት ታትሞ በእየቤተክርስቲያኑ የሚነበበው ወደላ የስሕተት ጥርቅም፥ መጽሐፍ ስላልሆነ በአጭበርባሪዎች ኪሳራ ተሰብስቦ ሲቃውንት ምን እንደሚሆን እስኪፈርዱበት፥ መጋዘን ገብቶ ይቀመጥ፥ ካልተመለሰ ግን በቅርቡ ሐዲስ ኪዳን አለመሆኑን በዝርዝር ለማስረዳት ዝግጁ ነኝ።

4. የእግዚአብሔር ወልድ ማደሪያ እንድትሆን የቀደሳት፥ ያበቃት መንፈስ ቅዱስ ነው ብለው ጽፈው ሲያስተምሩ ኑረው አሁን ደርሰው ጥንተ አብሶ አልነበረበትም እያሉ ይሰብካሉ።

5. አሁን ደግሞ አብያተ ክርስቲያናት ለመዋሐድ በሚጥሩበት ጊዜ ያለ ዕውቀት በድፍረት አንድ አይደለንም እያሉ ሰውን ያወናብዳሉ።

6. ሌላም ሌላም

የመንፈስ ትሑት ልጅዎ ዓለማየሁ ሞገስ።

ይህን መግለጫ ለ20 ሊቃነ ጳጳሳት ከሰጠሁ በኋላ በሊቄው አግካይነት ገብቼ ለብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ለመስጠት እጅ ነሣሁና መስቀል ስሜ ቁሜ ይህን መግለጫ እንዳነብ ቅዱስነትዎ ይፈቅድልኝ ዘንድ በትሕትና እለምናለሁ አልሁ። እሳቸው ግን አንተን አልሰማም ውጣልኝ አሉኝ። እኔም በትሕትና እጅ እየነሣሁ ጊዜ ባገኙ ጊዜ ያስነብቡት ከጠረጴዛው ላይ ትቸው ልሂድ አልኳቸው፤ እሳቸው ግን አሁንም ቤቱን አታቆሽሽ ይዘህ ውጣ ስላሉኝ፥ እኔም ስምተው የፈለጉትን ርምጃ መውሰድ እንጂ ለመስማትማ ክህነቱም የያዙት ሹመትና ስልጣንም ያስገድድ ነበር ብዬ እያኩተመተምሁ ይህ መጽሐፍ በአእምሮዬ ተፀንሶ ስለነበረ፥ አንዱ ከዚያ ከቆሙት ያጋጨንና እንኀሌ ይበሳሽብኛል ብዬ እንደ ልጅነቴ ሩጬ ወጣሁ።

የእለቃና የጉባኤ ሊቃውንት ታሪክና ግብር እስከዚህ ይብቃንና የቅዱስ ሲኖዶሉን ጸሓፍት ደግሞ እንይ።

በቅዱስ ሲኖዶስ ስም የሚጽፉት የሚሳሳቱት አንደኛ ጓደኞቻቸው ብዙ ካህናት በአማርኛ በዘመኑ የሚጻፉትን መጻሕፍትና ጋዜጣ ስለማያነቡ፥ የዘመኑን ሁኔታ ስለማይከታተሉ፥ የሚታዘበን ወይም

የሚያርመን የለም በሰው በማን አሰብኝ፥ ሁለተኛ ደግሞ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ከወጣ አንባቢውስ? ነቃፊውስ? ማነው ብለው ይለቁታል። ከዚህ እምነታቸው የተነሣ የፈለጉትን ወሽከተው፥ ጠቀስን እንባል እንጂ ጥቅሱን ከነገራችን ጋራ ማን ያስተያያዋል ይሉና ከታሪካቸው ጋራ ዝምድና የሌላውን ጥቅስ ይደረድራሉ። በዚህም የጽሑፉ ይዘት ፍየል ወዲያ፥ ቅንዝምዝ ወዲህ ሁኖ ያርፋል። ለዚህ መረጃም ተዐቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት (ከእስተኛች መምህራን ተጠብቁ)ንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት በሚል አርእስት ለምእመናን መመሪያ ብለው በአማርኛና በእንጊልዝኛ የጻፏቸውን ክታባት ማየት ይበቃል። (እነዚህን መጻሕፍት ማለት ቃሉን ማርከስ ነው)

ተዐቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት በሁሉም ሁሉን ይወቅ ከ48-54 ለለታተተ ከዚህ መግለጥ አያስፈልግም። በቃል ያጡትትን ከመድገም በቀር እጋነቡምና ተዐቅቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት የሚለው ክታባቸው በህያስያን ብጥልጥሉ በወጣ ባመቱ በሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ እያደርገንም ተመስግኗል። እሁንም በዓመቱ የፓትርያርኩ በዓል መጽሔት በብፁዕ አቡነ ገሪማ ተደግሟል፥ ግሩም ነው፥ ያስሄዳል፥ ያይጥ ምስክሯ ድንቢጥ ነው ይል የለ ተረቱ።

ሦስተኛው ደግሞ መጽሐፉ እንደወጣ፥ ያነበቡና ለቤተ ክርስቲያኗ ስም የሚቆረቆሩ ሊቃውንት በስልክ ደውለው፥ በገጽ ቀርበው እንዲህ ያለውን በሕተት እንኳን የተማረ የሚባል ሰው በቤተ ክርስቲያናችን ስምና፥ የጥጃ እረኛ እንኳ አያደርገውም እያሉ ቢነግራቸው፥ አናርምም ብለው ዝም እንዳይሉ፥ ለካስ በስሕተት የወጣው የመሰለን፥ እምነታቸው ኑሮ በዜና ቤተ ክርስቲያን ልዩ እትም መጋቢት 16 1988 ዓ.ም. ገጽ 11 ላይ ኢትኩን ስምዐ በሐሰት በሚለው ርእስ "መጽሐፉም በአሁኑ ጊዜ አሉ በተባሉት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ተዘጋጅቶና በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዐተ ጉባኤ ተመርምሮ፥ ትክክለኛ መሆኑም ተረጋግጦ የታተመና ምንም ስሕተት የሌለበት ነው ብለው" ሊቃውንቱንና የሲኖዶሱን አባላት በአንድ አንቀጽ ቁልጭ አድርገው ገልጠው ዐረፉ። ሁሉንም ለመረዳት ያን አንቀጽ ማንበብ ያስፈልጋል። 21 ሁነው፥ በወበራ (በደቦ፥ በጅጌ) የጻፉት መጽሐፍ ተብዬ ከጋዜጣ አናቅጽ አልፎ የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ነው ተብሎ በውድ ዋጋ ያውም በካያ ብር ምእመን ሁሉ ግዛው

ተብሎ መገደዱ በጣም ያሳዝናል። እሱም በእንግሊዘኛው ገጽ 15 ምዕራፍ 3 ሥላሴ በአራት። ነገር፤ በባሕርይ በሕልውና፥ በመለኮት፥ በፈቃድ ይለያያሉ ይላል፥ በዚህም ሦስት መለኮት፥ ሦስት ባሕርይ፥ ሦስት ህልውና፥ ሦስት ፈቃድ በሥላሴ አለ ማለት ነው። በዚህም የሥላሴን ህልውና፥ መንግሥት፥ ሥልጣን ያምባጓሮ ከተማ አድርገውት ዐረፉ። የሥላሴን መንግሥት በሦስት ሥልጣን፥ በሦስት መለኮት፥ በሦስት ፈቃድ ከከፋፈሉት ከዘነጣጠሉት በኋላ አንድ አምላክ ብለዋል፥ በዚህ ሁሉ የተለያየ መንግሥት እንዴት ብሎ ነው አንድ የሚሆን? ፍርዱ እንደ ተለመደው የአንባቢ ፋንታ ነው፥ ይሁን።

በዚህ መጽሐፍ ለዓለም ምንነታቸውን ገለጡ። ምን ይደረግ? አብዛኞቹ የኛ ሊቃውንት ቅዱስ ያሬድ ያዘጋጀውን ዜማ፥ ተዋነይ ያሳመረውን ቅኔ በቃል አጥንቶ መረግረግ ነው እንጂ፥ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳሳ ዘሸዋ እንዳሉት መጽሐፉንና ሃይማኖቱንግ የት አይተውት? የትስ ሰምተውት? የሚሉ የካህናታችን ነቃፊዎችና ሀያሲያን ብዙ ናቸው። እውነቱ ከተፈለገ በአማርኛ መጽሐፍ አንብቦ መረዳቱ ይቅርና የዕለት ጋዜጣ አንብበው የሚረዱ ከካህናታችን ከመቶ ስንት እጅ ናቸው? ሂሱንም ስማረም መማር እንጂ ብትር አይፈውስውም። (አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ 1974 ዓ.ም. ገች 88-89)

ሀያሲ እውነት ተናገረ ብሎ መደንፋትም እውነትን ማፈን ነው። ስለ ድንግል ማርያምም የሰጡት መረጃ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አበውን ከደው፥ መጽሐፈ ባልቴትን አጋነው ነው። አለቃ እንዳሉት ግን ፀረ ማርያም የሚያሰኝ አይመስለኝም። ለምን? ቢሉ የተሳሳቱት ማርያምን እናገናለን ብለው ነውና። ለማጋነንም ቢሆን ማርያም ቅድስት ናት፥ ውሸት አትወድም የተባለ እንደሆነ ግን ሌላ ክርክር ነው።

ወደ ሥረ ነገራችን እንመለስና አለቃ ለጦማር በሰጡት ቃለ ምልልስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያን ትምህርት እኔ የማላውቀው የለም ያሉት፥ በዜና ቤተ ክርስቲያን እንደ ተገለጠው ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዕውቀት፥ ትምህርት፥ ሊቅነት እንዲህ ከሆነ ለአስተዋይ አንባቢ የትምህርትና የሊቀነት ትርጓሜ ምን ይሆን? ያሰኛል። በተጠቀሰው ጋዜጣ አለቃ የኢትዮጵያን ሊቃውንት የምመራቸው እኔ ዕውሩ ነኝ ብለዋል፤ ይህ እውነት ከሆነ የጌታ ቃል በሁለቱም ተፈጸመ

ማስት ነው። (ማቴ.15:14-15፤ ሉቃ.6:39፤) የቢኖዶሱ ጸሐፍት አንዳንድ ጊዜ ዐቅማቸውን የሚያውቁ ይመስላሉ። እንደምን? ቢሉ፤ ስቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ተጠልለው፥ በገንዘቧ ተመክተው ነው እንጂ በራሳቸው ስምና ገንዘብ ግን አንድ አንቀጽም ጽፈው አያውቁ። ስለዚህ ሥራቸው ሁሉ በሰው ቁስል ዕንጨት ቢሰዱበት አያምም ሆነና ዐረፈ። እነሱም እገሌ ስለ ሃይማኖት መጽሐፍ ጽፎ ያሳትማል ያኗቸው እንደሆነ በእየማተሚያ ቤቱ ባቆሟቸው ሰላውዲዎች መሠረት እኛ መልስ ሳንሰጥ ገዝታችሁ አታንቡ እያሉ፥ ያውጃሉ። ስምን? ቢሉ ሰው አንቦ እንዳይበልጣቸው። መጽሐፉ ሲወጣ ግን እንኳን በመጽሐፍና በጋዜጣ አንቀጽም አያወጡ። ይዐም በሁሉን ሁሉን ይወቅ ተመስክሯል። ከመውጣቱ በፊት ሲደነፉ የነበረው ሁሉ ከወጣ በኋላ አንድ ዐረፍተ ነገር ስሕተት ነው ብሎ የጻፈ የለም። ይህም የደራሲውን ጥብዐትና ኦርቶዶክስነት ያሳያል። ከነአስቃ ዘንድ መጽሐፉ ባልቴትና ወንጌል ቢወዳደሩ፥ ወንጌል እስከ ሠራዊቷ ገሰባ ናት። ስሲቃውታችን ድካም ገጸ በረከት ከዚህ ቀጥሎ ሁለት ጥንታዊና ዘመናዊ መወድሶች ተጽፈዋል፤

<u>መጀመሪያ ጥንታዊው፤</u> ይህን መሳዩ ሊቅነት ከጥንት ተያይዞ የመጣ መሆኑን ለማስረዳት፤ <u>መወድስ፤ ዘአባ ቋያ ዘእዘዞ፤</u>

መካነ ስብዓቱ ሀብታት ደብረ ሊባኖስ
ዘውስቴትኪ ይምዕዝ ተክለ ሃይማኖት ናርዱ
ዓለመ መንና ዓለመ መንክራትኪ ይውዕዱ፥
ውሱዳ ለጢሮስ ቀናዕያን
እስ እምትካት ሐሜተ ለመዱ
ላዕሲኪ ተካየዱ
ንዋያተኪ ይንሥኡ ወጥሪተኪ ይሂዱ
ባሕቱ ሰዓተ ጸብዕ ቅድመ ወልድኪ አሐዱ
አሐደ ኢያከውኑ ባሕረ ተጋብአ እመ ነገዱ።
ለመጽሐፍሂ ቀላይ ዘባሕረ ትርጓሜ ሞገዱ
ይቀውሙ ውስተ ጽንፉ ወውስተ ዕመቁ ኢይወርዱ።

መጽሐፈ ቅኔ ዘብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ቁ. 863.

<u>ካልእ ዘመናዊ መወድስ፤</u>
ወለተ ክርስቶስ በስም ቤተ ክርስቲያን
ኢትዮጵያዊት ርትዕት ዘመግባረ ሠናይ አልብኪ
ትምህርተ መለኮት ምጡቀ ኢተምህርኪ
አኩነ አጽንዖ ዜማ
ወረቂቅ ቅኔ ኀሰሬ ዕድሜኪ
ወሥነ እእምሮ ኢለበውኪ
እስመ ሰንሊፍ ዘመነ እመ ተአንገዱ ብኪ
ይኅርብጦሙ ለሙሁራን እንግዳ ኀርብጥ ግብርኪ
ወእንዘ ቅውምት ውስተ ፍናት ትጼውዒ ባዕዳንኪ
ለውዳሴ ከንቱ ምትን በኢእምሮትኪ
ትሰድዲ መሃይምናነ እለ ይመጽኡ ወንገሌኪ።

ራሱን ለማደን ለሚፈልግ አንባቢ እስከዚህ የተጻፈው የሊቃውንቱ ምንነት ይገልጣልና ወደሌላው ርእስ እንሻገር።

በማስተማርም በኩል ሕዝቡ ሥራውን ትቶ በ11 ሰዓት ይሰበሰባል፤ እነሱ ግን በማያውቀው ቋንቋ የተቀረፀ ዜማ እያሰሙሁና ዓላማ በሌለው ምሕላ ጊዜውን አሳልፈው ይለቁታል። ይህም ወንጌል ለተራው ሕዝብ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ የተዘየደ አጥር ነው የሚሉ አሉ፤ የተዋሕዶ ብዙ ካህናት የሚፈልጉት ሕዝብ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ እንዳያማብብ፥ የተማረው እንዳያስተምር፥ ክርስቶስ ከነሥራው እንዳይነገር ነው የሚሉ አሉ። በጊዜአችን እንኳ ስንት ሊቃውንት ናቸው በሐሰት እየተከሰሱ እንዳያስተምሩ የተከለከሉ፤ ብሎም የተሰደዱ፤ ወንጌልን የምትሰብኩ ከሆነ ከኛ ቤተ ክርስቲያን አትገቡም እየተባሉ የተባረሩና ወደ ሌላ የሃይማኖት ድርጅት የገቡ፥ ወይም ቤተ ጸሎት የመሠረቱ እጅግ ብዙ ናቸው። እንደ መካነ ኢየሱስ ያሉት ምእመናንም ከቤተ ክርስቲያናችን አትገቡም ተብለው እየተባረሩ የሄዱ ናቸው። በእየሀገሩ ይልቁንም በአሜሪካ ያሉት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በነገድና በጎሳ ተከፍለው ፓትርያርክ ካልሆነ ብለው ነው ወይስ በሃይማኖት ተለይተው? ይህም ብዙዎች ጳጳሳት ለጎሳ፥ ለሹመት፥ ለገንዘብ የሚባክኑ እንጂ ለክርስቶስ አለመቆማቸውን ያስረዳል። መጽሐፍ እስ ከርሦሙ አምላኮሙ ይል የለ።

<u>ማስጠንቀቂያ፤</u> ካህንና መሶብ ተሰባብሶ ነው ስለሚባል፥ ሁሉንም መናገር አልፈቀድሁም፥ ከተነካሁ ግን የማውቀውን ሁሉ፥ ዕድሜ የንግግር ነጻነት ለሰጠን መንግሥት እንጂ፥ የምወከውክ መሆኔን በቅድሚያ አስታውቃለሁ።

<u>ለዚህ ምዕራፍ የተነበቡ መጻሕፍት፤</u>

1. ተዐቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት፥ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ለምእመናን የተዘጋጀ ትምህርት፤ አ/አ/ ሠኔ 4: 1986: ዓ.ም.

2. ቴዎፍሎስ (አባ ሊቀ ጳጳሳት ዘሐረር ወዘኩሉ አድያሚሃ) <u>መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከነትርጓሜው፥</u> (አርቲስቲክ ማ/ቤት፤ 1955 ዓ.ም.)

3. ኅሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላታ) መጽሐፈ ቅኔ፥ ብርሃንና ሰላም፥ 1901 ዓ.ም.

4. ዓለማየሁ ሞገስ፥ ሁሉም ሁሉን ይወቅ፥ ቦሌ ማ/ቤት አ.አ. 1987

5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ እምነት፥ ሥርዓት አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፥ አልቦ ማ/ቤት፥ ጥር 1988 ዓ.ም.

6. ጋዜጦች፤ መጋቢት 17:1988 ዓ.ም. ዜና ቤተ ክርስቲያንና ጦማር መጋቢት 18 1988 ዓ.ም.

## ምዕራፍ ስምንት

### ለሹመትና ክብር ሲሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን።

ከዚህ በፊት ቤተ ክርስቲያን በሚለው ምዕራፍ እንዳየነው ■ሃይማኖት ሳይሆን ለሹመት ሲሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያን የሚባሉ የሚከተሉት ናቸው። እነሱም የግሪክ ኦርቶዶክስ፥ የሮም ካቶሊካዊት፥ የእንግሊዝ፥ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ፥ የግብጽ፥ የአርመን፥ የእንጾኪያ፥ የሕንድ፥ እነዚህ ተለያይቶ ለመኖር ምንም በቂ ምክንያት የላቸውም። የሚያቀርቡት ግን በኬልቄዶን ጊዜ የተወራውን ውሸት፥ ውሸትነቱ ■ተረጋገጠ አሽቀንጥሮ ጥሎ በኅብረት መኻዝ ነው። ንጹሕና ቅዱስ ■ርስቲያን የሚያሰኝ። የምንለያየው በቃላት ነው እንጂ በትምህርት ■ይደለም እያሉ እያመኑ እንለያያለን ማለት በተጠየቅ አይሰድም።

1.የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ገ.108።

2. The Vienna Dialogue Communque's and Joint Documents, Booklet NR.1

3. Wort, und Wahrheit, Revue for Religin and Culture, Supplementary Issue, Number 5.July 1989,pp.49-50

4. አብያተ ክርስቲያን በአየጉባኤው የሚያነሡትም ሌላ ሌላውን ጥቃቅን ጉዳይ ነው እንጂ ስለ ባሕርያት አይደለም። ባሕርይ በተዋሕዶ በመለትለ መንፈስ ያለቀለት ነገር ከሆነ ውሎ አድሯል (አምነ ዝኩር pp.49-50)

የሮምን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና አስተዳደር ጠልተው የሄዱት ፕሮቴስታንት የሚባሉት ወንጌላውያን ደግሞ በደንብ የተማሩትና ታላላቆቹ ከላይ እንደተጠቀሱት ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት አምበቱን አዕማደ ምስጢር። ምስጢረ ሥላሴን፥ ምስጢረ ሥጋዌን፥ ምስጢረ ጥምቀትን፥ ምስጢረ ቁርባንን፥ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታንን ይቀበላሉ። ይኸውም አንዳንዱን በግልጽ ባነጋገር አንድ ሁለት ብለው በስም ጠርተው፥ የቀሩትን ደግሞ እንደ ጋብቻና ንስሓ ያሉትን በግብር ይቀበላሉ። ንስሓንም ይሰብካሉ። የሚያቀርቡት ምክንያት ሁሉ ላዩ የተከደነ ሲመስል ውስጡ ክፍት ባዶ ነው። ለእልክ ካልሆነ በቀር ቀዋሚነት የለውም።

በጸጋው ድነናል። ጻድቃን ከሞቱ በኋላ አያማልዱም ስለሚሉትም በምግባር በሃይማኖት በማስታረቅና በማማለድ የሰጠነው ማስረጃ ትዕቢትና ኩራትን ጥሎ፥ እልክን አውልቆ፥ ሹመትና ገንዘብን ትቶ፥ ትሕትናን

እርእ በርሳችን እንፋቀር የምትል ናት።
(1ዮሐ.4:16-21) እኛም እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ፍቅር ዐውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በርሱ ይኖራል። በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከኛ ጋር ተፈጽሟል፤ እሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና። ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፤ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም። እሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን፤ ማንም እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው። ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔር ሊወድ እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከሱ አለችን። (1ቆሮ. 13: በሞላ) እነዚህን የመሳሰሉ ለቁጥር የሚያስቱ ጥቅሶች ሞልተዋል። ታዲያ ክርስቲያኖች በዚህ ትእዛዝ የሚሄዱ ይመስላሉ ወይ? ወይስ እርስበርሳቸው የሚጣሉ፥ የሚናከሱ፥ የሚባሉ፥ የሚጋደሉ ከሆነ ቅዱሳት መጽሐፍት የሚጠቅሟቸው ለምን ይሆን? እርስ በርሳቸው መዋደዱና መረዳዳቱስ ይቅርና አንዱ ክርስቲያን ለጥቅም ሲል ብቻ ወንድሙን ይወጋዋል፤ በመካከለኛው ዘመን መካከለኛውን ምሥራቅ ሰላም ሲወረው ከሰላም ጋራ ሁነው ክርስቲያንን የወጉ፥ መንገድ የመሩ ካህናትና መነኮሳት በጣም ብዙ ናቸው። በኋላ ግን ያሰቡት ሹመት ስላልተገኘ፥ ጠጉራቸውን ቢነጩ ምን ይሁን? አሁንም በሌለ ባልነበረ ነገር አንድ ባሕሪ ሁለት ባሕሪ እያሉ፥ በቃል እንጂ በትምህርት ሳይለያዩ፤ አንዱ በሌላው ላይ ውሸት እያወሩ ሲፋጁ ይኖራሉ።

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ገጽ 108። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ትእዛዛትና ቃላት የሚያምኑ ከሆነ ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ፤ ተዋሕዶ፥ የግብጽ ቤተ ክርስቲያ፥ የአርመን፥ የሕንድ፥ የግሪክ፥ የሮም፥ ምስጢረ ጥምቀትንና ምስጢረ ቁርባንን የሚቀበሉ ወንጌላውያን ሁሉ፥ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የየራሳቸውን አገልግሎት እንደ ያዙ አብረው መቁረብ አለባቸው።

## ምዕራፍ ዐሥር

### ማስታረቅና ማማለድ

ስለማስታረቅና ማማለድ በሁሉም ሁሉን ይወቅ ምዕራፍ 2: ገጽ:43 እስከ 70 በስፊው ታትቷል። ያንን መላልሶ ከጥቅሱ ጋራ እያዛመዱ አንብቦ መረዳት ያሻል። ከዚህ ግን ከዚያ የቀረውን ጠቅስን እናልፋለን። ብዙ ሰዎች ሃይማኖትም እንደፍልስፍና በሐሳብ የሚሄድ ይመስላቸዋል። ይህ አስተሳሰብ ፍጹም ስሕተት ነው፤ ሃይማኖት በአስተርእዮ (በመከሠት) እግዘአብሔር አብ፥ እንደ ሙሴ ላሉት በገሃድ፥ በትእዛዝ የነገረው፥ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ለብሶ ለሐዋርያትና ለሰብዓ ሁለቱ አርድእት ያስተማረው፥ በመላ በእሱ ዘመን ይከተለው ለነበረ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ የሰበከው፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በግብሩ በእየዘመኑ ለተነሡ ነቢያትና ሐዋርያት የገለጠው፥ ያናገረው ራእይ፥ አስተርእዮ ሲሆን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ባለመገንዘብም ሆነ ወይንም ከእግዚአብሔር መንፈስ እነሱ የሚበልጡ መስሏቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ አያማልድም፥ አያስታርቅም፥ ሌሎች ደግሞ ጻድቃን ሰማዕታት በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እንጂ ከሞቱ በኋላ አያማልዱም ስለሚሉ የሁለቱም ሐሳብ ፍልስፍናና የራስ ግምት እንጂ ሃይማኖት አለመሆኑን ለማስረዳት ይህ ምዕራፍ ባጭሩ ተዘጋጅቷል። የተዘጋጀውም በጥቅስ ስለሆነ የተጠቀሱትን እያወጡ ማንበብ አስፈላጊ ነው።

ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው፥ በሥጋው ሞቶ ተነሥቷል፥ ተነሥቶም ዐርጎ በአባቱ ቀኝ፥ በሥልጣን ሁኖ ለዘለዓለም በመስቀሉ ጥንተ አብሶን እንደጠፋ፥ አሁን ደግሞ በእየጊዜው ተከታዮቹ በድካማቸው የሚሠሩትን ኀጢአት ሲፍቅም ከአባቱ ጋራ ሲያስታርቅም ሲያማልድም እስከ ምጽአት ድረስ ይኖራል። ክህነቱ ለዓለም ለዘለዓለም ነውና። ክህነቱ የመልከጼዴቅ ነው እንጂ የአሮን አይደለም። ያሮን ልጆች ክህነት ሲሞቱ ያልፋል፥ የክርስቶሱ ግን አንድኛ ሙቶ ስለተነሣና ለዘለዓለም ሕያው እንደ መልከጼዴቁ ስለሆነ ለዘለዓለም ይኖራል። (ዘፍ.14:18) የሳሌም ንጉሥ መልከጼዴቅም ኅብስትና የወይን ጠጅ አወጣ፥ እሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ።
(መዝ.109:4) እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት አንተ ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ፥ አይጸጸትምም። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ከምዕራፍ (ዕብ 5-9) የጻፈውን በጥንቃቄ መላልሶ ማንበብ ያስፈልጋል። ከዚህ ግን ዋና ዋናዎቹ ብቻ ይጠቀሳሉ።

እንግዲህ ክርስቶስ ደግሞ ሲቀ ካህናት ሲሆን ራሱን አላከበረም፥

ነገር ግን አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልድሁህ ያለው፥ እሱ በሌላ ስፍራ ደግሞ፤ አንተ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ነህ ይላል። እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል፤ ከብርቱ ጩኸትና እንባ ጋራ ጸሎትና ምልጃን አቀረበ። እግዚአብሔርም ስለመፍራቱ ሰማለት። (7:3) አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የለውም፥ ለዘመኑም ጥንት፥ ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፤ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘለዓለም ካህን ሁኖ ይኖራል። ይቀጥልና ቁጥር 23-25 ላይ ደግሞ፥ እነሱ ግን እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑ ብዙ ናቸው፤ እሱ ግን ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት ስላለው ስለነሱ ሲያማልድ በሕይወት ይኖራል። ስለዚህ (ደግሞ) በእሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።

ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ መጀመሪያ በላከው መልእክቱም (1 ጢሞ.2:5) አንድ እግዚአብሔር አለና፤ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ብሎ አማላጅነቱን በመካከለኛነቱ ገልጧል።

ሐዋርያው ዮሐንስም በመጀመሪያው መልእክቱ (1ዮሐ. 2:1-2) ልጆቼ ሆይ ኀጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኀጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፥ እሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኀጢአታችን ማስተስሪያ ነው። ለእኛ ኀጢአት ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኀጢአት እንጂ በዚህም ከአብ ዘንድ ጠበቃችንም አማላጃችንም አስተስርያችንም መሆኑን ገለጧል።

ክርስቶስ ከሞተ በኋላ አያማልድም የሚሉ ድኩማን መናፍቃንላ ምን ይዘው ተነሥተዋል? ቢሉ (ዮሐ.19:30) ጌታ በጊዜ ስቅለት መገረፍ፥ መገፋፍ፥ መሰደብ፥ መጻፍትን የመሳሰሉትን ፈጸምሁ ለማለት የተናገረውን ይዘው ተፈጸመ (ሁሉን ከኪሳቸው ጨምረው) ብኋል ብለው ሥራውን ሁሉ ከመሞቱ በፊት ጨርሷል ይላሉ። ቢያስተውሉ ኑሮ የመጣበት ተግባር ተገባደደ እንጂ አላለቀም ነበር። ሞት በሥጋ፥ ወሪደ መቃብር በአካለ ሥጋ፥ ወሪደ ሲኦል በመንፈስ፥ ትንሣኤ፥ በእየጊዜው ለሐዋርያት እየታዩ ማስተማር፥ ወደ አባቱ ከእነሥጋው ማረግ፥ ዐርጎ በክብር በሥልጣን መስኮት በቀኝ ከአባቱ ጋራ ተካክሎ መቀመጥ፥ መንፈስ ቅዱስን መላክ፥ በኋላም በኀልፈተ ዓለም በአባቱ ክብር በግርማ መለኮት

መጥቶ በሕያዋንና ሙታን ላይ ፈረዶ ለጻድቃን ዋጋቸውን፥ ለኃጥአን ፍዳቸውን መስጠት አለበት፥ ነበረበት።

ወንጌላዊው ዮሐንስም (1ዮሐ. 1:7) የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል ብሏል። አነጻን ብሎ ቢሆን ኑሮ ለጥንተ አብሶ ይሰጥ ነበር፤ ይህ ግን የአሁን ጊዜ ስለሆነ በእየጊዜው የምንሠራውን ኀጢአት ማስተሰረዩን ያሳያል። ይህም አባቱ ሆይ ሥጋዬን የበሉትን፥ ደሜን የጠጡትን ማራቸው ይቅር በላቸው (መ.ቅ.ገ.304:ቁ. 142) ካለው ጋራ ይመሳሰላል።

ይህ ሁሉ እያለ ተፈጸመ ብሏልና አያማልድም፥ ይላሉ። ምን ይደረግ የስምንኛ ነገር ቀድሰው ካቀረቡ፥ ግፉ ቢልም ዜማ ተምረው ፈትተው ከቀበሩ፥ ለዚህም ወፍራም ደመወዝ ካገኙ፥ ሃይማኖቱ ገደል ቢገባ፥ ምን ቸገራቸው፥ የተማረ ላልተምር ሲልም ለሙን አጥፍተው ከሰው ያጣሉታል። ሕዝቡም በማንበብ ፈንታ እነሱ የሚሉትን ነው የሚሰማ። ስለዚህ የሚያውቁትም ፈርተው ዝም ይላሉ።

ለፈውን ንባብ ለሁሉም ሁሉን ይወቅ አንባቢ በመተው ከነቢያት ሁለት ጠቅሰን የክርስቶስን አማላጅነት ዘግተን ወደ ቅዱሳን አማላጅነት እንመለስ፥ (ዕዝራ: ሱቱኤል: 5:26-29) እኔ የነገርሁህ ምልክት በሚገለጥ ጊዜ፥ እነሆ እንዲህ ያለ ወራት ይመጣልና፥ ዛሬ የምትታየው ዓለም ታልፋለችና፥ ዛሬ የተሠወረች መንግሥተ ሰማያትም ትገለጻለችና፥ እኔ ከነገርሁህ ከክፉ ሥራ የዳነ ሁሉ፥ ክብሬን የሚያይ እሱ ነው። ልጄ ክርስቶስ ከሉ ጋራ ካሉ ከጻድቃን ጋራ ይገለጣልና፥ የተነሡ ጻድቃን ደስ ይላቸዋል። ከዚህ በኋላ ልጄ ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ የጀመረውን አገልግሎት ይፈጽማል፥ እስትንፋስ ያለው ሰው ሁሉም ክብሩን ይፈጽማል።

ክቡር ዳዊትም (መዝ.2:7-8) እግዚአብሔርም አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፥ ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ፥ የምድርን ዳርቻም ለግዛትህ እሰጥሃለሁ ብሏል። ይህ ሁሉ የተነገረው ትስብእትን ሲያይ ነው። ይህን የተረዱ ሲቃውንት አበውም እግዚአብሔር አብን ስለልጅህ ማረን፥ እግዚአብሔር ወልድን ደግሞ ከአባትህ አማልደን እያሉ ሲጸልዩ፥ ሲያስተምሩ፥ ሲጽፉ ኑረው አልፈዋል።

የጌታችንን የመድኀኒታችንን የመሪያችንን፥ የፈጣሪያችንን ከአባቱ ጋራ እስታረቂነቱንና አማላጅነቱን በቅዱሳት መጻሕፍት ከተረዳን፥ በእኔ ያመነ እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠራል፥ ከዚያም የበለጠ

ይሠራል ባላቸው መሠረት በመከራ የክርስቶስ ተከታይ በመሆን፥ እሱን የመላሰሉትን የጻድቃን፥ የቅዱሳንን፥ የሰማዕታትን እስታራቂነትና አማላጅነት ደግሞ እንይ። (2ቆሮ.5:18-20) ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋራ ካስታረቀን፥ <u>የማስታረቅንም</u> አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሁኖ ዓለሙን ከርሱ ጋራ ያስታረቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፥ በእኛም <u>የማስታረቅ ቃል</u> አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ሁነን፥ ከእግዚአብሔር ጋራ ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።

<u>ከሙሴ ጀምሮ በጸሎታችው በደለኛን ከፈጣሪው ያማለዱ</u>

ሙሴ ስለ እስራኤል ዘፀ. 32:32፤

ሙሴ ስለማርያም ዘኁ. 12:13፤

ሙሴ ስለ እስራኤል ዘፀ. 14:17-20፤ ዘዳ.9:26፤

ሳሙኤል ስለ እስራኤል 1ሳሙ. 7:5፤

የእግዚአብሔር ሰው ስለ ኢዮርብዓም 1ነገ.13:4-11፤

ዳዊት ስለ እስራኤል 1ዜና: መ.21:17፤

ሕዝቅያስ ስለሕዝቡ 2ዜና:መ.30:18፤

ኢዮብ ለወዳጆቹ፤ ኢዮ.42:10፤

ይህ አንቀጽ የክርስቶስ ወንድሞችና ተከታዮች ሁሉ የማስታረቅና የማማለድ ሥልጣን ከእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው ቁልጭ አድርጎ ያስረዳል።

የክርስቶስ ተከታይ ሁሉ ወንድሙና ወዳጁ አይደለም ብሎ ለሚጠራጠር ደግሞ የሚከተሉት ጥቅሶች እነሆ! (ማቴ.12:46-50፤ ማር.3:31-35፤ ሉቃ.8:19-21) እጁንም ወደ ደቀመዛሙርቱ ዘርግቶ፥ እነሆ እናቴና ወንድሞቼ፥ በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እሱ ወንድሜም እኅቴም፥ እናቴም ነውና አለ። (ዮሐ.15:15) ከእንግዲህ ወዲህ ባሮቼ አልላችሁም፥ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆቼ ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና። (ዮሐ.14:19) ገና ጥቂት ዘመን አለ፥ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፥ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፥ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ። እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳ ላችሁ፥ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ። እንግዲያ

ሐዋርያት ተከታዮቻቸው ጻድቃን አብረው ከክርስቶስ ጋራ ሕያዋን ሁነው በሕይወት የሚኖሩ ከሆነ፥ እሱ ሲያማልድ እነሱ የማያማልዱበት ምክንያት ምን ይሆን?

ይህን ሁሉ ያላስተዋሉ አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆች ግን አማላጅ ወይም አስታራቂ አንድ ነው ይላሉ፤ ይህ ግን ከጌታም ትእዛዝ፥ እሱን ዘበሰማያትን ጸልዩ ብሎ ካዘዘው ትእዛዝና ከልማዱ፥ ከባህሉ ጋራ አይስማም። በባህሉም አማላጅ የሚለካው ብዙ ነው፤ ጌታም እንዳየነው የማማለድን ሥልጣን የሰጠው ለተከታዮቹ ሁሉ ነው። ወደ አብ የሚያቀርበውና የሚያስታርቀው ያማላጆች አለቃ በሩ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን እንጂ ወደ እሱ ልመናቸውን ለማቅረብ ሥልጣን ያላቸው ግን ቁጥርም የላቸው።

ከዚህም በላይ ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ብሎ አምኖ የተቀበለ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በእግዚአብሔር ቃል ተረጋግጧል፤ (ዮሐ.1:11-13) ወደ ወገኖቹ መጣ፥ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፥ ለተቀበሉትና በስሙ ለሚያምኑት ግን የእግዚአብሔር ልጆች ይሁኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ አልተወለዱም።

(1 ዮሐ.5:1) ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል።

(ሮሜ: 8:16-17) የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋራ ይመሰክራል፥ ልጆችም ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፤ አብረንም እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋራ አብረን ወራሾች እንሆናለን።

እንደዚህ ያለ ለቁጥር የሚያስቸግር መጥቀስ ይቻላል፥ ግን ወረቀት ስለተወደደ እስከዚህ ይብቃን። እግዚአብሔር አምላክ ልጅ እንጂ የልጅ ልጅ፥ ወይም የዘመድ የወላጅ ልጅ የለውም፤ የላከውን የባሕርይ ልጁን ክርስቶስን የተቀበለ ሁሉ የጸጋ ልጁ ነው። እንዲህ ከሆነ እንዴት ጻድቃን አያማልዱም ይባላል። መሪያቸው ክርስቶስ እንደሚያማልድ ተከታዮቹም ያማልዳሉ። ክርስቶስም ሆነ ጻድቃን አያማልዱም የሚሉ ሁሉ ከስሕተታቸው እንዲመለሱ በዚህ ምዕራፍ ይነገራል።

ከዚህ የተቀረውን በአድበንቲስት ምዕራፍ መደምደሚያ ተራ ቁጥር መ ይመለከቷል።

<u>ነፍሳት ከሞት በኋላ እያውቁም ለሚሉ፤</u>
ነፍሳት ከሕይወተ ሥጋ ይልቅ በሕይወተ ነፍስ የበለጠ ያውቃሉ፤ ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል፤

ሀ/ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ በሳኦል ላይ የሚደርሰውን መከራ ዘርዝሮ ተናግሯል፤ (1ሳሙ.28:15-19)

ለ/ አሁን በመስታዎት እንደምናየው ዐይነት በድንግዝግዝ እናያለን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት (እናያለን) ዛሬስ (አሁን) ከእውነት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ እንደታወቅሁ አውቃለሁ። (1ቆሮ.13:12) ይህም ነፍሳት ከሞቱ በኋላ አይሰሙም አያዩም የሚባለው ተረት መሆኑን ይገልጣል።

## <u>ምዕራፍ ዐሥራ አንድ</u>

### <u>ታላላቁ የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጉባኤ፤</u>

እስከ 4ኛው መቶ ዘመን ድረስ ክርስቲያንን የሚያሳድዱ ፈተናዎች በጣም ብዙዎች ነበሩ። ከልዩ ልዩ ባህል፥ ፍልስፍና፥ ልማድ፥ አምልኮ ጣዖት፥ አገር፥ ብሔር የመጡ፥ አሕዛብ፥ አይሁድ ያሳድዷቸው ነበር። በሰይፍ ይሰየፉ፥ በእሳት የተቃጠሉ፥ ለአራዊት ይጣሉ ነበር፥ ለአደባባይ መብራት ሠም ተለቅልቀው ይቃጠሉ ያበሩ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ምዕራፍ እንዳየነው ዘመነ ሰደት አልፎ፥ ዓመተ ሰማዕታት አልቆ፥ ዘመነ ሰላም ሲጀመር ደግሞ ኑፋቄ መልኩን ለውጦ ይበጠብጣት ጀመር። ስለዚህ እኒህ ኑፋቄያት የተወገዙባቸውን የዓለም አብያተ ክርስቲያን ዐበይት ጉባኤያት ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

### 1ኛው <u>የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጉባኤ፤</u>

<u>ሰብሳቢው ንጉሠ ነገሥት</u>፥ ቆስጠንጢኖስ፥
<u>የጉባኤው አፈ ጉባኤ</u> የእስክንድሪያው ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ፥ የጉባኤውን ውጤት ጸሎተ ሃይማኖትን ያረቀቀው ያን ጊዜ የእለእስክንድሮስ ሊቀ ዲያቆን፥ በኋላ የእስክንድሪያ ፓትርያርክ፥ ትልቁ <u>አትናቴዎስ፤</u>
<u>መናፍቅ</u> አርዮስ፥

ኑፋቄ፥ ወልድ ፍጡር፥
አርዮስ ገማሚና በዓለ ቅኔ ስለነበር፥ ዓለምን በማሳቱ አሁንም የጆሆባ ምስክሮች የእሱ ተከታዮች ናቸው።

ጉባኤው የተሰበሰበበትም ቦታ ኒቀያ፥ በዛሬው ቱርክ ውስጥ 325 ዓ.ም. የኤጲስ ቆጶሳት ቁጥር 318።

## 2ኛው. የዓለም አበያተ ክርስቲያን ጉባኤ፥

ሰብሳቢ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ፥
አፈ ጉባኤ (ዛሬ ሊቀመንበር፥ ሰብሳቢ) የእስክንድሪያው ፓትርያርክ ጢሞቴዎስ ዘአልቦ ጥሪት። ዋና ተከራካሪዎች ሁለቱ ጎርጎርዮሶች፥ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ።
መናፍቃን መቅዶንዮስና አቡሊናርዮስ፤
መናፍቅ፥ መቅዶንዮስ የቆስጥንጥንያ ፓትርያርክ ነው።
እሱም መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ መልእክተኛ እንጂ እኩያቸው አይደለም ብሏል። ተከታዮቹ አሁንም የጆሆባ ምስክሮች ናቸው። በሶርያ የምትገኝ የላኦዲኪያ ኤጲስ ቆጶስ አቡሊናርዮስ ደግሞ ወልድ በመለኮቱ ከአብ ጋራ አንድ ሲሆን ከማርያም ሥጋን በለበሰ ጊዜ ግን ነፍስና ዕውቀት የሌለውን ሥጋ በመልበስ፥ ለለበሰው ሥጋ መለኮት ነፍሥና ዕውቀት ሆነው የሚል ኑፋቄ አስተማረ፥ ሰበከ። ስዚህም አነጎርጎርዮስ ኢየሱስ ክርስቶስን በትስብእቱ ፍጹም ሰው ሁኗል፥ ከኀጢያት በቀር ፍጹም ሥጋ ለብሷል ብለው ከመጻሕፍት እየተቀቡ አስረድተው ረቱት። መቅዶንዮስንም በመሳ ጉባኤው የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ከአብና ከወልድ እኩልነት፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ አስረድቶ፥ ከ318 ጸሎተ ሃይማኖት ላይ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን የሚለውን አንቀጽ ጨምሮ ተለያየ።
ዘመን 381፥ ቦታ ቁስጥንጥንያ፥ የተሰበሰቡት፣ ጳጳሳት ቁጥር 150 ነበር።

## 3ኛው. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ፤

ሰብሳቢ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ፥

የጉባኤው አፈ ጉባኤ ወይም ሊቀ መንበር የእስክንድርያው ፓትርያርክ ትልቁ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር። የተሰበሰቡት ጳጳሳት 200 ሲሆኑ ቦታው ደግሞ ኤፌሶን።

ዘመን:431: መናፍቅ የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ንስጥሮስ፥ ኑፋቄ፥ እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት፤ የእግዚአብሔር አብ ልጅ በመሆኑ ከአብ ጋር እኩል ነው፥ ከእመቤታችን ሥጋን በነሣ ጊዜ ግን አካሉ ሁለት ነው፤ አንደኛው በመለኮቱ፤ የመለኮቱ፥ ሁለተኛው የትስብእቱ በትስብእቱ፤ አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ሁለተኛው የማርያም። አምላክን ሰው ሊወልደው ስለማይችል እመቤታችን ማርያም የክርስቶስ እናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም የሚል ኑፋቄ ስለ አስተማረ ብዙ መረጃዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሱ፤ ጠቅሰው አስረድተው፥ ንስጥሮስን ገዝተው፥ እመቤታችን ድንግል ማርያምም ወላዲተ አምላክ መባሏንና መሆኗን አረጋግጠው ጉባኤውን ዘጉ።

4ኛው ጉባኤ በኬልቄዶን፤

ሰብሳቢ ንጉሠ ነገሥት መርቅያን፥

የተሰበሰቡት ጳጳሳት 650፤ ዘመን 451 ዓ.ም. ቦታ ኬልቄዶን፥ መናፍቅ አውጣኪስ፥ ኑፋቄ፥ እግዚአብሔር ወልድ ከማርያም ሰውነትን (ሥጋ፥ ትስብእትን) በነሣ ጊዜ አምላክነቱ ሰውነቱን ስለዋጠው ረቀቀ፥ አቀለጠው፥ (ማሳሰቢያ፥ ይህንን ምዕራባውያን ወደ ጎድረት ይወስዱታል) በዚህ ጊዜ በሊቀ መንበርነቱ (በአለቃነቱ) የልዮን ወኪሎችና ዲዮስቆሮስ ተጣልተው ጉባኤው ያለ ጥሩ ውጤት ይለያያል። የዚህን ጉባኤ ውጤት በመላ ለማየት ስለ አውጣኪስ የተሰጠውን ምዕራፍ ስድስትን ይመለከቷል።

የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሏቸው እነዚህ ብቻ ናቸው። ከዚህ በኋላ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ጋር ሁና እስከ ሰባተኛው ጉባኤ ቆይታለች። ከዚያ በኋላ ግን የሮም ቤተክርስቲያን ብቻዋን ሁና እስከ 21 ደርሳለች። ይህም በ1962-65 እስከተደረገው የሁለተኛው የባቲካን ጉባኤ ማለት ነው።

## ምዕራፍ ፀሥራ ሁለት

### የቅድስት ድንግል ማርያም

ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም በሁሉም ሁሉን ይወቅ መጻፋችን ምክንያት ብዙ ጥያቄ ስለተነሣ በዚያ የተጻፈውና የተነገረው ሳይነካ እንዳለ ሁኖ፤ በይበልጥ ለመግለጥ፤ ያው ምዕራፍ ከዚህ መጻሕፍም በዚህ ምዕራፍ በሰፊው ይደገማል።

**የቅድስት ድንግል ማርያም አጭር ታሪክ፤**

የአካላዊን ቃል፥ የእግዚአብሔር ወልድን ሥጋ መልበስ የተናገረ ነቢይ ሁሉ በርዕቱም ሆነ በኢርቱዕ፥ ቅድስት ማርያምን ሳይጠቅስ ያለፈ የለም። ትንቢቱ የሚፈጸምበት ዘመን ሲደርስ በአባቷ ከነገደ ይሁዳ ከዳዊት ከሚሆን ከኢያቄም በእናቷ ከነገደ ሌዊ ከቤተ ክህነት ከምትሆን ከሐና በስለት፥ በቅዱስ ጋብቻ፥ በንጹሕ ፋካቤ ነሐሴ 7:5485 ዓ.ዓ. ተፀንሳ በዚያው ዓመት ግንቦት 1 ተወልዳ፥ በሦስት ዓመት ከስምንት ወር ከሦስት ቀን ታኅሣሥ 3 ቀን ቤተ መቅደስ ገብታ፥ ከደናግለ እስራኤል ጋራ አምላኳን እያገለገለች ኖረች፤ 15 ዓመት ሲሞላት በሊቀ ካህናቱ ሥልጣን በጌዶ (በተፀቅቦ) ለዮሴፍ ታጨች። ታጭታ ሳለ፥ መበሥሩ ቅዱስ ገብርኤል ዜናዌ ትስብእት፥ ሊቀ መላእክት ከእግዚአብሔር ተልኮ፥ አምላክ ወልደ አምላክ ዓለምን ለማዳን ከእሷ በመንፈስ ቅዱስ ግብር መወለዱን አበሠራት። በብሥራቱ እንደተስማማችም፥ ቃለ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፥ ከማሕፀኗ ተዋሕዶ፥ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቆይቶ፥ ፍጹም ሰው ሁኖ ተወለደ። ቅዱስ ገብርኤል መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ላይ ይመጣል፥ የልዑል ኀይልም የጸልልሻል፥ ሲላት፥ ባላት ጊዜ፥ እነሆኝ የእግዚአብሔር ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ በማለቷ ዓለምን ከግብርናተ ዲያብሎስ ለማዳን ለመድኀኔ ዓለም ደልድይ ሁናዋለች። እግዚአብሔር የሚሠራውን አብዛኛውን ጊዜ በፍቃዱ እንጂ በግድ፥ በኀይል አይሠራምና ዓለምን ለማዳን ተባብራለች የሚሉ አሉ። ይህም እውነት ነው። ተወለዶም ሔሮድስ ሊገለው ሲያሳድደው ምድረ ግብጽ ይዛው ከዮሴፍ ጋር ተሰዳለች፤ ከስደትም መልስ ከአደራ አባቱ ከዮሴፍ ጋር ሁና አሳድገዋለች። በሚያስተምርበትም ጊዜ ሀገር ላገር ምን ያገኘው ይሆን እያለች ለ3 ዓመት ከ3 ወር ስትንከራተት ኑራለች። ከዐረገ በኋላም ከሐዋርያት ጋራ 15 ዓመት ቆይታ ጥር 21 በ64 ዓመቷ ዐርፋለች። (መ.ቅ.ገ.217-118፤ ቀጥር: 38-47 የታምረ ማርያም መቅድም፤ ታምር ሁለት፤ ማቴ1:18-25፤ 2:13-23፤ ሉቃ.1:26-66፤ 2:1-52)

## ቅድስት ድንግል ማርያም

ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ፡ ማርያም እናታችን የጌታችንም
እናት ወላዲተ አምላክ ማርያም፥
ንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም
እኅቶሙ ለመላእክት (የመላእክተ እኅታቸው)
እሞሙ ለሰማዕት (የሰማዕት እናታቸው)

በዚህ መግለጫና ቅጽል ደጋግ፥ ታላላቅ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ይስማማሉ። እግላጅነቷንም የጻድቃን፥ የሰማዕታትን አማላጅነት ምሳሌነት፥ ተራዳኢነት፥ የቀዱሳን መላእክትን አማላጅነትና ተራዳኢነት በቅዱሳት መጻሕፍት አስረጅነት የሚቀበሉ ሁሉ፥ እሷም መትሕተ ፈጣሪ፥ መልዕልተ ፍጡራን ስለሆነች ወደ ፍቁር ልጇዋ ከሚያማልዱን ቅዱሳን የመጀመሪዋ ናት ብለን እናምናለን። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለቅድስት ማርያም የሚደረገው አገልግሎት ውዳሴው፥ ቅዳሴው፥ ማሕሌቱ፥ ዝማሬው፥ ተአምሩ ለቁጥር የሚያሳስተው መልክአ መልኩ፥ ሰዓታቱ፥ ኸረ! ስንቱ ተቆጥሮ! ይህ ሁሉ ተሰብስቦ ጊዜውን ያዘውና የሥላሴን አንድነት ሦስትነት መንገሪያ፥ የወንጌል መሰበኪያ፥ የክርስቶስን ሥራ፥ ተግባር፥ ሰውን ለማዳን ሲል የደረሰበትን ሥቃይ፥ መከራ፥ ሕማም፥ ግስረኛ ወቅት ጠፋና ሕዝቡ ክርስቶስን ሳያውቅ ሃይማኖቱን ሳይረዳ በአረሚነት እንደተወለደ በአካባቢው ያለውን ታቦት ፈጣሪዬ ነው እያለ መሞቱ ያሳዘናቸው አንዳንድ ዐዋቂዎች፥ ሥጉዎች፥ አሳቢዎች፥ ስለዚህ ከተአምሩም በግዕዝ ለሕዝቡ በማይገባው ቋንቋ ከሚፈሰው አገልግሎትም ተቀንሶ፥ ወንጌልም በብዙ ሳይሆን በጥቂቱ እንኳ ትሰበክ ይላሉ እንጂ፥ ማርያም አታማልድምማ ማን ብሎ? ቢልስ ማን ይቀበለዋል? አሁንም ይህ ታሰቦበት ለወንጌል መሰበኪያ ቦታና ጊዜ ሕዝቡ ከማይሰማው አገልግሎት ተቀንሶ ካልተሰጠ ለክህነት ወደ ጳጳሳቱ ገቢ የሚጎርፈው ሥላሴ ስንት ናቸው? መልስ ያካባቢውን ታቦት ቆጥሮ ይሆን ያህል። ማን ፈጠረ? መልስ አሁንም ያካባቢው ቅዱስ ማለት በዚች ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ቶሎ የሚቀር አይመስልም ብለው ወንጌልን ለሚሰብኩ ከቢጽ ሐሳውያን ልዩ ልዩ ስም ከአፅራረ ወንጌል ይሰጣቸዋል እንጂ ማርያምስ በሁሉም ሁሉን ይወቅ ምዕራፍ 24-26 እንደተገለጠው ግጥም አድርጋ ታማልዳለች፤ ታስታርቃለች።

## ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

### አጠቃላይ የቅድስት ድንግል ማርያም መገለጫ፥

የእኛ የጸጋ እናታችንና እመቤታችን ከጌታችንና ከልጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥላ የጻድቃን መሪ፥ የሰማዕት እናት፥ የመላእክት እኅት በመሆኗ አማላጃችን፥ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው የሥጋ እናቱ ወላዲተ አምላክ፥ መርዓተ እብ፥ ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ፥ ቅድስት ድንግል ማርያም መትሕተ ፈጣሪ፥ መልዕልተ ፍጡራን ናት። በዚህም መጻሕፍት ሁሉ ይስማማሉ።

እግዚአብሔር አብ ወዷታል፣ መርጧታል፣ አጽንቷታል፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንጽቷታል፣ ቀድሷታል፣ አመስግኗታል። በዘረዐ አዳም ከመጣው ከጥንተ አብሶም አንጽቶ የእግዚአብሔር ወልድ ማኅደር፥ እናት እንድትሆን አመቻችቶ አብቆቷታል። እግዚአብሔር ወልድ ደግሞ አባቱ እግዚአብሔር አብ በመንፈስ ቅዱስ ያከበረውን ተሰብእት በተለየ አካሉ ለብሶ ሰው ሁኖ ተወልዶ ዓለምን አድኖባታል። ስለዚህ ሁሉም ያመሰግኗታል።

የሁሉም ሁሉን ይወቅንና የዚህን መጽሐፍ ደራሲ አተረጓጎም ከማየት በፊት እንባቢ ሁሉ ሉቃ.1:26-55ን መላልሶ እንብቦ እንዲረዳ ይጠቆማል።

በስድስተኛው ወር መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ እንዲት ድንግል ተላከ፣ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደእሷ ገብቶ፥ ጸጋ የሞላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፥ ጌታ ካንቺ ጋራ ነው፥ ከሴቶች ሁሉ መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።

በዚህም እግዚአብሔር አብ ልኮ፥ እዝዞ፥ ቅዱስ ገብርኤል ሲቀ መላእክት ተልኮ፥ ታዝዞ አመስግነዋል። እግዚአብሔር አብ ሥላሴን፥ ቅዱስ ገብርኤል መላእክትን ይወክላሉ። ወዲያውም በምስጋናውና በሰላምታው ተደናግራና ተደናግጣ፥ ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች፥ እሱም የሚከተለውን መልሶ ያረጋጋታል፥ ያረጋግጥላታል። ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ተውልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፥ እሱም ታላቅ ይሆናል፥ የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ እምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፥ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም ብሎ፥ ማርያምም መልአኩን ወንድ

ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፥ መንፈስ ቅዱስ በአንች ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል፥ ስለዚህ ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። በዚህም የሁሉም የሦስቱም ኀይል መንፈስ ቅዱስ እንደሚጸልላትና በተለየ አካሉ ደግሞ በላይዋ ላይ መጥቶ ከጥንተ አብሶ ሁሉ እንደ ሚያነጻት ከእሷ የሚወለደው ደግሞ፥ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ መባሉን አብሥሮ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሞላባት፥ ሥሉስ ቅዱስም በኀብረት እንዳመሰገኗት ነግሮ ተመልሷል።
ቀጥሎም ቁጥር 42 ላይ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብላ ጮኸች፥ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማሕፀንነሽ ፍሬም የተባረከ ነው።

በዚህም መንፈስ ቅዱስ ርግጠኛው፥ ዋነኛው አመስጋኝ፥ ኤልሳቤጥ ግትያ ግራማሯን መሆናቸው ነው። በዚህም መንፈስ ቅዱስና ኤልሳቤጥ (ሰው) ተባብረው ማመስገናቸውን እንረዳለን። ይኸው መንፈስ ቅዱስ ካደረባት በኋላ ራስዋ ማርያም ደግሞ እነሆ! ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል (ብፅዕት ይሉኛል) ብላለች። ለማርያም ምስጋና ምኑ ተይዞ በሽ! በሽ! ነው፤ ሀልውና ሁሉ ያመሰግናታል፥ ያወድሳታል፥ ከሥላሴ ጀምሮ መላእክትም ሰውም እንደሚያመሰግኗት በዚህ እንረዳለን። ይህን የተረዳ፥ ከተረዳ ቅንዓት ዐይኑን ካልጨፈነው፥ ምቀኝነት ኅሊናውን ካላወረው በቀር ለማርያም ምስጋና አይገባትም አይልም።

በአባቶቻችን ለማርያም የታዘዘው ምስጋና ከአምስት አንድ ነው (አምሾ) በዚህም የዘወትር ጸሎታችንን ንስግድ ለመንግሥተ አብንና ስብሐት ለአብን ማስተዋል ይበቃል፤ ለሦስቱ ሥላሴ ሦስት፥ ለማርያምን አንድ ለመስቀለ ኢየሱስ አንድ። ከአምስት አንድ ይሉሃል ይህ ነው። ይህም ምስጋናም ሆነ የጸጋ ስጊድ ከሥላሴ ጋራ እኩል መካፈሏን ያሳያል። ከዚህ በላይ የሚሰጣት ግን ሥላሴን ከማርያም ያሳንሳል።

በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን በጣም በዛና ወንጌል እንዳትሰብክ ከለከለ፥ ብዙ ካህናትም ከአገልግሎትና ከተረት፤ ከመጽሐፈ ባልቴት በቀር ከመጽሐፍትና ከምስጢረ ሃይማኖት ምንም እንዳያውቁ አስተዋፅኦ አደረገ። በሰዓታቱ፥ በማሕሌቱ፥ በኪዳኑ በቅዳሴው ሁሉ እሷ ናት፥ ወንጌልን እናንብ፥ ሃይማኖት እንስበክ፥ በስምስጢረ ሥላሴ ለሕዝቡ በጥ ቂቱ እንግለጥለት፥ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሽ እንናገር የተባለ

እንደ ሆነ ታምሯ ሳለች ይባልና የወንጌሉ ነገር ይረሳል። ወንጌልን እናስተምር፣ ኢየሱስን እንሰበክ ብሎ አንዱ የኔ ቢጤ ችክ ያለ እንደሆነ ጴንጤ ነህ መሰል ዝም በል ሲባል፣ ተከታዩ ክርን እንደሆነ ይታየውና ጭጭ ይላል። ስለዚህ የኛ ቀሳውስት ከተአምረ ማርያም ውጭ በማሕሌት በኪዳን በሰዓታት ተወጥረው ስለተያዙ ይህን የጠቀስነውን ከያዙ ስለሃይማኖት ባያውቁ አይፈረድባቸውም። መልሳቸውንም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ የማያስማማው፤ እርስበርሳቸውም የሚያበጣብጣቸው ገድላገድሉ፣ ተአምረ ማርያሙ፣ መጽሐፈ ባልቴቱ ነው። ከቅዱሳት መጻሕፍት ትንሽ ማንበብ የጀመሩስት ቅዱሳን ሁነው እንደሚያድሩ ይታመናል። የኛ የማርያም ወዳጆች፤ ማርያም በሥላሴ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ያደረገች አስመስለው፣ ሥላሴን፤ አብ፣ ወልድን፣ መንፈስ ቅዱስን ተትው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይነበቡ ዋናው የቤተ ክርስቲያን መሥራች ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መድኀኔ ዓለም እንዳይሰበክ ማድረጋቸው ነው እንጂ አንድ እምስተኛ ምስጋናስ ይገባታል። እንዴታ! እንዴት ሁኖ ነው አንድ እምስተኛ (እሞሽ) መሆኑ? ስሚል፣ ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ (በአጠቃላይም ለስመ እግዚአብሔር) በዕፀ መስቀል አጠቃላይነት (ስም) ጌታ በዚህ ዓለም ከተቀበለው ጸዋትወ መከራና ለእሷ አሁንም እንደገና።

<u>ሰጊድም፤</u> በቦታው እንደምናየው፤ የጸጋ ሰጊድም እምሾ ይገባታል። ምስጋና እንደሚገባትና እንደምትመሰገን በትንቢትም ተነግሯል። ወትቀውም ንግሥት በየማንከ፤ በአልባሰ ወርቅ ዑዕጽፍት ወሑብርት፤ (በወርቅ ልብስ ተሸፋፍናና ተጎናጽፋ ንግሥት በቀኝህ ትቆማለች) ወይዘከሩ ስመኪ በኩሉ ትውልደ ትውልድ (ትውልድ ሁሉ ስምሽን ያስታውሳሉ።) ስለዚህ አሕዛብ ሁሉ ስምሽን ያስታውሳሉ፣ ስለዚህ አሕዛብ ሁሉ ይገዙልሻል፣ ያገለግሉሻል (መዝ.44:9፤16-17) ብሏልና።

## ምዕራፍ ዐሥራ አራት

### ድንግል ናት፣

ከመፅነስ በፊት ከመፅነስ በኋላ፣ ከመውለድ በፊት፣ ከመውለድ በኋላ ሁል ጊዜም ድንግል ናት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ በፊት እንዳየነው የመጣበት ዓላማ አንዱ ትንቢትን ሁሉ መፈጸም ነው።

ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እነሆ!

1. ስለዚህ ጌታ እራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ! ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች (ኢሳ.7.14) አዎ! በድንግልናስ እንደ ትንቢቱ ወልዳለች፣ ግን ከወለደች በኋላ ተፈትሖ ግህፀን ይኖርባት ይሆናል ለሚል ተጠራጣሪ ደግሞ የሚከተለው ጥቅስ የሰጠዋል፣

2. ወደምሥራቅም ወደሚመለከተው ወደ መቅደሱ በር አወጣኝ፣ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ ሰውም አይገባበትም፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል (ሕዝ.44:1) መጽሐፍ ቅዱስን ተቀብለናል፤ የእግዚአብሔርን ቃል እናምናለን የሚል ሁሉ በማርያም ድንግልና ማመን አለበት። ለምን ቢሉ ለነብዩ በነብዩ ይህ በር ለዘለዓለም ተዘግቶ ይኖራል ያለ እራሱ እግዚአብሔር አብ ስለሆነ። እግዚአብሔር ደግሞ አይዋሽም። ስለዚህ ማርያም የዮሴፍ ምሽት ነበረች፣ ሌሎች ልጆች ነበሯት የሚሉ ሁሉ ያላነበቡ ,ወይም ውሸታሞች ናቸው።

3. እንቴ ሙሽሪት የተቆለፈ ገነት (ተጋን) የተዘጋ ምንጭ፣ (የታተመ ነቅዕ) (መሐ.4:12) ይህም መግቢያ የሌለው ተጋን፤ አፍ የሌለው ምንጭ በማለቱ ዘለዓለማዊ ድንግልነዋን ያሳያል። በሐዲስም ይህ ትንቢት እንዴት እንደ ተፈጸመ የሚከተሉትን ያነቧል፣

4. (ማቴ.1:18፣ ሉቃ.1:26-46)

5. ይህንም ሲናገር ከሕዝቡ አንዲት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባሃቸው ጡቶቿ ብፁዓን ናቸው አለችው (ሉቃ.11:27)

በዚህም ራስዋ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ያለችው ተጀመረ። ድንግልነዋን፤ መመስገኗን፣ ምንነቷን ካየን እግላጅነቷን ደግሞ በሁሉም ሁሉን ይወቅና በዚሁ መጻሐፍ ባግላጅ ምዕራፎች ግገናዘብ እንችላለን። ከዚህ ቀጥለን ግን ስለ ጥንተ አብሶ እንይ።

## ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

### ከጥንተ አብሶ ድንግል ማርያም ነጻ ነበረች ወይ?

ስለ ጥንተ አብሶ የተነገረው ሁሉ ከዚህ በታች በዘገባ መልክ ተጽፏል። ጥንተ አብሶ ማለት አዳም በመበደሉ ምክንያት ፈጣሪው እግዚአብሔር ረግሞታል። ይህ ርግማንም እስከ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞት ድረስ፥ በጠቅላላ በዓለም ላይ ነበር ከመስቀልም በኋላ እያንዳንዱ በጥምቀት ካላስወገደው በፍጥረት ሁሉ ላይ ይኖራል፥ አሁንም አለ ማለት ነው። በዚህ ሐሳብ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ከሁለት ይከፈላሉ፥

1. የሮም ቤተ ክርስቲያን ከነተከታዮችዋ ከ1949 ዓ.ም. ወዲህ ጥንተ አብሶ የለባትም ትላለች።

2. ከግሪክ ጀምሮ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትና ሊቃውንት በሙሉ። ደራሲውም ምንም ለማንም ሳወግን ስለማርያም ጥንተ አብሶ ያገኘውን ማስረጃ እውነትን ለማወቅ ለሚፈልግ ከዚህ ቀጥሎ ጽፎ መርጦ መከተል ያንባቢ ፈንታ መሆኑን ገልጦ አልፏል፥ እንጂ፥ በዘገባው የራሱን እምነት አልገለጠም።

ነገሩን ሲያስተውሉት አንደኛ ቁጥሮች ማርያምን ያነጻትና ማኅደረ መለኮት እንድትሆን ያበቃት ያመቻቻት በእግዚአብሔር አብ ፈቃድና ምርጫ መንፈስ ቅዱስ ነው ያልን እንደሆን እንደሌላው ጸቂቀ አዳም፥ ተራ ፍጡር ትሆናለች ብለው ነው፥ የሁለተኛው ቁጥሮች ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ከጥንተ አብሶ ካነጻት በኋላ ጌታ ከድንግል የለበሰው ከኀጢአት በቀር ፍጹም ሥጋ አዳምን ነው። አምላክ ሰው ሆነ ይላልና ብለው፥ መንፈስ ቅዱስ ነው ያነጻት ይላሉ።

ለዚህ ክርክር ሁለቱም የሚጠቅሱት ከዚህ ቀጥሎ ተጽፏል። ጥንተ አብሶ አልነካትም፥ መንፈስ ቅዱስ አላነጻትም፥ አልቀደሳትም ለዚህ ተግባርም አላደራጃትም የሚሉት፥ ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ (ከፈጠራት በምንም አልረከሰች) የሚለውን ደራሲው ያልታወቀና እግዝእትነ ማርያም ነበረት እምቅድመ ዓለም በኀሊና አምላክ (እመቤታችን ማርያም ከዓለም በፊት በኀሊና አምላክ ነበረች) ነው። ለዚህም ተከራካሪዎች፥ ከፈጠራት እርሷ ኀጢአት ሠራች ያለ የለም፤ ከአዳም በመወለዷ በዘረዐ አዳም ከሚወርደው ጥንተ አብሶ መንፈስ ቅዱስ አነጻት፤ ጠበቃት ተባለ እንጂ። ሁለተኛው ከዓለም በፊት በኀሊና አምላክ ነበረች የተባለው ደግሞ አምላክ ከመፍጠሩ በፊት የሚፈጥረውን አስቀድሞ ስለሚያውቅና ስለሚመርጥ ለማርያም ብቻ መነገሩ አያቀጣም ብለው የሚከተሉትን ጥቅሶች ያቀርባሉ።

(ምሳ.16:4፤) እግዚአብሔር ሁሉን ለእራሱ በራሱ ፈጠረ፤ ኃጥእን ደግሞ ለክፉ ቀን።
(ማቴ.20:23) ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ። በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው።
(ማቴ.25:34) እናንተ ያባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።
(ሮሜ.8:28-29) እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፥ ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ፥ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።
(9:10-13) ይህ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ርብቃ ደግሞ ካንዱ አባታችን ከይሥሐቅ በፀነሰች ጊዜ፤ ልጆቹ ገና ሳይወለዱ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ፥ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር ሐሳብ ይጸና ዘንድ ለእርስዋ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት። ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። (ኤፌ.1:4፤) ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለብን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠ። (3:11) ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘለዓለም ሐሳብ ነበረ።

እግዚአብሔር ማናቸውንም ፍጡር እምቅድመ ዓለምም ሆነ አሁን ከመፈጠሩም ሆነ ከመወለዱም በፊት ማወቁንና መምረጡን የሚያስረዱ ከዚህ በላይ እንደተጠቀሱት ያሉ ብዙ መረጃዎች ስላሉ እመቤታችን እምቅድመ ዓለም በኅሊና አምላክ ነበረች የሚለው ከገድላገድል የመጣ ጥቅስ ከጥንተ አብሶ ነጻ አያወጣትም ይላሉ።

ስለዚህ የሁሉንም ጥቅስ ያላንዳች አድልዎ እናቀርባለን። በብሥራት ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ ያለውን ይዘው እመቤታችንን ጥንተ አብሶ አልነካትም ከአዳም ጀምራ ስትወርድ ስትዋረድ የመጣች ንጹሕ ዘር ናት የሚሉ አሉ። ሌሎች ደግሞ የውዳሴ ማርያምን አንድም ወኢረኩሰት እምዘፈጠራ =ከፈጠራት አልረከሰችምን ይጠቅሱና ጥንተ አብሶ አልነበረባትም ይላሉ፤ ይህ እንኳ ሁለት ጊዜ ጎመን ጥቅስ ነው፤ መጀመሪያ ባይው አይታወቅም፤ ሁለተኛ

ጥንተ አብሶ ነበረባትና መንፈስ ቅዱስ ከዚያ አንጻት ማለት በድላ ወይም ኀጢአት ሠርታ ነበር ማለት አይደለም፤ ለምን ቢሉ ጥንተ አብሶ በአዳም ስሕተት ምክንያት በልጅ ልጅ የተላለፈ በደል እንጂ አያንዳንዱ ግለሰብእ የሚሠራው ኀጢአት ወይም አበሳ አይደለምና። (ፀሥራተ ገ.ግ ትመህርተ መለኮት ገጽ 96)

ዘለዓለማዊ ድንግልናዋም በነቢያት ሲነገር ከጥንተ አብሶ ግን ነጻ ናት ያለ አንድም ስለሌለ፤ መልአኩም መንፈስ ቅዱስ በላይሽ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል ብሎ እንደሚያነጻት ተናገረ እንጂ፤ እኔ ወንድ ሳላውቅም እንዴት ይሆንልኛል ስትለው፤ ያለ ጥንተ አብሶ መውለዷን ለመናገር ምቹ ጊዜ ሳለው የመንፈስ ቅዱስን በላይዋ ላይ ማደር ተናግሮ ነው ያለፈው። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አበውም መንፈስ ቅዱስ እንደነጻት፣ እንዲሐ ሥጋሃ ኀድረ ላዕሌሃ (ሥጋዋን አንጽቶ በላይዋ ላይ አደረ ቅዱስ ያሬድ) ገሊላዊት ሐቀፈተከ፣ ነፍሳ ቀደሰከ፣ ወሥጋሃ አንጻሕከ (ገሊላዊት ታቀፈችህ፣ ነፍሷን ቀደስህ፣ ሥጋዋን አነጻሕ (መ.ቅ.ገ. 438.21) እያሉ ስለሚናገሩና አብዛኞቹ አባቶችዋም እንደ ዳዊትና ሰሎሞን የመሳሰሉት ወንጀለኞች ከዚያውም አመንዝሮች ስለነበሩ፣ በየት አልፎ ነው እሷ ከጥንተ አብሶ ነጻ የምትሆነው? ይላሉ። ለሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍትንና የቅዱሳን አበውን ትምህርት ከዚህ ቀጥለን አቅርበናልና አንባቢ በጥንቃቄ እንዲያነበው አደራ እንላለን።

1. ኢሳ.61:1-3፤ የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድኆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፣ ለተማረኩትም ነጻነትን፣ ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል። የተወደደችው የእግዚአብሔርን ዓመት አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ፣ እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፣ በአመድ ፈንታ አክሊልን፣ በለቅሶ ፈንታ የደስታን ዘይት፣ በሐዘንም ፈንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል። ይህን ጥቅስ ጌታም ቃል በቃል ደግሞታል። (ሉቃ.4:18-19) እሱም ትስብእትን ሲያይ የተነገረ መሆኑን፣ ለሥጋ፣ ለትስብእት የተነገሩ ቃላት በሚለው ሁሉም ሁሉን ይወቅ በምዕራፍ 4 አስረድተናል። ነቢዩ ቀብቶ ላከኝ ያለውን ሊቀ መለአኩ ቅዱስ ገብርኤል

መንፈስ ቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል፥ በአንችም ያድራል ማለት ያነጻሻል ባላት መሠረት እምላክ እንዲፀነስ መንፈስ ቅዱስ በማርያም ላይ ወርዶ ሥጋዋን ባነጻ በመንፈስ ቅዱስ ይተረጎማል። ይህችም የቅባት የማንጻት ትርጓሜ ናት። እምላካዊ ቃል ከሥጋዋ ጋራ አንድ አስኪሆን ድረስ በእርስዋ (በሥጋ) አድሮ ድል የነሣቻትንና ያረከሰቻትን የአዳምን ሥጋ አንጽቷታልና ብሏል (ግብረ ሕማማት ገ.205)

2. ቅዱስ ያሬድም፤

እመቤታችንና የድኅነታችን ምክንያት የሆነችው የእምላክ እናት ማርያም ከአዳም ሥር የተገኘች ናት። ነፍሷን አክብረህ፥ ሥጋዋን አንጽተህ ልጅህን በራስዋ እንዲያድር አደረግህ (የጥር:21: ዝማሬ)

ያማረ ኮከብ በማርያም አደረ

ሥጋዋን አንጽቶ በማርያም አደረ

ርዷን ቀድሶ መለኮቱን ከሥጋዋ ጋራ አዋሐደ (ነሐሴ 15:ዚቅ)

3.ያዕቆብ ዘሥሩግም፤

ከአብ የማይለይ ረጅም ፈትል፥ ሰማይና ምድርን የፈጠረ፥ በፈቃድህ ከሰማይ ወረደህ፥ የድንግል ማሕፀን ወሰነህ፥ የድሆች ልጅ ትንሽ ልጅ ብላቴና አቀፈችህ፥ ነፍሷን አከበርህ፥ ሥጋዋንም አነጻሕ፥ አጸነሃትም በእንተም አልደነገጠችም (መ.ቅ. ቁጥር:21፤ ገጽ:438)

4. ጎርጎርዮስ ዘኑሲስም፤

ቃል በግብረ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆነ የሚለው ትርጓሜም ከሓድያንና መናፍቃን እንደሚያስቡት ለመንፈስ ቅዱስ ሥጋ ኑሮት ወይም የተፈጠረ ሁኖ ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ የማርያምን ሥጋ አነጻ፥ ቀደሰ፥ የአብ አካላዊ ቃልንም ለመፀነስ የበቃች አደረጋት እንጂ ብሏል (ሃይ አበ. ገጽ:125: ቁጥር:19)

5. አባ ሕርያቆስ ዘብሕንሳም፤

ድንግል ሆይ! በኀጢአት ፍትወት የተፀነሽ አይደለም፤ በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐናና ከኢያቄ ም ተወለድሽ እንጂ (መ.ቅ.ገ. 217:38)

በሀገራችንና በዘመናችንም ስለ ሃይማኖት የጻፉ ሊቃውንትንም እንደሚከተለው አትተዋል፤

6. የቤተ ክህነቱ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ አለቃ አያሌው ታምሩም በ1953 ዓ.ም. ብርሃንና ሰላም በታተመው በኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 205 ቁጥር 21 ላይ

ይልቁንም መርጦ ከኀጢአት አንጽቶ (ይህስ እንዲያውም ሰብሐት ላቲና፣ ኀጢአት ሠርታ ነበረች ማለትን ያሳያል) በመንፈስ ቅዱስ ቀድሶ፣ ሥጋዋንና ነፍሷን ስተዋሐዳት ስእመቤታችን ድንግል ማርያም እንሰግዳለን ብለው ከኀጢአት ያነጻት መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ገልጠው ጽፈዋል። ይህን ጽፈው ሲኖሩ፣ እሳቸውን ተከትለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደራሲ አቶ ዐሥራት ገብረ ማርያም ከጥንተ አብሶ ያነጻት መንፈስ ቅዱስ ነው ብለው ጽፈው ሲሸጡ ጊዜ ቀንተው ጥንተ አብሶ አልነበረባትም እያሉ ገበያ ስመከልከል ገዝተዋል፤ አውግዘዋል፤ አውጀዋል፤ ስም አጥፍተዋል።

አለቃ አያሌው ታምሩ ቃላትን አነባብረው እንደ ክረምት ነጎድጓድ አከታትለው ስለሚለቁት ብዙ ሰው ሊቅ ናቸው ይላቸዋል እንጂ ሃይማኖቱን አያውቁትም። በዚህ ምክንያት ብዙው ሰው እሳቸውን አትንካ መላው አግራ ይጣላሃል ብሎኝ ነበር። ግን መላልሼ ነገሬአቸው የማይመለሱ ስለሆኑና በስሕተታቸውም ብዙ ሰው ይዘው ስለጠፉ፣ ጌታ ፈሪሳውያንን፣ ጳውሎስ በመላ አይሁድን፣ አትናትዮስ አርዮስን፣ የእስክንድርያው ጢሞቴዎስ የቁስጥንጥንያው ፓትያርክ መቅዶንዮስን፣ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ንስጥሮስን የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ (ሌላም ብዙ መጥቀስ ይቻላል) ዘልፈዋል፤ ገሥጸዋል። እኔም እሳቸውን ለመገሠጽ ሳይሆን ስሕተታቸውን ለማሳወቅ ስለሆነ አንባቢ እንደሚታገሠኝና ይቅርታም እንደሚያደርግልኝ አምናለሁ።

ማንም መናፍቅና ከሐዲ ከኀጢአት አነጻት ብሎ አያውቅም። ቅዱሳን አበው ያስተማሩን መንፈስ ቅዱስ ሥጋዋን አነጻት፣ ነፍሷን ቀደሳት ነው እንጂ ከኀጢአት አነጻት ያሉት አለቃ አያሌው ታምሩ ብቻ ናቸው። በዚህ ብቻ ቁመው ቢሆን ኑሮማ በጣም ጥሩ ነበር። ማንስ ስምቶኝ፣ ማንስ አርሞኝ በሰው የሚከተሉትን ደግመዋል።
(ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ27-28) ብዙ ዘመን ካለፈ በኋላ እግዚአብሔር ዓለምን በልጁ ሊዋጅና በክርስቶስ ሁሉ አዲስ እንዲሆን ሲፈቅድ፣ መበሥር መልአክ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም መጥቶ "መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፣ የልዑል ኀይል ይጸልልሻል፣ ስለዚህ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል አላት።

በዚህ ቃል የድንግል ሥጋዋም ነፍሷም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ፤

አዲስ ሕይወት አገኘ። እንደዚህ ያለ ዐረፍተ ነገር የሚሰጠው ኀጢአት ሠርቶ ለተመለሰ ሰው ነው እንጂ ስዘለዓለም ንጽሕት ለቅድስት ድንግል እመ አምላክ ማርያም አይደለም። በምንም ዐይነት ሕይወቷ አዲስ ሕይወት አገኘ አይባልም።

ይህም ላይገፉበት ለጥቂት ቀን ከፕሮቴስታንት ቤት ገብተው ያመጡት ዐረፍተ ነገር ነው እንጂ በእኛ እንዲህ የሚል የለም።
(ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገጽ 22) ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሰው ዘር ውጭ የሆነች ልዩ ኀይል አይደለችም ከዳዊት ከአብርሃም የተወለደች ድንግል ናት ብለው ተራ አድርገዋታል። በአንድ አራስ ሁለት ምላሱ።

በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 13 እምነት በኢትዮጵያ በሚለው የመጀመሪያው አንቀጽ የተጻፈውም የሥነ ጽሑፍንም ሆነ የሃይማኖታቸውን የሀገሪቷን ታሪክ ካለማወቃቸው በቀር የሚያሳየው አንድም ነገር የለው። ገጽ 8 ላይም፣ የውጭ ታሪክ ጸሐፊዎች የእሕዛብን ሀገሮች ሲያስሱ በኖሩበት የልማድ ቅያስ ተመርተው ኢትዮጵያ ጣዖት ታመልክ ነበር ብለው ጽፈዋል፥ ስሕተት ነው፥ ጥፋት ነው፥ ብለው ጽፈዋል፣ ስሑትና ደፋር ያሰኛ ጓደኛ መቼም የለ። ሁሉም በትክክል ወንጌል ዐመፀ እንደተባለው በመጀመሪያ ዓለም ሁሉ ከአንዳንድ እንደኑ ሔኖክ ካሉ ሰዎች በቀር ጣዖት አምላኪ ነበረ። ራሱ አብርሃም ሥርወ ሃይማኖትም አባቱ ታራም ጣዖት ያመልኩ ነበር። በእኛም በአኩስም፣ በፀደዋ በየሐ ያሉት ሐውልቶችና ጽሑፎች ኢትዮጵያ ጣዖት ታመልክ እንደነበረች ግዋም አድርገው ያስረዳሉ። እውነትን ቢፈልጉ ሊጠይቁ ይችላሉ። ግን መማር አይፈልጉም? ምን ይደረጋል?

ከዚህ የቀረውን ጉድለታቸውን ደግሞ ሊቀ መንበር ሁነው ባበላሹት ሐዲስ ኪዳንና በሁለቱ ባሕርያት አስተያየታቸው በምዕራፍ ሰባት ከዚህ በፊት ተገልጧልና አንባቢው እንዲያስተውለው አደራ ብለን ወደ ያዝነው ርእስ እንመለሳለን፥ እንመለስ።

7. መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ደግሞ መድሎተ እሚን በሚለው ነሐሴ 1:1954 በታተመው መጽሐፋቸው ገጽ 16 ላይ፣ (ሥላሴ) ሦስቱም አካላት በማሕፀኑ ማርያም አደሩ። ማደራቸውም አብ ለአጽንዖ፥ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ወልድ ለለቢስ ሥጋ ነው። በዚህ ጊዜ መለኮት ርቀቱን ለቆ ሳይገዘፍ፥ ሳይለውጥ፥ ትስብእትም ግዘፉን ለቆ ሳይረቅ፥

ሳይለወጥ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ በተዋሕዶ እንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ ሆነ። ወልድ በለቢስ ሥጋ ማለት ይህ ነው። አብ ለእጽነዖ እደረ ማለትም ሰማይና ምድር የማይወስኑትን ምሉእ፥ ስፉሕ፥ ረቂቅ መለኮትን እመቤታችን በጠባብ ማሕፀን እንድትችለው አጸናት ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለእንጽሖ ማለትም ትስብእትን ከአዳም መርገም አንጽቶ፥ ቀድሶ ለተዋሕዶ መለኮት የበቃ አደረገው ማለት ነው።

8. የቅዱስ ጳውሎስ ኮሌጅ ሁለቱ ሊቃውንት መምህራን ተባብረው በጻፉት፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት በሚለው ሠኔ 21:1982 (አልቦ ማ/ቤት) በታተመው መጽሐፋቸው ገጽ 28-29 ላይ፥ ቅድስት ማርያም በሥጋ ብቻ ሳይሆን በሐሳብም ድንግል ናት፥ በሐሳብዋ ድንግል ናት ማለትም ከኀጢአት ፍጽሞት ንጽሕት ናት ማለት ነው፤ በዚህም መሠረት እመቤታችን በኀልዮ፥ በነቢብ በገቢር ማለት በሐሳብም በቃልም በግብርም ኀጢአት የሌለበት ፍጽምት ንጽሕት ናት፤ ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጣት ጸጋ ነው፤ (ሉቃ.1:28፤) እንዳንዶች እመቤታችን፥ አድሮ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም፤ ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን እይደለችምና፤ ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው፥ ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት፤ ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት፥ የመናገር፥ የገቢር ኀጢአት ፈጽሞ የለባትም። ብለው ከኀጢአት ንጽሕት እንጂ ጥነተ አብሶ ግን እንደነበረባት አረጋግጠዋል።

9. አቶ ዐሥራት ገብረ ማርያምም ትምህርተ መለኮት በሚለው መጽሐፋቸው (ገጽ 95-96) የቅዱስ ገብርኤልን እርኬ ጠቅሰው መንፈስ ቅዱስ ማርያምን ከጥንተ አብሶ እንዳነጻት አብራርተው፤ ገልጸው ጽፈዋል።

ሰላም ለከ ገብርኤል ለማርያም ኀይለ ልዑል ጸለላ
መንፈስ ቅዱስ እንጽሓ ሥጋ አፃላ
ተፈሥሒ ሶበ ትቤላ= ገብርኤል ሆይ! ሰላም ላንተ ይሁን፥ ማርያምን ደስ ይበልሽ ባልሃት ጊዜ፥ የልዑል ኀይል ጸለላት፤ መንፈስ ቅዱስም ሰውነቷን እንጽቷታል። (አነጻት) ዝቅ ብለውም፥ እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ

ይሁንልኝ ባለች ጊዜ፥ ብላ እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ ባሳረፈች ጊዜ፥ ጌታን ከመውለዷ በፊት መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ቀድሶና አንጽቶ የጥንቱን የአዳምን ኀጢአት አስወግዶላታል ብለው ጥንተ አብሶ ወደጌታ ሳየተላለፍ ከማርያም ላይ መቅረቱን አስረድተዋል።

10. የአሁኑ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አቡነ ጳውሎስም ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በአሜሪካ በነበሩበት ጊዜ፥ በፍልሰታ ጾም ስለ ማርያም ባስተማሩበት ትምህርት በቴፕ በተቀዳው፤ ከጥንተ አብሶ ከአዳም ኀጢአት በቀር ኀጢአት አልሠራችም፤ ከጥንተ አብሶ ግን መንፈስ ቅዱስ አጽድቷታል ብለው፥ የኦርቶዶክሳውያን፥ ምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያን ተከታይ መሆናቸውን ገልጠዋል፤ አረጋግጠዋል። በዚህም የተማሩት ኦርቶዶክሳውያን ያመሰግኗቸዋል።

11. የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ለሃይማኖት ማስተማሪያ በባረኩት መጽሐፍና በግብጽ የሃይማኖት መጽሐፍም ከዐረብኛ ተተርጉሞ የሚከተለው አንቀጽ እነሆ!

<u>ስለእመቤታችን ያለ ጥንተ አብሶ መፀነስ የፊጠራ ታሪክ፤</u>

ቅድስት ሐዋርያዊትና ዓለም አቀፋዊትዋ ቤተ ክርስቲያን በምስጢረ ሥጋዌ የወልደ እግዚአብሔር፥ የቃለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ድንግል ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋ መልበስ በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ታምናለች። ያለ አዳም ኀጢአት፥ ያለ ጥንተ አበሶ የተወለደም እሱ ብቻ መሆኑንም ታምናለች። ከአዲሱ ሰውነት ኀጢአትም ነጻ እሱ ብቻ መሆኑን ታምናለች።

ከዚህ በታች የተጻፈው ኀይለ ቃል፤ በዘመናችን በያዝነው አቋም ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፥ ከሰላም ይልቅ መለያየትን ስለሚጋብዝ መጽሐፉን ለአንባቢ ጠቅሰን አልፈነዋል።

ፊርማ፥ ሐቢብ ጊርጊስ፥ የኦርተዶክስ አለት። (Comparative Theology Text Book 1948, P. 84-87 Cairo.)

12. ከዚህ በፊትም ዐፄ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክንና ንጉሥ ተከለሃይማኖትን ይዘው ቦሩ ሜዳ ላይ በ1874 ዓ.ም. ሦስት ልደቶችንና ሁለት ልደቶችን ሲያከራክሩ እንዲህ ተብሏል፤... የሦስት ልደቶች አፈ ጉባኤ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ተጠየቀ አሉና፥ እናትና ልጅን እኮ ልደት እንጂ ያገናኟቸዋል ሲሉ ጠየቁ።

(እስቃ ሥነ ጊዮርጊስ እንዲህ ብለው መጠየቃቸው እመቤታችን አዳም እስወሰዶት የነበረውን የጸጋ ልደት እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ተወልዳለች፥ ልጅዋንም እንደሷ የጸጋ ልደት ተወስደ ባይ ናቸውና፤ ይህ ልደት ያገናኛቸዋል ሰማስት ነበር።) መላከ ብርሃን ወልደ ዮሐንስ ግን ከአፋቸው ጠሰፍ አድርገው፤ ሁሉ ወደሚያውቀው ወደ ግዙፍ፥ ወደ ልደተ ሥጋ ሰውጠው፥ አባዬ! አባዬ! ያራዳ መምህር! የርሷ ልደት በዘር፥ በሩካቤ፥ የእርሱ እንበል ዘር ምን አገናኛቸው ብለው መለሱ። በዚህ ጊዜ ካደባባይ ያሰው ሁሉ ሣቀ፥ አደነቀ (መልአክ ብርሃን አድማሱ መጽሐፈ ቅኔ፤ ገ. 281-2)

13. የግብረ ሕማማት መተርጉምም የኢሳያስን ከ16:1-7 ገጽ 204-5 ላይ እንዲህ ብሎ ተርጉሟል፤ አብራርቷል። በአማርኛ የኢሳያስ ጥቅስ፤ የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን፥ ለታሰሩትም መፈታትን እነግር ዘንድ ልኮኛል። የተወደደችውን የእግዚአብሔር ዓመት፥ አምላካችንም የሚቀበልበትን ቀን እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ፥ እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፥ በአመድ ፈንታ አክሊልን፥ በልቅሶም ፈንታ የደስታን ዘይት፥ በሐዘንም መንፈስ ፈንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ እሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል።

የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሚለው እንሥቶ የዘሰዓስም ደስታ እስከሚለው ድረስ የሚከተለውን ትርጓሜ ሰጥቷል።

ይቤ መተርጕም ወቃሉስ መንፈስ እግዚአብሔር ዘላዕሌየ ይተርጎም በእንተ ዝንቱ መንፈስ ቅዱስ እንተ ርእየ ዮሐንስ መጥምቃዊ በኀበ ዮርዳኖስ በጊዜ ጥምቀተ አምላክ ቃል። እስመ ይቤ ውእቱ ስንስ ርኢኩ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ይወርድ እምሰማይ ወነበረ ዲቤሁ ምስለ ቃለ አብ እንዘ ይሰምዑ ኩሉ ሕዝብ እንዘ ሰምዐ ይከውን በእንተ ልደቱ። ይቤ በእንተዝ ቀብዐኒ ወፈነወኒ ይተረጎም በእንተ ቅብዐት ካዕብ በመንፈስ ቅዱስ ዘወረደ ላዕለ ማርያም ወእንጽሐ ሥጋ ዚአሃ ሰተወክፎ አምላክ በከመ ይቤላ ገብርኤል መልአክ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወየኀድር ወሰተ ከረሥኪ ዘውእቱ ያነጽሐኪ። ካዕበ ያቤላ እስመ ዘይት ወለድ እምኔኪ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ። ወዛቲመ ትርጓሜሃ ለቅብዐት፥

እስመ መንፈስ ቅዱስ አንጽሐ ሥጋሁ ለእዳም አንተ ኮነት ኀጢአት ሀአት ላዕሌሃ ዋእታ ወእርኮሰታ እስከ ኮነ አሐደ ኪነተ ባቲ እምላከ ቃል...።

ከማርያም ላይ የወረደ መንፈስ ቅዱስ አምላክን እንድትቀባል ሥጋዋን አነጻት ብሏል።

14. <u>ካልእ ጎርጎርዮስም፤</u>

ውእቱ ዘቀደሳ ወእንጽሓ ለእግዝእትነ ማርያም ወላዕሌሃ ከሡተ ምስጢረ ሥላሴ =እመቤታችንን ማርያምን የቀደሰትና ያነጻት፥ በላይዋ ላይም የሥላሴን ምስጢር የገለጠ እሱ ነው ብሏል።

15. <u>የቅባቶች ባለቅኔዎችም፤</u>

<u>መወድስ ዘአለቃ ኀበዜ ዘደብረ ወርቅ፤</u>

ኢናንክር ኀዳጠ ለመንፈስ ቅዱስ
ለንጽሕተ ባሕርይ ድንግል እመ እንጽሓ እምነውር
መሐፒልኑ ይትኀሠሥ ለእንተ ጻዕደወ ፀምር
ለርሉሕ ዳእሙ ይትኀሠሥ በግብር
አንክሮስ ናንክር
እመ አንጽሐ ኪያነ እምርሰሐተ ኄጋይ ጽቡር።
ርሱሕኒ እንዘ ሀሎ እጻዕድወ ሜላት ሥሙር
ለነዌ ጸውየ ነዌ እንበ ኢይጸዋዕ አልአዛር
ባሕቱ ኢሀሰወ ፍትሕ እምጣነ ኢይክል ፍጡር
በላዕለ ነጋሢ ፈቲሐ ፍትሕ ወአንድዶ እሳት በላዕለ ባሕር።

<u>ትርጉም፤</u>

ባሕሪዋ የነጻ ድንግልን ከነውር ቢያነጻት መንፈስ ቅዱስን ጥቂት እናደንቅም። ቀጥር:209፤ ገጽ 215፤ የግዕዝ ቅኔያት፥ የሥነ ጥባብ ቅርስ ሁለተኛ ክፍል፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት እ.እ. 1984።

ይህ መወድስ በቅባት በኩል ያለውን የጥንተ አብሶ እስተያየት ያጠቃልላል።

16. <u>በየእሊቃውንቱ እጅ የሚገኘው ምዕላድም እንዲህ ይላል</u>

ቅዱስ ቄርሎስ ንስጥሮስን ከረታበት አንቀጽ፤ እራቱ መናብርት በተሰበሰቡበት ቄርሎስ ንስጥሮስን እንዲህ ብሎ ይጠይቀዋል፤ የደስታ መጀመሪያና መጨረሻ ማርያምን እመቤቴ ሆይ! እይዞሽ አትፍሪ ከእግዚአብሔር ውድነትንና ባለሟልነትን እግኝተሻል እነሆ! ትፀንሻለሽ፥ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ በይው፥ እሱም የዓለም

መድኀኒት የሚሆን ነው። ብሎ የነገራትን ቃል ሐሰት ማለትሁ ነዋ! ሁለት አካልማ ቢሆን መድኀኒተ ዓለም መሆን በተቻለውን ነበር? ብሎ ጠየቀው፤ ተሐስወኑ ቃሉ ለገብርኤል እመ ይቤላ ለድንግል ጥንተ ትፍሥሕት ወፍጻሜ ሐሜት፥ ኢትፍርሂ ማርያም እስመ ረከብኪ ሞገስ በኀበ እግዚአብሔር ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ እንዳለ። ሁለት አካልማ ቢሆን በልጇሽ አምላክ ያድርበታል፥ የአምላክ ማደሪያ ይሆናል ባላት ነበር እንጂ መንፈስ ቅዱስ ያነጻሻል፥ እግዚአብሔር አብ ያጸናሻል፥ ቃል እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ፥ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ከሁለት አካል አንድ አካል፥ ከሁለት ባሕርይ አንድ መለትስ ሁኖ በማሕፀንሽ ያድራል ባላት ነበር? አለው።

17. እንዲያውም እንዳንዶቹስ በሮማዊት ቤተ ክርስቲያን፥ የማርያም ክብር እንዲህ የበዛው በሴቶች የአሕዛብ አማልክት፥ በሮሚቱ ዲያና፥ በግሪኪቱ አቴና፥ በኤፌሶኒቱ አረቴምዝ፥ የዜፍ የትልቁ የተረት አምላክ ልጆች ስለተተካች ነው፤ የቅዱስ ሚካኤል በዓል አከባበር በፀሐይ አምላክ በአፓሎና በዙሐል እንደተተካ (ድርሳን ሚካኤል ዘሠኔ) ጾመ ዮዲትና ጾመ አስቴርም በዐርብ ረቡዕ እንደተተኩ።

ክርስትና ብብዙ ሀገር የገባበትን ብሔር ልማድና ባህል እየያዘ ገብቷል፤ እንደገባ። ለምሳሌ በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእኛ ብዙ ማግባትን፥ ግዝረትን፥ ቀዳሚትን፥ ሴት ስትወልድና በወር አበባ መርከስን፥ ቶርበው የተጋቡ ሰዎች በበዓላትና በጾም ቢገናኙ ማደፍን ወዘተ የመሳሰሉትን ይዞ እንደሚገበሰበስ ይላሉ። ይወልደዋል ካስ ይመስለዋል አይገድምና ሁና ነው እንጂ ይህ እንኳ ትንሽ ቀነጣ።

(Il Grande Libro Della Mitologia Greca E Romana)

18. በጠቅላላ የግብጻውያንን አስተያየት የሚገልጥ እነሱ እንደጻፉት በእንግሊዝኛ ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን፤

<u>The Blessed Virgin</u>

She was born like all other human beings, with the original sin. But the Scriptures tell us that God Purged the sins of Isaiah, Sanctified Jeremiah from the womb, and in selecting the Baptist, He filled him with the Holy Spirit while Yet within the womb (Is. VI: 6-7, Jer.1:5; Luke 1:15)

If God so willed to sanctify His prophets there by eoabling them to carry out the mission eotrusted to them, how much more will He sanctify Her Who was to bear the Word Iocarnate within Her Womb? And as the Coptic Church expresses it: if He so desired to fit his servaots for their task, how much more will He fit the Queeo for Her Role? From her lifestory, we know that she was offered to the Temple wheo She was three years old, and lived there in uotil Her betrothal to Joseph. The high priests. through uoaware of the Majesty of the Role she was to fulfil, regarded Her with great esteem. So much so, tbat when the time came for Her to be married they dared oot follow to the letter the Law of Moses, but resorted to the method iodicated by God to this prophet for the cboice of Aaroo to the high Presthood, (Numbers XVIII;1-9). Consequently, they laid tbe rods of the men, decreed by the Mosaic Law eligible for Her, io the Temple; next moroiog, Joseph's rod was fouod budding. They betrotbed Her to him and eotrusted Her to his charge (Which was legal according to their Law)

,St. Luke tells us of the Angel Gabriel appearing to Her, hailing Her with words. "... Thou art highly favoured, the Lord is with thee, bleased art Thou among women..." (1:28-24) The Coptic Fatbers assert that had oot Mary so readily assented, declariog that she is "the haodmaid of the Lord", the Christ would oot have iocarnated through Her; accordingly, She had an active part in effecting the Salvatioo of mankind. As for St, Matthew, he tells us of the doubts which assailed Joseph and the appearance of the Aogel to him to coofort him (1;19-21)

The Coptic Church believes that She is Perpetual Virgio, according to the Scriptures. To cite but a few passages as

an example: King Solomon said of Her, "A garden inclosed is my sister, my spouse; a spring shut up; a fountain sealed..." (Song of songs IV: 12) While Exekiel descirbes how God took him to the gate that looks towards the east and "it was shut, aod He said uoto me, this gate shall be shut, it shall oot be opeoed, aod no man shall enter in by it; because the Lord the God of Israel hath entered by it, therefore it shall be shut" (XLIV:1-2) At the same time, when the Christ huog oo the cross, He said to His Mother: "Woman behold thy son!" then to His beloved disciple: "behold thy Mother". And the Evaogelist adds: "from that hour, that disciple took her to his own home" Now, according to the custom of the East, the widowed mother lives with her son; if she has no son, she lives with her daughter. under no circumtances does she lives with relatives, still less with strangers, so loog as she has sons or daughters. Our Blessed saviour gave us the example of liveing according to the social customs which clashed not with His teachings. He certainly .keew the prevaleot custom on this matter and therefore would oot have entrusted His Mother to His disciple who was a stranger. As for mentioning the Lord's "brothers" aod "sisters" that again has a special significaoce in the East, namely that all cousins are considered brothers and sisters -So much so, that in Egypt, it is commoo to call ao uncle "father" (addiog his name to it) and an aunt, "mother" with the same addition just to make the hearer realize that it is not the factual parent who is alluded to and just as the Blessed Virgin was born like the rest of the human race, so did she taste death in like manner. But, because God the Father overshadowed Her, aod the Holy Sprit came upoo Her, and the Incarnate Word dwelt with io Her Womb

taking from her His flesh, Her body was not left in the earth to decay like those of others; it was carried away by the angels. This carrying away of Her body's termed "Her Assumption" and is celebrated by the Coptic Church on the 22nd of August (16th Messra in the Coptic calendar)
To express their esteem of the Blessed Virgin, the Coptic Fathers were the first to entitle Her "Theotokos" (or Mother-of-God.) In addition, they call her "Mother of the Light," "Mother of the Mercy", "Mother of the Grace", "Ship of safety" and numerous other epthets. Also, in imploring the saints to intercede for mankind, they mention Her first and last. While during the prayers preceding the Liturgy, there is a chant entreating the celestial beings to intercede for us. The Blessed Virgin takes precedence even over the celestial hosts; and the coptic word used in petitioning Her is "presira" which denotes that Her mediation is authoritative. She was never defiled by bad desires, had remained from childood steadfastly just and has always walked along the right way without fault or stumbling...

St.Jacob of Sarug (1) (451-521)

* The Word of the Father came forth from His Bosom, and in another He put on a body.
Form one Bosom He came forth to another.
These pure bosoms were filled with Him.
Blessed is He who dwells in us.

St. Ephraim the Syrian

ST. Mary& The Original Sin:

The Orthodox Church, Whose love towards St. Mary is deeprooted, considers her more holy than all the heavenly

creatures, whilst a natural member of the human race. We do not however, set her apart from the human race by assuming that she was born without orginal sin, as if sbe was horn not of human seed.

This reality is declared in the following Theotokia

"How deep is God's abundance and wisdom,
that the Womb under judgement
buought forth children by incurring pain;
she became a fountain of immortality,
bringing forth Emmanuel without human seed,
so that He might destroy corruption of our nature".

ይህንም በዓለም ጉባኤ አረጋግጠዋል፤ cit.pp.49-50

Thus, the Church makes a distinction between St. Mary's life before and after the moment of divine incarnation.

In another theotokia we say;

"The Holy Spirit filled you completely,
filled every part in your soul and body,
O Mary, the mother of God".

St. Mary, herself declared her joy to God, her saviour... for indeed she was in need of salvation.

To this effect St. Ambrose says

"When the Lord wanted to redeem the world, He began His work with Mary, that she, through whom salvation was prepared for all, should be the first to draw the fruit of salvation from the Son".

St. Augustine also says;

"Mary sprang from Adam, and died in consequence of sin;
Adam died in consequence of sin;
and the flesh of the Lord, sprang form Mary,
and died to desory sin".

Lastly this Orthodox Concept preserved our Church from any exaggeration or confusion between Christ and His

Mother. No Orthodox theologian calls St. Mary 'Corredemptrix", and no worship is offered to her, but only veneration and praise...
In other words, in the Orthodox Church there is an accurate line that divides Christ from St. Mary, His Mother.
(Wort and Wabrheit, op.cit)

19. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በሌላው ሁሉ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ከማርቆስ አባታችን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን እናታችን እያለች ሙሉ በሙሉ ተስማምታ እንደኖረች በጥንተ አብሶም ተስማምታ ኑራለች። በቀደም ግን ያለምንም መረጃ ወይም ምክንያት፣ ቀድሞ ስትለው የኖረችን ሁሉ ጥላ፥ ሌሎች ብዙ ሊቃውንቶችዋ የጻፉትንም እንዳላየች ዐይታ፥ መስላ፥ ጥንተ አብሶ አልነበረባትም ብላ ጽፋለች። በዚህ ጊዜ ብዙ አስተዋይ አንባቢዎች ብዙ የኢትዮጵያ ካህናት በዘመናቸው የሚጻፉትን መጻሕፍት ስለማያነቡ፥ ጋዜጣም ስለማያነቡ፥ የዘመኑን ርምጃም ስለማይከታተሉ፥ አውግዘናል፥ ገዝተናል የሚሉም በስው ወሬ ስለሆነ ነው እንጂ ይህን የሚመስል ነገር የለም ብለዋል። ምክንያቱስ? ቢሉ፣ ብዙ ቄሶች አገሌ መናፍቅ ነው እያሉ፣ ስም ያጠፋሉ፣ መጽሐፉን አነበብኸው ወይ? ሲናገር ሰማኸው ወይ? ሲሏቸው ግን፣ የለም፥ ያነበበ ነገረኝ፥ ሲናገሩ ሰማሁኝ ብለው ያርፋሉ። ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ የቀራል እንጂ፣ እንኳን መጽሐፍና በአማርኛ ጋዜጣም እንኳ አንበው የማያውቁ፥ የአማርኛ ዐርቢ የሚባሉትን ሆሄያት የማያውቁ ብዙ ናቸው።
(የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምላኮትና የውጭ ግንኙነት ምዕራፍ 7 ገጽ 37) በዚህም ብዙ ሊቃውንት ተደናግረዋል፣ ተደንቀዋል፣ ይሁን እንጂ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ለመገናኘት አንድ ርምጃ ወደፊት ቀርባለች። የአብያተ ክርስቲያንን መዋሐድ የሚፈልጉም አበጀሽ ብለዋታል።

<u>የዚህ ርእስ መደምደሚያ፣</u>

ጥንተ አብሶ ከጥምቀትና ከስቅለት ወዲህ፣ እንኳንስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ይቅርና ከማንኛቸውም ክርስቲያን ላይ በክርስቶስ ሞት ተፍቋል፣ ተደምሷል፣ ወላዲተ አምላክ ማኅደረ አምላክ ያደረጋት ያበቃት፤ ያነጻት፤ ያመቻቻት ግን መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በብዙ መጻሕፍትና ሊቃውንት ተረጋግጧል። ጥንተ አብሶ ነበረባት አልነበረባትም በሚለው ሐሳብ ዓለም በሁለት ይከፈላል፣ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከነተከታዮችዋ ከላይ እንዳየነው ጥንተ አብሶ አልነበረባትም፣ ቅድስት ድንግል ማርያም እምቅድመ ዓለም ተመርጣ ዘእንበለ ኀጢአት ስትወርድ ስትዋረድ የመጣች ንጽሕት ኅርይት ዘር ናት ስትል፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ኦርቶዶክሳውያት ግብጻውያት፤ ሶርያውያት፤ አርመናውያት፤ ጽርእውያት (ግሪክ) ደግሞ ከጥንተ አብሶ ያነጻት መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ።

የሚሰጡት ምክንያትም ድንግል ማርያም ከሐናና ከኢያቄም በሕግ የተወለደች ከጥንተ አብሶ መንፈስ ቅዱስ ያነጻት እንጂ ከሰማይ የወረደች አይደለችም። ማርያም ሰው ካልሆነች ደግሞ አምላክ፣ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው አልሆንም ማለት ይሆንና፣ ሰው ሁኖ፣ ሥጋ ለብሶ አዳነን የሚለው ትምህርት ከንቱ ይሆናል። ምክንያቱስ ቢሉ ሰው የሆነው በእናቱ እንጂ በአባቱ አይደለምና። ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ አንባቢም፣ ኅሊናው የተቀበለውን ተከትሎ ወደ ፈለገው ሊወግን ይችላል። ንጽሕናዋንና ወላዲተ አምላክነቷን፤ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን ካመነ ጥንተ አብሶ ነበረባት አልነበረባትም በማለት ጽድቅ ይሉ ኩነኔ የለምና።

የሆነስ ሆነ አንተሳ ስለዚህ የምታምነው ምንድር ነው? ለሚለኝ ጠያቂ፣ የሁለቱም አስተያየት ከላይ ተገልጧል፣ ስለዚህ እንዲያው በሹክሹክታ፤ በግምት ሳይሆን ቅድስት የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሲኖዶስ ወስና በቃለ ዐዋዲ የምትሰጠውን ውሳኔ በደስታ እቀበላለሁ፣ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፣ ስሆን፤ ከዚህ በፊት የሚናገሩትን የማያዉቁ ጋዜጠኞች፤ መሳዮች በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም እንደጻፏቸው ሁለት አናቅጽ ግን መሆን የለባትም።

አብያተ ክርስቲያናቱ ግን ከሁለቱ አዱን አጽድቀው ወይም የወደዱትን ይዘው ቢገኙ በጣም ጥሩ ነበር።

ለዚህ ምዕራፍ የተነበቡ መጻሕፍት፤

1. ሃይማኖተ አበው፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት አ.አ. 1967።

2. መጽሐፈ ቅዳሴ፥ ብርሃንና ሰላም፥ አ.አ. 1964 ዓ.ም.

3. መጽሐፍ ቅዱስ፥ ብርሃንና ሰላም፥ አዲስ አበባ፥ 1964 ዓ.ም.

4. ህብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት) ስይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ፥ አልቦ/ ማ አዲስ አበባ፥ ሠኔ: 21: ቀን:1982 ዓ.ም.

5. ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፥ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1943።

6. አያሌው ተአምሩ፤ (አለቃ) የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፥ ብርሃንና ሰላም 1953: ዓ.ም. አልቦ: ማ.

7. አድማሱ ጀምበሬ (መልአከ ብርሃን) መድሎተ አሚን፥ ነሐሴ:1: 1954፥ አልቦ ማ/ቤት።

8. ዐሥራት ገብረ ማርያም፥ ትምህርተ መለኮት፥ አርቲስቲክ ማ/ቤት፤ 1983 ዓ.ም.

9. የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ማስተማሪያ፥ (ከዐረብኛ ተተርጉሞ) Comparative Theolgy Text Book 1948, p.84-87፥

10. Elmasry, Iris, H. Intraduction to the Coptic Church. Dar El Alam El Arabi.

11. Malaty, Tadrogy. (Fr. St. Mary. in the Orthodox Concept. St. Mark Church, Allen street Kensington, London. W.S. U.K.

12. በእየሊቃውንቱ እጅ የሚገኘው ምዕላድ።

13. ድርሳነ ሚካኤል

14. 1L Grande Libro Della Mitologia Greca E Romana. Michael Staglenton e Elizabeth Servan-Schreiber, Arnondo Mandatori, Editore, S.P.A. Milano 1979.

15. Wort und Wabrheit, Revue for Religin and Culture. Supplementary Issue, Nember 5.July 1989, pp.49-50.

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## ሃይማኖት፤

### ምግባር ከሃይማኖት፥ ሃይማኖት ከመግባር፤

በእኛ የተለመደው አነጋገር ምግባር ከሃይማኖት፤ ሃይማኖት ከምግባር ነው።

እንደኛ በባህላችን አነጋገር ከትልቁ ትንሹ፥ ከፍተኛው ኋለኛው ይቀድማል፤ ለምሳሌ መኳንንት መሳፍንት፥ ሴት ወንድ፥ እናት አባት፥ ዐርብ ረቡዕ፥ እሑድ ቅዳሜ ይላል። ሁለተኛ ደግሞ ከምግባርና ከሃይማኖትም ግብር ይቀድማል፥ ገብሩ ካግረ ከተምረደ ከለሰለሰ በኋላ ነውና ወደ ሃይማኖት የሚመለሰ።

ሃይማኖት ቢኖረውም ምግባር ከሌለው ለለ ማይጸድቅ በዚህ ጽሑፍ ደግሞ ምግባር የሚቆምበት መሠረት ሃይማኖት ስለሆነ ሃይማኖት ቀድሟል። ሃይማኖትና ምግባር ሁለቱ ሰው የሚቆምባቸው ሁለት እግሮች ናቸው፤ ይህኛው ቀኝ ያኛው ጋራ ነውም አይባሉም። ባንድ እግር አይኬድም አይቆምምና እኩል መታየት አለባቸው።

በሁሉም ሁሉን ይወቅ ምዕራፍ 35፥ ገጽ 207 ስለዚህ የተለጠው እንደ ተጠበቀ ሁኖ ከዚህ ግን፥ የመጽሐፉ ዓላማ በሃይማኖት ብቻ እንጸድቃለን፥ ጸድቀናል፥ ድነናል የሚሉ ሰላሉ፥ በሃይማኖት ድነናል ማለት ምን እንደሆነ ለማስረዳት በሰፊው ታትቷል።

ለወገበ ነጭና ለጠራዝ ነጠቅ ተማሪ አንዳንድ ጥቅስ ይይዝና ሃይማኖት ያለምግበር ወይም ምግባር ያለ ሃይማኖት የሚያድን ይመስለዋል። ግን ከላይ እንደተገለጠው ሁለቱም ካልተባበሩ አንዱ ብቻውን አያድንም። አንድ እሑድ ሰባኪ ስለሃይማኖት ይሰብክ ኑሮ እመኑ ትድናላችሁ እያለ ደጋግሞ ሲሰብክ የለግ ገር (ጎጋ) ምእመን እምነትን ተረድቻለሁ፥ እምላኪየን ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኀኒቴን ተቀብያለሁ፥ አምኛለሁ፥ በማመኔም ድኛለሁ። ጸድቂአለሁ እያለ ሲፈነጥዝ፥ በሚቀጥለው እሑድ ደግሞ ያው ሰባኪ ይሁን ወይም ሌላ አልታወቀም ስለምግበር እየሰበከ ደግ ሥሩ ትጸድቃላችሁ፥ ደግ ሥራ ያጸድቃል እያለ ሲያስተምር ሰማና የሚከተለውን ተቀኘ፤

እንድ ይበቃል የውንጌል ቃል

አለመስጠት ያጸድቃል

ይህም የምርምር ቅኔ ስለሆነ መስጠት ያጸድቃል አለ፥ ለምግባር፥ አለመስጠትም ያጸድቃል አለ በሃይማኖት ብቻ፤ ብሎ ተቀኘ። ሁለት ነገር

መዘባረቅ ምንድር ነው ብሎ ወይንም ለቅኔው ውበት ሲል እንዲህ ይበል እንጂ መስጠት ያለሃይማኖት ብቻውን አያጸድቅም፤ ሃይማኖት ያለምግባር አካል የለውም።

ማመን መቀበል እንጂ ማወቅ ብቻ አይደለም። ማመን ማወቅ ብቻማ ቢሆን ኑሮ አጋንንት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉና በጸደቁ ነበር።
(ማር. 1:24፤ 34፤ 5:6-7፤ ማቴ.8:29፤ ሉቃ.4:34፤ 8:28) ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ ጊዜ ሩጦ ሰገደለትና በታላቅ ድምፅ እየጮኸ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ! ካንተ ጋራ ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ አለ። በልዩ ልዩ ደዌም የታመሙትን ብዙዎቹን ፈወሰ፤ የብዙዎቹንም አጋንንት አወጣ። አጋንንትም ክርስቶስ መሆኑን ዐውቀው ነበርና ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም።

ይህ አገር አምኗል ሲባል የጊዜውን መንግሥት ሕግ፥ አስተዳደር፥ ስልጣን፥ ዳኝነት ተቀብሎ እየገበረ ይኖራል ማለት ነው እንጂ መንግሥት መኖሩን ዐውቆ፥ እያወቀ ቢሸፍት አመነ ማለት አይሆንም። ክርስቶስንም ማመን ትእዛዙን ተቀብሎ እሱን ተከትሎ መሄድ ነው።
በሃይማኖት ብቻ በጸጋው ድነናል የሚለው ትምህርት የመጣው በመካከለኛው ዘመን የሮም ቤተ ክርስቲያን ከሃይማኖት ይልቅ ምግባርን፥ ከክርስቶስ ከወልደ እግዚአብሔር ከዓለም መድኀኒት ይልቅ፥ ዛሬ በተዋሕዶ እንደሚደረገው፥ ከወንጌል ይልቅ ሥርዓተ ረበናትንና መጽሐፈ ባልቴትን ትሰብክ ስለነበረ አነሉተር ክርስቶስን ለማስገባት ሲሉ በጸጋው ድነናል አሉ። የውነታቸውን ነው፤ በዚያን ዘመን ኑረው ቢሆን ብዙዎች ፍቅረ ክርስቶስ ያደረባቸው ሁሉ እንደሚከተሏቸው አይጠረጠርም። ለመሆኑ የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች እነማናቸው ለሚል ጠያቂ ከዚህ ቀጥለን እናቀርብለታለን፤
(ሮሜ.1:16-17) በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኀይል ለማዳን ነውና። ጻድቅ በእምነት ወደ እምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈው የእግዚአብሔርም ጽድቅ ከእምነት በእርሱ ይገለጣልና። ጻድቅ በሃይማኖት (በእምነት) ይድናል። (3:21-22) አሁን ግን በኦሪትና በነ ብያት የተመሠከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፤ እሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው

የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፥ ልዩነት የለምና፥ ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር ጎድሏቸዋል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ በእምነት በደሙ ማስተስረያ ባደረገው (በኢየሱስ ክርስቶስ) በጸጋው ይጸድቃሉ።

(ገላ. 2: 15-16) እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን፤ ኀጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤ ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በኦሪት ሥራ እንዳልሆነ ዐውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በኦሪት ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በኦሪት (ሕግ) ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ በጸጋው ድነናል፥ ጸድቀናል፥ የሚለው አነጋገር የመጣው እንዲህ ካሉ ጥቅሶች ነው። ይህ የሚያሳው በፈረሳዊነት የምትጀነን፥ በሥርዓተ ሪበናት ተጠቅላ፥ በመጽሐፈ ባልቴት ተሸፍና ትግበሰበስ የነበረች ኦሪት ጽላሎትነቷን ጨርሳ ማለፏን እንጂ ግብር፥ ሥራ አያጸድቅም ለማለት አይደለም፤ ይህ ቢሆን ኑሮስ ዝቅ ብሎ የተጻፈውን በዚያው መልእክቱ በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ የሚጽፈው ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ አይጽፍም ነበር። (ለዚህ ምዕራፍ 17ን ያየዋል)

ቅዱስ ጳውሎስ እግር በእግር ጌታን ተከትሎ ነው የሚሰብከውና የሚያስተምረው፤ ጌታም በእሱ ያመነ እንደሚድን ደጋግሞ ነገሯል፤ አስተምሯል፤ (ዮሐ.3:14-18) ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል። በእሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም ለመፍረድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና፤ በእሱ የሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል። ብርሃንም ወደ ዓለም ስለመጣ፥ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። (ዮሐ3:36) በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ፥ ሕይወትን አያይም።

(ዮሐ. 6:28-29) እንግዲህ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን

እናድርግ? አሉት፣ ኢየሱስም መልሶ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።
(ዮሐ.11:25-26) ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞትም እንኳ ሕያው ይሆናል፣ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም፣ ይህን ታምኚለሽ? አላት።
(ማር.16:16) ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል። ወንጌላዊው ዮሐንስም (ዮሐ.20:30-31) ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ ነገር ግን እሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፤ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል።
ስለሃይማኖት (እምነት) ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጽፉትን ሁሉ ጽፎ ለመጨረስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቢአንስ አንድ አምስተኛውን መጽሐፍ ያስፈልጋል። ስለዚህ ከዚህ በላይ ለማንበብ ለሚፈልጉ በአጭሩ ትንሽ ጥቅስ ጠቅሰን ወደ ምግባር እንመለስ፣ ዕብ.11: ምዕራፉን በሙሉ ከፈለጉ ያንቡ።

## ምዕራፍ ፀሥራ ሰባት

### ምግባር፣

ጌታ ወደዚህ ዓለም ከመጣባቸው ሁለቱ ምክንያቶች፣ ቤዛና አርአያ፤ አንዱ በአርአያ ስም የሚጠራው ምግባር ነው። ምግባር ከተጠመቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጊዜ ስቅለቱ የሠራቸውን ሁሉ ለመፈጸም፣ መፈጸሙ ባይቻለም መፍጨርጨር፤ መሞከር ነው። እንደ ተጠመቀ ጾሟል፣ ጸልዮአል፣ ለተራበ አብልቷል፣ ለተጠማ አጠጥቷል፣ በሽተኛ ጠይቋል፣ ድውይ ፈውሷል፣ በጠቅላላውም በትዕዛዝ በጎ ሥሩ እያለ አስተምሯል። ሕገ ኦሪትንም የማያስፈልገውን ለጽላሎት የመጣውን እየሻረ፤ በዐሠርቱ ቃላት እንደ ተገለጠ አጥብቋል። ሐዋርያትም እሱን ተከትለው ስለምግባር ሰብከዋል፣ አስተምረዋል።

ለሁሉም መደምደሚያ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5-7 የተጻፈው ስለምግባር ስለሆነ፤ ክርስቲያን ሁኖ የክርስትናን ምግባር ማወቅ የሚፈልግ ሁሉ መላልሶ ማንበብ አለበት።

ከዚህ ግን ጎላ ጎላ ያሉት ብቻ ይጠቀሳሉ፥ (ማቴ5:3-12) በመንፈስ ድሆች (ትሑታን) የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነሱ ናትና። የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን ያገኛሉና፤ የዋሆች ብፁዓን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና። ስለጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ (የሚጸሙ) ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና። የሚምሩ (የሚራሩ) ብፁዓን ናቸው ይማራሉና። ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና፥ የሚያስታርቁ ብፁዓን ናችው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና፤ ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው። መንግሥተ ሰማያት የእነሱ ናትና። ሲነቀፏቸሁና ሲያሳድዷቸሁም በእኔ ምክንያት ክፍዉን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳደዋቸዋልና። (ማቴ.7:21-27) በሰማያት ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች፥ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርነምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደርግንምን? ይሉኛል። እኔም በዚያን ጊዜ ከቶ አላውቃችሁም፤ እናንተ ዐመፀኞች ከኔ ራቁ እላቸዋለሁ።
(ማቴ.5:20) ጽድቃችሁ ከጻሐፍትና ከፈሪሳውያን ካልበለጠ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም።

በመጨረሻውም ጌታ በዕለተ ምጽአት ሲመጣ የሚጠይቀው ምግባርን እንጂ ሃይማኖትን አይደለም፤ ምን ብሎ ለሚል ጠያቂም (ማቴ.25:31-46) ንጉሡም በቀኝ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፤ እናንተ ያባቴ ቡሩካን! ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና......።
(ራእ. 22:12-13) እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከኔ ጋራ አለ። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውንና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።

በጸጋው ድንናል አለ ተብሎ ንግግሩ የተጣመመበት ቅዱስ ጳውሎስም (ሮሜ: 2:6-11) በተነሣበት በዚያው መልእክቱ በሌለው እንኳ ሳይሆን፤ እሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክባል (ይከፈላል)፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናን ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ

የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፥ ለዐመፃ ለሚታዘዙ እንጂ ለእውነት ለማይታዘዙትና በእድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። ክፍውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፤ አስቀድሞ በእይሁዳዊ ደግሞ በግሪክ ሰው፤ ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞ ለግሪክ ሰው፤ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላምና። በ(1ቆሮ:6:9-10) ላይም እንዲህ ብሏል፤ ወይስ ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ። ሴሰኞችም ቢሆኑ ወይንም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች፥ ወይም ሰዶማውያን ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካራሞች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። በጸጋ ብቻ የሚዳን ቢሆን ኑሮ ይህን ሁል ምን አስፈለገው?

በ(2ቆሮ.6:4-7) ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፥ በመከራ፥ በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፥ በመጦም፥ በንጽሕና፥ በዕውቀት፥ በትዕግሥት፥ በቸርነት፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፥ በእውነት ቃል፥ በእግዚአብሔር ኃይል....።

(ገላ.5:18-26) ነገር ግን እላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ፤ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ፥ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስበርሳቸው ይቀዋወማሉ፥ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ (እሪት) በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው፤ እሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ሟርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት ይህንም የመሰለ ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን፥ የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። (ወንጌላዊ ሆይ! በጸጋው ጸድቀሃልና ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ኀጣውእ በድፈረት ትሠራለህ? አትሠራም፤ እንግዲያማ እፍህ የሚያወራውን ልብህ አያምንማ! እንዲህ ከሆነ ከጓደኛህ ቤተ ክርስቲያን ጋራ አትጣላ፥ ተግባብተህ፥ ተራርቀህ፥ ተባብረህ ኑር፤ ውዳሴ ከንቱ አያታልህ፤ ገንዘብ አይማርክህ፤ ትዕቢት አይጨፍንህ። የመንፈስ ፍሬ የተባሉት እነዚህሳ ደስ አይሉህም? እነሱም

## አንድ እረኛ፡ አንድ መንጋ

ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ናቸው። በእነዚህ ላይ ሕግ የለም። እነዚህን በመፈጸም ክርስቶስን ለማስደሰት ትፍጨረጨር የለም?
ያዕቆብም (2:14-26) ሃይማኖት ያለሥራ ዋጋ እንደሌለው ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው እያለ ገልጧል። ስለዚህ ብዙ ለማንበብ የሚፈልግ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንዲያነብ ይጋበዛል።

<u>ስለ ምግባርና ሃይማኖት አጭር ጥቅስ፤</u>

(ዮሐ.3:16-19፤ 6:29፤ 14:15፤ 21፤ 23፤ 24፤ ማቴ.25:31-46፤ ሮሜ.2:6፤ 13፤ 1ዮሐ.5:1-5፤ ያዕ.2:17፤ 20፤ መዝ.62:12፤ 1ጴጥ.1:17፤ 1ዮሐ.5:29፤ ገላ.6:9፤ 2ተሰ.2:3-13፤ ዕብ.13:2፤ ዘፍ. 19:2፤ 1ጢሞ.1:18፤ ያዕ.2:14፤ 21፤ ፤25፤ 17፤)

<u>፤ምግባርና የሃይማኖት መደምደሚያ፤</u>

ውድና ክቡር አንባቢ ሆይ! ሃይማኖት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ራሱ የገለጠው አስተርእዮ (ክሥተት) እንጂ የሰው ልጅ ፍልስፍና አይደለምና፥ በፊት የሰማሁት እንዲህ አይደለም፥ እኔ እንዲህ ባለ ነገር አልስማማም፥ ለልቡናዬና ለሐሳቤ እንጂ፥ ለእግዚአብሔር ቃል አልታዘዝም ማለቱን ትተህ፥ በትሕትና የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለህ፥ ሃይማኖትንና ምግባርን አስተባብረህ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ተሰናዳ። ለባልንጀራህም አስተምር፥ ሁለቱን ከሚያስተባብርም ጋራ ተስማማ። በትዕቢትም ይሁን ለሹመት ብለው ሰዎች የፈጠሩትን አጥር ንደህ ከክርስቲያን ወንድምህ ተደባለቅ። በዚህም እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ብሎ ያዘዘውን መድኅኒትህንና ፈጣሪህን ክርስቶስን ትመስላለህ።

## ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

### ሉተራውያን፤

እምነቱን አዕማደ ምስጢርና ስባቱን ህብታት በርቱዕም ሆነ በኢርቱዕ የሚቀበሉ፥ ተቀብለውም በሥራ የሚያውሉ ሁሉ ልዩነታቸው በሹመት፥ በገንዘብ፥ በትዕቢት አንጂ በሃይማኖት እንዳይደለ በዚሁ መጽሐፍ በሌላ ቦታ ተገልጧል። ሉተራውያንም እዕማደ ምስጢርን በሙሉ ምስጢረ ሥላሴ፥ ምስጢረ ሥጋዌ ምስጢረ ጥምቀት፥ ምስጢረ ቁርባን፥ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ብለው ስለሚያምኑ ከጥንት አብያተ ክርስቲያን፤ ከካቶሊክ፥ ከግሪክ ኦርቶዶክስ፥ ከኢትዮጵያ፥ ከግብጽ በመላ ከምሥራቃውያት ጋራ ይመሳሰላሉ።

ይህም በአግስበርግ ተአምኖ (እምክንዮ) The Augsburg confession= ሦስቱን አመክዮታት፤ የሐዋርያት አመክንዮ፥ የኒቅያን የሠለስቱን ምእት አመክንዮ (ጸሎተ ሃይማኖት) የአትናትዮስን አመክንዮ በመቀበላቸው በምስጢረ ሥላሴ፥ በምስጢረ ሥጋዌ፥ በምስጢረ ጥምቀት፥ በምስጢረ ትንሣኤ፥ በቤተ ክርስቲያን አንድነት ማመናቸው ይታወቃል። ለዚህም ሦስቱን አመክንዮታት በምዕራፍ 19 ይመለከታል።

በዚሁ መጽሐፍ አመክንዮታቱ እንደመግቢያ ከተገለጡ በኋላ በዋናው መጽሐፍ የሚከተሉተ አርእስት በአናቅጽ ቁጥር ተገልጠዋል፤

አንቀጽ 1 እግዚአብሔር አብ፤
አንቀጽ 2 ጥንተ አብሶ
አንቀጽ 3 ወልደ እግዚአብሔር
አንቀጽ 4 በጸጋው ድንናል
አንቀጽ 5 ቤተ ክርስቲያን
አንቀጽ 6 ጥምቀት
አንቀጽ 7 ቁርባን
አንቀጽ 8 ኑዛዜ
አንቀጽ 9 ንስሐ
አንቀጽ 10 ክህነት (ተክህኖ)

ከዚህ የቀረው ተክሊልና (ሥርዓተ አውስቦ) ቀንዲል ነው። እነሱንም በተግባር ሲሠሩዋቸው ይታያሉ። በጸጋው ድነናልንም በማስታ ረቅና በማግለድ ምዕራፍ ያዩአል።

የሁለቱ ልዩነትና ጠብ የመጣው ከሃይማኖት ይልቅ በዚያን ጊዜ በሮም ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና በነገድና ሕዝብ ኩራት፥ በጊዜው የሮም ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ይልቅ፥ እንደዛሬው ተዋሕዶ፥ጻድቃን ስማዕታትንና

የተከበሮ ሥርዓትን ታስተምር ስለነበረ፤ ክርስቶስን ለማስተማር መንፈስ ቅዱስን ለማሳወቅ ነበረ የሚሉ ብዙዎች ናቸው። አሁን ግን ከሁለተኛው የባቲካን ጉባኤ በኋላ ቢኖር ኑሮ ሉተር ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋራ ባልተጣላም ነበር የሚሉ አሉ።

ሉተራውያን ከካቶሊክ ጋራ በምስጢረ ሥላሴ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ይሠርጻል፥ በክርስቶስ ባሕርያት፥ በጥምቀት፥ በሥጋሁ ወደሙ፥ በሚሥጢረ ትንሣኤ፥ በንስሓ፥ በበጎ ሥራ፥ በሀልዎትና በረድኤተ መላእክት ያምናሉ፥ ይህ ከሆነ ልዩነታቸው ያለው በሥርዓት አገልግሎትና በትዕቢት ብቻ ሁኖ ይቀራል።

## ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

### አመክንዮታት፤ (የሃይማኖት መግለጫዎች)

አመክባዮታት ብዙ ናቸው፤ ለዚህ መጽሐፍ አንባቢ ግን ሦስቱ ብቻ ቀርበዋል። እነሱም የሐዋርያት፥ የኒቅያ፥ የአትናቴዎስ ይባላሉ። ለአንባቢ ማስተያየት እንዲመቸው በአማርኛና በእንግሊዘኛ ከዚህ ቀጥሎ እንሆ!

1. የሐዋርያት አመክንዮ (የእምነት መግለጫ)

ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፥ ሁሉን በሚችል አባት አንድ አምላክና በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ ከድንግል ማርያም ተወለዶ በጲላጦስ ጊዜ ታሞ፥ ተሰቅሎ፥ ሙቶ በተቀበረ በጌታችን በአንድያ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ። ወደ ሲኦል ወረደ፥ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ነተሣ፥ ወደ ሰማይ ዐርጎ፥ ሁሉን በሚችል አምላክ አባት ቀኝ ተቀምጧል። ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ ይመጣል።

በመንፈስ ቅዱስ፥ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን፥ በቅዱሳን ኅብረት፥ በሥርየተ ኀጢአት፥ በሥጋ (ሰውነት) ትንሣኤና በዘለዓለም፥ ሕይወት አምናለሁ። አሜን።

ይህ በግሪክና በላቲን ያለው ነው፥ በግዕዝ ግን በመጽሐፈ ቅዳሴ የአትናቴዎስን አመክንዮ የመሰለ ተጽፎ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት ትጠቀምበታለች፤ ስለዚህ ከውጭው የቅዱስ አትናቴዎስ ጋራ በመመሳሰሉ እሱም ተጽፏል።

2. <u>ሌላው የሐዋርያት አመክንዮ፤</u>

የጌታችንና የአምላካችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሚሆን፥ ፍጥረታትን ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ እናምናለን። በባሕርዩ ምክንያት የለበትምና። አስቀድመን እንደተናገርን በዘመኑ ሁሉ ይኖራል እንጂ ጥንት ወይንም ፍጻሜ የለውምና የማይጠፋ ብርሃን አለው፤ ወደ ርሱም መቅረብ የሚቻለው የለም። ሁለተኛ አይደለም፥ ሦስተኛም አይደለምና፥ አይጨመርበትም ብቻውን ለዘለዓለም የሚኖሩ አንድ ነው እንጂ የማይታወቅ የተሰወረ አይደለም። ሁሉን የያዘና ከፍጥረት ሁሉ በላይ የሠለጠነ መሆኑን በኦሪትና በነቢያት ፈጽመን ዐወቅነው እንጂ። የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አብ አንድ ነው፤ ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ ከርሱ ጋራ የተካከለ የሚሆን አንድያ ልጅ ሠራዊትንና ሢመታትን ሥልጣናትንም ሁሉ የፈጠረ፥ በኋለኛው ዘመን ሰው ይሆን ዘንድ የወደደ፥ ያለ ወንድ ዘር ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን የነሣ፥ ያለ ኀጢአትና ያለበደል እንደ ሰው ያደገ፥ በአንደበቱም ሐሰት የለበትም፤

ከዚህ በኋላ ታሞ በሞተ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፥ ወደ ላከውም ወደ አብ ዐርጎ ኀይል ባለውም ቀኝ በተቀመጠና፥ ከአብና ከወልድ ጋራ የሚኖር፥ ዓለምን ባዳነ፥ ከአብ የሠረፀ ጰራቅሊጦስ (አማላጅ፤ ጠበቃ) በሰደደልን (በላከልን) እናምናለን።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ የሚጣልም እንደሌለ እንናገራለን። የሥጋ ሕይወት የምትሆን ነፍስ ግን ንጽሕት ቅድስት ናት።

እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን። ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮአቸዋልና። ከሥጋ ጋራ የማትሞትና የማትለበለብ ነፍስ በሥጋችን እንዳለች እናስተውል።

እኛስ የሃይማኖት ለዋጮችን ሥራቸውን እንጸይፋለን፤ መለየታቸውንም ሁሉ፤ ሕግን መለወጣቸውንም፤ እነርሱ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና። ዳግመኛም የሞቱ የጻድቃንና የኃጥአንን ትንሣኤ እንዳለ እናምናለን። ሁሉም እንደየሥራው ፍዳውን የሚቀበልበት የፍርድ ቀን እንዳለ እናምናለን።

ዳግመኛ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ የተነሣ፥ ምንም ሕጸጽ እንደ

ሌሰበት እናምናሰን በእውነት ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ፥ የአብ ሊቀ ካህናት እሱ የሰውን ዘር ከእግዚአብሔር ጋራ አስታረቀ። እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር፥ እሬትና ነቢያትን የሚፈጽማቸው እንደ መጣ እናውቃሰን።
አሕዛብ ሁሉ የርሱን መንግሥት ተስፋ የሚያደርጉት እየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ከዕሤይ ሥር የተገኘ፥ ሥልጣኑ በትከሻው ላይ የሆነ፥ ክብር ምስገናና ገናንነት፥ ቡራኬ፥ ውዳሴ፥ መመስገን ለርሱ ይገባዋል፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፥ አሜን። (መ.ቅ.ገ. 101-105)

3. <u>አመክንዮ (ጸሎተ ሃይማኖት) ዘሠለስቱ ምእት፤</u>

ይህን ግን የኒቅያው አመክንዮ የሚሉትም እሱ።
ሁሉን በያዘ ሰማይና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እምናለሁ። ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ በተወለደ የአብ አንድያ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ በተወለደ እንጂ ባልተፈጠረ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋራ እኩል በሚሆን፥ ሁሉ በርሱ በሆነ ሰሰኛ፥ ሰሰሰዎች፥ እኛን ለማዳን ከሰማያት በወረደ፥ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው በሆነ፥ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመንም ሰሰኛ በታመመ፥ በተሰቀለ፥ በሞተ፥ በተቀበረ፥ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተሰይቶ በተነሣ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ፥ በክብር ወደ ሰማይ ባረገ፥ በአባቱም ቀኝ በተቀመጠ፥ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት በሚመጣ፥ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው (በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ) እምናለሁ።

ሕይወትን በሚሰጥ ጌታ ከአብ በሠረፀ፥ ከአብና ከወልድ ጋራ በሚሰግድለትና በሚመሰገን፥ በነቢያት በተናገረ፥ በመንፈስ ቅዱስም እምናለሁ። በአንዲት ቅድስት ከሁሉ በላይ በሆነች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እምናለሁ። ኀጢአትን ለማስተሰረይ (በምትሰጥ) በአንዲት ጥምቀት እምናለሁ። በትንሣኤ ሙታንና በሚመጣው ሕይወት ተስፋ አደርጋለሁ። አሜን።

f. The Apostiles' Creed

f believe in God, the Father almighty, maker of heaven and earth: and in Jesus Christ, his only Son, our Lord: who was conceived by the Holy Spirit, born of the Virgin Mary,

suffered under Pontius Pilate, was crucified, dead, and buried: he descended into hell, the third day he rose from the dead, he ascended into heaven, and is seated on the right hand of God, the Father almighty, whence he shall come to judge the living and the dead.

I believe in the Holy Spirit, the holy Christian Church, the Communion of saints, the forgiveness of sins, the resurrection of the body and the life everlastion. Amen.

II. The Nicene Creed

I believe in one God, the Father almighty, maker of heaven and earth and of all things visible and invisible. And in one Lord Jesus Christ, the only-begotten Son of God, begotten of the Father before all ages, God of God, Light of Light, very God of very God, begotten not made: being of one substance with the Father, through whom all things were made: Who for us men and for our salvation came down from heaven, was incarnate by the Holy Spirit of the Virgin Mary, and was made man: who for us, too, was crucified under pontius pilate, suffered, and was buried: the third day he rose according to the Scriptures, ascended into heaven, and is seated on the right hand of the Father: he shall come again with glory to judge the living and the dead, and his kingdom shall have no end.

And in the Holy Spirit, the lord and giver of life, who proceeds from the Father who together with the Father and the son is worshiped and golrified: Who spoke by the prophets.

And I believe one holy, Christian, and apostolic church. I acknowledge one Baptism for the remission of sins, and I look for the resurrection of the dead and the life of the age to come: Amen.

III. The Athanasian Creed

Whoever wishes to be saved must above all else, hold the true Christian faith. Whoever does not keep it whole and undefiled will without doubt perish for eternity.

This is the true Christian faith, that we worship one God in three persons and three persons in one God without confusing the person or dividing the divine substance

For the Father is one person, the son is another, and the Holy Sprit is still another, but there is one God-head of the Father and of the Son and of the Holy Spirit, equal in glory and coequal in majesty.

What the Father is, that is the Son and that is the Holy Sprit: the Father is uncreated, the Son is uncreated, the Holy Spirit is Uncreated; the Father is eternal, the Son is unlimited, the Holy Sprit is unlimited:

the Father is eternal, the Son is eternal, the Holy Spirit is eternal; and Yet they are not three enternals but one eternal,just as there are not three who are uncreated and who are unlimited, but there is one who is uncreated and unlimited.

Likewise the Father is almighty, the son is almighty, the Holy Spirit is almighty, and Yet there are not three who are almighty but there is one who is almighty.

So the Father is God, the son is God, the Holy spirit is God and Yet they are not three Gods but one God.

So the Father is Lord, the Son is Lord, the Holy Spirit is Lord and Yet they are not three Lords but one Lord.

For just as we are compelled by Christian truth to acknowledge each person by himself to be God and Lord, so we are forbidden by the Christian religion to say that there are three Gods or three Lords.

The Father was neither made nor created nor begotten by anybody.
The Son was not made or created, but was begotten by the Father.
The Holy Spirit was not made or created or begotten, but proceeds from the Father.
Accordingly there is one Father and not three Fathers, one Son and not three sons, one Holy Spirit and not three Holy Spitits.
And among these three persons none is before or after another,
none is greater or less than another, but all three persons are coequal and coeternal, and accordingly, as has been stated above, three persons are to be worshiped in one Godhead and one God is to be worshiped in three persons.

Whoever wishes to be saved must think thus about the Trinity.

It is also necessary for eternal salavation that one faithfully believe that our Lord Jesus Christ, Became man for this is the right faith, that we believe and confess that our Lord Jesus Christ, the Son of God, is at once God and man:
he is God, begotten before the ages of the substance of the Father, and he is man, born in the world of the substance of his mother, perfect God and perfect man, with reasonable soul and human flesh, equal to the Father with respect to his Godhead and inferior to the Father with respect to his manhood.

Although he is God and man, he is not two Christs but one Christ:

One, that is to say, not by changing the Godhead into flesh but by taking on the humanity into God.

One, indeed, not by confusion of substance but by unity in one person.

For Just as the reasonable soul and the flesh are one man, so God and man are one Christ,

Who suffered for our salvation, descended into hell, rose form the dead,

ascended into heaven, is seated on the right hand of the Father, whence he shall come to judge the living and the dead.

At his coming all men shall rise with their bodies and give an account of their own deeds.

Those who have done good will enter eternal life, and those who have done evil will go into everlasting fire.

This is the true Christian faith. Unless a man believe this firmly and faithfully, he canot be saved.

**እነዚህን እመክንዮታት የሚቀበል ሁሉ ክርስቲያን ነው፤ ስለሆነ፤ የቀረው ችግር ሁሉ በክብ ጠረጴዛ በውይይት፥ መሪዎች ሰላም፥ ከፈለጉ፥ ሊፈታ ይችላል።**

## ምዕራፍ ሦያ

### ክርስትናን ያስፋፉ ታላላቅ አበው፤

ክርስትና በአብዛኛዉ ዓለም የተስፋፋው ከጳራቅሊጦስ እስከ አራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ 451 ዓ.ም. ነው። በዚህ ዘመን ከሐዋርያት ስጥቀው ብዙ ንጹሓን፥ ተጉሣን፥ ኅያላን ሰባክያን፥ ደራስያን፥ ጸሓፍያን ሊቃውንት ተነሥተዋል። የክርስትና ሃይማኖት ከዚህ የደረሰው በመንፈስ ቅዱስ ርዳታና በእንደዚህ ባሉት ሰዎች ትጋት ነው።

ጌታ እንዳረገ፥ ሐዋርያትን ባይልክ፥ ቅዱስ ጳውሎስን ባያስነሣ፥ ሰባክያንንና ሊቃውንትን በእየጊዜው ባይቀሰቅስ፥ ይህን ጊዜ፤ ክርስቶስ አይሁድ የሰቀሉት ሌባ ነው ተብሎ ይረሳ ነበር። ስለዚህ ሁሉንም ባይሆን ጥቂቶቹን ዋና ዋናዎቹን በእየጊዜው እየተነሡ፥ አሕዛብን በስብከት፥ መናፍቃንን በትምህርት እየመለሱ እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ክርስትናን ያደረሱትን ከዚህ ቀጥለን በዘመን ተራ እናቀርባለን።

ፓፒያስ (60-130) የፍሪጂያ ከተማ የኤራጳሊስ ጳጳስ፥ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር፥ የፖሊክርፕ (ብዙ ፍሬ) ጓደኛ ነበር። ከ110-130 የኤራጳሊስ ከተማ ጳጳስ ሁኖ ኑሯል። በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ብዙ በተአምራት የተሞሉ መጻሕፍት ጽፏል፤ ትውፊትን አስፋፍቷል፤ ለእሱ ትውፊትና ቅዱሳት መጻሕፍት እኩል ነበሩ። የጌታችንን ስብከት በአምስት ቅጽ መጽሐፍ ጽፏል።

ኢግናትዮስ (ኢግናጢዮስ)

ኢግናጢዮስ የእንጾኪያ ጳጳስ በትምህርቱ ኀይለኛና ብርቱ ስለነበረ ከአንጾኪያ እስከሮም ስወታደር ታጅቦ በእግሩ ሂዶ በ84 ዓመቱ ለአራዊት ተጥሎ በሰማዕትነት ሙቷል። በመንገዱ ሲሄድ የአስሚርና ጳጳስ ፖሊክርፕና የአካባቢው ክርስቲያን በክብር ተቀብሎታል። እሱም በዘመኑና በአካባቢው በነበሩት መናፍቃን ላይ ስድስት ክታባት (መልእክታት) ጽፏል፥ ከሌሎች ታላላቅ መጻሕፍቱ ይልቅ ኢግናጢዮስ የሚታወቀው በእነዚህ ነው። እነሱም ክርስቶስ መስሎ ተወለደ እንጂ እግናዊ አይደለም በሚሉ በዶኪስቴና በአይሁዳዊነት ላይ የተጻፉ ናቸው። ኢግናጢዮስ የተወለደበትና የሞተበት ቀን አልታወቀም፤ የሆነ ሁኖ በጌታ ዘመን ተወልዶ በ84 ዓመቱ ከ107 ዓ.ም. በፊት ሙቷል። ስለ አግናጥዮስ (ኢግናጢዮስ) ብዙ አፈ ታሪክ ይነገራል፤ አንዳንዶች ኢግናጥዮስን ከላቲን ቃል ኢግኒት ከሚለው ጋራ ያያይዙና በትምህርት ሊቅ ስለሆነ እሳቱ ይሉታል። ሌሎች ደግሞ ኢግናጢዮስ ቴዎፎሮስ ስለሆነ ስሙ እምላክን የተሸከመ ወይም አምላክ የተሸከመው ብለው ይፈቱና ጌታ

ለሐዋርያት ትሕትና ለማስተማር ከፊታቸው አቁሞ የተጠቀመበት ሕፃን እሱ ነው። ወይም ሕፃናትን ተዋቸው ወደ እኔ ይምጡ ብሎ ሐዋርያትን ባዘዛቸው ጊዜ መጀመሪያ የባረከውና የዳሰሰው ሕፃን አግናጢዮስ ነው ብለው አመቻችተው ይተረጉሙሉ። ያም ሆነ ይህ ፍቁረ እግዚአብሔር ሁና ክርስቶስን ለብሶ፥ ስለ ክርስቶስ ለአራዊት ተጥሎ ሙቷል። ኢግናጢዮስ የመጀመሪያው ትልቁ የክርስትና ተዋግኢ ነው።

<u>የሮሙ ቀሌሚንጦስ</u>፤ ከ90-100 የሮም ጳጳስ የነበረ ቀለሚንጦስ ነው። ብዙዎች ከቅዱስ ጴጥሮስ ቀጥሎ የነበረው ጳጳስ ነው ሊሉ ሌሎች ደግሞ ቅዱስ ጴጥሮስ የሞተ በአሞሳው ውስጥ በኔሮን ዘመን ስለሆነ ከጴጥሮስና ከቀሌሞንጦስ መካከል ሌላ ሁለት ጳጳሳት አሉ። እሱ ግን የጴጥሮስም የጳውሎስም ተማሪ ሊሆን ይችላል ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ከዚህ ግን ቀሌምንጦስ የሚፈለገው ስለ ሕይወት ታሪኩ ባይሆን ስለሥራው ነውና ተግባሩን እንመልከት። በትውፊት ሐዋርያት ትምህርታቸውን ያወረሱ ለቀሌሞንጦስ ነው ይባላል። እሱም አብያተ ክርስቲያንን የሚያቃርቡና የሚያጠነክሩ ብዙ ክታባት ጽፏል፤

በ96 ዓ.ም. የቆሮንቶስ ካህናትና ምእመናን በተጣሉ ጊዜ በሮም ቤተ ክርስቲያን ስም የሽማግሌ ክታብ ለማስታረቅ ጽፏል። በዚህም መዓርጋተ ክህነትን ገልጦ፥ ምእመናንም ለካህናት እንዲታዘዙ ገልጧል፥ አዝዟል። ካህናትን የሾመ ጌታ ስለሆነ የቆሮንቶስ ምእመናን ያወረዷቸውን ጳጳሳትና ቀሳውስት እንዲመልሱና በዚህም ንስሓ እንዲገቡ አዝዝዋል።

በቅስናም በጵጵስናም ተግቶ ሲያስተምር ኑሮ በዘመነ ደግትያኖስ በሰማዕትነት ሙቷል።

በመንፈሳዊ ሕይወቱም ትጉህ፥ ጽሙድ፥ መስተጋድል ነበረ።

<u>ፖሊካርፕ</u> (ብዙ ፍሬ፥ፍሬው)

ፖሊካርፕ (70-155) የእዝሚርኒ ጳጳስና ሰማዕት፥ ስለእሱ የሚናገሩት ምንጮች ሁሉ፥ ታማኝ ካህን የሐዋርያዊት ትውፊት ጠበቃ፥ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ዐምድ ይሉታል። ፖሊካርፕ የወንጌላዊው ዮሐንስ ተማሪ ነበር፤ ያጳጳሰውም እሱ ነው። ብዙ መጻሕፍትን ጽፏል፤ የሚታወቀው ግን በገድለ ሰማዕታቱ ነው።

<u>አቲናጎራስ</u>፤

አቲናጎራስ በሁለተኛው መቶ ዘመን የነበረ የክርስቲያን ተዋግኢ

(ተከራካሪ፥ ጠበቃ Apologist) ነው። ክርክሩም በአፍላጦን ፍልስፍና ተመሥርቶ ለንጉሡ ነገሥቱ ለማርቆስ አውሬሊዮስ የቀረበ ነው። የሚያሳየውም በክርስቲያን ላይ የሚነዛው የስም ማጥፋት ዘመቻ ሐሰት መሆኑን ነው። እሱም እግዜር አለ አያሉም፥ የሰው ሥጋ ይበላሉ፥ በቤተ ዘመድ መካከል ያመነዝራሉ ነው። የዚህን ሐሰትነት ካስረዳ በኋላ ስላማዊነታቸውን ገልጦ የዜግነት መብት ለክርስቲያን ሁሉ ይጠይቃል። የሰውነትን ትንሣኤ የሚያስረዳም ጽፏል።

<u>የጎሉ ኢሬኔዎስ፤</u> (Irenaeus of Gaul)

ኢሬኔውስ ከ175-195 የሊዮንስ ጳጳስ የነበረ፤ የእዝሚርኒ ተወላጅ የፖሊካርፕ ተማሪ ነው። ለጥቂት ቀንም ሮም አስተምሯል ይባላል። በግኖስቲክ ላይ መጽሐፍ ጽፏል። የሐዋርያት ትምህርትም ልክ መሆኑን በሰፊው አስረድቷል።

<u>ዮስጢኖስ ሰማዕት</u> (Justin, martyr)

የመጀመሪያው ተዋሕዶ ሰማዕት 100-165 በጥንት በሰማርያ፥ ሴኬም በኋላ ኔያፖሊስ (ናብሉስ) በምትባለው ከአሕዛብ ቤተ ሰብእ ተወለደ። ትምህርትን የማይጠግብ፥ እውነትን ፈላጊ ነበርና ከአሕዛብ ፍልስፍና እስቶይክን፥ አፍላጦንን፥ አርስጣጣሊስን፥ ፒታጎራስን አጠና። እነዚህ ሁሉ ለአእምሮው ርካታን ስላልሰጡት አሁንም እውነትን ሲፈልግ በ130 ዓ.ም. ክርስትናን አገኘና ተጠመቀ። ከ130-135 ኤፌሶን አስተማረ፤ በዚህ ጊዜ ከአይሁዳዊው ትሪፎ ጋራ ተጋጨና የመጀመሪያውን ተዋሥኦ ወይም ተቃሕዎ በትሪፎ ላይ ጻፈ። ከዚያን በኋላ ሮም ሂዶ የክርስትና ትምህርት ቤት መሥርቶ ብዙ መናፍቃንና አሕዛብን የሚያሳፍሩ የተዋሥኦ መጻሕፍት ጻፈ። ዮስጢኖስ የመጀመሪያው ፈላስፋ የክርስቲያን ተዋሕዶ መሆኑ ነው። በመጨረሻው ተገርፎ፥ ተደብድቦ፥ ተከልሎ ሰማዕት ሁኗል። አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ቅዱስ ይሉታል።

<u>ቴርቱሊያኖስ</u> (Tertullian)

ቴርቱሊያኖስ (160-220) የሰሜን አፍሪካ የካርታጅ ተወላጅ፥ ወላጆቹ ከአሕዛብ ነው ናቸው። በአሕዛብ ሥልጣኔ አድጓል፥ ሕግ ተምሯል፥ ለተወሰነ ጊዜም በሮም በጥብቅና ሠርቷል። ሕግ ማጥናቱም በኋላ የመንፈሳውያን ቃላት ውሳኔ ለመቅረጽ ረድቶታል። በላቲን መንፈሳዊ መጽሐፍ ለመጻፍ የመጀመሪያው ቴርቱልያኖስ ነበር። ከእሱ በፊት ክርስቲያን መንፈሳዊ ነገር ሁሉ የሚጻፈውና የሚነገረው በሮም

መንግሥት ሁሉ በግሪክ ነበር። በ195 ክርስትናን ተቀብሎ ወደ ትውልድ ሀገሩ ተመልሶ፤ ቀሶ የንኡስ ክርስቲያን አስተማሪ ሁኗል። በዚህ ጊዜ በ207 አካባቢ የሞንታናውያን ትሩፋት ይስበውና ወደ እነሱ ክፍል ይገባል፤ ገብቶም የራሱን ትምህርት ቤት ይከፍታል፤ ሞንታናዊነትም እስከ 4ኛው መቶ ዘመን እየተንገዳገደ የቆየ ቤተ ክርስቲያን ያልተቀበላቸው ኑፋቄ ነው።

ሞንታናዊነት በንስሓ ለሚመለሱ ሰዎች መቀጮው ከረበናት የመጣ፥ የክርስቶስ መንፈስ የሌለው፥ እንደ መጽሐፈ ቄድር ያለ ጨካኝ ቅጣት ያዝዛል፤ የብትውና ተጋድሎው ስውነትን በረሃብ በጾም፥ በጸሎት፥ በስጊድ በሕርመት እስከ ማደንዘዝ ነው። ሁለተኛ ጋብቻ ከሞተም በኋላ ይከለክላል። ውትድርና ከክርስትና አይስማማም ብሎ ይከለክላል፤ በዚህም የጀሆባ ምስክሮች አባት መሆኑ ነው። ወደ ማመንዘር ስለሚስብ ቴያትር ቤት መግባትንና ማኅበራዊ ጭዋታን፥ ዘፈንን፥ ዳንስን፥ ዓለማዊ ሙዚቃን ይከለክላል።

ሞንታኒዝም በዚህ ሂደቱ ክርስቲያንን ከኅብረተ ሰብ የሚለይ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ባለመቀበሏ ቴርቲልያኖስም የቤተ ክርስቲያን ሊቅ እንጂ አባት ሳይባል ቀረ። ጠበቃ እንደ መሆኑ መጠን የሕግን ቃላት ውሳኔ በማወቁ ሌሎች ተዋሣእያን ያላወጡትን ወይም ያልደረሱበትን ፍርፕርፕ አድርጎ ጽፏል። በተዋሥእውም የክርስትናን ጠላት አሳፍሯል፤ ክርስቲያንን አኩርቷል፤ አስተምሯል። በክርስቲያን ላይ ትወራ ለነበረው የስም ማጥፊያ ሁሉ አሳምሮ መልሷል። ለግኖስቲካውያን በቂ መልስ ሰጥቷል። ምስጢረ ሥላሴን ከእሱ በፊት ከነበሩት በተሻለ አብራርቶ ጽፏል። ሥላሴ የሚለውን ቃል (Trinitas) በላቲን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረጸው እሱ ነው። በዚህም ላቲን ለግሪክ ቃል ተርጓል። ቴርሪሊያኖስ ይጽፍ የነበረው በላቲንና በግሪክ ነው። በላቲን የጻፋቸው እስካሁን ብዙዎች አሉ። ከቅዱሳት መጻሕፍት ይልቅ የሚያደላው ለትውፊት ነው። ከጸጋ እግዚአብሔር ይልቅ በትሩፋት ይመካል።

<u>የእስክንድርያው ቀሌሜንጦስ፤</u> (Clement)

ቀሌምንጦስ (155-220) ምናልባት ከአቴና ተወልዶ የአሕዛብን (የግሪክን) ፍልስፍና ተምሮ በኋላ ወደ እስክንድርያ ሂዶ ትምህርተ መለኮትን ከጳንጤኑስ ተምሮ፥ መምህሩ በ190 ሲሞት ወርሶ፥ እስከ 202 መራ አስተማረ፤ በ202 በሴፕቲሚዮስ ሴቩሩስ ምክንያት ወደ ቂሳርያ

ሲሰደድ መንበሩን አርጌኒስ ወርሶታል። ከ18 ዓመት በኋላ በስደት በ220 ዓ.ም. ሙቷል።

ቀሌሜንጦስ እንደ ቴርቱሊያኖስ የአሕዛብ ፍልስፍና፥ ትምህርት፥ ማኅበራዊ ኑሮ አያስፈልግም አይልም ነበር። እንዲያውም የአሕዛብ ፍልስፍናና ትምህርት ብዙ የእውነት ቅንጣት ስላለው ቤተ ክርስቲያን ችላ ልትለው አይገባም ይል ነበር። ከዚህም ጋራ የመጨረሻው ዕውቀት ግን የሚገኘው ራሱን በቅዱሳት መጻሕፍት በገለጠው በእግዚአብሔር ነው ይላል፤ ብሎም ብዙ መጻሕፍት ጽፎ አስረድቷል። ቀሌሜንጦስ ከሚገኘው ምንጭ ሁሉ ከጥበብና ከዕውቀት መዝገብ ማስተዋልን ስለክርስቶስ መሰብሰብ አለብን እያለ ያገኘውን ሁሉ ያነብ ይመረምር ነበር።

<u>ኪፕርያኖስ፤ የካርታጁ፤</u> (Cyprian)

የካርታጁ ኪብርያኖስ (200-258) በካርታጁ ከሠለጠነ ባህላዊ ሀብታም ቤተ ሰብእ ተወልዶ፥ በ245 ክርስትናን ተቀበለ። ከመጠመቁ በፊት የተማረው ጥብቅናና የአሕዛብን ፍልስፍና ነበረ። እንደ ተጠመቀም የወንጌልን ቃል ለመፈጸም ንብረቱን በሞላ ሸጦ ለነዳያን መጸወተ። ወዲያውም በማስተማሩና በትሩፋቱ፥ በብሕትውና፥ በድኅነቱ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማወቁ ታወቀ፥ ተወደደ። በለዚህ በተጠመቀ በሁለተኛ ዓመቱ ቀሰሰ። በሦስተኛ ዓመቱ ከእሱ በፊት የነበረው ጳጳስ ሲሞት ሕዝቡ ተሰብስቦ በአንድ ቃል ለጵጵስና መረጠውና በ248 የካርታጅ ጳጳስ ሆነ። በሊቅነቱና ፈጥኖ በመሾሙ ከእሱ በፊት የነበሩ አረጋውያን ቀንተው ብዙ ተንኮል ሸረቡበት። በዳክዮስ (250-51) ስደት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አበው ተመክሮ በስደት ተሸሽጎ ሕዝቡን በመልእክት እየመራ አሳለፈ፥ ዳክዮስ ሲሞት ወደ መንበሩ ተመለሰ። በስደቱ ጊዜ ብዙዎች ለጣዖት ሠውተዋል፤ የቀሩት ደግሞ ለሹማምቱ ጉቦ እየሰጡ ሠውተዋል፥ የንጉሠ ነገሥቱን አማልክት ተቀብለዋል፥ ለንጉሥም መሥዋዕት አቅርበዋል የሚል መረጃ ተቀብለው ነበር።

የሠውትንና ሳይሠው በጉቦ መረጃ ያገኙትን እንዴት እንቀበላቸው የሚል ጉባኤ በ251 ኪብርያኖስ ጠራ። ለምን ቶሎ ቅስና አልተሰጠኝም የሚል ፌሊቺሲሙስ የሚባል ዲያቆንና ከኪፕርያኖስ በፊት ለምን እኔ አልተሾምሁም የሚል ቀናተኛ ኖባቱስ የሚባል ቄስ ተነሡበት። ኖባቱስ ብዙ አክራሪዎችን ይዞ፥ ከካርታጅና ከሮም አስተባብሮ የሮም ጳጳስ እሁናስሁ ሲል አውሬሊዮስ ስለተመረጠ ከቤተ ክርስቲያን ተለየ። ውስጡ

ሹመት ይሁን እንጂ አፍአዊ ሙግት ግን በጉቦ ሳይሠው ያመሰጡት በጥቂት ቀን ንስሓ ይመስሉ፥ የሠውት ግን ረጅም የንስሓ ጊዜ ይሰጣቸው ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ከደው የተመለሱትና ከተሰዩ የተጠመቁት እንደገና ይጠመቁ ወይስ በአንብሮ እጅ እንቀበላቸው ነበር። በዚህም ከሮሙ ጳጳስ ከእስጢፋኖስ ጋራ ተጋጨ። የአፍሪካና የእስያ ትውፊት ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውጭ በ255-56 በተደረጉት ጉባኤዎች ምስጢራትን አንቀበልም አሉ። ይህ ጭቅጭቅ ሳይወሰን የጋለርዮስ ስደት ተነሣና ኪፕርያኖስና እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ስለሞቱ ሳይወሰን ቀረ።

የኪፕርያኖስ ክታባት የሚያስዩት ጥሩ ካህንና ዐዋቂ አስተዳዳሪ መሆኑን እንጂ በጣም የተማረ ነባቢ መለኮትነቱን አይደለም።

የኪፕርያኖስ ጽሑፎች የተሠማሩት፥

ሀ/ ድንግልና፥

ለ/ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ከጳጳስ በታች፥

ሐ/ ጸጋ እግዚአብሔርን ለማግኘት ምጽዋትና አምልኮ ጣዖትን ያወግዛል። ቤተ ክርስቲያንን እንደ እናቱ አድግጎ ያልያዘ እግዚአብሔርን እንዳባቱ ሊያገኘው አይችልም ይል ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ድኅነት የለም ለሚለው አባባልም ደራሲው እሱ ነው። የጳጳሳቱን እኩልነት ይደግፍና የሮምን ጳጳስ አለቅነት ፍለጋ ይቃወም ነበር። ጥምቀት ከክርስትና (ከጥምቀት) በፊት የነበረን ኀጢአት ያነጻል፤ ከጥምቀት በኋላ የተሠሩ ኀጢአቶች ግን በመላ ምግባር ይልቁንም በምጽዋት መፋቅ አለባቸው ይል ነበር። ስለ ሥጋሁ ወደሙ ያለው አስተያየቱ በመላ ቤተ ክርስቲያን ይልቁንም በምዕራብ ታላቅ ተጽዕኖ አድርጓል። የቁርባንን መሥዋዕታዊ ጠበዕይ ተቀበለ፤ አስተማረ። ካህን የክርስቶስ ተከታይ፥ ወራሽ፥ እንደራሴ ነው፤ በእሱ አምሳልም መሥዋዕት ስለ ኀጢአት በጉባኤው መካከል ያቀርባል።

የጌታ ሥጋና ደም አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔርና ደም መሆኑንና በመንበር ላይ በእየዕለቱ የሚሠዋ መሆኑን በደምብ ያስረዳ ኪፕርያኖስ ነው። ከዚያ በፊት ብዙ ክርስቲያኖች መንበር ይሉ መሥዋዕት የለንም እያሉ በአሕዛብ ፊት ይፎክሩ ነበር።

የኪፕርያኖስ ጽሑፍና ሥራ ከሱ በፊት በትውፊት ስም የተሰበሰበውን የመጽሐፈ ባልቴት ተረት በታትኖታል።

<u>ኦሪጌኒስ፤</u> (Origen)

ኦርጌኒስ (185-254) በእስክንድርያ ከአንድ ሰማዕት ተወልዶ በ18 ዓመቱ ለእስክንድርያው ንኡስ ክርስቲያን ትምህርት ቤት መምህር ሁኖ ተሹሟል። ተሹሞም በዓለም የታወቀች አድርጓታል። ኦርጌኒስን የመሰለ በሊቅነት፥ በደራሲነት በጥበዐት በእስክድርያ አልነበረም፥ አልተተካም ይባላል። ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር ካለው ፍቅር የተነሣ ወንዶች በምሽቶቻቸው ጠርጥረው ወደ ትምህርቱ ለመሄድ እንዳይከላከሉበት በገዛ እጁ ሕጽው ሁኗል። በዚህም ጳጳሱ ዲሜጥሮስ መጀመሪያ እንደሰማ መልካም አድረግህ ብሎ ካደነቀ በኋላ፥ በትምህርቱ ብዙ ተከታይና እድናቂ ስላገኘ፥ ቀንቶ አላቀስምህም ብሎታል። ቅስናውን ግን እየሩሳሌም ጳጳስ ሰጥቶታል። እንደ ጀሮም አባባል ማንም ሰው በሕይወቱ ሙሉ አንብቦ የማይዘልቀው መጽሐፍ ጽፏል። አናቅጹንና ደብዳቤውን ጭምር ቆጥሮ ከ6000-8000 መጻሕፍት ጽፏል ይላሉ ልዩ ልዩ ምንጮች። ይሁን እንጂ ብዙዎች ከ6000 በላይ እንደ ጻፈ ተስማምተዋል። ጽሑፍና ስብከቱ እንደመብዛቱ ምቀኛውም በርክቶበታል።

ይህም እሁን በሀገራችን እንደሚታየው ማለት ነው። አንድ ጥሩ ሰባኪ ተነሣ ተብሎ ሰው ወደዚያ የሄደ እንደሆነ በሁለተኛው ይከሰሳል፤ በዚያም በዚያም በሐሰት ስም አጥፊ ይነሣና ቢሆን ይታሰራል፥ ይገደላል፤ ብልጥ የሆነ እንደሆነ ይሰደዳል። ይህም በቀድሞ ዘመን እንደ ኦርጌኒስ ባሉ ሊቃውት ሲደርስ የኖረ የነበረ፤ የሰው ልጅ ጠማማነት ባለበት ዘመን ሁሉ እየተፈጸመ የሚኖር ነው። ስሙን ሲያጠሩ ከሚኖሩት ታላላቅ ሥራዎች፤

1. ኤክላፕላ= ስድስት ዕጥፍ የቅዱሳት መጻሕፍት የንጽጽር ጽሑፉ
2. በረገድ (በሴማ) የተዘጋጀ ትምህርተ መሰኮቱ።
3. ወደር የለሽ ለሴልሰስ መልስ የተሰጠ ተዋሥኦው፥ ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ መጻፋቸውን እያመነ፥ በእስክንድርያ ምሳሌያዊ (ተምሳሌት) አተረጓጎም ወደቀና እግዚአብሔር በእየዘመኑ በአስተርእዮ ይለያያል እንጂ በገጽ አንድ ነው አለና በኋላው ለተነሡ ለብዙ መናፍቃን መሪ ሆነ። እነሱም ቴዎዶቱስ፥ አርቴምን፥ ጳውሎስ ሳምሳጢ፥ ጵራክስያስ፥ በረለስ፥ ሰባልዮስ ናቸው። (ሁሉንም በመናፋቃን ምዕራፍ ያይዋል)

የእስክንድርያው ፓትርያርክ ዲሜጥሮስ በሥራውና በሊቅነቱ ቀናበትና 20 ዓመት ካስተማረበት ትምህርት ቤት ምኑንም ምኑንም ለቃቅም ገዝቶ አባረረው። እሱም ቂሳርያ ሂዶ ሌላ ትምህርት ቤት መሥርቶ እንደ ገና 20

ዓመት እስተምሮ በዓለም ላይ ሁሉ ተጽዕኖ አሳድሮ በዳክዮስ ስደት ጊዜ በጢሮስ እስር ቤት ተወርውሮ ተሠቃዮ፥ ተሰብሮ፥ ከብዙ ስቃይ በኋላ በ254 ዓ.ም. በሰማዕትነት ዐረፈ።

<u>የእስክንድርያው ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ፤</u>

ቅዱስ እለእስክንድሮስ (በ328 ዐረፈ) ከ313-328 የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ነበረ። በዘመኑ አርዮስ ተነሥቶ ወልድ ፍጡር ነው እያለ ቢያውከው ሁለት ጊዜ በሀገረ ስብከቱ ጉባኤ አድርጎ ረቶ ገዘተው። አርዮስ ግን ከስሕተቱ አልመለሰም ስላለ በመጀመሪያው የዓለም ጉባኤ በኒቅያ በ325 ዓ.ም. 318 ኤጲስቆጶሳት ባሉበት የጉባኤው ስብሳቢ በመሆን ገዝቶታል። እምነቱም አብ ከመውለድ ወልድ ከመወለድ በቀር አብና ወልድ እኩል ናቸው ነበር። አርዮስን ከመገዘት በኋላ መንበሩን የወረሰው ያን ጊዜ ሊቀ ዲያቆኑ አትናቴዎስ ነበር። እለእስክንድሮስ ብዙ መልእክታት ጽፏል።

<u>ትልቁ አትናቴዎስ</u> (296-373)

አታናቴዎስ የግብጽ ተወላጅ፥ ትምህርቱ ግሪክ ክላሲክ የሀብታም ልጅ ነው። የሃይማኖቱን ትምህርት የተማረው ጳኔዎስ በመሠረታት እራጌኒስ ባስፋፋት የእስክንድርያ ንኡስ ክርስቲያን ትምህርት ቤት ነው። ከዚያ ተምሮ በ312-318 ለ6 ዓመት በአንባቢነት አገልግሏል። ከ318-328 የእለእስክንድሮስ ሊቀ ዲያቆን ሁኖ ለ10 ዓመት አገልግሏል። በእየጊዜው እለእስክንድሮስ አርዮስን ሲያወግዝ ሲከተል ኑሮ ከእሱ በኋላ ዋናው ተከራካሪ አትናቴዎስ ነበር። በ325 ሦስቱ መቶ (ሠለስቱ ምእት) አርዮስን ለማውገዝ ሲሰበሰቡ የአትናቴዎስ ቁጥር ከእነሱ ውስጥ አልነበረም፤ ክርክሩን ግን እያስናዳ ለእለእስክንድሮስ የሚሰጠው እሱ ነበር።

እለእስክንድሮስ በ328 ሲሞት በደመቀ እልልታ ይደለዎ ተብሎ ተሾመ፤ በጵጵስናም 45 ዓመት ቆየ። ይሁን እንጂ በዘመነ ጵጵስናው እንደሱ ደጋግሞ ስደት የደረሰበት የለም። በገዥዎችና በነገሥታቱ ዘንድ ተንኮል እየሸረቡ፥ የአርዮሳውያን ጳጳሳት አምስት ጊዜ ከመንበሩ እያወረዱ አሰደዱት።

1. በ336 በቆስጠንጢኖስ ወደ ትሪየር ተሰዶ ለአንድ ዓመት ቆይቶ በ337 ቁስጠንጢኖስ ሲሞት ተመለሰ።

2. በ339 ደግሞ በቆንስጣቴዎስ ትእዛዝ ወደ ሮም ተሰዶ እስከ 346 ቆየና በቆንስጣስ ተጽዕኖ ተመለሰ። ሮም በነበረበት ጊዜ እስከ ዕለተ

ዕረፍቱ የቆየ ጥሩ ግንኙነት አዘጋጅቶ ተመለሰ።

3. ከ10 ዓመት በኋላ የምዕራቡ ንጉሠ ነገሥት የቆንስጣስ ተጽዕኖ በቆንጣቴዎስ ላይ ያለው ሲዳከም፥ አሁንም ከመንበሩ አውርዶ፥ የአሱን ወዳጅ አርዮሳዊ ሹሞ አሰደደው። በዚህ ጊዜ በዚያው በአስክንድርያ ውስጥ እየተዘዋወረ ሕዝቡን በመልእክት ያስተዳድር ነበር፤ ቀጣዩ ንጉሠ ነገሥት ዮልያኖስ በ361 ዓ.ም. እስኪነግሥ ድረስ።

4. ዮልያኖስ ደግሞ በዓመቱ በ362 አሰደደው። ግን ያሰደደው ዮልያኖስ በ363 ሞተና አሁንም በድል አድራጊነት ሕዝቡ ይወደው ስለነበረ ወደ መንበሩ ተመለሰ።

5. 365-6 አጭር ስደት በኋላ ተመልሶ ለቀረው ሕይወቱ እስከ 373 ዓ.ም. ሕዝቡን ሲረዳ መንጋውን ሲመራ ኑሮ በአስክንድርያ ዐርፎ ተቀብሯል። አጻጻፉ መጠነኛ፥ እንጎሱ በጣም ብልኅ ነበር። ብዙ መጻሕፍት ሃይማኖቱን የሚገልጡ፥ ቤተ ክርስቲያኑን የሚደግፉ፥ መናፍቃንን የሚያሳፍሩ ጽፏል።

ከ318 ዓ.ም. በፊት ገና በ20 ዓመቱ ውስጥ ሳለ፥ በእንተ ተሰብእ በሚል (ሚስጢረ ሥጋዌ) ርእስ የቃለ እግዚአብሔርን ሰው ሁኖ ለወደቀው ሰው አርአያ እግዚአብሔርነቱን መመለሱንና ማዳኑን ገልጦ አብራርቶ ጽፏል። እንደ ጳጳስነቱ ትልቁ የአርዮስ ተቀናቃኝና ጠላት ነበር። ከ339-359 የኒቅያን ሃይማኖት የሚገልጡ ተከታታይ መጻሕፍት ጻፈ። <u>የሚያብራሩትም እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ አባቱ ጋራ በመለኮት ባሕርይ አንድ ነው፤ የሰም አንድ ባሕርይ ሳይሆን ከተመሳሳይ ባሕርይ ነው የሚሉትን ሐረጎች ነበረ።</u> በመለኮቱ ከአብ ጋራ እኩል ነው፤ ከአንድ ከዚያው ባሕርይ ነው፥ እውነተኛ አምላክ ከእውነተኛ አምላክ ነው የሚለው ትምህርቱ በቁስጥንጥንያ በተደረገው የዓለም ጉባኤ 381 አጽድቆስታል።

ይህም በቀጸዶታውያን አበው ሥር። በምንኩስናም በኩል በበረሐ ቅዱስ እንጦንስን ተከትሎ ለጥቂት ቀን ስለቆየ ብዙ ሥርዓተ መነኮሳትን ሠርቷል። ወደ ምዕራብ ቤተ ክርስቲያንም ወደ ሮም ተሰዶ በነበረበት ጊዜ ምንኩስናን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስገባው እሱ ነው። አትናቴዎስ እርቶዶክስ ሃይማኖቱን አጥርቶ የሚያውቅ፥ ጥቡዕ ካህን፥ በመከራ ታጋሽ፥ ነገሥታትንና ጠላቶቹን የማይራራ፥ ጠንካራ መምህር ነበር።

<u>ቅዱስ ባስልዮስ</u> (329-379)

<u>ሦስቱ ዝነኛ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቀጰዶቃውያን፥</u> ቅዱስ ትልቁ ባስልዮስ፥ ወንድሙ የኒሲሱ (ኒሳ) ጎሪጎርዮስ፥ ወዳጃቸው ጎርጎርዮስ ዘናዝያዚስ የአርዮስን፥ የመቅዶንዮስን የአፖሊናሪዎስን ኑፋቄያት ለማጥፋት የታገሉ ምሁራን፥ ጥቡዓን፥ ርቱዓነ ሃይማኖት በዓለም አብያተ ክርስቲያን በቅዱስነታቸው የታወቁ፥ ቅዱሳን አባቶች ናቸው።

ቅዱስ ባስልዮስና ወንድሙ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ አላቸው፤ ከ14 ቅዳሴያት ሁለቱ የእነሱ ናቸው፤ እነሱም ህልው እግዘእ እግዚአብሔርና ነእኩቶ ስገባሪ ሠናያት ይባላሉ። ስለዚህ ሁሉንም በተራ፥ መጀመሪያ ባስልዮስን ከዚያ ወንድሙን በመጨረሻ ወዳጁን አድርገን እናቀርባለን። ቅዱስ ባስልዮስ በቀጳዶቅያ ውስጥ ባለችው ቂሳርያ በ330 ከፍጹም ደጋግ ሀብታም ቤተ ሰብእ ተወለደ። በማንኛቸውም የታደለ ቤተ ሰብእ እንደ እነሱው ያለ ለማግኘት አይቻልም ባይባልም በቀላሉ አይገኝም። አባቱ ተናጋሪና (Orator) ጠበቃ ነበረ፤ እናቱ ደግሞ በትሩፋቷ የታወቀች ዝነኛ ነበረች። የእናቱ አባት አያቱ ሰማዕት ነው። የአባቱ እናት አያቱ ማክሪና ደግሞ የጸንጦሱ ገባሬ መንክራት ወተአምራት ጎርጎርዮስ ደቀ መዝሙር ነበረች።

አራት ወንድማማች አንድ እኅት ነበሩ፤ እነሱም ባስልዮስ፥ ጎርጎርዮስ፥ ጴጥሮስ፥ ማካርዮን፥ መካሪና ይባላሉ። ባስልዮስ፥ ጎርጎርዮስ፥ ጴጥሮስ ጳጳስው ቤተ ክርስቲያንን በጥሩ አመራር ሲያገለግሉ፥ ሕዝቡን ሲያስተምሩ፤ መናፋቃንን ሲያስፍሩ ኑረዋል። ማካርዮን ደግሞ በድንግልና ቀስ፥ በትሩፋት ተጠምዶ ሲያገለግል ኑሯል። እኅታቸው መካሪናም በእኔስ ውስጥ ስፊ ገዳም ሠርታ ለዚያ ንብረቷን ሁሉ አውርሳ፥ በድንግልና በተጋድሎ ተጠምዳ ምድራዊ ሕይወቷን በቅድስና አሳልፋለች። አባታቸውም ኤስድሮስ ይባላል።

ባስልዮስ መጀመሪያ ሥጋዊ ትምህርቱን የተማረው በትውልድ ሀገሩ በቂሳርያ፥ ቀጰዶቅያ፥ ከዚያ ቁስጥንጥያ፥ መጨረሻ አቴና ነው። በአቴና አምስት ዓመት ቆይቷል። ከዚህ ነው፤ በኋላ ከነገሠው ዮልዮስ ጋራ የተዋደነው። በፊት ከሀገር ቤት ከሚያውቀው ከጎርጎርዮስ ዘናዝያንዚስ ጋራም በደንብ የተጎዳኙና የዕድሜ ልክ ወዳጅ የሆኑት አሁንም ከአቴና ነው።

## ክርስትናን ያስፋፉ ታላቅ አበው

በ356 ወደ ሀገሩ ቀጳዶቅያ ተመልሶ ንግግር እያስተማረ ተከናውኖለት ሲኖር፥ አንድ ቀን ከእኅቱ ጋራ ሲነጋገር የዚህን ዓለም ከንቱነት ተረዳና በ357 ተጠመቀ። በዚህ ጊዜ ነው ማክሪና የገዳምን ኑሮ በአኔሲ ውስጥ የመሠረተችው። በዚህ ጊዜ ባስልዮስም አብን መምሰል ፈለገና ስለገዳም ሕይወት በደምብ ለማወቅ ፈለገ። ወስኖም፥ በቀጳዶቅያ ከሰባስቲ ካለው ኤዎስጣቴዎስ ደቀ መዛሙርት ሌላ ግብጽን፥ የሲርያን፥ የሜሶጶጣምያን ገዳማት ጎበኘ። ሲመለስ ንብረቱን ሁሉ ለነዳያን መጽውቶ በብሕትውና ለመኖር በኢሪስ ወንዝ ገንገብ፤ (ጋግት) በአኒሲ ማዶ በቂሳርያ አጠገብ ገብቶ በጾም፥ በጸሎት፥ በስጊድ ተጠመደ። ወዲያውም ፍጹምነትን የሚፈልጉ ብዙ ቀናዕያን ክርስቲያኖች መጥተው ከበቡት። ምንም እሱ የመሠረታቸው ገዳማት እንደ አባ ጳኩሚስች ባይበዙም፥ በጳኩሚስ ሕግ አሰባሰባቸው። የምግባርና የተጋድሎ ጥሩ ሕጊ አወጣላቸው። በዚህም የምሥራቅ ገዳማት ሕግ አውጭ ተባለ። ከተግባረ እድና ከጸሎት ጋራ ትምህርት (ጥናት) ተጨመረ። መነኮሳት ሁሉ ሥሩ፥ ጸልዩ፥ ተማሩ (አጥኑ) ተባሉ።

ከጓደኛው ከጎርጎርዮስ ዘናዝያንዚስ ጋራ ከኦርጌኒስ ብዙ ጥሩ ጥሩ ጽሑፎች ሰበሰበ። በዚህ ሁኔታ ባስልዮስ አምስት ዓመት ያህል ቆየ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከአንባቢ (Lector) በላይ ማዕረግ አልነበረውም። ከ362-370 የነበረው አዲሱ የቂሳርያ ጳጳስ ኤውሴብዮስ እንዲህ ያለውን ጥቡዕና ጠንካራ ሰው ርዳታ ፈልጎ ካለበት ጠርቶ አቀሰሰው። ነገር ግን ሕዝቡ በግብሩና በትምህቱ ተማርኮ ስለወደደው ጳጳሱ ቀናና ጭቅጭቅ ሲነሣ ስለሆነ በዚያው ዓመት 362 ዓ.ም. ለቆስትፋጥሎስት ወደ ገዳሙ ተመለሰ። ግን በ365 ዓ.ም. ገደግ በባሌንስ ጊዜ በተነሣው ክርክር የሚረዳው ከእሱ የተሻለ ስላጣ ጠርቶ አማካሪው አደረገው፤ የሀገረ ስብከቱን አስተዳደርም ሰጠው። ባስልዮስ በዚህ ጊዜ ሁሉ የዕመድ መነኮስ ሕይወቱን ቀጠለ። በ368 ደግሞ በቀጳዶቅያ ረኀብ ተነሣና፥ ቢነሣ፥ ከፊተኛው ምጽዋት የተረፈውን ሁሉ ለቃቅሞ ለችግረተኞች መጸወተ።

በ370 ኤውሴብዮስ ሲሞት በአርዮሳውያን ትግል መካከል ተመርጦ ጳጳስ። በዚህም እስከ 379 ቆየ።

በዚህ ባጭር የጵጵስና ዘመኑ በጳንጡስ እንዳደረገው፥ በቀጶዶቅያም ሥርዓተ ገዳማትን ሠራ፤ ካህናትን አደራጀ፤ ሥርዓተ ቅዳሴን አከናወነ። የሥነ ጥበብ፥ የእንዱስትሪ፥ የዕጓለማውታ፥ የሱባኤ ሕንጻዎችና ግቢዎች

አሠርቶ ከቂሳርያ ውጭ ሌላ ቂሳርያ ፈጠረ።

ሃይማኖቱንም በክላሲካል ዘይቤ አጣፍጦ እያቀረበ ለሕዝቡ አብራራ፥ አስተማረ። ኢፖስታሲስ (አካል) የሞውስዮስ፥ የሞኢስዮስ ከአንድ ባሕርይ፥ ከተመሳሳይ ባሕርይ የሚሉትን ውሳኔያትም ግልጥ ትርጉም ሰጠ። እሱም በ381 ቁስጥንጥንያ ላይ በተደረገው የዓለም ጉባኤ ተቀባይነት አግኝቶ አለፈ።

ከአትናቴዎስ ቀጥሎ የአርዮስ ታላቅ መዶሻ ቅዱስ ባስልዮስ ነበረ። ብሕትውናን በሦስት ሕግጋት ወስኗል፤ ምግባር፥ የረጅም ጊዜ ሕግ፥ ያጭር ጊዜ ሕግ፥ በሚል በሰፊው ተንትኗል። ስብከት፤ በስድስቱ ቀን የእግዚአብሔር አፈጣጠር ተነሥቶ አብራርቶ ሲያስተምረው የኖረን በጽሑፍ ለትውልድ ትቶ አልፏል። የስድስቱ ቀን ፍጥረት አተረጓጎሙ ከሳይንስ ጋራ ይስማማል።

ምስጢረ ሥላሴን በኤውኖሚኡስ ላይ በጻፈው 5 ቅጽ መጽሐፍ ተንትኖ አስረድቷል። በዚህ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ጋራ በማንኛቸውም ሁኔታ ዕሩያን (እኩል) መሆናቸውን ገልጦ አስረድቷል። ሃይማኖቱን የሚገልጡ ብዙ መልእክታትና ደብዳቤዎችም ጽፏል።

<u>ጎርጎርዮስ (የኒሱሲው) (331-395)</u>

ወንድሙ በጣም ይጫነው ነበር፤ እሱም ጌታው፥ የኔታ ይለው ነበር። በንግግር ትምህርቱ ዓለማዊ ስለሆነ፥ የሥጋዊ ተግባር ስለያዘ ባስልዮስ ሲያስብ፥ በንስሓ ተመልሶ ቅዱስ ባስልዮስ ወደ መሠረተው ገዳም ገባ። በ371 የቅዱስ ባስልዮስን ግብዣ ተቀብሎ የኒሳ ጳጳስ ሆነ። ነባቤ መለኮት እንጂ ጥሩ አስተዳዳሪ ስላልነበረ ብዙ ችግር አጋጠመው። ይህም በዝቶበት አርዮሳውያን ጳጳሳት ንጉሡ ባሌንን አታለው በ376 ከመንበሩ አወረዱት፤ ግን ከሁለት ዓመት በኋላ ባሌን ሲሞት በ378 ወደ መንበሩ ተመለሰ። ደረጃ በደረጃ ዝናው እየታወቀ ሄደና በ379 የሲርያን ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ለማስታረቅ ተጠየቀ። በ381 በቁስጥንጥንያው ያለም ጉባኤ ላይም ከመሪዎቹ አንዱ ነበር። ከዚህ በፊት ከአንጾኪያው ጉባኤ ተሳትፎ የሳባስቴ ጳጳስ እንዲሆን ተመረጠ፤ የኒሳው ጎርጎርዮስ፤ ነባቤ መለኮት፥ ቁባ አሳቢ፥ በዕውቀት የተራቀቀ፥ በጥንታዊውና በአዲሱ የአፍላጦን ፍልስፍና የተካነ፥ የታወቀ ዝነኛ ተናጋሪ (Orator) የብሕትውና መጽሐፈ መነኮሳት ደራሲ ነበር።

ዋና ዋነዎቹ መንፈሳውያን መጻፎቹ የሚገልጡት የአርዮስን ተከታይ የኤውናሚዮስን፥ የአፖሊናሪስን ኑፋቄ ከንቱነት ነው። የንኡስ ክርስቲያን ትምህርቱ ንኡስ ክርስቲያንን ለሚያስተምሩ መምህራን ታስቦ የተዘጋጀ ስለሆነ፤ ምስጢረ ሥላሴን፥ ምስጢረ ሥጋዌን፥ ምስጢረ ጥምቀትን፥ ምስጢረ ቁርባንን፥ ምስጢረ ድኅነትን፥ እነዚህን አምስቱን አዕማደ ምስጢራት በደንብ አድርጎ ተንትኖ ያስረዳል። አብዛኛው የትርጓሜ መጽሐፍ ግን የኦሪጌኒስን ተጽዕኖ የተከተለ ነው።

<u>ጎርጎርዮስ ናዝያንዚኖስ</u> (329-389)

ይህ ጎርጎርዮስ የባስልዮስ በሁሉም ጓደኛ ነው። በዕድሜ፥ በትምህርት፥ በፍልስፍና፥ በሀገር፥ በብሕትውና፥ በሃይማኖት በጽጽስና አንድ ናቸው። ጎርጎርዮስ በቀጳዶቅያ የናዝያንዙ ጳጳስ እሱም ጎርጎርዮስ የሚባል ልጅ ነው። አባቱና እናቱ መንፈሳዊ ትምህርት በደምብ እንዲማርላቸው ይፈልጉ ነበር። አባቱ ወዲያው እንደ ተጠመቀ በግብረ ገብነቱ ተመርጦ የተሾመ እንጂ በጣም የተማረ አልነበረምና ልጁ እንዲማርለት ይፈልግ ነበር።

ጎርጎርዮስ የተማረው መጀመሪያ ከዚያው ከተወለደበት መንደር በናዝያንዙ፥ ቀጥሎ በቂሳርያ፥ ቀጳዶቅያ፥ እስክንድርያ፥ አቴና ነው። የሁለቱ የባስልዮስና የእሱ ፍቅር የጠበቀው በአቴን ዩኒቨርሲቲ ነው። ትምህርቱን እንደጨረሰ ንግግር፥ ጥብቅና፥ ሕግ አስተምሯል። ከዚያ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሽማግሌ አባቱን ለጥቂት ቀን ከረዳ በኋላ ቅዱስ ባስልዮስ በሠራው ገዳም በኢሪስ ወንዝ አጠገብ ገብቶ ዘጋ። ጠባዩ ብሕትውናና ጾሙና፥ ጸሎት ስለሚፈልግ ከዓለሙ ኑሮ ይልቅ ገዳም ይወዳል። በ362 በተጽዕኖ አባቱ ጎርጎርዮስ አቀሰሰው። በ372 አሁንም በተጽዕኖ የባሲና በቀጳዶቅያ ውስጥ ያለች አውራጃ ጳጳስ ሁኖ ተሾመ፤ እሱ ግን እንኳን ሊያስተዳድራት ሂዶም አልጎበኛት። አባቱ ሸመገልሁ ብሎ ስላስቸገረው እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በ374 የእሱ አቡነ ቀሲስ ሁኖ እየረዳ በናዝያንዙስ ቆየ። ከሞተ በኋላ ግን አሁንም ወደ ሰለፍኪያ፥ ኢሳውሪያ ሂዶ በብሕትውና ተቀመጠ። በ379 ግን የቁስጥንጥንያ ሕዝብ ስለጋበዘው በቅዱስ ባስልዮስ ገፋፊነት ሂዶ አናስታሲስ (ትንሣኤ) የምትባል ቤተ ክርስቲያን (መቃኞ) ሠርቶ የሠለሰቱ ምእትን ጸሎተ ሃይማኖት እየሰበከ ከአርዮስ ክሕደት ብዙ ሕዝብ ወደ ኦርቶዶክስ መለሰ። በዚህ ሁኔታ ሳለ ሁለተኛው የዓለም ጉባኤ በቁስጥንጥንያ በ381፤ በጢሞቴዎስ

የእስክንድርያው ፓትርያርክ አሌ ጉባኤ ተደረገ። በጉባኤው ላይም ጎርጎርዮስ የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሁና ተመረጠና በመንበሩ ተቀመጠ። በኋላ ግን ምቀኞቹ ምርጫው ትክክል አይደለም እያሉ ስላጉረመረሙ፤ የአርዮስ ኑፋቄም ስለተወገደ፥ እሱም ማስተማር፥ መስበክ፥ መጾም መጸለይ እንጂ ጭቅጭቅ ስለማይወድ ወደ ናዝያንዙ ትውልድ አገሩ ተመልሶ በርስቱ ላይ ገዳም ሠርቶ በተጸምዶና በተጋድሎ ኖሮ ዐረፈ።

ጎርጎርዮስ ዘናዝያንዙ ራእዩና አቅሞ የማይስብም ቢሆን የንግግርና የስብከት ስጦታው ሰሚውን ሁሉ የሚስብ ነበር። ብዙ መጻሕፍት ጽፏል፤ ክታባት አዘጋጅቷል፥ መልእክታት በብዙ ምክንያት ልኳል። ስሙን የሚያስነሡት ግን የሚከተሉት ናቸው፤

ከሁሉም በላይ መወሣት የሚገባቸው በአርዮስ ላይ የተጻፉትና የተሰበኩት ምስጢረ ሥጋዌን የሚገልጡት አምስቱ ክታባት፤ የኤውኖሚያንን ክሕደት ብትንትኑን ካወጣ በኋላ የእግዚአብሔር ወልድን ከአባቱ ጋራ በመለኮቱ እኩልነት (ዕሩይ) ገልጦ አስረድቷል። ከዚህም ቀጥሎ የመቅደንዮስን ክሕደት (መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያንሳል) የአፖሊናርዮስን ደግሞ ሥጋ እንጂ ነፍስንና መንፈስን ከማርያም አልነሣም የሚለውን ብትንትኑን አውጥቶ የኦርተዶክስ መልስ ሰጥቷል።

<u>በአጠቃላይ ሦስቱ ቀጸዶቃውያን፤</u>

ሦስቱ ቀጸዶቃውያን በመንፈስ ቅዱስ እነሣሽነት፥ እንደ አንድ ልብ መካሪ፥ አንደ እንድ ምላስ ተናጋሪ ሁነው፥ በጽሑፍ፥ በማስተማር፥ በስብከት በሠለስቱ ምእት የተጀመረውን ምስጢረ ሥላሴን፥ ምስጢረ ሥጋዌን፥ ምስጢረ እድጎናትን፥ ምስጠረ ጥምቀትን፥ ስብዓቱ ሀብታትን፥ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፥ ሥርዓተ ቁርባንን (ቅዳሴን) ለመጭው ትውልድ በደምብ አዘጋጅተው፥ አበጅተው አልፈዋል።

Ousia= ባሕርይ, Upostasis Hypostasis አካል፤ Prosopon= Person ገጽ፥ Omoousios ካንድ ባሕርይ፥ ከዚያው ባሕርይ፥ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ= Omoiousios Homoiousios ከእምሳያ ከተመሳሳይ ባሕርይ የሚሉትን በግኖስቲካውያን ጊዜ ተወልደው በአርዮስ ምክንያት ቅዱስ አትናቴዎስ አሳምሮ የቀረጻቸውን ውሳኔያት ጠርበው አዘጋጅተው እየዋለሉ እንዳያስቸግሩ አንዳንድ ትርጉም ሰጥተው አስተምረዋል። አርዮስ በክሕደት፥ እርጌኒስ በስሕተት፥ አፖሊናርዮስ ያስ

ዕውቀት ያበላሹትን የእግዚአብሔር ወልድን ከአባቱ ጋራ በመለኮቱ አኩልነት ሠለስቱ ምእትና ቅዱስ አትናቲዎስ በወሰኑት መሠረት አደላድለው ለትውልድ አስረክበዋል። መቅዶንዮስ ያፈረሰውን የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር ሥልጣንና ዕሩይነት ከአብና ከወልድ የማይለይ አኩል እንደሆነ በስፋው አስረድተዋል።

ለምስጢረ አድኅና ዓለምም መድኅኔ ዓለም ለዓለም ሲል ተወልዶ፥ 30ዓመት በዚህ ዓለም በአካለ ሥጋ ኑሮ፥ 3 ዓመት ሀገር ለሀገር እየዞረ አስተምሮ፥ ተገፎ፥ ተገርፎ፥ ተሰቅሎ፥ ሙቶ ራሱን ለሰው ሲል ለአባቱ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦ፥ ፍጹም ካሣ ክሦ ማዳኑን ከነምክንያቱ ዘርዝረው አስረድተዋል።

የቤተ ክርስቲያንንም አስተዳደር በጽሑፍ፥ በስብከት፥ በአርአያ ሥርዓት አሲዘዋል። ምንኩስናን (ሥርዓተ ገዳም) በተለየ ቅዱስ ባስልዮስ ከእንቱ ከማክሪና ጋራ ሁና ጥሩ መልክ ሰጥቶታል። በግብጽ ከባስልዮስ በፊት የገዳምን ሥርዓተ ማኅበር የሠራው አባ ጳኩሚስ ነው። ወደ ምዕራብ ያሸጋገረው ግን ቅዱስ ባስልዮስ ነው። ከዚህም በላይ ቅዱስ ባስልዮስ ከክርስትና ከጓደኛው ከጎርጎርዮስ ጋራ ሁና ብዙውን የአሕዛብን ፍልስፍና ከክርስትና አቀራርቧል። ለምሳሌ በስድስት ቀን እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ የሚለው የመጀመሪያው የኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ከሳይንስ ጋራ እንዲስማማ ዕለቱን በዘመን ለውጦ ተርጎሟል። ስለ ጥንተ አብሶ፥ ስለ ጸጋ እግዚአብሔር፥ ስለሚስጢራተ ቤተ ክርስቲያንም በስፋው አያተቱ እስረድተዋል። ከጸጋ እግዚአብሔር ጋር በሥራ ፍጹም ለመሆን በተግባርም እያሳዩ አስተምረዋል።

ሦስቱ ቀበዶቃውያን አበው በአርግጥ እንከን የለሽ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ነበሩ።

<u>የሚላኑ አምብሮስ (340-397)</u>

የሚላኑ ጳጳስ ቅዱስ አምብሮስ የተወለደው በትሪየር ከአንድ የሮማን መኮንን የጎል ሀገር ገዥ ነው። የክላሲካል ፍልስፍናና ሕግ፥ ግሪክ ቋንቋ ተምሯል። በሮማውያን ፍርድ ቤት ልምምድ ካደረገ በኋላ በ370 ዓ.ም ላይ በ374 ከተማዋ ሚላና በሆነው ሊጎርያ ሀገር ገዢ ሁኖ ተሹሞ ሳለ በ374 ከተማዋ ሚላኖ ግዛት ሁኖ ተሹሞ ሳለ ነበር።

ወዲያውኑ ተጠምቆ ተከኖ የሚላና ጳጳስ ተብሎ ተሾመና ወዲያው መንፈሳዊ ትምህርቱን በደምብ ተማረ፤ ቅዱሳት መጽሕፍትን በቀድሞ የግል መምህሩ ሲምፕሊኪያኖስ መሪነት አጠና። እንደ ጳጳስነቱ የተዋጣለት ሰባኪ ነበረ። ቅዱስ አውግስጢኖስንም ወደ ክርስትና የመለሰው የአምብሮስ ስብከት ነው። አውግስጢኖስም ይወደው፣ ያከብረውም ነበር። በዕውቀቱና በስብከቱ መሳፍንቱ፣ ነገሥታቱ ሁሉ ይወዱትም ያከብሩትም ነበር። ያከብሩት ከነበሩት ከምዕራቡ ክፍል ለመጥቀስ ያህል፣ ግራትያን፣ ማክሲመስ፣ የዳግማዊ ባሌንቲንያን እናት ንግሥት ዮስጢና፣ ቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ ይገኙበታል።

በትምህርቱ እርዮሳዊነትንና አረማዊነትን ጠንክሮ ተዋጋ፤ ቤተ ክርስቲያንን ከሥጋዊ አገዛዝ ነጻ አወጣ። ሥነ ምግባር ሲበላሽ ይገሥጽ፣ ይገዘት ነበር። ገዥዎችም አስተዳደር ሲያበላሹ፣ ፍርድ ሲያበላሹ፣ ፍርድ ሲያጣምሙ፣ ያለምንም ፍርሃት ያርም፣ ይገሥጽ ነበር። በጽሑፍ በኩል፤ ለንኡስ ክርስቲያን ሃይማኖትና ምስጢራት ማስተማሪያ ጽፏል፣ ይህም ዝነኛ ያደረገው ሥራ ነው። ግሪክ ማጥናቱም እንደኛ መንፈሳዊ ትምህርቱን በደምብ እንዲያውቅ፣ ሁለተኛ ብሕትውናንና ሥርዓተ መነኮሳት ወደ ኢጣልያ ለማስገባተ ረድቶታል። መልእክታቱም ታሪክ አዘሎች ናቸው። የዘመኑ ሊቃውንት ደግሞ በቅዱስ አትናቴዎስ ስም የሚታወቀውን ጸሎተ ሃይማኖትን የደረሰው እሱ ነው ይላሉ። በምንኩስናውና በብሕትናውም ፅሙድ ወመስተጋድል እንደ ነበረ ብዙ ምንጮች ይናገራሉ።

<u>ቅዱስ አውግስጢኖስ (354-430)</u>

አውሬልዮስ አውግስጢኖስ በሰሜን አፍሪካ፣ ታጋስት፣ ኑሚድያ፣ በ354፣ ከአረሚ አባት ከክርስቲያን እናት ተወለደ። የወላጆቹ ኑሮ መካከለኛ ነበር። ሞኒካ እናቱ አክራሪ ክርስቲያን፣ ሥነ ሥርዓት አዋባቂ፣ ተቆጣጣሪ እናት ነበረች። አባቱ ፓትሪክዮስ፣ ዛሬ በእኛ አንዳንድ ሰዎች ሲሞቱ ሲጠማሩ በድኑን አልክፉት፣ ወአልክፍዎ ለበድን ይላል ብለው ቆርበው እንዲሚሞቱ፣ በ372 ዓ.ም. ተጠምቆ ሞተ።

አውግስጢኖስ አብዛኛውን ጊዜ በእናቱ ተቆጣጣሪነት የጥንት ሥነ ጽሑፍ፣ ንግግር፣ ፍልስፍና አጠና። በወጣትነቱ አልተጠመቀም እንጂ ንኡስ ክርስቲያን በልጅነቱ ተምሯል። በንግግር የታወቀ ነበር። ግሪክ ግን በደምብ አላጠናም። መጀመሪያ የተማረው ከትውልድ ሀገሩ ከማዳውራ

ሁለተኛ ደረጃ ከካርታጅ ዩንቨርስቲ ነው። ከላቲን ቤተ ክርስቲያን በሊቅነቱ ከአውግስጢኖስ የደረሰ የለም ይባላል። ሊቅስ የእስክንድርያው አርጌኒስም ነበረ፤ ከሐሳቡ ብዛት የተነሣ በጥቂት ነገሮች ተሳሳተ እንጂ፥ ከቅዱስ ጀሮም ማስፋ ግን ተረጋግጧል። ከ16ኛ ዓመቱ በቀር የቀረውን ሕይወቱን በሥራ ተጠምዶ ነው ያሳለፈው። ከ372-85 የጭን ገረድ ነበረችው፥ ከእሷ አንድ ወንድ ልጅ ወልዶ ኢዮዳቱስ (ሀብተ እግዚአብሔር፥ ጸጋ እግዚአብሔር፥ ቴዎድሮስ) አለው። እሱም በ390 ሞተ። ስም የለሽ የጭን ገረዱንም በሕግ ተሞሽሮ አሥርጎ ለማግባት ሲል ፈታት። ፈትቶ ሮም ሂዶ ቂቄሮስን (Cicero) አንብቦ ወደ ፍልስፍና ተሰወጠ፤ በዚህም ስሁሉም ነገር ሁለት መርሕ፤ እሳት፥ ውሃ፥ ብርሃን፥ ጨለማ፥ አምላክ፥ ቁስ አለው የሚል በጥንት ተረት የተሰወሰ ማኒ፥ ማኒዎስ የሚባል የፋርስ ሰው የፈለሰፈውን ሃይማኖት ከነፍልስፍናው ታቅፎ ለ10 ዓመት ያህል ኖረ። በኋላ ያንጊዜ ዋና ከተማ ወደነበረችው ወደ ሚላኖ ሄደና በቅዱስ አምብሮስ ስብከት ተማርኮ በ386 ዓ.ም. ተጠመቀ። ከጥምቀቱ በኋላ ወደ ትውልድ ሀገሩ አፍሪካ፥ ወደ ታጋስት ተመልሶ ገዳም መሥርቶ ማኅበረ መነኮሳት ሠራ። በዚህም በመላ ሀገሪቱ ዝናው ተነሣና በ395 ዓ.ም. የሂፖ ጳጳስ ረዳት ስመሆን ጸደቀ። ጳጳሱ ሲሞትም ሿቹን ተክቶ እስከ ዕለተ ሞቱ የሂፖ ጳጳስ ሁኖ ኖረ።

በጽድስናውም ከዚህ በላይ እንደ ተገለጠው፥ ነባቤ መለኮትና የቤተ ክርስቲያን ሰው መሆኑን በትምህርቱ፥ በስብከቱ፥ በግብሩ አስመስክሯል። ብዙ መጻሕፍት ጽፏል፤ በእነሱም ካቶሊኮችም ሆነ ወንጌላውያን (ፕሮቴስታንት) ያመሰግኑታል። ስሙን ካስጠሩት መጻሕፍት ውስጥ ሁለቱ ሳይጠቀሱ አይታለፍም፤

1. Confessione, ኑዛዜ (ተአምኖ) ራሱ በራሱ የጻፈው የሕይወት ታሪክ ሲሆን፥ ማንኛቸውም ሰው ኀጢአቱን ለጌታ ተናዝዞ፥ በመናዘዝ እንዴት እንደሚያስተስርይ ያስተምራል።

2. De Civitate Dei (ስለ እግዚአብሔር ከተማ) ሙሉ የክርስትና ረጅም ተቃሥኦ ነው። ሐዲሱ ሃይማኖት ክርስትና ነው የሮምን መንግሥት ስመውደቅ ምክንያት የሆነው የሚለውን ወሬ ከንቱ መሆኑን በመረጃ አስወግዷል። በብዙ መናፍቃን ላይም ጽኑ ተቃሥኦ እያቀረበ መልስ አሳጥቷል። የእነዚህ የሁለቱ መጻሕፍቱ በዓለም አሉ ከሚባሉት ታላላቅ መጻሕፍት ነው ቁጥራቸው።

የሮም ግዛት የነበረችውን ካርታጅን ባንዳልስ በወረሯት ጊዜ፤ ብዙ ገዳማት መሥርቶ፥ መጻሕፍት ጽፎ፥ ክርስትናን አጠናክሮ በ430 በሀገሩ ውስጥ ዐርፏል። ከዚህ የቀረውን የዚህን ትልቅ ሰው ታሪክ ለማወቅ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ማንበብ ያሻል።

ጀሮም Jerom (345-419)

አውሳቦስ ኢኤሮኒሞስ ጀሮም የቅዱሳት መጻሕፍት ሊቅና ተርጓሚ በሰሜን ምሥራቅ ኢጣልያ አስቲሪዶን ከክርስቲያን ቤተ ሰብእ ተወለደ። ጀሮም የተማረውና የተጠመቀው ሮም ነው፤ ከዚያ በኋላ በአኩላ ብሕትወናና የምንኩስናን ሕይወት ከመጀመሩ በፊት ወደ ጎል ሂዶ ነበር። ከዚያ ወደ ፍልስጥኤም ጉዞውን አመራ፤ ግን በመንገድ አንጾኪያ ዐርፎ የአፖሊናርዮስን ስብከት ሰምቶ በሲርያ በረሃ ለአምስት ዓመት ያህል በብሕትውና ገብቶ ከጸሎቱና ከተጋድሎ ተጠምዶው ሌላ ዕብራይስጥ አጠና። ከዚያ ሲመለስ የአንጾኪያው ጳጳስ ጳውሊኖስ አቀሰሰው፥ ከዚያ ቆስጥንጥንያ ሂዶ ከ382-385 ያለውን ጊዜውን አሳልፎ ወደ ሮም ተመለሰና የፖፕ ዳማሰስ ጸሐፊ ሁኖ እየሠራ ምንኩስናንና ብሕትውናን በሚገባ ሰበከ።

ከዳማሰስ ሞት በኋላ፥ አንጾኪያን፥ ግብጽን ጎብኝቶ፥ በመጨረሻ ቤተልሔም ገብቶ የገዳሙ አለቃ ሁኖ፥ መላ ሕይወቱን ለጥናት ሰጠ። በዚህም 34 ዓመት ተቀመጠ። በብሳጊዮስና በአርዮስ ላይ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል። ጀሮም የሚነግው ከሊቅነቱ ይልቅ ከቱባዎቹ ቋንቋዎቹ ዕብራይስጥና ግሪክ ወደ ላቲን ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጎሙ ነው። እሱም ቡልጋቴ ወይም ቡልጋታ ይባላል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድርስ ለብዙ መቶ ዓመታት ለምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊው ትርጉም ሁኖ ኑሯል። የትሬንቴ ጉባኤም የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን የሚነበበው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ቡልጋታ እንዲሆን ወሰኗል። በሊቅነቱ ከአውግስጢኖስና ከኦሮጌኒስ ይወዳደራል። ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ከመተርጎም ሌላ ከቅዱሳት መጻሕፍት ብዙዎችን በአንድምታ አትቷል። የታላላቅ ሰዎችን ታሪክና ገድል ከግሪክ ወደ ላቲን ተርጉሟል። ከዚህም በላይ ዕረፍት የለሽ ጠባዕዩ (ባሕርይ) በአርዮስ፥ በበላጊያኖስ፥ በኦርጌኒስ እንዲጽፍ ገፋፍቶት ጥሩ ጥሩ የተቃሥኦ መጻሕፍት ጽፏል።

<u>ዮሐንስ አፈወርቅ</u> (344-407)

በስብከትና በንግግር ዝነኛው ዮሐንስ አፈወርቅ፥ ትልቁ የአንጾኪያ ትምህርት ቤት ዶክተር በአንጾኪያ በ344 ገደማ ተወለደ። አባቱ ሴኩንዱስ የሮም ንጉሠ ነገሥት የምሥራቁ ክፍል ገዥ ነበረ። ግን ሳያሳድገው ዮሐንስ እንደ ተወለደ ሞተ። እናቱ አንቱሳ በ20 ዓመቷ መበለት ሁና ልጅዋን በደምብ ተቆጣጥራ ለማሳደግ በትል ዳግመኛ ሳታገባ ቀረች። በዚህም ከሞኒካ የተሻለች ዕድለኛ ናት፤ ስለምን ቢሉ ልጅዋን ዮሐንስን እንደ አውግስጢኖስ ያለ የኀርምስና ፈተና አልነካውምና።

ዮሐንስ የክላሲክን ሥልጣኔ በሞላ፥ ንግግር፥ ፍልስፍና ከታወቁት የአሕዛብ መምህራን ሊባንዮስና አንድራጋቲዮስ ተምሯል። ሕግም በተጨማሪ ሳይማር አልቀረም።

ይህ ሁሉ ሲሆን እንደ ዘመኑ ልማድ አልተጠመቀም ነበርና የአንጾኪያ ጳጳስ ሚልጦስ በ370 አጥምቆ አንባቢነት ሾመው፤ ሰጠው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በብሕትውና፥ በቀኖና፥ በጾም፥ በጸሎት ተጠመደ። ግን መበለት እናቱን መርዳት ስላለበት እስከ ጊዜ ዕረፍቷ 373 ዓ.ም. አብሯት ሲጦራት ሲረዳት ቆየ። እሷ በሞተች በዓመቱ በአንጾኪያ አጠገብ ካለው ተራራ ገዳም ገብቶ አራት ዓመት ቆየና እንደገና በብሕትውና ካንድ በአት ገብቶ ዘግቶ 3 ዓመት አሳለፈ። በዚህ ጊዜ ጥብቅ የመቁነን ኑሮው ጤንነቱን አዳከመበት።

በ380 ገደማ ወደ አንጾኪያ እንዲመለስ ከእግዚአብሔር በራእይ ታዘዘና በሚልጦስ ፓትራያርኩ ግቢ አንድ ዓመት እንዳገለገለ ሚልጦስ ዲቁና ሾመው፤ በዚህ ማዕረጉም አምስት ዓመት አገለገለ። ይህ ሁሉ ሲሆን የተጋድሎ ልምዱን አላቋረጠም።

በዚህ ጊዜ ብዙ መጻሕፍት ጻፈ፤ ይልቁንም ለቅስና መርሕ የሚሆን፥ በመንፈሳዊ ቅናት፥ በንግግር በችሮታ ራሱን ፍጹም አድርጎ አዘጋጀ፤ አካባቢው ዐወቀው፤ የዚያን ጊዜው ፓትሪያርክ የሚልጦስ ወራሽ ፍላብያኖስም ጠርቶ አቅስስ የካቴድራሉ ሰባኪ በ40 ዓመቱ በ386 አደረገው። በሚቀጥሉት 12 ዓመታት በአንጾኪያና በአካባቢዋ አድባራት ዓመት በዓል በሆነ ቁጥር እየዞረ የሚሰብክ እሱ ነበር፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን በደንብ ስለሚያውቅ፥ የንግግር ችሎታ፥ የስብከት ስጦታ ስለነበረው ሕዝቡ ሰምቶ አይጠግበውም ነበር። በዓቢይ ጾም ዘወትር፥ በቀረው ግን በበዓል ይሰብክ ነበር። የሚሰብከውም ጽፎና በቃል አጥንቶ

ስለሆነ ለትውልድ ተርፏል። ለንኡስ ክርስቲያን ያደረጋቸው ንግግሮችም በማስተማሪያነት ለትውልድ ተላልፈዋል።

በ387 ንጉሠ ነገሥቱ ግብር በመጨመሩ የከተማው ሕዝብ ተናደደና ሐውልቱን አቃጠሰበት፤ በዚህም ተናዶ ከተማውን አቃጥላለሁ ብሎ ቢነሣ ፓትርያርኩ ፍላብያኖስ አማለደ፤ ዮሐንስም ስለከና ከተማዋን ከጥፋት አዳናት። ዮሐንስም በሕዝቡ ዘንድ መደነቅንና መወደድን አተረፈ።

በዚህ ዝናውም ሳይፈቅድ ተገዶ የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሁኖ በ398 ተሾመ። በዚህ ጊዜ የቁስጥንጥንያ ነገሥታት አንደኛ የነገሥታቱ ዘመንና እንደ አሁኑም የብሪቲሽ ዘውድ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂና አስተዳዳሪዎች ነበሩ፥ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደሞ የቤተ ክርስቲያንን ነጻነት የሚፈልግና የሚጠብቅ፥ መኳንንት፥ መሳፍንት፥ ነገሥታት፥ አስተዳደር ሲያጓድሉ፥ ፍትሕ ሲያጣምሙ፥ በሥልጣን ሲባልጉ የሚገሥጽ ነበረና፤ በዚህ ግብሩ ከሥጋዊ ባለሥልጣኖች ጋራ ተጣልቶ ሳለ የእስክንድርያው ቴዎፍሎስ በሀገሩ ያሉትን ጣዖታትን በማጥፋቱ የበላይነት ተሰማውና ቁስጥንጥንያንም በእሱ ቱኪ ለማስተዳደር ፈልጎ፥ ዮሐንስ በሰብከቱ ያስቀናቸውን መኳንንትና 26 ጳጳሳት ሰብስቦ፥ በ403 በእእከ አዳራሽ፥ ኬልቄዶን አጠገብ ጉባኤ አድርጎ ገዝቶ አስወረደው። በንጉሡና በንግሥው ባናደዳት አውደክስያ ትእዛዝ መጀመሪያ ወደ አንጾኪያ አጠገብ ተሰደደ፤ ከዚያ ደግሞ ቶሎ እንደማይሞት ሲታወቅ ጊዜ ወደ ፖንጦስ በመንገድ ሲሄድ እንዲሞት ተዘየደና በመንገድና በረኃብ 407 ዓ.ም. ሞተ።

ጠባዩ የሰብከት እንጂ የስርብትና ሰው አልነበረም፤ ለመርሑ እንጂ ለመተዳደር የሚያጎበድድ ሰው አልነበረም። በጽሑፍ ብዛት ከአርጌኒስ በቀር የሚበልጠው የለም። የጽሑፍ ውጤቱ ቦ ባም ብዙ ነው።

<u>የእስክንድርያው ቅዱስ ቄርሎስ (380-444)</u>

ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያው በእስክንድርያ ከክርስቲያን ቤተ ሰብእ በ380 ተወለደ። እግዚአብሔርን ለማገልገል ልክ እንደ ነቢዩ ኤርምያስ ከማሕፀን ተመርጦ፥ በልጅነቱ ወደ ገዳም ገብቶ ቃለ እግዚአብሔርን ተማረ። በሊቅነቱ በእስክንድርያ ከነበሩት ታላላቅ ሊቃውንት አንዱ ነው። በቤተ ክርስቲያኑ ስርብትናም በኩል ከአጎቱ ከፓትርያርክ ቴዎፍሎስ አያንስም።

በ403 በአጎቱ መሪነት ከአአክ ጉባኤ ላይ በተመልካችነት ተካፍሎ ነበር፤ ስለዚህ በስርብትናው በስኋል።

በ412 አጎቱን ቴዎፍሎስን ወርሶ የአስክንድርያ ፓትርያርክ ሆነ። ከዚህ በኋላ ከዘሩ በመጣው የመናፍቃን፥ የአሕዛብ፥ የካሓድያን ጥላቻ በአዲሱ የአፍላጦን ትምህርት፥ በአርዮሳውያን፥ በናባትያን፥ በአይሁድ፥ በአርጌኒሳውያን፥ በንስጥሮሳውያን። በአሕዛብ፥ በአረማውያን ላይ ብዙ የተዋሥኦ መጻሕፍት ጻፈ። እሱም እንዳጎቱ የቁስጥንጥንያ አሰቃ ለመሆን ወንተረጅ (ምኞት) ነበረውና የቁስጥንጥንያን ሁኔታ በጥብቅ ሲከታተል ሳለ የቆስጥንጥንያው ፓትርያርክ ንስጥሮስ በአቡነ ቀሲሱ ቀስቃሽነት፥ ክርስቶስ ሊለያዩ የሚችሉ ሁለት ባሕርያትና ሁለት አካላት አሉት፥ ማርያምም፥ ሰው አምላኩን ለመውለድ ስለማይችል፥ ወላዲተ ሰብእ እንጂ ወላዲተ አምላክ አይደለችም አለና ተነሣ። በዚህ ጊዜ ሲቫኝ ጢስ ወጋኝ፥ በቁስጥንጥንያ ላይ ያለው ትውፊታዊ ቅናትና በአንጾኪያ ላይ ያለው የትምህርተ ክርስቶስ ፍርሃት ገፋፍቶት፥ የሮሙን ጳጳስ ቸለስታይ አንደኛንና በእስክንድርያ በተደረገው ጉባኤ የገዛ ጳጳሳቱን ድጋፍ ተመርኩዞ ለንስጥሮስ ይህን ዐይተህ እስከ 12 ቀን ንስሐ ገብተህ መልሱን ላክልን ብሎ 12 ግዝት ላከለት። ትምህርቱም ከሁለት አካል አንድ አካል፥ ከሁለት ባሕሪያት አንድ መለትስ፥ ወይም ውሑድ ባሕርይ (God-Man, Theanthropos) ማርያምም ወላዲተ አምላክ እንጂ ወላዲተ ሰብእ አይደለችም ነበር።

እሱም ሳይመልስ ስለቀረ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋራ ተማክሮ በኤፌሶን በ431 ጉባኤ አደረገና ንስጥሮስን አውርዶ ሌላ ጳጳስ የእሱ ቱኪ አሾመ። ከዚህ በኋላ ከላይ በተጠቀሱት መናፍቃን ላይ ሲጽፍ እስከ 444 ኑሮ በሰላም ዐረፈ።

Fysisን ግን በሁለት ትርጉም አካልና ባሕርይ (Personና nature) ብሎ ሲሠራበት ነው የኖረ። የሚያስተምረውም

1. በ325 በኤፌሶን ጉባኤ በአርዮስ ላይ በ318 ጳጳሳት የተወሰነውን ወልድ ከአባቱ ከአብ ጋራ እኩል ነው የሚለውን፥

2. በሁለተኛው የዓለም ጉባኤ በቁስጥንጥንያ መንፈስ ቅዱስ ሕጹድ ነው በማለት በቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ በመቅዶንዮስ ላይ፥ መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ ሥላሴ አንድ ሲሆን በአምላክነትም ከአብና ከወልድ እኩል (ዕሩይ) ነው የሚለውን፤

3. በኤፌሶን ጉባኤ በ431 በንስጥሮስ ላይ የተወሰነውን ነበር። ትምህርቱም በተከታዮቹ 451 በኬልቄዶን፥ በ680 በቁስጥንጥንያ በተደረጉት የዓለም ጉባኤያት ከሞተ በኋላ ተቀባይነት አግኝቶ አልፏ ል።

## ለዚህ ምዕራፍ የሚነበቡ መጻሕፍት፤

1. ሉሌ መልአኩ፥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1986 ዓ.ም.

2. መጽሐፈ ቅዳሴ፥ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1988 ዓ.ም.

3. Cayre, F.A.A., Manual of Patrology, Tr.H. Howit, A.A., First Volume, Society of John the Evangelist, Paris, Tournai, Roma, 1936.

4. Meyer, Carls, The Church from Pentecost to the present, Moody Press, Chicago 1973.

5. The new International Dictionary of the Church, Douglas, J.D 1974.

6. The Oxford Dictionary of the Christian Church, Cross, F.L. 1957.

7. Renwick, A.M., The Story of the Church, Inter-Varsity Press, London, 1971.

8. Stephanidou, Basiliou, Church History, from the Beginning to the Present, (in Greek), Astir, Athene, 1947.

## ምዕራፍ ሃያ አንድ

### ፀሠርቱ ቃላትና ሐዲስ ኪዳን፣

ኦሪትና ወንጌል፣ ኦሪት የወንጌል መንገድ ጠራጊ እንጂ ዘለዓለማዊት ሕግ አይደለችም፣ ይህንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅዱሳት ሐዋርያቱ ደጋግመው አብራርተው፥ አስተምረዋል። ብዙ ሰዎች ግን በራሳቸው ሐሳብና ፍልስፍና እየተመሩ፥ ኦሪትንና ወንጌልን አያግቱ፥ ሁለቱንም አንድነት ይዘው ለመሄድ ሲሞክሩ፥ (ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ ባንድ ጊዜ አይወጣምና) ከሁለቱም ሳይሆኑ ይቀራሉ። ለዚህ ርእስ ምክንያት የሆነውም የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ስለቀዳሚት ሰንበት ያላቸው የተዛባ አስተያየት ነው። ስለነሱ ስሕተት በጠቅላላ በሚቀጥለው ምዕራፍ በራሳቸው እርስ ገልጠናል። ከዚህ ግን ጌታ (ማቴ.5:17) ኦሪትንና (ሕግን) ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፥ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም ያለውን ሳያስተነትኑ እንዳለ በድፍኑ ይዘው ኦሪት አልተሻረችም የሚሉ ስላሉ፥ ይህ ሐሳብ በዚህ ምዕራፍ ተተንትኖ ተጽፏልና መላልሶ አንቦ መረዳቱ ደግሞ ለአስተዋዩ አንባቢ ፋንታ ይሁን።

ለዚህም ሁለት ትርጉም አለው፣ አንደኛው በኦሪትና በነቢያት ክርስቶስ መጥቶ ዓለምን ያድናል ተብሎ የተነገረውን ትንቢት በግብር አፈጽማለሁ ማለት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በአባቱ ቃልነት በኦሪት በፀሠርቱ ቃላት የመሠረታቸውን አሁን ጣራ (ባጥ) ይደፋላቸዋል፣ በአዕማድ በግድግዳ ያጸናቸዋል፣ ይዘሽ ቆይኝ እንደቀዳሚት ሰንበት ያለውን ግን በዝምታ ይዘለዋል። ጌታ በትምህርቱ፥ ሐዋርያት በስብከታቸው ያልደገሙት ሥርዐተ ኦሪት፥ ሥርዐተ ረበናት ሁሉ ተሽሯል፥ አልፏል፥ ተተክቷል፥ ለምሳሌ ቀዳሚት ሰንበት ወደ እሑድ ተዛውራለች፣ ግዝረት በጥምቀት ተተክቷል፣ ጾመ አስቴርና ጾመ ዮዲት በዐርብ ረቡዕ ተተክተዋል።

<u>ያጠበቃቸውም በሚከተሉት ትእዛዛት ነው፣</u>

(ማቴ.5.17-48) አትግደልን እንኳን መግደልና፥ አትቆጣ፥ አታስቆጣ፥ አታመንዝርን ሴትን በዐይነ ፍትወት አትመልከት፥ ካላመነዘረች አትፍታ፣ በእውነት አትማልን የእግዚአብሔር እምላክህን ስም ከንቱ እታድርግን በጭርሱ አትማል፣ እውነትን እውነት፣ ሐሰትን ሐሰት በል እንጂ፣ አትበቀል፣ ቀኝ ጉንጭህን ቢመታህ ግራዋን መልስለት እንጂ፣ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፣ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፣ የባልንጀራህን ምሽት፥ ሎሌውንም ገረዱንም፥ በሬውንም አህያውንም፥

ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛቸውንም አትመኝ ብሎ ያዘዘውን በአሪት፣ አሁን ግን እንኳንስ አንተ ትበድለውና ቢበድልህ እንኳ፤ በጥፊ ቢመታህ እንኳ ያልተመታችውን ግራ ጉንጭህን ስጠው ብሎ ከዘዳ.20:13-16 የተጻፉትን ስለባልንጀራ የሚናገሩትን ትእዛዛት አጠቃሎ ተናግሯል። አባትህንና እናትህን አክብር የሚለውን ትእዛዝም ግሣጼ ጨምሮ አጠናክሯል፤ (ማቴ.15:1-9) አትስረቅንም የባልንጀራህን ገንዘብ አትመኝ ብሎ ዘግቷል። ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድንም፤ ወንድምህን አታስቆጣ፣ በሐሰት አትመስክር የባልንጀራህ የሆነውን ሁሉ አትመኝ ብሎ አጥብቆ ዘግቷል፤ ቆልፏል።

ከግብጽ ከባርነት ቤት ያወጣውህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፤ ከኔ በቀር ሌላ አማልክት አይኑርህንም (ዘፀ.20:1-2) መምህር ሆይ! ከትእዛዛት ሁሉ ታላቋ የትኛዋ ናት ብሎ አንድ የኦሪት ፀዋቂ ቢጠይቀው፣ ጌታ እምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀሊናህ ውደድ፣ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይች ናት፣ ሁለተኛይቱም ይችን ትመስላለች፣ እሷም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትለዋ ናት፣ ኦሪትና ነቢያትም በነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸንተው ይኖራሉ ብሎ ዐሠርቱ ትእዛዛትን ሊደመድም ስለ ሰንበት አላነሳም።

ወዳጅህን ውደድ፣ ጠላትህን ጥላን፣ እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ ለሚያሳድዱችሁ ጸልዩ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ በሰማይ ያለው አባታችሁ ፍጹም ልጆች እንድትሆኑ ብሎ የወንጌልን መልክት ሲዘጋ ቀዳሚት ሰንበት በፀጸዱ አልነበረችም። ራሳቸው እንደሚሉት የሰንበት ትርጉም ዕረፍት ነው። ከዘለዓለማዊቱ ዕረፍት ግን እስራኤላውያን እንደማይገቡ ተናግሯል፤ ይህም ሐዲሲቱ ሰንበት እሑድ መሆኗን ይገልጣል። በከመ መሐልኩ በመዓትየ ከመ ኢይበውኡ ውስተ ዕረፍትየ (በቁጣዬ ወደ ዕረፍቴ እንደማይገቡ እንደማልሁ) እንዳለው የቀደሙት እስራኤል ለእሑድ አክብሮት አልበቁም (መዝ.94:11) ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ይዞ ያሁኗ ሰንበተ ክርስቲያን ሰንበተ አይሁድ አለመሆኗን በሚከተለው ገልጧል፤ (ዕብ.4:3-11) ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም፣ እንግዲህ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ምያለሁ እንዳለ፤ እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን፤ ስለሰባተኛው ቀን በአንድ ስፍራ፣ እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ ብሏልና፣ በዚህ ስፍራም ደግሞ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ፤ እንግዲህ

እንዳንዶች በዚያ ሳይገቡ ስለቀሩ፥ ቀድሞም የምሥራች የተሰበከላቸው ባለመታዘዝ ምክንያት (ጠንቅ) ስላልገቡ፤ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ፤ በፊት እንደተባለ፥ ይህን ከሚያህል ዘመን በኋላ በዳዊት ሲናገር፥ ዛሬ ብሎ አንድ ቀን እንደገና ይቀጥራል። ኢያሱም አሳርፏቸው ቢሆን ኖሮ ከዚያ በኋላ ስለሌላ ቀን ባልተናገረም ነበር። እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶለታል። ወደ ዕረፍቱ የገባ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ እርሱ ደግሞ ከሥራው ዐርፏልና።

እንግዲህ እንደዚያ ያለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ። በዚህ አንቀጽ ከሰንበተ አይሁድ ሌላ፥ ሌላ ሰንበት እንዳለ፥ በነቢያት እንደተነገረ በአሪት እንደተሰበከ መሳልሶ እንበ ይረዷል። ጌታችን ሰንበተ አይሁድን ቢያከብር ኑሮ በሚከተሉት ዐረፋተ ነገር አይከሰከስም ነበር።

1:1: እንግዲህ ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም ነገር ግን ደግሞ እራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፥ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ አይሁድ ሊገሉት በጣም ይፈልጉ ነበር። (ዮሐ.6:18)

1:2: (ዮሐ.5:8-18) መፃጉዕን ተነሣና አልጋህን ተሸከመህ ሂድ ብሎ በለተ ሰንበት ስለፈወሰው አይሁድ ሰዓሬ ሰንበት ብለውታል፤ ምክንያቱም ኤርምያስ (17:27) የሰንበትን ቀን እንድትቀድሱ፥ በሰንበትም ቀን ሸክምን ተሸክማችሁ በኢየሩሳሌም በሮች እንዳትገቡ ብሎ ነበርና አልጋውን ተሸክሞ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ሰንበትን ሻረ ቢ ሉት እሱም የፈወሰኝ አዘዘኝ ቢላቸው ይህ ሰው ከእግዚአብሔር አይደለም እያሉ አጉረመረሙ።

1:3: በርሻ መካከል ሲያልፉ ደቀ መዛሙርቱ እሸት እያሹ ሲበሉ አይሁድ አይተው፥ እነሆ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ አሉት፥ እሱ ግን ሥርዓተ መቅደስን ጠቅሶ በሰንበት ቢሠሩ በደለኞች አለመሆናቸውን አስረድቷል። (ማቴ.12:1-8)

1:4: የሰንበተ አይሁድ፥ የቀዳሚትን መሻር ቅዱስ ጳውሎስም በመልክታቱ ደጋግሞ አጽድቆታል፤ (ቆላ.2:16:17) እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሲመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና። አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።

2. ይህን ይዘው የቤተ ክርስቲያን አበው እንደሚከተለው ጽፈዋል፤

2:1. ወኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያጽርኡ ተገብሮ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት ከመ አይሁድ= ክርስቲያን እንደ አይሁድ ቅዳሜ ሥራ መፍታት የለባቸውም፤ (ፍትሐ ነገሥት፥ አንቀጽ: 15)

2:2. ውእመቦ እምክርስቲያን ዘይገብሩ ግብረ አይሁድ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት፥ ውእቶሙ ይከውኑ ስዱዳነ እምቅድመ ገጹ ለክርስቶስ (ፍትሐ ነገ አንቀጽ15) በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት= በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት የአይሁድ ሥራ ሲሠሩ የተገኙ ከክርስቶስ ፊት ይሰደዳሉ።

2:3. ወሰዐራ ለሰንበተ አይሁድ ወሠረዐ ህየንቴሃ ዕለተ እሑድ ቅዱስተ= የአይሁድን ሰንበት ሽሮ በእሷ ፈንታ ዕለተ እሑድ ቅድስትን ሠራ፤ (የግዝረት ሰንክሳር ጥር 6)

ቀሌምንጦስም፥ ወእመ መጽአ እግዚእ ለሰንበት፥ ፈደየ ዕዳሃ ለዕለተ ቀዳሚት ሰንበት በእንተ ዘኢንብረ ባቲ ቀዳሚ እመ ፈጠረ ሰማየ ወምድረ= ሰማይና ምድርን በፈጠረ ጊዜ ቅዳሜን ሳይፈጥርባት ስለቀረች ዕዳ ነበረባት፤ ሰው በሆነ ጊዜ ግን የዕውር ዐይን ፈጠረባት፥ አልአዛርን አስነሣባት፥ የ18 ዓመት ጎባጢት አቃናባት ብሏል።

2:4. ወለከሰ ትኩንከ በዓለ ዕለተ እሑድ ባሕቲታ= ለአንተስ ዕለተ እሑድ ብቻ በዓል ትሁንህ፤ (የሐዋርያት ሲኖዶስ)

2:5. ቅዱስ ያሬድም ኢታንሥእ እዳዊከ ወእገሪከ በዕለተ ሰንበት= (በዕለተ ሰንበት እጅህን እግርህን አታንሣ ያለውን የኢሳያስን ቃል ከእሑድ ጾመ ድጓ ላይ ሠራ እንጂ ቅዳሜ ላይ ቅንዋት ነው የሠራ።

2:6. ወኢታብኡ ጾረ ክብደ ውስተ ኆኆዊሃ ለኢየሩሳሌም= ከባድ ሸክም በኢየሩሳሌም ደጃፎች አታግቡ ያለውን የኤርምያስን ቃል ከቅድስት ጾመ ድጓ እሑድ ላይ ሠራ እንጂ ቅዳሜ ላይ አልሠራም።

የሰንበተ አይሁድ ቀዳሚት ሰንበት ሐቁ ይህ ሲሆን አድቬንቲስቶች ለማስመሰል ጌታና ሐዋርያት ቀዳሚትን ያከብሩ ነበር በማለት፤ እያሉ የሚጠቅሷቸውም ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፤

ጌታችንን ሰንበትን ያከብር የነበረ ምን ቀን ነው? ይሉና፥ ሉቃ 4:16ን ይጠቅሳሉ፤ ምንድር ነው እሱ? እስኪ እንየው፤ ወደ አደገበትም ወደ ናዝሬት መጣ፤ እንደልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ፤ ሊያነብም ተነሣ፤ ይህ የተጠቀሰበት ምክንያት እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ የሚለው ዐረፍተ ነገር ነው፤ ይህ ነው የነአባባ

ጥቅስ፤ እኔን ያዋለኝ። አይሁድ ይሰበሰቡ የነበረ ቅዳሚ ቅዳሚ በምኩራብ፥ (እንደዛሬው ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን እሑድ እሑድ) ስለሆነ ነው እንጂ ሰንበትን ለማክበርማ ቢሆን ኖሮ፥ ዕውር እያበራ፥ ድውይ እየፈወሰ፥ እንካሳ እያረታ፥ ለምጣም እያነጻ፥ ሰዓሬ ሰንበት እየተባለ መቼ ይከሰስ ነበር። ይህስ በሰፊው ዝቅ ብሎ ተገልጧል። ቀጥሎም ድንግል ማርያምስ የምታከብረው ምን ቀን ነበር ብለው ሉቃስ 23:56ን ይጠቅሳሉ፤ እሱስ? ቅዳሚን እንደ ትእዛዙ ዐረፉ፤ ይህም ሳያያይዙ የተጠቀሰ ነው። አይሁድ ሰንበትን የሚሽረውን ሁሉ እንደ ለለጸድ በድንጋይ ወግረው ቀጥቅጠቅ ስለሚገሉ፤ ጌታቸውን ክርስቶስን የገደሉ እነሱን ስለማይምሯቸው ሞት ፈርተው ነው እንጂ ሰንበትን ለማክበር አይደለም።

ሐዋርያትስ ምን ቀን ያከብሩት ነበር ይሉና አሁንም (ግብ.ሐ.17:1-2) ጠቅሰው፥ ወደ ተሰሎንቄ መጡ፤ በዚያም የአይሁድ ምኩራብ ነበረ፤ ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነሱ ገባ፤ ሦስት ሰንበት ያህል ከእነሱ ጋር ከመጽሐፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር። አሁንም የሚያስተምሩት ሕዝበ አይሁድን ስለነበረ፥ እሱም የሚገኘው ከምኩራብ ቅዳሚ ስለሆነ፥ ሕዝቡን ፍለጋ እንጂ ሰንበትን ለማክበር አይደለም፤ ቅዱስ ጳውሎስ ቀዳሚትን ቢያከብር ኑሮስ አብያተ ክረስቲያን ሁሉ እሑድ እሑድ እንዲሰበሰቡ አያዝዝም ነበር። (1ቆሮ.16:1-3)

ይህ ምዕራፍ ለአድበንቲስት መግቢያ ተጽፏል፤ ከዚህ የቀረውን ግን በምዕራፍ 23 ያስተካክሏል።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

### የሰባተኛው ቀን አድበቲንስት፤

ሰባተኛውን ቀን ቀዳሚትን የሚያከብሩ አብዛኛውን ጊዜ ስለ ዳግም ምጽአት የሚያወሩ ሰዎች የሰባተኛው ቀን አድበንቲት የሚባሉ ድርጅቶች አሉ። መሥራቹም ዊሊያም ሚለር ይባላል፤ የተመሠረተበት ዘመን የ19ኛው መቶ ዘመን የመጀመሪያው፥ ክፍለ ሀገሩም አሜሪካ ነው። ሚለር ማንበብ የሚወደው ከቅዱሳት መጻሕፍት ነቢያትን ከዚያውም ዳንኤልና ራዕየ ዮሐንስን ነበር። በሁለቱ ነቢያት አገኘሁት ብሎ፥ ክርስቶስ እራሱ የዳግመኛ መምጫዬን ዕለት የሚያውቅ ፍጡር የለም ብሎ የተናገረውን ጥሶ ከክርስቶስ ከራሰህ እኔ አውቃለሁ ብሎ 1843 ትመጣለህ፤ ይመጣል ብሎ ወሰነ፣ በዚህ ጊዜ ችግር አጋጥሞት ነው ብሎ ለሚቀጥለው ዓመት 1844 ብሎ ቀጠረ፤ አሁንም ቀረ፤ እስከ 1849 ጠብቆ ተሳስቻለሁ ብሎ ተናዘዘና ትምህርቱን አቆመ። ተከታዮቹ ግን አሁንም በቅርቡ ይመጣል ለሺህ ዓመት በምድር ላይ ክርስቶስ ድግስ ደግሶ ወዳጆቹን ግብር ያገባል እያሉ ይሰብካሉ።

ከአቶ ሚለር ቀጥላ ትልቋ የአድበንቲስት ሐዋርያ ወይዘሮ አሌኒ ኋይት ናት። እሷም በራእይ አየሁ እያለች ከ50 በላይ መጻሕፍት ጽፋለች። ይሁን እንጂ የአድበንቲስ ነቢያት በቀጠሩት መሠረት ከ7 ጊዜ በላይ፥ ክርስቶስ ቀጠሮውን አክብሮ እስካሁን አልመጣም። ምን ይሁን የዓለም አስተዳዳሪ ነውና ሥራ በዝቶበት ይሆናል ከማለት በስተቀር ምን ይባላል?

የወ/ሮ አሌኒ ጉድ ኋይት መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥለው ይታያሉ፤ ስለሙ ነው እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚከብሩ እነሱ ናቸው። እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገደላ ገድልና ተአምረ ማርያም። የተዋሕዶ ተከታይ ከወንጌል በላይ የሚያከብር ተአምረ ማርያምናን ገድላገድሉን እንደሆነ የአድበንቲስት ተከታዮች ከቅጠላ ቅጠል ይህን ብሉ ያን አትብሉ የሚል ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደሌለ ያውቃል፤ ወይዘሮ አሌኒ ግን ቡና አትጠጡ፥ ሻይ አታፍሉ፥ ሲጃራ አታጤሱ ብላ ስለከለከለች እንደባሕታዊ ወይም ናዝራዊ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተለይተው በብሕትውና መንገድ ሲሄዱ የኖራሉ ለመግቢያ ያህል ይህን ከሰጠን፤ ይህ ጥናት የሚመለከተው የእያንዳንዱን ድርጅት ስለሆነ ወደ እምነታቸው እንመለስ የአድበንቲስት እምነት ወይም አዕማደ ሚስጢር በሚከተሉት 27 አናቅጽ ይጠቃለላል፤ ይህም ከራሳቸው መጽሐፍት ነው የተቀዳው። እነሱም በመዘክረ ጎዳጉ ተጠቅሷል።

<u>አዕማደ ሃይማኖት ዘሳብዕ ዕለት አድቨንቲስት፤</u>

<u>ቅዱሳት መጻሕፍት፤</u>

1. በመንፈስ ቅዱስ ተነሣሥተው የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሰዎች የጻፉአቸውና የተናገሯቸው የእግዚአብሔር ቃላት እንደሆኑ በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት ቅዱሳት መጻሕፍት ያምናሉ።
ቅዱሳት መጻሕፍት የማይሳሳቱ የፈቃዱ መግለጫ ናቸው፤ እንደሆኑ እናምናለን ይላሉ። ይህ ግን በቃል እንጂ በግብር ግን ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ነው ነገሩ። በዚህም ምዕራፍ 23 የተጻፈውን ማየት ይበቃል። 1
(አኀዞች የሚያሳዩት ከመዘክረ ኀዳጉ የተጠቀሰውን የመጀመሪያውን ያአድቨንቲስት መጽሐፍ ቁጥር ነው።)

2. <u>ትምህርተ መለኮት፤</u> አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሦስት አካል አንድ አምላክ አለ። እግዚአብሔር ሕያው፥ ኀያል፥ ሁሉን ዐዋቂ፥ ከሁሉ በላይ የትም ነዋሪ ነው። በራሱ አስተርእዮ ይታወቃል፤ ከፍጠረቱ ሁሉ ለዘለዓለም በግደት፥ አምልኮት፥ አገልግሎት ይገባዋል፤ 2

3. <u>እግዚአብሔር አብ፥</u>
ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር አብ፥ ፈጣሪ፥ ነቅዕ (ምንጭ) ጠባቂ፥ ከፍጥረት ሁሉ በላይ ነው። ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ማሓሪ፥ ቸር፥ ለቁጣ የዘገየ፥ ርሑቀ መዓት፥ ብዙኀ ምሕረት፥ ጽኑዐ ፍቅር ወተአምኖ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ የሚገለጡ ኩነታት የእግዚአብሔር አብም ናቸው። 3

4. <u>እግዚአብሔር ወልድ፤</u>
ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ በመልበሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ። በእሱ ነገሮች ሁሉ ተፈጠሩ፤ የእግዚአብሔር ባሕሪ ተገለጠ፤ የሰው ድኀነት ተፈጸመ፤ በዓለም ይፈርድበታል፤ ዘለዓለም እውነተኛ አምላክ፥ እውነተኛ ሰውም ሆነ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ ከድንግል ማርያም ተወለደ። እንደ ሰው ኖረ፤ ተፈተነ፤ ግን በፍጹም የእግዚአብሔርን ጽድቅና ፍቅር አሳየ። በተአምራቱ የእግዚአብሔርን ኀይል ገለጠ፤ የእግዚአብሔር መሲሕ ይመጣል ተብሎ የተነገረው እሱም እንደሆነ ተረጋገጠ። በፈቃዱ በመስቀል ላይ ስለ ኀጢአታችን በእኛ ፈንታ ታመመ፥ ሞተ፤ ከሙታን ተነሣ፤ ስለኛ በሰማይ መቅደስ ለማገልገል ወደ ሰማይ ዐረገ። ሁሉን ነገር ለማስተካከል፥ ለሕዝቡም መጨረሻ ድኅነት በክብር ዳግመኛ ይመጣል። 4

5. <u>እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤</u>
ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ወልድ ጋራ በፍጥረት፥ በሥጋዌ፥ በድኅነት ይሠራ ነበር፤ ሠርቷል። የክርስቶስን ሕይወት በኀይል ሞላ፥ የሰውን ዘር ያስረዳል፥ ይሰባል፥ የሚመለሱለትንም ያድሳል፥ ወደ እግዚአብሔር መልክአ ይለውጣል። ከአብና ከወልድ ከልጆቹ ጋራ እንዲሆን ተልኮ፥ መንፈሳዊ ስጦታን ለቤተ ክርስቲያን ያድላል። ለክርስቶስ እንድትመሰክር ኀይል ይሰጣል፤ ያሠለጥናል፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማዘከር ወደ እውነት ሁሉን ይመራል። 5

6. <u>ትምህርተ ፍጥረት፤</u>
የሁሉም ነገር ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው፤ እውነተኛውን የአፈጣጠር ዝርዝር በቅዱሳት መጻሕፍት ገልጧል። በስድስት ቀን ጌታ ሰማይና ምድርን፥ በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ፈጠረና፥ በሰባተኛው ቀን ከመጀመሪያው ሳምንት ሥራው ዐረፈ። በዚህም የፍጥረት ሥራውን ፈጸመበት፤ ዘለዓለማዊ ማስታወሻ ሰንበትን መሠረተ። በፍጥረት ሁሉ መደምደሚያ የመጀመሪያዎች ወንድና ሴት በአርአያ እግዚአብሔር ተፈጠሩ። ዓለም በተፈጸመ ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጥ በጣም ጥሩ ነበር። 6

7. <u>ተፈጥሮ አዳም ወሔዋን፤</u>
እያንዳንዳቸው ከማሰብና ከመሥራት ሥልጣን ጋር፥ ወንድና ሴት በአርአያ እግዚአብሔር ተፈጠሩ። ምንም ነጻ ሁነው ቢፈጠሩም ለሕይወትና ለስትንፋስ ከእግዚአብሔር የማይነጠል፥ የማይለይ የአካል፥ የአእምሮ፥ የመንፈስ አንድነት ነበራቸው፤ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አምላክን እንታዘዝም ባሉ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጥገኝነታቸው ተገነጠሉ፤ ከአምላክ በታች ከትልቁ ቦታቸውም ወረዱ። አርአያ እግዚአብሔርነትም ከእነሱ ተወግዶ የሞት ተገዥዎች ሆኑ። ይህን የወደቀ ባሕርይንና ተከታዩን ትውልዶቻቸው ይከፋፈላሉ። በደካማነትና በክፋት ዝንባሌ ይወለዳሉ። እግዚአብሔር ግን ዓለሙን በክርስቶስ ከራሱ ጋራ አስታረቀው፤ በመንፈሱም መለሰው። ለስብሐተ እግዚአብሔር ተፈጥረው እሱንም እንዲወዱ እርስ በርሳቸውም እንዲፋቀሩ ይጠራሉ። ለአካባቢያቸውም እንዲጠነቀቁ ይመክራሉ። 7

8. <u>በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ያለው ትልቁ ክርክር፤</u>
በክርስቶስና በሰይጣን መካከል ስለ እግዚአብሔር ጠባይ፥ ሕግ፥ በመላው ዓለም ላይ ስላለው ልዑላዊነት የሰው ዘር ሁሉ በትልቁ ክርክር ተወጥሮ ይኖራል። ይህ ጠብ የተጀመረው ለመምረጥ ችሎታ ተሰጥቶት የተፈጠረ ፍጡር እራሱን አግንኖ፥ የእግዚአብሔር ባላጋራ ሁኖ ከመላእክትም ብዙዎቹ ወደ ሽፍትነት በመራ ጊዜ ነው። በዚህ ዓለምም በመፃ አስገብቶ አዳምንና ሔዋንን አሳተ። ከዚያ ወዲህ ይህ ዓለም የትግል ሜዳ ሆነ፤ ክርስቶስም ከዚህ ተጋድሎ ሕዝቡን ለመርዳት፥ እንዲመሩ፥ እንዲጠብቁ፥ እንዲከላከሉ፥ እንዲረዱ መንፈስ ቅዱስንና መላእክትን ይልካል። 8

9. <u>ሕግግተ ክርስቶስ፤</u>
ክርስቶስ በሕይወቱ ለእግዚአብሔር ፍቃድ ፍጹም በመታዘዝ፥ ታሞ፥ ሙቶ፥ ተነሥቶ፥ በሃይማኖት የተቀበሉት ሁሉ ዘለዓለማዊ ሕይወት ያገኙ ዘንድ ለሰው በደል ማስተሰርያ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አቅርቧል። ይህ ፍጹም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ሕግ ቀጥተኛነትንና ቸርነት ከሷል። የክርስቶስ ሞት ቤዛ፥ መስተስርዩ አስታራቂና አዳኝ ነው። የክርስቶስ ትንሣኤ በኩይ ኀይላት ላይ ማሸነፍን፥ ስርየትን ለተቀበሉ ሁሉ ደግሞ በኀጢአትና በሞት ላይ መጨረሻው ድል ማድረግ እንደሆነ ያረጋግጣል። በሰማይና በምድር ያለ ጉልበት ሁሉ የሚሰግድለት የኢየሱስ ክትስቶስን ጌትነት የገልጣል። 9

10. <u>ፍጻሜ በሌለውና በጽኑዕ ፍቅር እግዚአብሔር ክርስቶስ ሆነ፤</u>
ወሰን በሌለው ፍቅር ምክንያት እግዚአብሔር ክርስቶስ ሆነ፤ አምላክ ሰው ሆነ፤ እኛ በእሱ የእግዚአብሔር ጻድቃን እንሆን ዘንድ እሱ ኀጢአት ሆነ፤ ኃጥእ ተባለ፤ ከኃጥአን ተቆጠረ። በመንፈስ ቅዱስ ተመርተን፥ ችግራችንን እንረዳለን፤ ኀጢአታችንን እናውቃለን፤ ክበደላችን እንመለሳለን፤ ኢየሱስ፡ ጌታ፥ መሲሕ፥ ቤዛ፥ አርአያ እንደሆነ እንቀበላለን። በክርስቶስ ጸድቀናል፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ሁነን ከኀጢአት ባርነር ነጻ ወጥተናል። በመንፈስ እንደገና የተወለድን እንቀደሳለን፤ መንፈስ አንኅላችንን ያድሳል፤ የእግዚአብሔርን የፍቅር ሕግ በልቦናችን ይጽፋል። መንፈስ ቅዱስ በሕይወት እንድንኖር ኀይል ያሳድርብናል። በእሱ ከኖርን የመለኮት ጠባይ ተካፋዮች እንሆናለን፤ አሁንና በፍርድም ጊዜ ለድኅነታችን ርግጠኞች ነን። 10

11. <u>የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፤</u>

ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝና ጌታ ነው ብለው የሚያምኑ ማኅበር ናት። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ከብሉይ ኪዳን ቀጥለን እኛም ከዓለም ተጠርተናል። በቃሉ ለአምልኮት ለአገልግሎት፥ የጌታን እራት ለማክበር፥ የሰውን ዘር ሁሉ ለማገልገል፥ በመላው ዓለም ወንጌልን ለመስበክ አንድነት እንሰበሰባለን። ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንዋን የምታገኘው ሥጋ ከለበሰው ከእግዚአብሔር ቃል ከኢየሱስ ክርስቶስና ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው። ቤተ ክርስቲያን በጸጋ የተወለደች የእግዚአብሔር ቤተ ሰብእ ናት። እባሎችዋም በሐዲስ ኪዳን መሠረት ይኖራሉ። ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ እሱ ራሱ እለቃዋ የሆነ የእምነት ማኅበር የክርስቶስ አባል ናት። ቤተ ክርስቲያን ላነጻትና ለቀደሳት ክርስቶስ ለሞተላት ሙሽራ ናት። በድል አድራጊነት የከበረች አድርጎ ለራሱ ያቀርባታል። በዘመናት የሚኖሩት ምእመናን ሁሉ በደሙ የተበጃቸው ያለ እንከን ያለ ንስሓ ንጹሕ ናቸው። 11

12. <u>የዓለም ቤተ ክርስቲያን፤</u>

የዓለም ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ካመኑ ምእመናን ሁሉ የተሰበሰበች ናት፤ ዐመፃ በሚበዛበት በኋላ ዘመን ግን የእግዚአብሔርን ትዛዛትና የኢየሱስን እምነት የሚጠብቅ ትርፍ ይጠራል። ይህ ትርፍ የፍርድ ሰዓት መድረሱን ይናገራል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ያውጃል። ይህ ዐዋጅ በራእየ ዮሐንስም 14 በተጻፉት በሦስት መላእክት ይመለሳል። እማኝ ሁሉ በዚህ በመላው ዓለም ላይ ምስክርነት እንዲሳተፍ ይጠራል። 12

13. <u>የክርስቶስ አካል አንድነት፤</u>

ቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ፥ ከነገድ፥ ከጎሳ፥ ከአባት፥ ከቋንቋ፥ የተጠሩ እባላት ያሉባት አንድ አካል ናት። እኛ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነን፤ የዘር፥ የባህል፥ የትምህርት፥ የሥልጣኔ፥ የነገድ፥ የብሔር፥ ብሔረ ሰብእ፥ የከፍተኛና ዝቅተኛ፥ የሀብታምና የድኃ ልዩነት በመካከላችን የለም። ሁላችንም በአንድ መንፈስ፥ እርስ በርሳችንና ከእሱ ጋራ ባስተሳለረን በክርስቶስ እኩል ነን። ያለምንም አድልዎና ልዩነት የምናገለግልና የምንገለገል ነን። በኢየሱስ ክርስቶስ እስተርእዮና በቅዱሳት መጻሕፍት አንድ እምነትና ተስፋ እንካፈላለን። አንድነታችን የሚመነጨው በጸጋ ከወለደን ከሦስቱ አካል አንድ አምላክ ነው። 13

14. <u>ጥምቀት፤</u>
በጥምቀት ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ታምነን ከኀጢአት መሞታችንና በአዲስ ሕይወት ለመጓዝ መወሰናችንን እንመሰክራለን። እንዲህ ክርስቶስ ጌታና መድኀኒታችን መሆኑን አረጋግጠን ሕዝቡን ሁነን፥ የቤተ ክርስቲያኑ አባል ሁነን እንቀበላለን። ጥምቀት ከክርስቶስ ጋራ አንድ የመሆናችን አምሳል ነው። በዚህም የኀጢአትን ይቅርታና መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን። ሥርዓቱ የሚፈጸመውም ከውኃ በመጥለምና አምነትን በኢየሱስ ክርስቶስ በማረጋገጥ ነው። ከጥምቀት የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ይቀድማል። 14

15. <u>የጌታ ራት፤</u> (ሥጋሁ ወደሙ፥ ቁርባን)
የጌታ ራት፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አምሳል እሱ ጌታችንና መድኀኒታችን እንደሆነ አምነን የምንካፈልበት ነው። በዚህ ተግባር ክርስቶስ ሕዝቡን ለማገናኘትና ለማጽናት የሚገኝበት ነው። በተካፈልነ ቁጥር ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ በደስታ የጌታን ሞት እንሰብካለን። ለጌታ ራት መዘጋጀት እራስን መመርመር፥ ንስሓ መግባት፥ መናዘዝ ያስፈስጋል። ጌታ በሕጽበተ እግር በአዲስ ንጹሕ ሁኑ ለማሰት፥ እርስ በርስ ለመረዳዳት ፈቃደኛ መሆንን ለመግለጥ፥ በክርስቶስ ትሕትና ልቡናችንን በፍቅር አንድ እንድናደርግ አዝዞናል። የቁርባንን አገለግሎት ለሚያምኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ክፍትና ግልጽ ነው። 15

16. <u>መንፈሳዊያን አገልግሎቶችና ተሰጥዎች፤</u>
እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን አባል ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግልበትና የሰውን ዘር የሚረዳበት መንፈሳዊ ተሰጥዖ ያስያል። መንፈስ ቅዱስ እንደፈለገ ለሁሉም አባል የችሎታና የአገልግሎት ተሰጥዎችን ያድላል። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህ ተሰጥዎዎች አገልግሎት፥ ሃይማኖት፥ አምነት፥ ትንቢት፥ ሀብተ ፈውስ፥ ማስተማር፥ ማስተዳደር፥ ማስታረቅ፥ ራስን መሠዋት፥ ፍቅር፥ ሌሎችን ለመርዳት ጥበዓት ወዘተ. የመሳሰሉትን ያካትታል። ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ተሰጥዎች ከሠራች ከእኩይ ተጽዕኖና ከክሕደት ትጠብቃለች። 16

17. <u>ሀብተ ትንቢት፤</u>
ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ፀብተ ትንቢት ነው። ይህም በወ/ሮ ኤሌኒ ኋይት እንደታየው የትሩፍ ቤተ ክርስቲያን ምልክት ነው። 17

18. <u>የክርስቲያን ሕይወት ትምህርት፤</u> (የእግዚአብሔር ሕግ) ታላላቆች የእግዚአብሔር ሕግ መርሖች በዐሠርቱ ቃላት ተከተው በክርስቶስ ምሳሌነት ተፈጽመዋል። ስለሰው ጠባይ፥ አመል፥ ግንኙነት፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር፥ ፈቃድ፥ ሐሳብ አጠቃሰው ይገልጣሉ። በሰው ሁሉ ላይ የመፈጸም ግዴታ አላቸው። በመንፈስ ቅዱስ ወኪልነት ኀጢአትን ጠቁመው የመድኀኒትን ግዴታ ያነቃሉ። ድኅነት በጸጋ እንጂ በሥራ አይደለም። ፍሬው ግን ለዐሠርቱ ቃላት መታዘዝ ነው። 18

19. <u>ሰንበት፤</u>
ደጉ ፈጣሪ ከሰባት ቀን ፈጠራ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈና ዐርፎ ለፍጥረት ማስታወሻ በመላው ሕዝብ ሰንበትን ሠራ። የማይለወጠው አራተኛው የእግዚአብሔር ትእዛዝ በባተኛው ቀን ሰንበትን የዕረፍት ቀን ይሁን ብሎ ያዝዛል። ይህም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ጋር ይስማማል። ሰንበት እግዜርና ሰው የሚገናኙባት የደስታ ቀን ናት። ሰንበት በሕዝብና በእግዚአብሔር መካከል የምትኖር ዘለዓለማዊት የኪዳን ምልክት ናት። ይህን ቅዱስ ጊዜ በደስታ ከማታ እስከ ማታ፥ ከዕርበተ ፀሐይ እስከ ዕርበተ ፀሐይ ማክበር የእግዚአብሔርን የፍጥረትና የአድኅኖት ሥራ ማክበር ነው። 19

20. <u>መጋቢነት፤</u> (አስተዳዳሪነት)
ከጊዜ፥ ከሀብት፥ ከዕድል፥ ከችሎታ፥ ከክብረት፥ ከመሬት ቡራኬና ውጤት ጋራ አደራ የተባልን የእግዚአብሔር መጋቢዎች ነን። ለደምበኛ አጠቃቀማችን በእሱ ዘንድ ተጠያቂዎች ነን። የእግዚአብሔርን ባለቤትነት በተአምኖ እሱንና መሰሎቻችንን ለማገልገል እናረጋግጣለን። ዐሥራት በማውጣትና ቀዳምያት በማውጣት ቤተ ክርስቲያንን በመደገፍና ወንጌልን በማስፋፋት ጌትነቱን እንገልጣለን። መጋቢነት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ዕድል ነው። 20

21. <u>ክርስቲያናዊ ምግባር፤</u>
በሰማያዊ መርሖች መሠረት የምናስብ፥ የምናስላስል፥ የምናወጣ የምናወርድ እንድንሆን ተጠርተናል። መንፈስ የጌታን ባሕርይ፥ ጤና፥ ደስታ፥ ሕይወት እንዲፈጥርብን ራሳችንን ማዘጋጀት አለብን። ይህም ደስታችንና ጨዋታችን ከፍተኛውን የክርስቲያን ጣዕምና ውበት መከተል አለበት ማለት ነው። ምንም የጊዜንና የባህልን ልዩነት ብናውቅም፥ ልብሶቻችን የጸጥታንና የጨዋን መንፈስ የሚገልጡ እንጂ ብልጭልጭና

ብርቅርቅ መሆን የለባቸውም። ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሆነ ልንጠነቀቅለት ይገባል። ከበቂ ልምምድና ዕረፍት ጋራ በቅዱሳት መጻሕፍት ንጹሓን ተብለው የተወሰኑትን ጤናማ ምግቦች መመገብ አለብን። እርኩሳን ከተባሉትም መራቅ አለብን። የሚያሰክሩ መጠጦች፥ ሲጃራ፥ ወሰን የለሽ መድኀኒት፥ ለሰውነታችን ጎጅዎች ስለሆኑ ከነዚህ መራቅ አለብን። በዚህ ፈንታ ወደ ክርስቶስ ሥነ ሥርዓት በሚመራ ሐሳብ መጠመድ አለብን። 21

22. <u>ጋብቻና ቤተ ሰብእ፤</u>

ጋብቻ በመለኮት በገነት ተመሠረተ፤ ተመሥርቶ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሕይወት ሙሉ ተዋሕዶ ፍቅራዊ አንድነት መሆኑ ተረጋገጠ። ጋብቻ ለክርስቲያን ከእግዚአብሔርና ከእሚኑ ጋራ የሚተሳሰርበት ቃል ኪዳን ነው። ስለዚህ ተጋቢዎቹ የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መሆን አለባቸው። የጋራ ፍቅር፥ መከባበር፥ መተፋፈር ይህን ዝምድና በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል የሚበይዱ ሙሻ ዙሮች ናቸው። ስለ ፍች ጌታችን፥ ከማመንዘር በቀር ምሽቱን ፈቶ ሌላ የሚያገባ አመነዘረ ብሎ አስተምሯል። እግዚአብሔር ቤተ ሰብእን ይባርካል፤ እርስ በርሳቸው ተረዳድተው ወደ ፍጹምነት እንዲደርሱ ይፈቅዳል። ወላጆች ልጆቻቸውን እግዚአብሔርን እንዲወዱትና እንዲታዘዙለት አድርገው ማሳደግ አለባቸው። በምሳሌአቸውና በቃላቸው ክርስቶስ መፍቀሬ ሰብእ፥ (ሰው ወዳጅ) በዓለ ሥርዓት፥ ዘለዓለም ለሰላሳ፥ ተንከባካቢ፥ የእግዚአብሔር አካል ቤተ ሰብእ እንዲሆኑ የሚፈልጋቸው መሆኑን ማስተማር አለባቸው። 22

23. <u>የክርስቶስ ሥራ በሰማይ መቅደስ፤</u>

በሰማይ ሰው ሳይሆን ጌታ ራሱ የሠራት እውነተኛዋ ድንኳን መቅደስ አለች። አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ስዘለዓለም ለኃጢአት ማስተስርያ ያቀረበውን የመስዋዕት ጥቅም እያቀረበ፥ በሰው ልጅ ፈንታ ክርስቶስ በውስዊ ያገለግላል፤ የኛ ትልቅ ሊቀ ካህናት ሁኖ የማግለዱን ሥራ የጀመረውም በዕርገቱ ጊዜ ነው። በ1844 ዓ.ም. በ2300 ቀናት በትንቢቱ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ሁለተኛውን የተልእኮ ተግባር ጀመረ። 23

24. <u>ዳግም ምጽአት (ሁለተኛው ምጽአት)፤</u>

ሁለተኛው የክርስቶስ ምጽአት የቤተ ክርስቲያን ቡራኬ ተስፋ፥ የወንጌል አፍላ ነው። የጌታችን ዳግም መምጣት፤ ቃል ስቃል፥ አካላዊ፥ የሚታይ

መላ ዓለማዊ ይሆናል። ሲመለስ ጻድቃን ተነሥተው ከሚኖሩት ቅዱሳት ጋራ በአንድነት ወደ ሰማይ ያርጋሉ፤ ኃጣአን ግን ይሞታሉ። ትንቢቱ ሁሉና የዘመኑ ሁናቴ የክርስቶስ መምጣት እርግጥ እንደሆነ ያሳያሉ። 24

25. <u>ሞትና ትንሣኤ፤</u>

የኀጢአት ዋጋ ሞት ነው፤ ብቻውን ሕያው እግዚአብሔር ግን ለዳኑት የዘለዓለም ሕይወት ያድላል። እስከዚያው የሞቱ ሁሉ አይሰሙም። የሕይወታችን ክርስቶስ ሲመጣ የተነሡት ጻድቃንና ያሉት ቅዱሳን በክብር ተነሥተው ከጌታቸው ጋራ ይገናኛሉ። ሁለተኛው ትንሣኤ፤ የጻድቃን ትንሣኤ ከ1000 ዓመት በኋላ ይሆናል። 25

26. <u>ከምጽአት በፊት የዘመኑ ብፁዓንና የኀጢአት ፍጻሜ፤</u>

ክርስቶስ ከጻድቃኑ ጋራ ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው ትንሣኤ መካከል ለሺህ ዓመት ይነግሣል። በዚህ ጊዜ ክፉዎች ይፈረድባቸዋል፤ መሬት ፈጽሞ ባዶ ትሆናለች፣ በሰይጣንና ሠራዊቱ ተወራ እስትንፋስ ያለው የሰው ዘር አይታይባትም። በመጨረሻው ክርስቶስ ከቅዱሳኑና ከቅድስት ከተማው ጋራ ከሰማይ ወደ ምድር ይወርዳል። ዓለም ከኀጢአተኞች ለዘለዓለም እንዲህ ሁና ነጻ ትወጣለች። 26

27. <u>ሐዲሷ መሬት፤</u>

ጽድቅ በሚሰፍንባት በሐዲሷ መሬት፣ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ቤት፣ ዘለዓለማዊ ሕይወት፣ ፍቅር፣ ደስታ፣ በፊቱ ትምህርት፣ መልካም አካባቢ ለዳኑት ያዘጋጃል። በዚህ እግዚአብሔር ራሱ ከሕዝብ ጋር ይኖራል፤ ሥቃይና ሞት ያልፉሉ። ትልቁ ጥል ያልቃል፤ ኀጢአትም ከዚያ ወዲያ አይሠራም። ነፍስ ያለውም የሌለውም እግዚአብሔር ፍቅር ነው ይላል፤ እሱም ለዘለዓለም ይነግሣል። 27

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት

### የአድበንቲስቶች ኢክርስቲያናዊ ትምህርት፤

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አርእስት ወይም አዕማደ እምነት እንዲሁ ሲያዩዋቸው ክርስቲያናዊ ይዘት ያላቸው ይመስላሉ፤ በመዘክረ ጎዳት በተጠቀሱት መጻሕፍት እንዳተቱት ግን አብዛኞቹ ክርስቲያናዊ ይዘት የላቸውም።

በሃይማኖት የጀሆባ ምስክሮችን፥ በምግባር አሪታውያንን ይቀርባሉ። ከወንጌል አሪትን፤ ከክርስቶስ ሙሴን ያከብራሉ። ስለዚህ እነዚህ አሪታውያንና የጀሆባ ምስክሮች አርዮሳውያን፥ ሰላሞች፥ በጉርብትና እንጂ በሃይማኖት ከክርስቲያን ጋራ ተዋሕደው፥ አብረው አይኖሩም። የሰላሙ የታወቀ የለየለት ስለሆነ አያነጋግርም። የጀሆባውን ግን በቦታው እናየዋለን። እነዚህማ መጽሐፍ ቅዱስን ይሰብካሉ፥ ክርስቶስን አምነው ተቀብለው ያስተምራሉ፥ ለምን ክርስቲያን አይደሉም ትላቸዋለህ? ለሚለኝ ጠያቂ መልሱ የሚከተለው ነው፤

1. ከዐሠርቱ ቃላት አንዱ በሐሰት አትመስክር ነው፤ ከዐሠርቱ ቃላት በአንዱ የበደለ ሁሉንም ሽረ ተብሎ ተነግሯል። (ያዕ.2:10) እነሱ ግን ይህን ጥሰው የሚከተለውን በሐሰት ያስተምራሉ፤

ሀ/ <u>በመጀመሪያ በሚወጹት በራቧ በአሪት ላይ፥</u> የክርስቲያን ምግባራቸው የሚመራው አሪት ይዛው በሞተች በሥርዐተ ረበናት ነው። እሱም ከዚህ በፊት በተጠቀሰው መጽሐፍ ከገጽ 280-289 ተገልጧል። ይህም የአዳምና ሔዋን ምግብ ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረ ቅጠላ ቅጠልና ፍራፍሬ ብቻ ስለሆነ በዚሁ ይብቃን የሚል ነው። ይህም ሐሰት ነው፤ ከጥፋት ውሃ በፊትም ሥጋ ይበላ ነበር፤ አቤል የበግ ጠባቂ ነበረ ይላል ቅዱስ መጽሐፍ (ዘፍ.4:1-5፤) የማይበላውን እንዴት ይጠብቃል? ዝቅ ብሎም ቃኤልና አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረባቸውን ሲገልጥ፥ አቤል ደግሞ ከበጎቹ በኩራትና ከስቡ አቀረበ (4) ይላል። እሱ የማይበላውን ለአምላኩ የሚሠዋ ማን ነው? ዝቅ ብሎ 7:2-4 ላይ ደግሞ ንጹሑን ርኩሱን ለይቶ፥ ከንጹሑ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነው እንስሳም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት... ይዘህ ግባ ብሎ ከኖህ በፊት ሥጋ መበላቱን ግልጥ አድርጎ ይናገራል። ይህ ጥቅስ ለአድበንቲስት ቅዱስ መጽሐፍ፥ ማጭበርበሪያ እንጂ መመሪያ እንዳልሆነ ገልጦ ይናገራል።

ለ/ ቀዳሚትን የማያከብር ሁሉ ክርስቲያን አይደለም ይላሉ፤ ለዚህም የዓለም መድኀኒት፥ የቤተ ክርስቲያን መሥራች፥ የእግዚአብሔር

አብ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ ዓለም ሳለ ያከብራት ነበር እያሉ የፈጠራ ወሬ ይነዛሉ፤ በሥጋ ከመወለዱ በፊት በመለኮቱ ከአባቱ ጋራ የሠራው ለሕገ ወንጌል በግልጥ እሱ ራሱ ካላዘዘው በቀር ትእዛዝ ነው፣ ሕግ ነው ተብሎ አይጠቀስም። እነሱ ግን ሰንበትን አከብሯል፣ አክብሯትም ብሎ አስተምሯል፣ አዝዟል ይላሉ። ይህ ግን በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በወንጌል በአሉታ እንጂ በአውንታ አይገኝም። ጌታን በእየጊዜው አይሁድ ይከሱት የነበረ፤ ሰንበትን ይሽራል፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው አይደለም እያሉ ነው። እነሱ ግን ጌታንም ሐዋርያትንም ሰንበትን ያከብራሉ ብለው የሚጠቅሱት አይሁድ ከተሰበሰቡበት ለማግኘት ቅዳሜ ቅዳሜ ቤተ መቅደስና ምኩራብ እየሄዱ ማስተማራቸውን ነው። ሰው በሚሰበሰብበት ቀንና ቦታ እየሄዱ ማስተማር አምልኮት መፈጸም፣ ዕለቱንም ማክበር፣ ሕግ መሥራት ከሆነ፣ ቅዱስ ጳውሎስም አቴና፣ አርዮስፓጎስ እየሄደ ይሰብክ ነበረና የግሪክን አምላክ መቀበሉ ነው። ወይም ለእነሱ ሥርዓት ሠራ ማለት ይሆናል?

የክርስቶስንና የሐዋርያትን ሰንበት አክባሪነት ለማስረዳት ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 252-259 አትተዋል። ለሁሉም ከዚህ በታች ወንጌላዊና ክርስቲያናዊ መልሶች እንሰጣለን።

ሐ/ ጌታ ዐሠርቱ ቃላትን ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም ብሎ (ማቴ.5:17-19) ሲናገር፣ ተናግሮ ሌሎችን ሲያጠብቅ ቀዳሚትን ሳያነሣት አልፏል፤ በዚህም በዝምታ መዝለሉ ነው። <u>ጥቅሱም፤</u> እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ፤ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከእነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር፣ ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል። የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል ብሎ አጥብቆ ከተናገረ በኋላ አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትፍታ፤ አትማል፤ ዐይን ስለ ዐይንን፤ ጠላትህን ውደድን እያጠበቀ እሱ እንደሚፈልገው ተንትኖ አስተምሯል (ማቴ.5:21-48) ከዚህ ላይ ቀዳሚትን ቢፈልጋት ኑሮ መናገር ይችል ነበር። ሌሎችንግ፣ የሚፈልጓቸውን አትግደልን፤ አታመንዝርን፤ አትፍታን፤ አትማልን፤

ጠላትህን ውደድን አጥብቀው ሂዱል፤ (ማቴ.5.21-48) ከዚህ የቀረውን ከሁሉም ሁሉን ይወቅ ገ.209-212 ይመለከቷል። አይሁድ ቅዳሜ ቅዳሜ በምኩራብ ወይም በቤተ መቅደስ ስለሚሰበሰቡ፥ ሕዝቡን ለማግኘት ቤተ መቅደስ እሱም ሆነ ሐዋርያት ይሄዱ ነበር እንጂ፥ ለአምልኮት ወይም ለአገልግሎት ቢሄዱ ኑሮ ሰንበትን አክብሩ ብለው ያስተምሩ ነበር። ግን ዓላማቸው ሕዝቡን ለመሰብክ እንጂ ሰንበትን ለማክበር ስላልሆነ አንድ ቀንም ብለው ስለሰንበት ተናግረው አያውቁም። ከዚህ የቀረውን በዐሠርቱ ቃላት ምዕራፍ 21 ይመለከቷል።

<u>ቀዳሚትና ሐዋርያት፤</u>

ለማጭበርበሪያ ጌታ በሞተ ጊዜ ሰንበትን ለማክበር ዐርፈው ተቀምጠው ውለዋል ብለው ሉቃስን ይጠቅሳሉ፤ ሐዋርያት በዓል ሻራችሁ ብለው እንደ ሰለጸድ ይገሉናል ብለው እንጂ ሰንበትን ለማክበር እንዳልሆነ፥ ሁለት ጊዜ ጌታ ሲገለጥላቸው፥ እሑድ እሑድ ቤት ዘግተው ነው የነበረ፤ ጌታም የተገለጠላቸው በተዘጋ ቤት ገብቶ ነው፤ አሁንሳ ቅዳሜን ነው ወይንስ እሑድን ሲያከብሩ ቤት ዘግተው ይውሉ የነበሩ? (ዮሐ.20:19፤26፤) ነጻ ቢሆኑና ሰንበትን ለማክበር ቢችሉ ኑሮ ቤተ መቅደስ ሂደው ያከብሯት ነበር። እሽ ቅዳሜስ ይሁን እሑድን ከቤት ተዘግተው ለምን ዋሉ? በዚህም ሁለቱንም ቀን ከቤት ያዋለችው ጰራቅሊጦስ መጥቶ እስኪያላቅቃቸው ድረስ አጅሬ ፍርሃት መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ ላይ ወንጌሉ አይሁድን ስለፈሩ ተዘግተው ነበር ስለሚል ሊያመልኩ ጸጥ ብለው ዋሉ ማለትም ያላዋቂ ነመን ጥቅስ ነው ብለን ከማለፍ በቀር ምን ይባላል?

ሐዋርያት ግን ለራሳቸው ተግባር መሰብሰብ የጀመሩ ከትንሣኤ እሑድ ጀምሮ መሆኑን የጌታ ሁለት ጊዜ በዚያች ቀን መገለጡና ቅዱስ ጳውሎስም በ1ቆሮ.16:1: በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ስትሰበሰቡ ማለት ለክርስትና አገልግሎት ከትንሣኤ ጀምሮ እሑድ መከበሩን ያሳያል። በተቀረ አድቨንቲስቶች እንደሚሉት በሮም ጳጳስ ትእዛዝ በአራተኛው ዘመን ተጀምሮ ቢሆን ኑሮ ምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያን አይቀበሉትም ነበር። እንዲህ ያለ ታሪክ ከመቶ ዓመት ወዲህ ከግልገሏ ዲቃላ ያድቨንቲስት ድርጅት ከወ/ሮ ኤሌኒ ጉድ ኋይት ወዲህ በቀር የትም አይገኝም። የሮም ቤተ ክርስቲያን የተመረጠችውም ጠላት ለማቃለል ይመስላል።

መ/ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በእርሻ መካከል አለፈ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተራቡና እሸት እየቀጠፉ ይበሉ ጀመር፤ ፈሪሳውያንም ዐይተው፥ እነሆ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ አሉት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ ዳዊትና ከርሱ ጋራ የነበሩት በተራቡ ጊዜ፥ እሱ ያደረገውን፥ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንደገባ፥ ለካህናቱ ብቻ እንጂ ለእሱና ከእሉ ጋራ ለነበሩት ሊበሉት ያልተፈቀደውን የመሥዋዕቱን ኅብስት እንደበላ፤ አላነበባችሁምን? ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ከመቅደስ የሚበልጥ ከዚህ አለ። ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኀጢአት የሌለባቸውን ባልኰነናችሁም ነበር። የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና። በዚህም በሰንበት የሠሩትን ኀጢአት የለባቸውም በማለቱ በሰንበት መሥራት ኀጢአት አለመሆኑን ተናግሮ የቀዳሚትን ክብር በእርቱዕ ሽሯል። (ማቴ.12:1-8 ማር.2:23-28)

ሠ/ ከዚያም አልፎ ወደ ምኩራባቸው ገባ፤ እነሆም እጁ የሰለለች ሰው ነበረ፤ ይከሱትም ዘንድ በሰንበት መፈወስ ተፈቅዷልን ብለው ጠየቁት። እሱ ግን ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበት በጉድጓድ ቢወድቅበት ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው? እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንዴት አይበልጥም? ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዷል አላቸው። ከዚያም በኋላ ሰውየውን እጅህን ዘርጋ አለው። ዘረጋትም እንደ ሁለተኛዋም ደኅና ሆነች። ፈሪሳውያን ግን ወጥተው እንዴት አድርገው እንደሚያጠፉት ተማከሩበት። ስለ እዳነ ሳይሆን ሰንበትን (ቀዳሚትን) ስለሻረ። በስንበት መልካም ሥራ መሥራት ተፈቅዷል በማለቱም እርሻንና ንግድን ሁሉ መፍቀዱ ነው። ማቴ.12:9-15 (ማር.3:1-6፤ ሉቃ.6:1-11)

ረ/ ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፤ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል እንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት። በእነዚህ ውስጥ የውሃውን መመላለስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ይገኙ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውሃውን ያናውጥ ነበርና፥ ከውሃው መናወጥ በኋላ መጀመሪያ የገባ ከማናቸውም ካለበት ደዌ ይድን ነበር። በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ። ኢየሱስም ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ እስካሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ

ነበረ ዐውቆ፥ ልትድን ትወዳለህን? አለው። ድውዩም ጌታ ሆይ! ውኃው በተናወጠ ጊዜ፤ በመጠመቂያይቱ ወስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም፤ ነገር ግን እኔ ስወጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው። ወዲያውኑ ሰውዬው ዳነ፡ አልጋውን ተሸክሞ ሄደ። ያን ቀን ሰንበት ነበር። ስለዚህ አይሁድ የተፈወሰውን ሰው፥ ሰንበት ነው አልጋህን ልትሸከም አልተፈቀደልህም አሉት። እሱም ያዳነኝ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ አላቸው። እነሱም ይህን ያለው ማን ነው? ብለው ጠየቁት። ዳሩ ግን በዚያ ስፍራ ብዙ ሕዝብ ነበረና ኢየሱስም ርቆ ስለነበረ፥ የተፈወሰው ማን እንደሆነ አላወቀም። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና፥ እነሆ! ድንሃል፥ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኀጢአት አትሥራ አለው። ሰውየውም ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደሆነ ለአይሁድ ነገራቸው። ስለዚህ በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር። ሊገሉትም ይፈልጉ ነበር። ኢየሱስ ግን አባቴ እስከዛሬ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው። እንግዲህ በሰንበት ስለሻረ ብቻ ሳይሆን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላለ ጭምር አይሁድ ሊገሉት ያሳድዱት ነበር። በዚህም በጥንተ ተፈጥሮ በአባቱም ከእነሱም ተከብራ የነበረች ቀዳሚት በዘመነ ሥጋዌ እንደ ተሻረች፥ ከዚህ በታች በዘመነ ሐዋርያት እንደምናየው ያረጋግጣል።

በቀዳማዊት አባቴም ይሠራል፤ እኔም እሠራለሁ ማለት፥ በዕለተ ሰንበት፥ ሰንበት ተሽራለች ማለት ነው። በሚያስተምርበት ዘመን የጌታ ሥራ፥ ድውይ መፈወስ፥ ሙት ማንሣት፥ ለምጻም ማንጻት፥ እንካሳ ማርታት የመሳሰለውን ደጋግ ሥራ መፈጸም ነበር። በሚያስተምርበት ዘመን ከጥምቀት እስከ ስቅለት ይሠራው የነበረ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን እንጂ፤ እርሻ፥ ቁጥቋጦ፥ ቁፋሮ አልነበረም። ስለዚህ በነ መሥራት ሁሉ ተፈቅዷል። ከፉግ! ለአማኒ፥ ለክርስቲያን፥ ለክርስቶስ ተከታይ በዘወትሩም ክልክል ነው። ስለዚህ ይህን መሳልስን እንብበን የእነወይዘሮ እሌኒ ጉድ ኋይትን ወሬ አሽቀንጥረን መጣል አለብን (ዮሐ.5.1-8)

2. <u>ስለ ቀዳሚት ወይም ሰንበተ አይሁድ፤</u>

እድበንቲስቶች ቀዳሚት ወይም ሰንበተ አይሁድ ምን እንደነበረች ለማወቅ ቢፈልጉ፤ ለእሑድ ወይም ለሰንበተ ክርስቲያን ጥላ እንደነበረች ይመልከቱ።

በሰንበተ አይሁድ የሠራ ይገደላል (ዘኁል.15:32-36) በቀዳሚት ሰንበተ አይሁድ የሠራ ያርፋል (ኢ.ያ.6:15-16). የተሠራችው ለጽላሎትነት ስለሆነ ያው መሥራት አስቀጣም፤ አሽለመም።

እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል፥ ወይም ስለወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፈርድባችሁም፤ እነዚህ ሊመጡ ላሉት ነገሮች ጥላ ናቸው፥ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው። (ቆላ.2:16-17) ጌታም ሆነ ሐዋርያት ሰንበተ አይሁድን አክብሩ ብለው ስላላዘዙ መጽሐፍ ቅዱስን እንቀበላለን እያሉ በግብራቸው ግን የሚክዱት አድበንቲስቶች ውሸታቸውን ጥለው እውነቱን፥ ጽድቁን ቢቀበሉ እንዴት ጥሩ ነበር? መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን፥ ከቃሉ አንወጣም፥ አናጎድልም እያሉ በኩራት እየተንበጠረሩ፥ ከላይ እንዳየነው ከዐሥርቱ ትዕዛዛት አንዱን በሐሰት አትመስክር የሚለውን ጥሰው በተራ ሰው ላይ እንኳ ላይሆን በራሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ፥ ያባቱን ትእዛዛ ተቀብሎ ሰንበትን ያከብር ነበር እያሉ በማስመሰል፥ ያላከበሩትን አከበሩት እያሉ ያወራሉ፤ ይሰብካሉ።

3. <u>ስለ ሥጋውና ደሙ፤</u>

ጌታ እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙን ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፤ ሥጋዬን የሚበላ፥ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ፥ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና እያለ፥ ሥጋዬን ስትበሉ፥ ደሜን ስትጠጡ ታስቡኛላችሁ ያለውን ይዘው፥ ምሳሌና መዘክር እንጂ፥ አማናዊም አይደለ፥ ኀጢአትም አያስተሰርይም ይላሉ። በዚህም ጌታ ቁርባንን ሲሠራ ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው ያለውን ተላስተሃል ብለው ግረግቸው ነው፤ ሊቅና ዐዋቂ ከሆኑ ላይቀር እንዲህ ነው። ስለዚህ ርእስ በሰፊው ለማወቅ የሚፈልግ ዮሐ.6:26-58 ማቴ.26:26-29፤ ሁሉም ሁሉን ይወቅ ገጽ 90-108 ያንብብ፤

4. <u>ምስጥረ ትንሣኤ ሙታን፤</u>

በዚህ ደግሞ ከጀሆባ ከእርዮላውያን ጋራ ተስማምተው የጸደቁ ስዘለዓለም በሕይወት ከጌታቸው ጋራ በተድላ በደስታ ይኖራሉ፤ የተኮነኑ ግን እንደ ደረቅ ዕንጨት አንድ ጊዜ ተቃጥለው አመድ ይሆናሉ ይላሉ፤ በዚህም

የተሸከሙትን መጽሐፍ ቅዱስ መካዳቸው ነው። ነፍስ የመለኮት ቁራጭ ስለሆነች ለዘለዓለም ጸድቃ ወይም ተኩንና እንደ ሥራዋ ትኖራለች እንጂ ተቃዋሚ ሆነ ታሽታ አትጠፋም። ስለዚህም፣ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፣ ባፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፣ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። (ዘፍ.2:7:) ሌላውን እንሰሳ ሁሉ የፈጠረው በደመ ነፍስ እንጂ ከራሱ ባሕሪ ከእስትንፋሰ ከፍሎ አይደለም። ስለዚህም የሰው ነፍስ የመለኮት ቁራጭ በመሆኗ ጌታዋን ብትበድል ትቀጣለች እንጂ መሞት ወይም መበነን አትችልም። ኢዮብም (2:3) እስትንፋሴ በእኔ የእግዚአብሔር መንፈስ በአፍንጫዩ እስካለ ድረስ፥ ከንፈሬም ኀጢአት አትናገርም ብሎ የነፍስን ሕያውነት ተናግሯል። ስለዚህ ጻድቃን በደስታ ከጌታቸው ጋራ ኃጥአን ደግሞ በሥቃይ ካሉቃቸው ከሰይጣን ጋራ ለዘለዓለም እንደሚኖሩ የሚከተሉት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ያበረዳሉ፣

ሀ/ ማር 9:43-48፤ እጅህ ብታሰናክልህ ቆርጠህ ጣላት፣ ሁለት እጅ ኑሮህ ትሉ ወደማይሞትበት፥ እሳቱ ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት ከመሄድ ጉንድሽ ሁነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻላልና። እግርህ ብታስትህ ቆርጠህ ጣላት፥ ሁለት እግር ኑሮህ ትሉ ወደ ማይሞትበት እሳቱም ወደ ማይጠፋበት ገሃነመ እሳት ከመጣል አንካሳ ሁነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃልና። ዐይንህ ብታስትህ አውጥተህ ጣላት፥ ሁለት ዐይና ሁነህ ትሉ ወደ ማይሞትበት፥ እሳቱ ወደ ማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት ከመጣል፥ አንድ ዐይና ሁነህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻልሃልና። በዚህ ጥቅስ ሁለት የተለያዩ ዓለማት እንዳሉ ግልጥ ብሎ ይታያል። እነሱም ዘለዓለማውያን እንጂ ፍጻሜ ያላቸው አይደሉም። ቀጥሎም፣ ለ/ ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የሚለብስ አንድ ባለጸጋ ሰው ነበረ። ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። አላአዛር የሚባል አንድ ድኃ በቁስል ተወርሶ ከደጅ ተኝቶ ነበር፣ ከባለጸጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፣ ውሾች እንኳ መጥተው ቁስሉን ይልሱ ነበር፣ ድኃውም ሞተ፣ መላእክትም ወደ አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት። ባለጸጋውም ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ ዐሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ፥ አላአዛርንም በቅፉ አየውና፥ እሱም እየጮኸ አብርሃም አባት ሆይ! ማረኝ! በዚህ በነበልባል እሠቃ ያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አላአዛርን

ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን ልጄ ሆይ! አንተ በሕይወት ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ፤ አልአዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እሱ በዚህ ይጽናናል፤ አንተም ትሠቃያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋራ ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፣ ከዚያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል አለ። እሱም እንኪያስ አባት ሆይ! ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመሰክርላቸው አለ። አብርሃም ግን፤ ሙሴና ነቢያት አሉአቸው እነሱን ይስሙ አለው። እሱም አይደለም አብርሃም አባት ሆይ! ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሓ ይገባሉ አለ። አብርሃምም ሙሴንና ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም አንዱ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው። (ሉቃ.16:19-31) ይህ ደግሞ አንደኛ አድበንቲስቶችና መስሕታን የጀሆባ ምስክሮች ሲአልና ነነት የለም እያሉ የመቀባጥሩትን ቅጀት ያፈርሳል፤ ሁለተኛ አሁንም እነዚህ ሁለቱ የእውነት ተቃራኒዎች ሙታን አይነሡም እያሉ የሚነዙትን የባልቴት ተረት ብትንትኑን ያወጣዋል።

ሐ/ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃት ሰዓት ይመጣል፣ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፣ ዕድሉንም ከግብዞች ጋራ ያደርግበታል፣ በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። (ማቴ.24:50-51) በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል ዘለዓለማዊ ፍጻሜ የሌለው የትንቢት ግሥ ነው።

መ/ በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና፤ (ዮሐ.5:28-29) ከዚህ ደግሞ ሙታን መሰማታቸውንና ኃጢአንም ጻድቃንም መነሣታቸውን ይናገራል።

ሠ/ በምድርም ትቢያ ውስጥ ያንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት፤ እኩሌቶቹም ወደ ዕፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና። ጥበበኞችም እንደ ሰማይ ፀዳል፤ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ። (ዳን.12:2-3)

ረ/ በኋላም በዳግም ምጽአቱ በአባቱ ክብር፤ በክብሩ ከመላእክቱ ጋራ ሲመጣ፤ መጥቶ በጻድቃንና በኃጥአን ላይ ፈርዶ፣ ለጻድቃን ፈርዶ፣ በኃጥአን ፈርዶ፣ ጻድቃንን ወደ ተዘጋጀላቸው የዘለዓለም ሕይወትና መንግሥት፣ ተድላ ጠርቶ፣ ኃጥአንን ደግሞ ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ገሃነመ እሳት፣ ለዘለዓለም ሥቃይ አስናብቶ በአባቱ ቀኝ ተቀምጦ ይገዛል።

እነዚያም ወደ ዘለዓለም ኩነኔ፥ ጻድቃን ግን ወደ ሕይወት ይሄዳሉ፤ (ማቴ.25:31-46) በዚህም ለሁሉም እንደ ሥራው የሚከፍል መሆኑንና ጻድቃንና ኃጥአንም ለዘለዓለም የሚኖሩ መሆናቸውን ግልጥልጥ አድርጎ አስተምሯል።

ለ/ እግዚአብሔር ልጁን ለሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት መስጠቱን ደግሞ የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ።

ቀ/ (ዮሐ.6:27) ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ።

በ/ (10:27-29) በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለምም አይጠፉም። ከእጄ ማንም አይነጥቃቸውም።

ተ/ (ሮሜ.2:6-7) እርሱም ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይሰጠዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምሥጋናንና ክብርን የማያጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣቸዋል።

ኀ/ (6:22-23) አሁን ግን ከኀጢአት አርነት ወጣችሁ፤ ለእግዚአብሔር ተገዝታችሁ፤ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ። መጨረሻውም የዘለዓለም ሕይወት ነው። የኀጢአት ደሞዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘለዓለም ሕይወት ነው።

ነ/ (ቲቶ.1:2) ይህም ሃይማኖት በዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ላይ የተመሠረተ ነው። የማይዋሽው አምላክ ይህንን ሕይወት ለመስጠት ከዘለዓለም በፊት ቃል ገባልን።

አ/ (1ዮሐ.2:25) ይህም ክርስቶስ የሰጠን ተስፋ የዘለዓለም ሕይወት ነው።

<u>ዘለዓለም ሕያውነት፤</u>

ከ/ (ሉቃ.20:34-39) ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ፤ ይጋባሉ፤ ያን ዓለምና ከሙታን ትንሣኤ ሊያገኙ የሚገባቸው እነዚያ ግን አያገቡም፤ አይጋቡምም፤ እንደ መላእክት ናቸውና፤ ሊሞቱም ወደፊት አይችሉም፤ የትንሣኤም ልጆች ስለሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። ሙታን እንዲነሡ ግን ሙሴ ደግሞ በቁጥቋጦው ዘንድ ጌታ የአብርሃም የይሥሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ በማለቱ አስታወቀ፤ ሁሉ ለርሱ ሕያዋን ስለሆኑ፤ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም። ሙታን አይሰሙም የሚለውን

የደካሞች ባሕቴት ግምታዊ ተረትም ይህ የጌታ ቃል አምላክ ሕያዋን እንጂ አምላክ ሙታን አይደለም በማለቱ ብትንትኑን ያወጣዋል። ሞት ለነፍስ ከሥጋ መለየት እንጂ አእምሮ ማጣት አይደለም።

ወ/ (1ቆሮ.15:53-55) ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፥ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ፥ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።

<u>የዚህ ርእስ መደምደሚያ</u>

አድበንቲስቶች ክርስቲያን ለመሆን በሚከተሉት ምክንያቶች አይችሉም፤

ሀ/ ከዐሠርቱ ትእዛዛት ወይም ቃላት አንዱ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር ነው። (ዘፀ.20:16) እነሱ ግን በተራ ሰው ሳይሆን ያውም በፈጣሪያቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያልሠራውን ሠራ እያሉ፤ በሐዋርያትም ላይ ያልሠሩትን ሠሩ፥ ያላደረጉትን አደረጉ፥ ያልሆኑትን ሆኑ እያሉ፥ የውሸት ፕሮፓጋንዳ (ስርብትና) በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ ይነዛሉ። ሳያውቁት ይዘውት በሚዞሩ መጽሐፍ ቅዱስም እናምናለን እያሉ ይንጠረዘዛሉ።

ለ/ በሰርየተ ኀጢአት (ለኀጢአት ማስተስርያ) ነው፤ ሥጋዬን ለትበሉ፥ ደሜን ለትጠጡ ካልኖራችሁ በራሳችሁ (በሥራችሁ) ሕይወት የላችሁም ብሎ የሰጠውን ሥጋ መለኮት፥ ደመ መለኮትም (ቁርባን) ካንተ የምንበልጥ እኛ ነን በለው፥ ሥጋዬ ያልኸው መታሰቢያ እንጂ አማናዊም አይደለም፥ ኀጢአት ለማስተስርይም አይችልም ብለው፥ የክርስቶስን ትእዛዝ ባለመቀበላቸው ክርስትናን የመሠረተው የክርስቶስ ተከታዮችም ሆነ ታዛዦች አይደሉም። ማመን፥ መከተል፥ የመሪውን ትእዛዝ መቀበል እንጂ ማወቅና ማጭበርበር ብቻ አይደለምና። (ማቴ.26:26-28፤ ዮሐ:6:31-70፤ 1ዮሐ.2:4-6)

ሐ/ ሕፃን ባለማጥበቃቸውም ከሐዋርያት ጋራ አይመሳሰሉም፤ (ግብ.ሐ.16:15፤33)

መ/ ቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ለማዕታትን በሕይወተ ሥጋ ነው እንጂ ከሞቱ በኋላስ አያማልዱም ይላሉ፤ ድውይ ፈውሱ፥ ሙት አንሡ፥ እንካሳ አርቱ፥ የምትፈልጉትን ለምኑኝ እሰጣችኋለሁ ሲላቸው፤ እስከ

ዕለተ ሞታችሁ ያሳቸው ይመስል። እግዚአብሔርም እምላከ ሕያዋን እንጂ እምላከ ሙታን ይመስል። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ከሰጠ የማይጸጸት አምላክ ነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተቀባዩ ንቆት፤ ጠቅጥቆት ካልሄደ በቀር፤ እግዚአብሔር ተጠጥቶ ከዚህ ዓለም አሳፊ ሕይወት፤ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት በሞት ድልድይነት ተሸገረ ብሎ ስጦታውን አይቀማም፣ ከዚህ ላይ ግን ጻድቃን ከሞቱ ወዲያ አያማልዱም የሚሉ ወንጌላውያን የሚከተሉትን ጥቅሶች መሳልሰው እንዲያነቡ በትሕትና ይጋበዛሉ። ከዚያው ጌታ በኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠራል፣ ከዚያም የበለጠ ይሠራል ብሏል፣ (ዮሐ.14:12) የሱ ሥራ ምንድር ነው? በመጀመሪያም በመስቀል ላይ፣ ኋላም ሙቶ ተነሥቶ በአባቱ ቀኝ ሁኖ በጠቅላላ ለዓለም ለእያንዳንዳችንም ሲያማልድ እንደሚኖር በቅዱሳት መጻሕፍት ቁልጭ ብሎ ተጽፏል፣ ተነግሯል፣ ሲነገርም ይኖራል። ይህ ከሆነ ጻድቃን ስማዕታት፤ ሐዋርያት አያማልዱም፤ ከሞቱ በኋላ ቃል ኪዳናቸውን ተገፈዋል የሚለው፤ የፈጠራ ትምህርት ከሄት መጣ? ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቃለሁ የሚል ሁሉ ማወቅ ብቻ ሳይሆን የሚያዝዙትንም መከተል አለበት።

ከሁሉም እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከሰጠ፤ ተቀባዩ ካሳጠፋ በቀር፤ የማይቀማ፤ ከማስ ያማይጸጸት መሆኑን ለማወቅ ተሽከመውት ከሚዞሩት መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ቁጥሮች እንዲያነቡና እንብበውም እንዲቀበሏቸው፤ ለመጽደቅ ሐሳብ እንዳላቸው ይጋበዛሉ።

(ዘፍ.22:16-18፣ መዝ.88(89)19-51፣ 94(95):11፣ 131(132):11፣ ኢሳ. 14:24-27፣ 62:8:12፣ ሉቃ.1:73-75፣ ሮሜ.11:29፣ ዕብ.3:11፣ 6:17-18)

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች በተረጋገጠው በማይታበለው ቃሉ መሠረት፤ ስምኑ ይሰጣችኋል፣ ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል፣ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ ይሠራል፣ ከዚያም የበለጠ ይሠራል፣ ድውይ ፈውሱ፣ ሙት አንሡ ለምጻም እንጹ፣ በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሁን ብሎ ቃል ኪዳን ገብቷል። ቃል ኪዳኑም ለዘለዓለም ነው እንጂ እስከትሞቱ ወይም እስከታረጁ ወይም እስከ እገሌ ቀን የሚል አይደለም። ይህንንም የሚከተሉት ጥቅሶች ያረጋግጣሉ፣ ማቴ.10:1፣ 8፣16:19፣ 18:18፣ 19:27-28፣ ዮሐ.20:23፣ ማር.6:7፣ ሉቃ.9:1፣

ለምን ይሰጣችኋል፤ ማቴ.7:7-11፤ ማር.11:24፤ ዮሐ.14:13-14፤ 15:7፤ 16:23-24፤ ያዕ.1.5፤ 1ዮሐ.3:22፤ 5:14-15።

ነፍስም ዘለዓለም ሕያው ናት፤ ነፍስ ለጊዜው እስከ ትንሣኤ ከሥጋ በሥጋዊ ሞት ትለያለች እንጂ ለዘለዓለም ሕያው እንደሆነች ይህንን የሚክዱ እንደ አድበንቲስትና የጆሆባ ምስክሮች ተሸክመውት ከሚዞሩት መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉት እናቅጽ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እንዲያነቡ ይጠቆማሉ፤ ገና በጥንተ ተፈጥሮ፤ (ዘፍ.2:7) እግዚአብሔር አምላክም ሰውም ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። እግዚአብሔር ከፈጠረው እንስሳ ሁሉ ሕያው ነፍስ ያለው እስትንፋስ ከሰው በቀር የለም። በዚህም ነፍስ የመለኮት ቁራጭ፥ ቅናሽ መሆኗን እንረዳለን። መለኮት መንፈስ ነው አይሞትም፤ ነፍስም ለጊዜው በመዋቲ ሥጋ ትደር እንጂ መንፈስ ናት፤ ለዘለዓለም ሕያው ናት። መክ.12:7፤ አፈርም ወደ ነበረበት ሳይመለስ፤ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ። ማቴ.10:28፤ ሥጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን ለመግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ። (ሉቃ.12;20) ማር.9:43-48፤ 1ቆሮ.15:53-55፤ ራእይ:20:4-6

አድበንቲስቶች ምንም እንኳ እርስ በርሳቸው ቢረዳዱ፥ ትምህርት ቤት ቢከፍቱ፥ ሆስፒታል ቢሠሩ፥ የጸሎት ቤት ቢያንጹ በብዙ ሥራቸው አይሁድን ስለሚመስሉና ከክርስቲያን ይልቅ እስራኤልነት ስለሚቀርባቸው፥ ከወንጌል ኦሪትን ስለሚወዱ፥ ከክርስቶስ ይልቅ ሙሴን ስለሚያከብሩ በየጊዜው የሚፈጥሩት መጽሐፈ ባልቴትም ስለሚነትታቸው ከማኅበረ ክርስቲያን ጋራ ለመደባለቅ ብዙ ዘመን ይወስድባቸዋል ያውም ቢፈልጉ።

የክርስቶስን መምጫ ቀን እናውቃለን በማለትና ዘለዓለማዊ ኩነኔ የለም በማለት ከጆሆባ ምስክሮች ጋራ ስለሚመሳሰሉ ወንጌልን ትተው አንድ መጽሐፍ አውጥተው ሃይማኖታቸውን ቢሰብኩ ጥሩ ነበር፤ የማይቀበሉትን መጽሐፍ ተሸክሞ ከመዞር።

ሰው ዘለዓለማዊ ነው፤ ጆሆባውያንና አድበንቲስቶች የሰው ሕይወት መነሻ እንጂ መድረሻ፤ ጥንተ ተፈጥሮ እንጂ ፍጻሜ እንደሌለው ለማወቅ ቢፈልጉ የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንቡ። ዳን.12:2፤ ማቴ.25:46፤ ዮሐ.6:27፤ 10:28፤ ሮሜ:2:7፤ 6:22፤ 1ጢሞ.6:19፤ ቲቶ:1:2፤ 1ዮሐ.2:25፤ ዩሁዳ:21፤ ሉቃ.20:36፤ ዮሐ.6:50፤ 8:51፤ 11:26፤ ሮሜ:2:7፤ 1ቆሮ.15:53፤ 2ቆሮ.5:1፤ 1ተሰ.4:17፤ 2ጢሞ.1:10፤

Books Consulted on the Seventh-day Adventists Doctrine.
Aeschliman, Carlos E., The Faith of Jesus. First Edition, Central Amercan Union.

1. Seventh-day Adventists Believe...
A Biblical Exposition of 27 Fundemental Doctrines Ministerial Association General Conference of Seventh-day Adventists 6840 Eastern Avenue NW. Washington, DC 20012. First Printed May 1988, 80,000 Second June 1988, 100,000

1. እምነ ገክር ገ.4.
2. " " ገ:16.
3. " " ገ:28.
4. " " ገ:36.
5. " " ገ:58.
6. " " ገ:68.
7. " " ገ:78.
8. " " ገ:98.
9. " " ገ:106.
10. " " ገ:118.
11. " " ገ:134.
12. " " ገ:152.
13. " " ገ:170.
14. " " ገ:180.
15. " " ገ:194.
16. " " ገ:206.
17. " " ገ:216.
18. " " ገ:232.
19. " " ገ:248.
20. " " ገ:268.
21. " " ገ:278.
22. " " ገ:294.
23. " " ገ:312.
24. " " ገ:332.

25. " " ገ:348.
26. " " ገ:362.
27. " " ገ:374.

2. Adventists Affirm, Vol 8 No 2. A Pbublication Affirming Seventh-day Adventist Beliefs Fall 1994.

3. Adventits Affirm, Vol 8, No.3 A Publication Affirming Seventh-day Adventist beliefs Year-end 1994,

4. Haynes, Carlyle, Seventh-day Adventists, Their work and Teaching, Review and Herald Publication Association, Taroma Park Washington, D.C.1940.
5. Ruth Tucker, Strange Gospels, Marshall Pickering, 1991.

6. Seton, Benard E, These Truths We Hold. Studies in Christian Doctrine, Volume 1. Review and Herald Publishing Association, Washngton, D.C. 20012. 1981. of the same Author and Title Second Volume.

7. Spicer, William, A., Signs of Christs Coming foretold in Mathew 24 Reivew and Herald Publishing. Association, Washington D.C.1941.

## ምዕራፍ ሃያ አራት

### ሰባልዮሳውያንና አርዮሳውያን፤

ቅዱስ ጳውሎስ (2ጢሞ.3:5-9) ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን ዕወቅ። ሰዎች እራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብ የሚወዱ ትንቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ እራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨቃኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው፣ ኀይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ ወደ እየቤቱ ተሹሎክሉከው እየገቡ ኀጢአታቸው በልዩ ልዩ ምክንያት የሚወሰዱትን ሁል ጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይቻሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ ከነዚህ ዘንድ ናቸውና ያለውም ደርሶባቸው ሰባልዮሳውያን አርዮሳውያን ተሸክመውት ዓለምን ለማታለል ከሚዞሩት መጽሐፍ ቅዱስ አንዷ ዐረፍተ ነገር እንኳ አትገባቸውም። ወይም ዐይተው እንዳላዩ ይዘሏታል። ስለዚህ ሰባልዮሳውያንና አርዮሳውያን በቅድሚያ ለአጠቃላይ መግቢያ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንዲያነቡ ይለመናሉ፤ ለእነዚህ መናፍቃን እመልሳለሁ የምትልም ልብ አድርገህ እንድታጠናው ትመከራለህ። እግዚአብሔር አብ በተለየ አካሉ አምላክ፤ ማቴ.11:25፤ ዮሐ.17:3፤ ዘፍ1:1፤ ዘፀ.3:5-22፤ 20:2-7፤

እግዚአብሔር ወልድም ፍጹም አምላክ ነው፤ ዮሐ.1:1-5፤ ኢሳ.9:6፤ ይሁ.1:4፤ ማቴ.12:18፤ 17:5፤ ማር.9:7፤ 14:36፤ ሉቃ.9:35፤ መዝ.2:7-9፤ ኢሳ.42:1፤ 2ጴጥ.1:17፤ 1ጢሞ.1:17፤

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው፤ ሐዋ.5:3-4 ሦስቱም በሥላሴ ስም ይጠቀሳሉ፤ (ማቴ.28:19) ሦስቱ ስላሴ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልእክት አይደሉም (ዮሐ.10:30፤ 1ቆሮ.8:4፤12:3፤ ኤፌ.4,6፤ ዮሐ.3.16፤ ሐዋ.4:12፤ 10:30፤ ዮሐ.14:6፤ ማቴ.11:27፤ 16:17፤ 1ዮሐ.5:12፤ 2:23፤ 2ዮሐ.1:9፤ 1ዮሐ.4:15፤ 5:5፤ 20፤ 4:15፤ ሮሜ.8:9፤

የሰባልዮስና የአርዮስ ተከታዮች በዘመናችንም በሀገራችን ገብተው ጎጋውን ሕዝብ ስለሚያተራምሱት ከዚህ ቀጥለን በሰፊው እናያቸዋለን።

**በመጀመሪያ ሰባልዮሳውያንን፤**

ሰባልዮሳዊነት መቼ እንደ ተጀመረ ዘመኑ፣ የት እንደተነሣ ምንጩ፣ አይታወቅም፤ ገንኖ የተሰበከው ግን በሁለተኛና በሦስተኛው መቶ ዘመን ነው። በእስያና በሮም የዞሩት ግን ፕራክስያና ኖየቶስ ይባላሉ። ከእነሱ

በኋላ ታላቁ ሰባኪው ሰባልዮስ ስለነበረ በእሱ ስም ተጠርቷል። ይህን ኑፋቄ የሮም ቤተ ክርስቲያን በፖፕ ካሊስቱስ መሪነት ገዝታዋለች።

ሰባልዮሳዊነት ብዙ የስምና የግብር፥ የአቀራረብ መሻሻል መለዋወጥ ደርሶበታል። በስም (Monarchianism, Patripassianism Sabellianism, Unitarianism, Modalism) በእስተርእዮና በግብር በብሉይ ኪዳን አብ ፈጣሬ ዓለማት፥ ወሃቤ ሕግ (ሕግ ሰጭ) በሐዲስ ኪዳን ከድንግል ማርያም ተወልዶ መድኀኔ ዓለም፥ በሐዋርያት ላይ ወርዶ በልሳን ሲያናግር፥ ጥበዓት (ድፍረት) ሲሰጥ ደግሞ ቀዳሲ ይባላል እንጂ፥ ያው አንድ ገጽ፥ አንድ አካል ነው ይላሉ። ሰባልዮሳውያንና አርዮሳውያን (የጆሆባ ምስክሮች) የመሐመድ ፊታውራሪዎች ናቸው። የጆሆባ ምስክሮችስ ከቦታቸው እንደምናየው ለክርስትና ከመሐመዳውያንም ይርቃሉ። እነዚህ ሁለቱ ሰባልዮሳውያንና የዘመኑ አርዮሳውያን ተሸከመውት ከሚዞሩ መጽሐፍ ቅዱስ አንዷን ቃልም አያምኑ፤ ከሁሉም የሚያሳዝነው ክርስቲያኑን ለማሳት መጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ በገዛ መጽሐፋችን ያልተማረውን ጎጋ ሕዝብ ማጭበርበራቸው ነው።

በዚህ ምዕራፍ የጀመርነውን ሰባልዮስን ከጨረስን በኋላ በሚቀጥለው ደግሞ አርዮሳውያንን እናያለን። ሰባልዮሳውያን ሦስት ሥላሴ የሚባል ነገር የለም፤ እግዚአብሔር አንድ ገጽ ነው ይላሉ፤ ልክ እንደመሐመድ። በኦሪት እግዚአብሔር አብ፥ በወንጌል እግዚአብሔር ወልድ፥ በቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይባል ይላሉ። ይህም አንድ ሰው እንደ ግብሩና በታው፥ ስሙ እንደሚለዋወጠው ማለት ነው፤ ይኸውም መኪና ሲነዳ ነጂ፥ ወይም ሾፌር፥ ወይም ተሳፍሮ ይሄድ እንደሆነ ተሳፋሪ፥ በእግሩ ይሄድ እንደሆነ እግረኛ፥ ውሃ ይዋኝ እንደሆነ ዋናተኛ፥ እንደ ሥራው እንደሚባል ማለት ነው እንጂ ሦስት ገጽስ የለውም ይላሉ።

ከዚህም በላይ በዘመኑ አርዮሳውያንና ሰባልዮሳውያን ሥላሴ የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ ክርስቲያናዊ አይደለም ይላሉ። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የአምላክን ዋሕድና (አንድነት) ሦስትነት የሚገልጡ ፀረፍተ ነገሮች ሳሉ፥ በበዓለ ሰዋስው ደምብ ይህን አሳብ ለመግለጥ የሰሜን አፍሪካ ነባቤ መለኮት ቴርቲሊያኖስ Trinitas (trinity) Trias ብሎ ሰየመው። Trinity በእንግሊዘኛ፥ ሥላሴ በግዕዝና በአማርኛ

ምስትነት ማለት ነው። ምሥጢረ ሥላሴ ባጠቃላይ ከሁሉም ሁሉን ይወቅ ከገጽ 23-42 በሰፊው ተገልጦና ያነን ያነቧል። ከዚህ ግን ሰባልዮሳውያን እንደሚሉት እግዚአብሔር አንድ ገልጽ ብቻ እንዳልሆነ አስረድተን እናልፋለን። በሀገራችንም Only Jesus (ኢየሱስ ብቻ) የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን፥ ሰባልዮሳውያን ይባላሉ። ለስሕተታቸው ምክንያት የሆነውም የሚከተለው ጥቅስ ነው፤ ዮሐ. ምዕራፍ:14: ቁ.8-11፤ ፊሊጶስም ጌታ ሆይ! አብን አሳየንና ይበቃናል አለው። ኢየሱስም አለው፤ አንተ ፍሊጶስ ይህን ያህል ዘመን ካንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? <u>እኔን ያየ አብን አይቷል፥</u> እንዴትስ አንተ! አብን አሳየኝ ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፥ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፥ እኔን ያየ አብን አይቷል አለ እንጂ እኔ አብ ነኝ አላለም። እኔን ያየ አብን አየ ማለትም እኔና አብ እንመሳሰላን ማለት እንጂ እኔ አብ ነኝ ማለት አይሆንም። አንድ ገጽ ሰባልዮሳውያን እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ አብ ነኝ ብሎት ያርፍ ነበር።

ከዚህ ቀጥሎም ዮሐ.14:20፤ እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ። በዚህም አንዱ ባንዱ እግዚአብሔር በሰው ቢያድር፥ ሰው ማኅደረ አምላክ መሆኑን፥ ሰው ደግሞ በእግዚአብሔር ቢኖር የእግዚአብሔር ታዛዥ መሆኑን ይገልጣል እንጂ እንደ ሰባልዮሳውያን ከእግዚአብሔር ጋር ተደባልቆ አንድ ገጽ መሆናችንን አይገልጥም።

ሁለተኛውም ቁ.23 ኢየሱስም መለሰ አለውም፤ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደሱም እንመለሳለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። አሁንስ አብና ወልድ ስላደሩበት ሰውየው ከሁለቱ ጋር ተጨፍልቆ አንደ ገጽ ሆነ ማለት ነው? ወይስ መንፈስ ቅዱስን ተካው ማለት ይሆን? ያለፀዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል ሆነና ዐረፈ። አብና እኔ አንድ ነን ስላለ አንድ ገጽ ነው ይላሉ፤ ሁለተኛው 17:11፥ ቅዱስ አባት ሆይ! እነዚህን የሰጠኸኝን እንደኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው። አብና እኔ አንድ ነን ያለው ወልድ ወይም ኢየሱስ አሁን ደግሞ ምእመናኑ እንደኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው ካለ ምእመናን ሁሉ ተሰብስበው ከአንድ አምላክ ጋር ተደባልቀው አንድ ገጽ ይሁኑ ማለት ይሆን? ሦስት አካል፥ ሦስት ገጽ፥ በሥላሴ ብዙ አማልክትን

ያሳያል ሲሉ፥ ወይም ፈርተው ሲሸሹ ምእመኑን ሁሉ አግልክት አደረጉትና ዐረፉ።

ወደ እኔ መጥተው ሲያስረዱኝ ይሞክሩት አራቱ ሰባልዮሳውያን መጀመሪያ ሰዋስው አይገባቸውም፤ ነጠላና ብዙ ወይም አንድና ብዙ አይለዩም። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ከቅዳሴ በቀር ሌላ የማያውቁትን ሰዎች የሚያታልሉ ናቸው። የሥላሴን አንድነት ሦስትነት ራሳቸው በጠቀሱት በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ለማስረዳት እጀምራለሁ። ይህን ለማስረዳት የተማረው ሰው የሚያስፈልገው ትንሽም ሦስትነት ነው እንጂ አብና ወልድን አባትና ልጅንማ ለማስረዳት ዐይን ጨፍኖ መጻሕፍተ ሐዲሳትን መግለጥ ብቻ ይበቃል። በዚሁ መሠረት የተጠቀሰውን ወንጌል ከመጀመሪያው ምዕራፍ ጀምረን አላልፈን እንጥቀስ፤

1. ዮሐ:1:1፤ በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ገና በመጀመሪያ <u>ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ</u> ብሎ ሁለት መሆናቸውን ይናገራል።

2. 18 መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ በንኳ የለም። በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጅ እርሱ ተረከው። አሁንም ሁለት እንደሆኑ አባትና ልጅ እንዳሉ ተናገረ።

3. 29-35 በበነጋው ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እሱ ሲመጣ ዐይቶ እንዲህ አለ፤ እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤ አሁንም በተዛራፊ ሁለትነታቸውን ተናግሯል።

4. ከዚህ ቀጥሎ ይኸው ዮሐንስ በጊዜ ጥምቀት ሦስትነታቸውን ሥሉስ ቅዱስ ሦበት ገጻት መሆናቸውን መስክሯል። ማቴ.3:16-17፤ ማር.1:10:11፤ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔር መንፈስም እንደ ርግብ ወርዶ በእሱ ላይ ሲቀመጥ ዐየ። እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። በዚህም በእግዚአብሔር አብ በድምፁ፥ እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም በመወለዱ በአካሉ፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ በመቀመጡ ሦስትነታቸው ፍርጥርጥ ብሎ ተገልጧል። የሥጋና የነፍስ ዐይን ላለው ከዚህ የበለጠ መነጠር የለም። ይህም የአባትና የልጅ ምስክር ነት በደብረ ታቦር ተደግሟል፤

5. ማቴ.17:5፤ ማር.9:2-5፤ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።

መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን የሚባለው ይህ ሁሉ እየተካደ ነው። ይህን የመሰለው መረጃ ተገልብጦ አያልቅም፤ ግን ለአንባቢ እስኪሰለቸው ወደዚያው ወደ ዮሐንስ ወንጌል ተመልሰን የመሰለንን ያህል ጠቅሰን ወደ ሌሎች አርእስት እንለፍ፤

6. ዮሐ.3:16-18፤ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈርድበትም፤ በማያምን ግን በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።

ከዚህም በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ስም ያላመነ ተፈርዶበታል፤ ይፈረድበታል አለ እንጂ በእኔ በእግዚአብሔር አብ ስም ያላመነ አላለም። ኢየሱስ እግዚአብሔር ወልድ በፈቃዱ በመንፈስ ቅዱስ ሥምረት በእግዚአብሔር አብ ላኪነት ሰዉን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋ ለብሶ ሲወለድ የተሰጠው ስም እንጂ የእግዚአብሔር አብ ስምም አይደለ። በቅዱሳት መጻሕፍትም በቦታው እንደምናየው እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ስሜ ነው ሲል ተሰምቶም አይታወቅ። (ማቴ.1:21-23) እንደ ሰባልዮሳውያን ሥጋ የለበሰ እግዚአብሔር አብ ከሆነ እኔ ነኝ ቢል ምን ቸገረውና ነው ልጄ! ልጄ! የሚል? እሱን ኢየሱስንም አባቴ! አባቴ! ምን አሰኘው? ለአንባቢ መረጃው ይህ ብቻ እንዳይመስለው ትንሽ እንጨምርበት እንጂ ከሰባልዮሳውያን ትምህርት ልክ እንደ ጂሆባ ምስክሮች የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እውነት የለችም። በሁለቱም ዘንድ እውነት (ጽድቅ) እንዳትንካቸው የጎሲና ልብሳቸውን ከፍ ከፍ አድርገው ጎን ጎኑን ነው እያለፉ የሚሄዱ።

7. 34-36፤ እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፥ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና። አባት ልጁን ይወዳል፥ ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል። በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው። በልጁ በማያምን ግን የለዓለም ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም። አሁንስ በልጁ በልጁ ከማለተ በእኔ ማመን አይቀናም ወይ?

8. 4:34፣ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ፣ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው። ላኪና ተላኪ ሁለት አካላት እንዳሉ ጥቅሶች ሁሉ ይመሰክራሉ።

9. 5:17-18፣ ኢየሱስ ግን አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፣ እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው። እንግዲህ ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋራ አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፣ አይሁድ ሊገድሉት በጣም ይፈልጉት ነበር። ከዚህም ተላኩሀ ከማለት እኔው እራሴ መጣሁ አይቀልም ወይ?

10. 19-46፣ ስለዚህ ኢየሱስ መልሶ እንዲህም አላቸው፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ፥ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፣ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፣ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ፣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድንም ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብንም አያከብርም። እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ በላከኝም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው።

አንባቢ ሆይ! ይህን ምዕራፍ ካነበብህ በኋላስ አሁንም አንድ ገጽ፥ አንድ አካል ብቻ ነው የሚታይህ? የእግዚአብሔር አብ አባትነት፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅነት አይታይህም ወይ? እንደዚህ ያሉትን ጥቅሶች ገልብጬ እጨርሳለሁ ማለት ቢያንስ የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ አራተኛ እጽፋለሁ ማለት ስለሆነ የጥቂቶችን ምዕራፍና ቁጥር ሰጥተን ወደ ሌላው እናልፋለን።

11. 6:29፣ 32፣ 37፣ 38፣ 40፣ 44፣ 57፣ 69፣ 7:16፣ 8:14-20፣ 25-30፣ 38፣ 40፣ 42፣ 49፣ 54-55፣ 9:4፣ 10:7-9፣ 15፣ 17-18፣ 25፣ 29፣ 30፣ 32፣ 36-38፣ 11:27፣ 41-42፣

12. 27-28፣ 44-45፣ 49፣ 13:1፣ 3፣ 20፣ 14:1-3፣ 6፣ 12፣ 15-16፣ ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ እኔም አብን እለምነዋለሁ፣ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋራ እንዲኖር ሌላ አጽናኝ (ጠበቃ አማላጅ) ይሰጣችኋል፣ ከዚህ ላይስ ሦስት መሆናቸውን ግልጥ አድርጎ ተናገረ። ለሥሉስ ቅዱስ ከዚህ

የበለጠ ማስረጃ የለም። 20-21፤ 23-24፤ 26፤ 28፤ 31፤ 15:1-2፤ 8-10፤ 15-16፤ 21፤ 23፤ 26፤ ይህም ሥላሴን ይገልጣል። 16:3፤ 5፤ 7-10፤ 13-15፤ 17፤ 23፤ 26-30፤ 32፤...።
አንድነትና ሦስትነት የተገለጠበት ስለሆነ ምዕራፍ 17ትን በሙላ ማንበብ ያስፈልጋል። በተለይ 21 ቁጥር ደግሞ አንተ አባት ሆይ! በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነሱም ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምንሃለሁ። ይህ ጥቅስ ደግሞ አብና እኔ አንድ ነን በሏልና አንድ ገጽ አንድ አካል ነው እያሉ የሚቃጁትን ቅጀት ብትንትኑን ያወጣዋል። 19:7፤ 20:17፤ 21፤ ሌሎች ወንጌላትና ሐዋርያትም ከዚህ ያላነሰ ማስረጃ እንዳላቸው የተረጋገጠ ነው ከዚህ ግን ስለ ብራና ዋና ዋናችን ጠቅሰን እናልፋለን፤ ማቴ.27:46፤ በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ይህም አምላኬ! አምላኬ! ስምን ተውኸኝ ማለት ነው። ሌላ ሰሚ ከሌለ ለምን? ወደ ማን ይጮሃል?
28:18፤ ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፤ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስም ስም እያጠመቃቸኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። ስጭና ተቀባይ ከሌለ እንዴት ሥልጣን ሁሉ ተሰጠኝ ይላል። በግብረ ሐዋርያት ኢየሱስን ለማሳወቅ ሲባል በኢየሱስ እመኑ ለማለት እንደተነገረው ቢሆን ኑሮ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ብሎ እንዴት ያዝዝ ነበረ?

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ከሐዋርያት ትንሽ እንጥቀስ፤

13. <u>ሐዋርያት፤</u>

ቅዱስ ጴጥሮስ የጰራቅሊጦስ ዕለት፥ ግብ.ሐዋ.2:....፤ እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፤ ሞት ይይዘው ዘንድ አይችልምና። ከዚህም አስነሺና ተነሺ ስላሉ ሁለት መሆናቸው ተረጋግጧል። አለፍ ብሎም ቁጥር 34-36 ላይ ዳዊትን ጠቅሶ (መዝሙር 109:1) ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ከእግርህ መርገጫ እስካደረግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው አለ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም (ቅቡም ኀሩይም መሲሕም ማስያስም) እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይወቅ። ከዚህም ሁለት ጌቶች እንዳሉ ቁልጭ ብሎ ይታያል።

ቀጥሎም ከቁጥር 13-16፥ የአብርሃምና የይሥሐቅ የያዕቆብም አምላክ የአባቶቻችን አምላክ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቆርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው። እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ካዳችሁ፥ ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፤ የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፥ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፤ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን። በስሙ ማመንም ይህን የምታዩትንና የምታውቁትን አጸናው፤...። አንድ ጊዜ ቢሆን ኑሮ በእግዚአብሔር እንጂ በኢየሱስ ስም በማመን ዳነ አይልም ነበር። 2ጴጥ.1:17፤

14. <u>ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስም፤</u> በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፥ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብርና ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ዐየና እነሆ! ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ። (ግብ.7:56) አሁንም አንድ ነው የሚል እንዳለ ዐይኑ ልቡናው ታውሯል ከማለት በቀር ምን ይባላል?

15. <u>ቅዱስ ጳውሎስ</u>

ሀ/ ሮሜ 1:7-9 ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን። እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ፤ በልጁ ወንጌል በመንፈሴ የማገለግለው እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና።

ለ/ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለኛ ሙቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያስረዳል። ይልቁንስ እንግዲህ አሁን ጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን። ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋራ በልጁ ሞት ከታረቅን (ከተራረቅን)፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን። (5:8-11)

ሐ/ 8:31-34፤ እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ከሆነ ማን ይቃወመናል? ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእሱ ጋራ ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም? እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ የሚኮንንስ ማን ነው? የሞተው፥

ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

መ/ 15:6፤ በአንድነት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት እንድታመሰግኑ፤

ሠ/ 1ቆሮ.1:4፤ ስክርስቶስ ኢየሱስ ስላመናችሁ በተሰጣችሁ ስእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ሁል ጊዜ ስለእናንተ አምላክን አመሰግናለሁ።

ረ/ 8:6፤ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእሱ የሆነ፥ እኛም ለእሱ የሆን አንድ እምላክ አብ አለን፤ ነገር ሁሉም በእሱ በኩል የሆነ እኛም በእሱ በኩል የሆን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።

ስ/ 2ኛ.ቆሮ.1:3፤ የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

ቀ/ ኤፌ.1:3፤ 17፤ በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

በ/ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት መግቢያ የመጀመሪያዎች ምዕራፍ ሁሉ ከ1-3 ያሉት ቁጥሮች አንድ ገጽን፥ የሰባልዮስን ሐሳብ ይቃወማሉ። ሮሜ:ም.1:1-4፤ 1ቆሮ.1:1-4፤ 2ቆሮ.1:1-4፤ ገላ1:1-5፤ ኤፌ.1:1-4፤ ፊል.1:2፤ 2:6-11 ቆላ.1:1-3፤ 15-20፤ 1ተሰ.1:1፤ 2ተሰ.1.1፤ 1ጢሞ.1:1-2፤ 2ጢሞ.1:1-2፤ ቲቶ:1:1-4፤ ፊል.1:3፤ ዕብ.:1-8፤

ተ/ 2ቆሮ.13:13፤ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔር እብም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከእናንተ ጋራ ይሁን፤ እሜን።

ቅዱስ ጳውሎስ እውነተኛው ሐዋርያ በዚህ ዐይነት የሥላሴን ሦስት ገጽነት፥ ሦስት አካልነት ሲያስተምር ኑሯል፤ አስተምሯል እንጂ በምንም ምን ከሰባልዮሳውያን ንኪኪ የለውም።

ኀ/ ያዕ.1:1፤ 1ጴጥ.1:3፤ 2ጴ.1:1-2፤ 1ዮሐ.1:3፤ 2:22-23፤ 3:23-24፤ 5:3-5፤ 9፤ 12፤ 19-21፤ 2ዮሐ.1:3፤ 9፤ ይሁ.1:1፤ ሩእይ.1:45፤ 1ዮሐ.2:22፤

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አንበ የሐዋርያትን ትምህርት ተረድቶ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ወይም ኢየሱስ ብቻ ነን የሚሉ ሰባልዮሳውያን ምን እንደሆኑ ተረድቶ በቅዱሳት መጻሕፍት ይረቷል።

<u>የሰብከት ዘዴአቸው፤</u>
አብዛኛውን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ይጠቅሱና በኋላ ለማፍረስ ይሞክራሉ፤ ይህም ጎጋውን ሕዝብ ዋና ማደናገሪያቸው ነው። ገንዘብ ቢኖረ ኖሮ በስፋው መጽሐፍታቸውን ዘርዝሮ ማሳየት ጥሩ ነበር። ከዚህ ግን እንደ ደራሲው ዐቅመ ነዋይ ተጠቅሶ ታልፏል።

## <u>ለሰባልዮስ ኑፋቄ የተጠቀሱ መጻሕፍት፤</u>

1. መጽሐፍ ቅዱስ (ቅዱሳት መጻሕፍት)
2. <u>የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች፥</u> አልቦ ደራሲ ወቤተ ማኅተም ወ ዓ.ም.
3. መለስ ወጉ፥ <u>ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ</u> 1987።
4. ተክለ ማርያም ገዛኸኝ (ቄስ)፥ <u>መለኮታዊ ኀይል፥</u> አዲስ አበባ ሐምሌ 20:1961 ዓ.ም. አልቦ ማኅተም ቤት
5. <u>በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፊልጉ፥</u> አሁንም አልቦ ማኅተም ቤት
6. <u>አንድ መንጋ፥</u> አሁንም አልቦ ማኅተም ቤት ወ ዓ.ም.
7. <u>አዲስ ልደት፥</u> አዲስ አበባ፥ ጥር 20:1967 ዓ.ም. ንግድ ማተሚያ ቤት።
8. <u>ጥያቄዎቻችሁና መልሶቻችሁ፥</u> ከመጽሐፍ ቅዱስ፥ 1974 ዓ.ም. አልቦ ማኅተም ቤት
9. <u>The Identity of Jesus Christ.</u> Thomas Nelson Inc, Publishers 1982, Printed in United States of America.

## ምዕራፍ ሃያ አምስት

### አርዮስ

የአርዮስ ተከታዮች የጀሆባ ምስክሮች የሚሉት ትምህርት በሁሉም ሁሉን ይወቅ ገጽ ከ37 ጀምሮ የተገለጠው እንደተጠበቀ ሆኑ፥ ከዚህ ደግሞ ስለአርዮስና ኑፋቄው ወይም ክህደቱ ባጭር ይገለጣል። አርዮስ በ3ኛው ክፍለ ዘመን በሊቢያ ተወልዶ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ዓለምን በክህደቱ በጥብጦ፥ በኑፋቄ መርዙ መርዞ፥ በክርስቲያን መካከል የጥላቻ እንክርዳድ ዘርቶ፥ በቀጥታ የጸላኤ ሠናይ አገልጋይ፥ የእውነት ደመኛ ሁኖ ያለፈ ፀረ ክርስቶስ ካሓዲ ነው። እሱም በአንጾኪያ ትምህርቱን ጨርሶ፥ በእስክንድርያ ውስጥ ቅስና ተቀብሎ ኑሮ በ318 ላይ ወልድ ፍጡር ነው እንጂ አምላክ አይደለም የሚል ክህደት ጀመረ፥ በዚህም መካከለኛው ምስራቅ በመላ ተበጠበጠ። ጥሩ ገጣሚና ተናጋሪ በመሆኑ ብዙ ተከታይ አገኘ። ከአውራጃ ወደ አውራጃ እየተዘዋወረ ሲያስተምር የብዙ አውራጃ ጳጳሳት ገዙቱት። የእስክንድርያው ፓትርያርክ እለእስክንድሮስም በክሕደቱ እንዲጸጸት፥ ከስሕተቱ እንዲመለስ ቢመክረውም እምቢ ስላለው ገዘተው።

ቤተ ክርስቲያን ለሦስት መቶ ዓመት በሮም አረመኔ መንግሥት ስትሰደድ ኑራ፥ አሁን አዲስ ነጻነት አግኝታ በቁስጠንጢኖስ ምክንያት የዕረፍት አየር መተንፈስ ስትጀምር፥ በአርዮስ ላይ መንፈስ እርኩስ አደረና ይበጠብጣት ጀመር። ንጉሡ ቆስጠንጢኖስም ለማስታረቅ ሞክሮ ስላልተሳካለት፥ በኒቂያ ጉባኤ ተሰብስቦ እንዲወሰን ጉባኤ ጠራ። በዚህ ጉባኤም ከአርዮስ ደጋፊዎች ሌላ 318 ኤጲስ ቆጳሳት በእለእስክንድሮስ በእስክንድርያው ፓትርያርክ መሪነት፥ በቅዱስ አትናቴዎስ አቀንቃኝነት፥ አርዮስን አውግዘው ጸሎተ ሃይማኖትን ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም እስከሚለው ድረስ ጽፈው፥ የተወሰኑ ቀኖናዎችን ሠርተው ተበተኑ። አርዮስና ተከታዮቹ ሊቃነ ጳጳሳትና ካህናት እንደ ሁኔታው በድብቅም በገሃድም እየሰበኩ እስከ ዘመናችን ደርሰዋል። አርዮስ ያለው ወልድ ፍጡር ብቻ ነበር። ተከታዮቹ የጀሆባ ምስክሮች ግን እንደ ዝምብ ቆሻሻውን ሁሉ ሰብስበው በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ዓለምን ያግስሳሉ። በምንም በመጥፎነታቸው ከአርዮስ ቢብሱም ሥረ ወጡ አባታቸው አርዮስ ስለሆነ ትምህርታቸውን ከዚህ ቀጥለን እናያለን። ታማኝ የአርዮስ ተከታዮች የጀሆባ ምስክሮች አዕማደ ክሕደት የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ ወልደ ፍጡር ነው ይላሉ።

ሰ/ ጠቅላላ ትንሣኤ ሙታን የለም፤ የተወሰኑ 144000 በራዕየ ዮሐንስ እንደተጻፈው ብቻ ናቸው ይላሉ፤ ራእ.14:1፤ 7:4፤

ሐ/ የሥላሴን ሦስትነት አሽቀንጥረው ጥለው፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ያለውን ምስክርነት ክደው እንደሰባልዮስና መሐመድ አንድ ገጽ ይላሉ።

የማይቀበሉትን መጽሐፍ ቅዱስ ተሸክመው እየዞሩ ጎጋውን ከማታለል ይልቅ እሱን ስሚፈልጉትና ስሚያምኑበት ትተው ከአይሁድ ወይም ከመሐመዳን ጋራ ቢደባለቁ በጣም ጥሩ ነበር፤ ግን ከዚያም ቤት እሳት እሰ እንዲሉ በእምላክ አንድ ገጽ ይስማሙ እንጂ በትንሣኤ ሙታን፣ በፍርድ፣ በማርያም ድንግልነት በነፍስ ሕያዊትነት፣ በእግዚአብሔር ሐቀኝነት፣ እውነተኛና ደልዳላነት ሁለቱም፣ አይሁድም መሐመዳንም ስለሚያምኑ አይቀበሏቸውም። ጠበቃ በሌለው ክርስትና ይቦርቁ እንጂ በጓደኞቻቸው አይሁድና ስላምማ ድንጊያና ሰይፍ ስላለ በአጠገባቸውም አይዞሩ።

መ/ ነፍስ ከሞተ ሥጋ በኋላ አትሰማማም አትለማም ይላሉ።

ሠ/ ክርስቶስ እንደ መሥዋዕተ ኦሪት በግ ተሠውቶ ያሕቤ ተደስቶበት፣
እሮ ቀረ እንጂ በሥጋ አልተነሣም ይላሉ።

ረ/ በነቢያት ሲነገር የኖረውን የቅድስት ማርያምን ድንግልና ይክዳል።

ሰ/ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ኀይል እንጂ አካል ስለሌለው ዝርው መንፈስ ብቻ ነው ይላሉ።

ቀ/ ሥላሴ የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ስለሌለ አንቀበልም ይላሉ፤ ይህ የፍጹም ሞኝ ክርክር ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስም በሦስትነትም በአንድነትም በግልጥ ተዘርዝረዋል፤ ቃሉን ግን እንደሰጥሰው ጸሐፊ የሰየመው በሦስተኛው መቶ ዘመን የነበረ የሰሜን አፍሪካ በላቲን ቋንቋ ጸሐፊ ተርቲልያኖስ ነው። ይህም ስጥሰው ጸሐፊ ስም፣ ቅጽል፣ ተውላጠ ስም (ወዘተ) እያለ እንደሚያወጣው ማለት ነው፤ እንጂ የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት እየተነገረ የመጣ ከኦሪት ጀምሮ ሲሆን በሐዲስ፣ በወንጌል ግን በክርስቶስ በደምብ ተብራርቶ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ፣ በደብረ ታቦርና ዮርዳኖስም የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ አብ ሲመስክር፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በእምሳለ ርግብ ከራሱ ላይ ዐርፏል።

በ/ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከድንግል መወለዱን ይክዳሉ።
ተ/ የጌታንን ዳግመኛ በሥጋ እየታየ መምጣት አያምኑም።
ኀ/ በገሃነምና በዘለዓለማዊ ቅጣት አያምኑም
ነ/ ነፍስ ለዘለዓለም አትኖርም ይላሉ።
አ/ መድኀኔ ዓለም ሰውን ከበደሉ በቂ ካሣ ሰጥቶ አላዳነውም ይላሉ፥ ብለው የዓለም ቤዛነቱን ይክዳሉ።

ይህ ትምህርት በሁሉም ሁሉን ይወቅ ከ37-45ና 199-200 የተገለጠ ስለሆነ ሐተታውን ከጥቅሶቹ ጋራ አምብቦ ይረዱል። (ከዚህ በላይ ለማወቅ የሚፈልግ፤ መሰለ ወጉ፥ ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ)

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

### በየጊዜው የተነሡ መናፍቃን፤

በዚህ ምዕራፍ፥ ሕገ ኦሪት እንዳትጠፋ፥ ክርስትና እንዳትስፋፋ ብለው ይጥሩ ከነበሩ ቢጽ ሐሳውያን ጀምሮ በዘመናችን የክርስትናን ኀብረት እስከ ሚበጠብጡት ሐሳውያን ሰባኪያን ድረስ ግልጥ ብለው ተጽፈዋል። በዚህ ምዕራፍ ያሉት፤ መናፍቃን በሙሉ ቢገዘቱም ባይገዘቱም ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸው ናቸው። ለምን ቢሉ ይህ መጽሐፍ የሁሉም ሁሉን ይወቅ ተከታይ ስለሆነ አንባቢ ከቤቱ ሆኖ ሃይማኖቱንና ጠላቶቹን፥ ጓደኞቹንም ዐውቆ ራሱን ተሳስቶ እንደሆነ እንዲመለስ ያላወቀውም ካለ እንዲያውቅ ስለታሰበ ነው።

1. <u>ረባናተ አይሁድ፤</u>

ከሁሉም አስቀድሞ በዘመነ ሐዋርያት ግብ.ሐ.15 ላይ እንደተጻፈው የአይሁድ ረበናት የነበሩ ቢጽ ሐሳውያን፥ ሠርጎ ገቦች፥ የሚጠመቁ ሁሉ ሥርዓተ አይሁድንና ሕገ ኦሪትን ማክበር አለባቸው እያሉ የክርስትናን እድገት ስላደናቀፉ፥ ቢያደናቅፉ፥ ሐዋርያት ተሰብስበው ሕገ ኦሪትን ሽረናል፥ ወንጌልን ተቀብለናል፥ ሥርዓተ ረበናትን በሙሉ ሰርዘናል ብለው ሠርጎ ገብ አይሁድን አሳፍረው መልሰዋል። (15:1-29)

2. <u>ናዝራውያን፣</u>

ይህ ስም መጀመሪያ ለመቀለጃ ለመላ ክርስቲያን ተሰጥቶ ነበር፣ በኋላ ግን ክርስትና እያየለ በሄደ፥ ጳውሎስን ያስቸግሩ ለነበሩ አይሁድ ተሰጠ። እየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. ከመጥፋቷ በኋላ ጥቂት አይሁድ ከዮርዳኖስ ማዶ በፔላ ጥገኛ ሁነው ይኖሩ ነበር። ልጆቻቸው አይሁዳውያን ክርስቲያን ሁሉ ልማደ አይሁድን ከተዉ በኋላም ከሥርዓተ አይሁድ ተጣብቀው ቀሩ። የሙሴን ሕግና ሥርዓትም ረባናትን አጥብቀው ይጠብቃሉ፥ ይገዘራሉ፥ ቀዳሚትን ያከብራሉ። በሥራቸው ሁሉ የዘመናችንን አድበንቲስቶች ይመስላሉ። በሀገራችንም የጎጃም ደጋ ደጋው፥ መንዝ፥ ጥድላ ደላንታ በመራቤቴ ይልቁንም በምሪት መስሎቻቸው ሞልተዋል። በዓላትን በጥንቃቄ እንደ አይሁድ በማክበርና አንደ አይሁድ ከጎረቤት ርክስት በመራቅ እንድናሰን የሚሉ ሁሉ የነሱ ርዝራዦች ናቸው።

3. <u>ኤቢዮሳውያን፣</u>

እነዚህ ከናዝራውያን ጋራ ዲመሳሰላሉ፣ ተከታዮቻቸውን ሰባክያን አያላኩ ቅዱስ ጳውሎስን ያሳድዱ የነበሩ ናቸው። (ግብ.ሐ.14:19-20፣ 22፣ ገላ.2:1-32፣) ናዝራውያንና ኤቢዮሳውያን ስማቸው ይለያይ እንጂ ግብራቸው አንድ ነው።

4. <u>ዶኪስታውያን፣</u> (ግሪክ ዶኪስቴ ትምህርታቸው ዶኪስቲዝም)

ክርስቶስ ሰው ይመስላል፣ ሰው መስሎ ታየ እንጂ ሰው አይደለም ይላሉ፣ ይህ ኑፋቄ በኋላም በ13ኛው ዘመን አልቢጌንስ በሚባል ሰው መሪነት ተነሥቶ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን በጥብጧል።

በዚህም ከዚህ በታች ከተገለጡት ግኖስቲካውያንና ማኒካውያን ጋራ ይመሳሰላሉ።

5. <u>ግኖስቲስት</u> (ግኖስቲስዝም፣ ግሪክ ግኖሲስ ዕውቀት፥ ግኖስቲስቱ ዐዋቂዎች) ግኖስቲሲዝም የመዳን ሐሳብ በዕውቀት ነው እንጂ በእስትርእዮ (በመገለጥ) አይደለም። ይህ ኑፋቄ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በዘመነ ሐዋርያት ነበር። በዚያ ዘመን ያለምን ምስጢር እናውቃለን የሚሉ ግኖስቲስቱ ነበሩ። አነሱም ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩ የብዙ አማልክት ትምህርት ተከታዮች ነበሩ። ግኖስቲስቶች የሚስማማቸውን ከአየቤተ ማኅት ተበደሩ። ከክርስትናም ከወንጌሎች ለእነሱ ሐሳብ የሚስማሙትን ወስደው ለራሳቸው ሐሳብ የሚስማማ የጥርቅም ወንጌል

አዘጋጁ። ይህም ለሁለትነት ሐሳብ የሚስማማ ነበር። ቁስ የመንፈስ ተቃራኒ፥ ዓለም ደግሞ እምላክ የለበትም ተባለ። ግኖስቲስ ምንም እንደተደራጀ ሃይማኖት ቢጠራም የብዙ ኑፋቄ ምንጭ ሁኖ፥ እየሆነ ኑሯል። በሐዋርያት ዘመን የተፈጸመው የገሃድ እስተርአዮ የስም በማለት በእየጊዜው ስተነሡት ከሕደቶች ምንጩ ግኖስቲዝም ነው።

ይህ ክሕደት የብዙ ፍልስፍና ጥርቅም፥ የሰው ልጅ ቅጀት ስለሆነ ብዙ የተለያዩ ፅንሰ ሐሳቦችን ይዞአል። ከነሡም የመጀመሪያ በዓለም ሁለት ደግና ክፉ አማልክት አሉ ብሎ ከዞራስታር ጋራ ይመሳሰላልና ደግ ደጉ ነገር ሁሉ ከደጉ አምላክ ወጣ፥ ይወጣል፤ ክፉ ክፋው ነገር ሁሉ ከክፋው አምላክ ይወጣል፤ ወጥቷል። ከነዚህ ከሁለቱ ታላላቅ አማልክት ደግሞ ሌሎች ትንንሾች ደጎችና ክፉዎች አማልክት ተገኙ ይሉና እስከ ቆሌ (አድባር) ይወርዳሉ። ከደጋጉ አንዱ እየሱስ ነው። ይህ ፅንሰ ሐሳብ ነው እንደነ ባሁላ ላሉት ምንጭ የሆነው። ዓለምን የፈጠረ ከክፉዎቹ አማልክት አንዱ ነው አሉ። ስሙንም ደሚዮርጎስ ወይም ዲሚውርጎስ (ፈጣሪ፤ ሠሪ) አሉት። ኢየሱስ ክርስቶስ በምትሐት እንጂ በእማን አልተወለደም የተሰቀለውም ስምዖን ቄሬናዊ እንጂ እሱ አይደለም። እሱ ሊሰቀል ሲል፥ ተሰውሮ፥ ተለውጦ ከታናናሹ አማልእክት አንዱን ሆነ። በክርስቶስ ፈንታ ዮሐንስ ወይም ስምዖን ተሰቅሏል እንጂ እሱ አልሞተም የሚለው ሐሳብ ለሰልምና የዚህ አባባል ምንጭ ሆነ። ከዚህ በላይ ክርስቲያንን ለማታለል ብዙ መጻሕፍት ጽፈዋል። እምነታቸው በሚከተሉት አዕማድ ይጠቃለላል፤

ሀ/ ከዓለም (ከቁስ) የተለየ አንድ አምላክ አለ፤ ስሙም ዝምታ ወይም ጥልቀት (ጥልቅ) ይባላል። እሱም ዘለዓለም በተከታታይ ሥርፀት የሚገለጥ ሥልጣን ወይም ኀይል ነው ይላሉ።

ለ/ ኤዎኖች (ዘመናት) በእግዚአበሔር (አምላክ)ና በፍጡር መካከል ያሉ ማዕከላውያን ናቸው። እንደ እምላክ ዘለዓለማውያን ናቸው። ዘለዓለምም ሴትና ወንድ እየሆኑ ከእሱ በጥምድ በጥምድ ይመነጫሉ። የመጀመሪያዎቹ ከእሱ ወጥተው እነሱ ደግሞ ሌሎችን ያሠረፃሉ። የዘመናት ፍጹም ተከታታዮች ፍጻሜን ይቀርጻሉ።

ሐ/ ሥርፀቱ ከዋናው አምላክ እየራቀ በሄደ ቁጥር ፍጹምነት እየቀነሰ፥ እየደከመ ይሄዳል።

መ/ ሰው ግን የመለኮት ፍንጣቂና ፍጹምነት ስላለው ይህን ያህል የተበላሸና የረከሰ አይደለም።

የድኅነት ዋናው ሐሳብ የመለኮትን ፍንጣቂ ከቁስ ለመለየት ነው። ከመጀመሪያዎቹ ኤዎኖች አንዱ በአጋጣሚ በጥምቀት ጊዜ ከክርስቶስ ጋራ ተገናኝቷል፣ እስከ መስቀሉ ድረስ። ይህ ኤዎን ከሰው ባሕርይ ጋራ ለጊዜው የተገናኘ ይመስላል። ድኅነት በዕውቀት እንጂ በክርስቶስ ሥራ የሚገኝ አይደለም።

ሠ/ ከመለኮት ፍንጣቂ ድኅነትና ከከፍተኛው ዓለም ሥርዓት መደራጀት በኋላ በዲሚዮርጅ ተገዥነት ሁሉም ዓለም ይቃናል። የቁስ ዓለም ከሚኮነኑት ሰዎች ጋራ ይጠፋል። ከዚህ ሁሉ ነው፤ የጀሆባ ምስክሮችና የአድበንቲስት ኃጥአን እንደ ደረቅ ዕንጨት ለአንድ ጊዜ ተቃጥለው ይጠፋሉ የሚለው ሐሳብ የተወለደው። ከዚህ ርእስ በርስ ከሚጣላ ጭፍን ሐሳበ ተነሥተው ብዙዎች ለሞራል የተለያዩ ሐሳቦች አስተማሩ። ብዙዎች ቁስ፣ ሥጋ፣ ሰውነት መናቅ አለበት፤ ለመንፈስም መገዛት አለበት፤ ስለዚህ ነው የሀገራችን ባሕታውያን አንዳንዶቹ፣ ሰውነታቸውን የሚያሳድፉ፣ ቁሻሻ የሚለብሱ፣ በልዩ ልዩ ተባይ ሥጋቸውን በሞላ አካላታቸውን የሚያጋልጡ። ሌሎች ደግሞ ሥጋንም የሠራው አምላክ ስለሆነ በክበር፣ በደምብ፣ በክብካቤ መያዝ አለበት ይላሉ። የግኖስቲክ ዋና ሰባኪዎቹ ባስንቲኖስና ባሲሊዲስ ነበሩ። ሁለቱም በሁለተኛው መቶ ዘመን በእስክንድርያ ተወልደው ያደጉ ናቸው። እንደ ግኖስቲካውያን ታላቁ አምላክ በራሱ ኑዋሪ ነው፤ በጣም ሩቅ ነው፤ ሊታወቅ አይችልም። ያለትጥል የመጀመሪያው መርሕ፤ ከዘመንና ከሰውጥ በላይ የሆነ ነው። በዘመናችን እንዳሉት እንደ ጀሆባ ምስክሮችና ሰባልዮሳውያን፣ ግኖስቲኮች ክርስቲያን ሳይሆኑ ክርስቲያን ነን ይላሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትን ግልብጥበጣቸውን አውጥተው፤ ፈርዖንና አክዓብ ቅዱሳን ነበሩ፤ ሙሴና ኤልያስ ደግሞ ኃጢአተኞች ናቸው፤ የብሉይ ኪዳን አምላክም በጣም ክፉና መጥፎ ነው እያሉ አስተማሩ።

ጽድቅ የሚገኘው በጥልቅ ዕውቀት በመንፈሳዊ ርቀት እንጂ በአስተርእዮና በጸጋ እግዚአብሔር አይደለም አሉና ዐረፉ። በሌላም አነጋገር ለመጽደቅ ተራቃቂ፣ መንፈሳዊ፣ ዐዋቂ መሆን ያስፈልጋል አሉ።

6. <u>ሌው ማርኪዮን፤</u>

ሌላው ደግሞ የግኖስቲካውያን ተንዳኝ የሲኖፔው ማርኪዮን በ170

ዓ.ም. ሮም ላይ የሞተው ነው። እሱም በሞላ ብሉይ ኪዳንን ነቀፈ፣ የብሉይ ኪዳን እምላክም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እምላክ አይደለም አለ። ምንም እንኳ ባሕታዊ አኗኗሩ ብዙ ተከታይ ቢያፍራለትም በሚያስተምረው ኑፋቄ መገዘቱ አልቀረም።

7. <u>ሞንታኖስ፣</u>

ሞንታኒዝም በሁለተኛው መቶ ዘመን በአርዳቦ፥ ሚዚያ፥ ትንሽ እስያ ተወላጅ በሞንታኖስ መሪነት የተነሣ ኑፋቄ ነው። የተስፋፋበትም በሚዚያ፥ በፊርጂያ በሰሜን አፍሪካ በካርሳጅ ነበር። ከእሱ በፊት የነበረው ኑፋቄ ሞንታኒዝም ጽድቅና ብቃት የሚገኘው በዕውቀት በመንፈሳዊ መራቀቅ፥ በአእምሮ ምጥቀት ነው ይል ነበር። ይህ ደግሞ በሀብተ መንፈስ ቅዱስ፥ በጸጋ ጰራቅሊጦስ ነው አለ። ትምህርቱም በሁለት አርእስት ይከፈላል።

ሀ/ ሦስተኛውና መጨረሻው አስተርእዮ (መገለጥ) እሱም የጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያውና መሣሪያውም ሞንታኖስ ነው። ጰራቅሊጦስም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አስተርእዮ ይፈጽማል፣ ያብራራል፣ ያስተካክላል፣ ለተከታዮቹም ይገልጣል። ግብሩም የጸጋን ስጦታ በሰፊው መናኘት ነው።

ለ/ የጌታ መምጣት አይቀሬ ነው። በቅርቡ ይፈጸማል፣ ጌታ በሕዝቡ ላይ 1000 ዓመት ለመንገሥ ዳግመኛ በቅርቡ ይመጣል። አዲሱ አስተርእዮ በሕርመት፥ በቀኖና፥ በጾም በጸሎት፥ በብሕትውና ከክርስቶሱ የጠበቀ ነው። ክርስቶስ ስለ ሥጋ ደካማነት ብሎ ያላላውን ሥነ ምግባር ያጠብቃል፣ በመጀመሪያ ከእነመጀመሪያውም ጋብቻ ተንቅፎ ነበረ፣ በኋላ ግን ተከታይ ሲበዛ አንደኛው ተፈቅዶ ሁለተኛው ተከለከለ። በመጨረሻ ከጥምቀት በኋላ የተሠሩ ኀጢአቶች አይሰረዩም ተባለ። ከዚህ በላይ የተባሉትን የጠበቁ ክርስቲያኖች መንፈሳዊያን፥ የቀሩት ደግሞ ልክ እንደ ግኖስቲክ ነፍሳውያን ተባሉ። ልክ አሁን አንዳንዶች በአካባቢያችን እንደሚያደርጉት ቤተ ክርስቲያንን የሚመመራት መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ምእመን በተመ ስጦ ገብቶ ነው። በመንፈስ ቋንቋና ትንቢትም እንናገራለን። ስለዚህ ካህና ት፣ ዲያቆን፥ ቄስ፥ ጳጳስ አያስፈልጉም ስላሉ፥ በእየአውራጃው ያሉ ያካባ ቢ ካህናት ጉባኤ እያደረጉ ገዘቷቸው። በመጨረሻ በ202 የሮም ጳጳስ ገዘ ታቸው። ይህ ኑፋቄ ይገዘት እንጂ በልዩ መልክና ቅርጽ እስከ ዘመናችን ደርሷል።

8. <u>አፅራረ ሥላሴ</u> (አንዲትርያዲክ ወይም አንቲትርያዲክ)

የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የክርስትናን መሠረት የሚቃወሙ ጥርቅሞች ነበሩ። ስእነሱም ዋናው መሪያቸው ጳውሎስ ሳምሳጢስ፥ (ጳውሎስ ዘሳምሳጢ) ነበረ። እሱም አምላክ አብ ብቻ ነው፤ ወልድ ግን በጥበበ እግዚአብሔር የተሞላ ደግ ትልቅ ሰው እንጂ አምላክ አይደለም ብሎ አስተማረ፤ በዚህ ክሕደቱም ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን ተለየ።

9. <u>ፐላጊዮስ፤</u>

ከ355-425 የነበረ የእንግሊዝ ጭዋ መነኮስ ነው፤ ኑፋቄውን ወይም ስሕተቱን በሮም አደባባይ ነዝቷል። ፐላጊዮስ ከእንግሊዝ ተነሥቶ ኢየሩሳሌምን፥ ግብጽን፥ ሰሜን አፍሪካን ቃኝቷል። ኑፋቄውን በሰሜን አፍሪካ አስፋፍቷል። ይህንን ክሕደቱን በሮም ሲያስተምር ኬሌስትዮስን አገኘውና ሰብኮ ታማኝ ተከታይ አደረገውና ተያይዘው ሲሲሊንና አፍሪካን በ409 ዓ.ም. ገደማ ሰበኩ፤ ብዙ ተከታይም አገኙ። ግን በ411 ዓ.ም. በካርታጅ ጉባኤ ተወገዙ። በዚህ ጊዜ ፐላጊዮስ ወደ ምሥራቅ ሲሸሽ ኬሌስትዮስ አፍሪካ ቀረ። በ415 በኢየሩሳሌም ጳጳስ በዮሐንስ ተካደ። በ415 መጨረሻ ደግሞ የተወገዘበት ዓመት ሳያልቅ በሊዲያ ዲዮስጳሊስ ጉባኤ፤ ሁለት አልፎሃጅ የፈረንሳይ ጳጳሳት ልክ አይደለም ብለው እየተራከሩ ሳለ ልክ ነህ ተባለ። እነዚህ የምሥራቅ ጳጳሳት በምን ልክ ነህ እንዳሉት አልታወቀም፤ ተታለውም ይሁን ተስማምተው። የሮም ሁለቱ ሊቃነ ጳጳሳት ቀዳማዊ እኖስንትና ዘዚመስ ገዝተውታል፤

የሆነስ ሆነና ኑፋቄውሳ ምንድር ነው ለሚል ጠያቂ መልሱ፤

ሀ/ ይህ ሰው የተደናቀፈው በቅዱስ አውግጢኖስ ሰው ቅዱስና ደግ እንዲሆን፥ ጸጋ እግዚአብሔር፥ ረድኤተ እግዚአብሔር ያስፈልገዋል በሚለው ትምህርት ተላልኮ (በአልክ) ያለምንም ጸጋ እግዚአብሔር ርዳታ ሰው በገዛ ግብሩ ሊበቃ ይችላል፤ ስለዚህም ኀጢአት የማይሠሩ ብዙ ሰዎች አሉ ብሏል።

ለ/ ጥንተ አብሶ የሚባል ነገር የለም። አዳም ከመበደሉም በፊት የተፈጠረው የመዋቲና የሥጋዊ ስሜት ተገዢ ሁኖ ነው። እኛስ የበደለን በምሳሌው ነው። የሰው ኀጢአት በዝንባሌው የተተከለ ልማድ ነው።

ሐ/ ስለዚህ ጥምቀት ለድኅነት አስፈላጊ አይደለም። ግን ለመንግሥተ ሰማይ (ቤተ ክርስቲያን) አባል ለመሆን ያስፈልጋል። ጊዜ ያዊ ኀጢአትንም ያስፍቃል። በጥምቀት የሚሰጠው ቀዳሺ ጸጋ ለመንፈሳዊ

ሀብተ ምስጢር መሠረት አይደለም፣ የጊዜያዊ ኀጢአት መፈወሻና የክርስቲያን ፈርጥ፣ የመለኮት ልጅነት ምሳሌ እንጂ።

መ/ አዳም ባይበደልም ይሞት ነበር።

ሠ/ የአዳም መውደቅ የበደለ ራሱን ብቻ ነው።

ረ/ አዲስ የሚወለዱ ልጆች አዳም ከመበደሉ በፊት እንደ ነበረው ሁነው ነው የሚወለዱ።

ሰ/ የሰው ዘር ስለአዳም ኀጢአት አይሞትም፣ አይነሣም።

ቀ/ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ሁለቱም አንድ ዐይነት ጸጋ ያስገኛሉ። ፐላጊዮስ በዘመናችን ተጠራጣሪ እንጂ ብዙ ተከታይ የለውም።

10. <u>አውሳብዮስ፣</u>

የሰባልዮስን ክሕደት ያስተማረ፣ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ እግዚአብሔር ይጠራ እንጂ ሥላሴ የሚባል ነገር የለም፣ እግዚአብሔር አንድ ገጽ አንድ አካል ነው ብሎ ያስተማረ እንደ መቅዶንዮስና እንደ አቡሊናርዮስ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ ጉባኤ የተገዘተ ነው።

11. <u>አርጌኒስ (አርጌኒስ)</u>

በ185 ግብጽ፥ እስክንድርያ ተወልዶ፥ ከዚያው አድጎ፥ ተምሮ በ18 ዓመቱ ጀምሮ ሃይማኖት ሲያስተምር በመናፍቃን ላይ ብዙ መጻሕፍት ጽፎ በ254 ዓ.ም. ሙቷል። ልዩ ልዩ ምንጮች ከ6000 እስከ 8000 መጻሕፍት ጽፏል ይላሉ። የሆነ ሁኖ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሱ የጻፈ አለመኖሩ ተረጋግጧል። የግሪክን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ የመሠረተው እሱ ነው። ባሕርይንና አካልን የሚገልጡ ቃላት ለመጀመሪያ ጊዜ የወሰነ እሱ ነው። በጣም የተማረ ስለ ነበረ ብዙ ቀናተኞችም ነበሩበት። በሕፃንነቱ (በጉርምስናው) ወንዶች ምሽቶቻችንን ያባልጋል ብለው እንዳይጠረጥሩት ጉያውን ቆርጦ ነበር። በዚህም የእስክንድርያው ዲሜጥሮስ እንደስግ አበጀህ ብሎ የትምህርት ቤቱ ርእስ መምህር አድርጎ ሾመውና በኋላ ብዙ ሰው ሲከተለው ጊዜ ቀንቶ አለቀስህም አለው። ይህን ግፍ የሰሙ የፍልጥኤም ቂሳርያ ቴዎክቲስቱና የኢየሩሳሌም እለእስክንድሮስ አቀሰሱት። ግን በእስክንድርያው ዲሜጥሮስ በሁለት ጉባኤ ተገዘተ።

በመጨረሻው ጠላቶቹም በዙ፥ እሱም ቤተ ክርስቲያን የማትቀበላቸውን ኑፋቄያት አስተማረ፣

1. ነፍስ ከቀድሞ ጀምራ የተፈጠረች ዘለዓለማዊት ናት።
2. እግዚአብሔር መሐሪ ነው፤ ስለዚህ ያጠፋውን ሁሉ በመጨረሻ ቀጥቶ ይምረውና ፍጥረት ሁሉ ከፈጣሪው ጋራ ይገናኛል።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ እንደገና አጋንንትን (ሰይጣናትን) ለማዳን ይወለዳል።

ወልድ ከአብ ያንሳል እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ብሏል። በዚህ ኑፋቄውም ከሞተ 299፣ (300 ዓመት ገደማ) የቁስጥንጥንያ ጉባኤ በ553 ዓ.ም. ገዝተውል።

12. <u>እንቲዲቆማርያጦስ፤ (እንጢዲቆማርያጦስ)</u>

ፀረ ማርያም ማለት ነው። ጌታን ከወለደች በኋላ ማርያም ከዮሴፍ ጋራ ተገናኝታለች፣ ልጆችም ወልዳለች ይላሉ። ይህን ግን ስለማርያም በተጻፈው ምዕራፍ ሁሉም ሁሉን ይወቅ ገጽ 154-160ና ከዚህም ያይዋል።

13. <u>ሳዊሮስ፤</u>

የህንደኬው ሳዊሮስና የእስክንድርያው ታውዳስዮስ ወልደ እግዚአብሔር የታመመና የሞተው በግድ ያለፍቃዱ ነው እያሉ አስተምረዋል። የዚህ ማረጋገጫ ግን በቅዱሳት መጻሕፍት የለም። እንዲያውም በተቃራኒው ብዙ መረጃ አለ።

14. <u>መንክዮስ፤</u>

መንክዮስ የክርስቶስ ሥጋ ምትሐት ነው የሚል መናፍቅ ነው፤ እውነተኛው ትምህርት ግን ክርስቶስ የለበሰው ሥጋ ፍጹም ትስብእት ነው፤.ከኀጢአት በቀር ፍጹም ሰው ነው። (ዮሐ.1:14፤ 20:20፤ ማቴ.28:9፤ 24:36-43)

15. <u>እፍትኪስ፤</u>

ይህ ደግሞ የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ የወረደ ነው ይላል። በዚህም ከእሁናቹ ስባልዮሳውያን ጋራ ይመሳሰላል። እውነቱ ግን ሰውን ለማዳን ሰው ሁኗል፤ ከድንግል በነቢያት እንደተነገረው በመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል። በዚህም (ኢሳ.7:14፤ 9:6፤ ሉቃ.1:31፤ ዮሐ.1:14) ከዚህም በላይ ከሰማይ ሥጋ ቤት አለ የሚል በቅዱሳት መጻሕፍት ስለሌለ የሁለቱም መናፍቃን ሐሳብ ቅጀት ነው ከማለት በቀር ምንም መልስ የለውም።

16. <u>አርሲሳን፤</u>

እነዚህ መናፍቃን ደግሞ ክርስቶስ ወደ ሲኦል የወረደው በሥጋና በነፍስ ነው ይላሉ። እውነተኛው እምነት ግን የሚለው በሥጋ ሞተ፥ ተቀበረ፥ በነፍስና በመንፈስ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚያ ላሉት ከአዳም ጀምሮ በግዞት ለነበሩት ነጻነትን ሰበከ ነው። (1ጴጥ.3:18-20)

17. <u>ፍላብያኖስ፤</u>

ለክርስቶስ ሁለት ገጽ አለው፥ አንድ የመለኮት፥ ሌላው ደግሞ የትስብእት ይላል። ይህ ኑፋቄ የንስጥሮስን ስለሚመስል ከንስጥሮስ ጋራ በኤፌሶን ዓለም አቀፍ ጉባኤ በ431 ተወግዟል ለማለት ይቻላል።

18. <u>ክርታርዮስ፤</u>

ይህ መናፍቅ ከጥምቀት በኋላ ንስሓ የለም ይላል። በዚህም ምስጢረ ንስሓን ክዶ ሥርዓተ ንስሓን አፍርሷል። (ማቴ.18:21-35፤ ሉቃ.17:3-4)

19. <u>ሰዱቃውያን፤</u>

የፈሪሳውያን ተቃራኒዎች የቤተ አይሁድ አንድ ክፍል ድርጅቶች ነበሩ። ክሕደታቸውም ትንሣኤ ሙታንና መላእክት የሉም ማለት ነበር። በዚህም የዘመናችንን ኮሚኒስቶች ይመስላሉ። ሰዱቃውያን ራሱን ጌታን ጠይቀውት ረቷቸዋል። (ማቴ.22:23-33፤ ማር.12:18-27፤ ሉቃ.20:27-40)

## <u>ለዚህ ምዕራፍ የተጣከሩ መጻሕፍት፤</u>

1. <u>ሃይማኖተ አበው፤</u> ትንሣኤ ዘጉባኤ፥ ማ/ቤት አዲስ አበባ፥ 1967 ዓ.ም.
2. ሉሌ መልአኩ፥ <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥</u> ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ፥ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1986 ዓ.ም.
3. <u>መዝገበ ሃይማኖት፥</u> በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የተዘጋጀ፥ አልቦ ማ/ቤት፥ 1959 ዓ.ም.
4. <u>ምስጢረ ሥላሴ፥</u> ብርሃንና ሰላም፥ 1903 ዓ.ም.
5. ስንክሳር፥
6. ቅዱሳት መጻሕፍት
7. <u>ዐሥራት ገብረማርያም፥</u> ትምህርተ መለኮት፥ አርቲስቲክ ማ/ቤት፥ 1983 ዓ.ም.

8. Cayre', F, A.A. Manual of Patrolgy and History of Theology, Society of John the Evangelist, Paris, Tournai, Romam 1936.

9. A Dictionary for Believers and Non- Believers, Progress Publishers, Moscow, 1989.

10. Hardon, John A. Modern Catholic Dictionary, Robert Hale, London, 1981.

11. Renwick, A.M. The Story of the Church, Intervarsity Press, London, 1971.

12. Stephanidou, Basiliou, Church History, (in Greek) Astir, Athine, 1948.

## ምዕራፍ ሃያ ሰባት

### አጠቃላይ ምኞት፤

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ክርስቲያን ሁሉ ለያይቶት የኖረን የባህልና የጥቅም ወንዝ ተሸጋግሮ እንዲገናኝ የመጀመሪያውን ድልድይ ለመጣል ነው። ስለዚህ እንዴት ተገናኝቶ ይታረቅ ለሚለው ጥያቄ የሚከተሉት ምኞቶች ቀርበዋል።

የኬልቄዶን ጉባኤ ተሳታፍያን የተባሉት በሹመት እንጂ በሃይማኖት እንዳልሆነ ከታወቀ 50 ዓመቱን አክብሯል። እስካሁን የቆየም በአለፉት መንግሥታት ዘመን የንግግር ነጻነት ስላልነበረና የዘመኑ መሪዎችም ለለያይተህ ግዛ ስርብትናቸው ይረዳል ብለው ስላመኑና፤ ኅጋው ሕዝብም ከሚያውቀው ተረት ጋራ የማይስማማ እውነት ስለማይቀበል ነው። አሁንም እንኳ የተለያየነው በእምነት፥ በትምህርት ሳይሆን በቃላት ነው የሚል ቢጻፍ፥ መጽሐፉ ሰውን ለማስበርገግ ፀረ ማርያም ነው ተባለ። (የኢ.ኦ.ተ.ቤክ. እሥ. አ.ው.ግ.ገ.108 ጦማር: 18:1988 ዓ.ም. ገጽ: 11ና:2።) ስለዚህ፤

1.ገንዘብ ያላቸው ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያውቁት የሮም፥ የግሪክ፥ ፕሮቴስታንት የሚባሉት የሉተር ተከታዮች ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን የክርስቲያንን ውሕደት የሚረዱ ክታባት እያሳተሙ ቢበትኑ።

2. ሳያውቁ በአንጎት ቤተ ክርስቲያን ላይ ጥላቻ የሚሰብኩትን ሰፍላፊዎች እስኪያውቁ ዝም ቢያሰኙ።

3. በአምስቱ አዕማደ ምስጢርና በሰባቱ ህብታት የማያምኑ የክርስቲያን ክፍሎች ሁሉ የአገልግሎት ባህላቸውን እንደያዙ ከሚቀርባቸው ቤተ ክርስቲያን ለመቁረብ እንዲችሉ፥ ለዚህ የመሪዎች ጉባኤ በቅርቡ ተደርጎ ቢፈቀድ።

4. ሁሉም የሰመደውን የአገልግሎት መዝሙር፥ ማሕሌት፥ ጸሎት፥ ቋንቋ እንደያዙ ቢገናኙ።

5. በሃይማኖት ከተስማሙ በምግባር በኩል ላለመጣላት ለጊዜው መስማማት።

6. ላልተማረ ምግባርና ሃይማኖት ስለሚደባለቁበት ለይቶ ማስተማር። ሃይማኖት የሚባሉ፥ አምስቱ አዕማደ ምስጢር፥ ሰባቱ ህብታተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ጾም፥ ጸሎት፥ ምጽዋት ደግሞ ከነመሰላቸው ምግባር ናቸው።

7. ያለ ዕውቀት ከለላም ይልቅ ጥልን የሚሰብኩትን በቅድሳት መጻሕፍት አስረድቶ ከስሕተታቸው እንዲመለሱ ማድረግ፥ በትዕቢት ተወጥረው እምቢ ቢሉ ግን ለቤተ ክርስቲያን መንገር።

8. ለመጀመሪያዎቹ 30 ዓመታት ያህል እንደ መጀመሪያዎቹ የሦስቱ ዘመን የክርስቲያኖች መሪዎች ሁሉ እኩል ታይተው፥ በአገልግሎት መጨረሻ የሁሉም ስም በክህነት ዕድሜ ቅድሚያ እየተጠሩ ቢቆዩ።

9. በኋላ መግባባት ሲመጣ፥ ፍቅር ሲጠና ግን አዲስ ጉባኤ ተሰብስቦ የቅድሚያን ነገር በምርጫ ወይም በዕጣ ቢወሰን።

10. የሮም ቤተ ክርስቲያንም ከሁሉ አስቀድማ ለኦርቶዶክሳውያን ዕንቅፋት የሆነውን ከወልድም ያሠርፃልን ብታነሣ። (ማንሣትዋ አይቀሬ ነውና)

11. አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በቋንቋና ባገልግሎት ልዩ ስሆኑ ለአኃት ቤተ ክርስቲያን እባሎች ክፍት ቢሆኑ። የአነጽዋቸው ለጊዜው የማይጠቀሙባቸው ከሆነ።

12. በልማድ የቅዳሴ ጊዜ የሚወስኑ ሰዎች አሉ፤ እነዚህም እንደ ብዙዎቹ ለህገሩ አየር የሚስማማውን ዐይተው መወሰን እስኪችሉ ድረስ፥ እንደ ሃይማኖት ነውና የሚያዩት፥ ለጊዜው በክርክር ሳይሆን በምክክር

ለማስረዳት መሞከር። ከክርስቲያን በጣም ጥቂቶች ከቁርባን በፊት ረጅም ጾም የሚያዝዙ አሉ። የሚሰጡት ምክንያትም ምግብ በልቶ አይቆርብም ነው። የዛሬው ዘመን የሳይንስ ጥናት ግንኛቸውም የሚበላው ምግብ በ 6 ሰዓት ውስጥ እንደሚሟሟ ያስረዳል። ከዚያ በላይ ጹሙ ማለት ግን በሳይንስም ሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ የለውም። ስለ ቁርባን ያለው እምነት እንጂ ጊዜው ግን በእየዘመኑ እየተለዋወጠ ስለመጣ፥ አሁንም ሕዝቡ በሚመቸው ጊዜ ጳጳሳቱና የእየቤተ ክርስቲያኑ አለቆች ሊወስኑ ይችላሉና በዚህ ጊዜ ካልተቀደሰ መሥዋዕቱ አያርግም፥ እግዚአብሔር ይቆጣል፥ መቅሠፍት ይወርዳል ብሎ፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት ያልተገኘ ወሬ መንዛትም አይገባም፤ አይገባምና መተው። የቅዳሴ ሰዓት በመላ ዓለም አንድ ጊዜ መሆን አለበት የሚሉም አሉ፤ ይህ ግን ጉድለትም ችግርም አለውና እንዳላዩ ዐይቶ እንዳልሰሙ ሰምቶ መዝለል ነው። ጉድለቱ እግዚአብሔር ከተወሰነ ሰዓት በቀር ሁልጊዜ ጸሎትም ሆነ መሥዋዕት መቀበል አይችልም ወይም አይፈቅድም ማለት ይሆናል። ችግሩ ደግሞ ምእመናኑ በፈለጉ ጊዜ እንዳይቆርቡ ያደርጋል። ብሎም በትዕግሥት ጊዜውን ጠብቆ ይሁን እንጂ ዛሬ ካልሆነ ብሎ መተናነቅ አይበጅም።

13. ክርስቶስና በገባበት ሀገር ሁሉ የብሔሩን ባህል እየለበሰ አጎንብሶ ነው የገባው። እንደ ኢትዮጵያ ባለው፥ ሕገ ኦሪትን ተቀብሎ በኖረ ሀገር ሕገ ኦሪትን፥ ሥርዓተ ረበናትን፥ እንደ አውሮጳ ባለው በአሕዛብነት በኖረው የአምልኮ ጣዖትን ልማድ፥ እንደ አምላክ ፀሐይ አፓሎ ሥርዓት፥ የልደት አከባበርን የመሳሰለ ይዞ ነው የሚሄደው እንደዚህ ያለው ልማድ በጊዜው ስለሚጠፉ ዝም ብሎ እውነተኛውን እየለበሱ መቆየት።

ይህ ሁሉ ከተፈጸመ እውነተኛውን ካስመሰይ ለይቶ እየተረዳዱ መኖር። አስመሳይ ክርስቲያን የሚባሉት በክርስቲያን ስም የሚነግዱት፥ አርዮሳውያን፥ ሰባልዮሳውያን፥ የሰባተኛው ቀን አድበንቲስት ሦስቱ ናቸው። እምስቱን አዕማደ ምስጢርና ሰባቱን ሀብታተ ቤተ ክርስቲያን በርቱዕም ሆነ በኢርቱዕ የሚቀበል ሁሉ ክርስቲያን ነው።

14. ሃይማኖት በአምስቱ አዕማደ ሚስጢር ይተነተናል፤ ጸጋ እግዚአብሔር ደግሞ በሰበዓቱ ሀብታት ይገኛል። እነሱም፤ አምስቱ አዕማደ ምስጢር፤ ምስጢረ ሥላሴ፥ ምስጢረ ሥጋዌ፥ ምስጢረ ጥምቀት፥

ምስጢረ ቁርባን፥ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው ሰባቱ ሀብታተ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ፤ ጥምቀት፥ ሜሮን፥ ንስሓ፥ ቁርባን፥ ተክሊል፥ ቀንዲል፥ ክህነት ናቸው።

እነዚህን የሚቀበሉ ሁሉ በአነጋገር፥ በአባባል፥ በአፈጻጸም የተለያዩ ቢመስሉም በግብር ከእመናቸው ክርስቲያኖች ናቸው። ብዙ ወንጌላውያን ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀትንና ቁርባንን በቃል ይቀበሉና የቀሩትን ደግሞ ዝም ብለው በግብር ይፈጽሟሉ፤ ለምሳሌ ጋብቻን፥ ንስሓን፥ ተክሊልን ወዘተ. ስለዚህ በዚህ ጥናት መሠረት ክርስቲያን የሚባሉ፥ ያለመለያየት አብረው መኖር የሚገባቸው፥ የግሪክ ኦርቶዶክስ፥ የሮም ካቶሊክ፥ የግብጽ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፥ የአንጾኪያ፥ የአርመን አብያተ ክርስቲያን፥ የሮም ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ምክንያት በማርቲን ሉተር መሪነት የተለዩት ወንጌላውያን ሁሉ ምስጢረ ሥላሴን፥ ምስጢረ ሥጋዌን፥ ምስጢረ ቁርባንን በቃል የሚያምኑ የቀሩትን የጌታን ትእዛዛትና ምስጢራት በግብር የሚፈጽሙ ሁሉ ክርስቲያን ናቸው።

እነዚህ ሁሉ የሚለያዩት ባለመግባባትና በሹመት፥ በፍቅረ ንዋይ፥ በኩራት መሆኑ ተረጋግጧል።

እነዚህ ሁሉ አንድ ከሆኑ ከእነዚህ የሚለዩት እስመሳይ ክርስቲያኖች ደግሞ እነማናቸው? ለሚል ጠያቂ መልሱ ባጭሩ ይህ ነው፤ የሥላሴን አንድነት፥ ሦስትነት፥ እኩልነት፥ ዘለዓለማዊነት፥ አንድ አምላክነት የማያምኑ፥ ምስጢረ ሥጋዌን ይልቁንም የክርስቶስን በድንግልና መወለድ፥ ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ፥ ፍጹም ሰው፥ ፍጹም አምላክ መሆኑን የማያምኑ፥ የተጠመቀ ሁሉ በጥምቀት ከእግዚአብሔር ዳግም መወለዱን የማያምኑ፥ በስንዴና በወይን አምሳል የሚዘጋጀው ቁርባን ፍጹም ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ሁኖ የቀረበውን ኀጢአት የሚያስተሰርይ መሆኑን የማያምኑ፥ ምንም በጎ ሥራ ቢሠሩ ሃይማኖት ስለሌላቸው እንደ መጻሕፍቱ አይጸድቁም። ስለዚህ ምንም መጽሐፍ ቅዱስን ተሸክመው ቢዞሩ እኒህ ክርስቲያን መሳይ ከሓድያንና አረማውያን ክርስቲያን አይደሉምና፤ ከክርስቲያን ጋራ ለመደባለቅ ፈቃዱም ሆነ ዕውቀቱ ስለሌላቸው ከማስጠጋቱ ማራቁ ይሻላል። ያለዚያም ከዚህ መጽሐፍና ከሁሉም ሁሉን የተጻፉትን መልሶች እየሰጡ መመለስ ነው።

## አንድ እረኛ፥ አንድ መንጋ

ይህን መጽሐፍ የምታነቡ ሁሉ ክርስቶስን የተቀበሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በፍቅር፥ በኅብረት፥ በአንድነት፥ እግዚአብሔር በልጁ ሥር እንዲኖሩ ያደርግ ዘንድ እንድትጸልዩ በኢየሱስ ክርስቶስ ትለመናላችሁ። ለዚህም ፈቃድህ ይሁን፥ መንግሥትህ ትምጣ ብላችሁ ጸልዩ ተብለን ታዝዘናል። አፍ ተልብ አይደለም እንጂ መጸለያችንስ አልቀረም። አፍ ተልብ ሁነን ጸልየን መልሳችንን ለማግኘት፥ ለመቀበል ያብቃን። አሜን።

### <u>መፍትሔ ቃላት፤</u>

መለትስ መለኮትና ትስብእት፥ አንድ መሆኑን በተዋሕዶ ስማሳየት ከሁለቱ ከመለኮትና ትስብእት የመጀመሪያዎቹ ቀለማትና ሆሄያት መለትስ ተወስደው አምላክም ሰውም ነው ተብሎ በተዋሕዶ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሚለውን ብዙ ትርጉም ያለውን የዋለለውን ቃል ለመተካት የተቀረጸ ቃል። ለመጀመሪያው ጊዜ ስለሆነ በጽሑፍ ላይ የዋለ፥ አንባቢ ሊያስተውለው ይገባል። መለኮቱንና ትስብእቱን አዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ መለትስ ለሆነ ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም በትስብእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የሚሰጥ ቃል ነው።

<u>መቀናጆ</u>= መቀናጦ፥

<u>መደዴ</u>= ያልተማረ፤ ግርፍጥ፤ ባላገር፤ ገልቱ፤

<u>ሥጋ መለኮት</u>= ሥጋሁ ወደሙ፤ ቁርባን

<u>ስርየት</u>= የኀጢአት ይቅርታ፥ እግዚአብሔር ለኀጢአተኛ የሚያደርገው ይቅርታ

<u>ተዝኅሮ</u>= ትዕቢት፥ ኩራት፥ መጀነን፥ መምበጥረር።

<u>ትሩፍ</u> =የቀረ፥ ወደኋላ የተተወ፥

<u>ትሩፋት</u>= ምግባረ ሠናይ ሁሉ።

<u>ትሩፋን</u>= ናቡከደርንጸር ኢየሩሳሌምን ወርሮ ሲሄድ፥ ንቆ ትቷቸው የሄደ የእስራኤል ደካሞች።

<u>ትውፊት</u>= ዘአንበሩ አበው።

<u>አውሰቦ</u>= ጋብቻ።

<u>አማናዊ</u>= እውነተኛ፤ እርግጠኛ፤ ያው፤ ልዩነት ወይም ለውጥ የሌለው።

<u>ኩነት</u>= ሁኔታ፥ ህልውና፥ ለፍጡር ተፈጥሮ፤

## መፍትሔ ቃላት

<u>ውሑድ ባሕርይ</u>= መለትስ፥ ወይም አምላክነቱንና ትሰብእቱን በአንድ አካል ያዋሐደ አምላክ ወሰብእ፥ ወልደ አብ፥ ወልደ ማርያም። አምላክም ሰውም፥ በተዐቅቦ ተዋሕዶ ያለመቀላቀል፥ ያለመለወጥ፥ ያለመከፋፈል፥ ያለመለያየት በተዐቅቦ በመለትስ የሚኖር።

<u>ጌዶ</u>= የጊዜ ገደብ፥ እስከዚህ ድረስ እንዳትነካ ብሎ የሚወስን ውል። በዚህ ሕግ መሠረት ሕፃን ልጅ እስከ 12 ዓመቷ ሳትነካ ተወስና ትዳራለች።

<u>ጎጋ</u>= በስሜት የሚነዳ፥ ያልተማረ፥ ተራ ሕዝብ።

<u>ጥንተ አብሶ</u>= በአዳም በደል ምክንያት የመጣ ኃጢአት፥ እስከ ክርስቶስ ሞት ድረስ በዓለም ነግሦ የኖረ፥ ከዚያ ወዲህ ደግሞ በጥምቀት ከእያን ዳንዱ የአዳም ልጅ የሚወገድ።

<u>ጸሊአ ቢጽ</u>= ወንድምን መጥላት፥ ጓደኛን አለመውደድ፥

<u>ፍቅረ ንዋይ</u>= አፍቅሮ ንዋይ፥ ገንዘብ ያለልክ መውደድ።

## ለአንድ አረኛ፥ አንድ መንጋ የተጠቀሱ መጻሕፍት፤
## በአማርኛ


ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)ና ስይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ፥ አልቦ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ ሠኔ:21:1982።

ሃይማኖተ አበው፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1967 ዓ.ም.

ሃይማኖት የለያየንን መቃብር አንድ አያደርገንም፥ አልቦ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1987 ዓ.ም.

ሉሌ መልአኩ፥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት (አሳታሚ) አልቦ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1986 ዓ.ም.

የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች፥ አልቦ ደራሲ ወኢ ቤተ: ማኅተም፥ ወዓ.ም

በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች፥ ያስማኅተም ቤት በእየጊዜው የተበተኑ ክታባት፥

1. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እምነት አንቀጾች፥
2. የሐሰትና የእውነት ሃይማኖት
3. የማንን እንስማ?
4. አንድ አምላክ አንድ አካል ብቻ።

መለስ ወጉ፥ ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ፥ Ethiopian Outrearch Ministry, York PA. 17405, United State of America.

መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ፥ እምነት፥ ክፍል አንድ፥ አልቦ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1987

መዝገበ ሃይማኖት፥ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የተዘጋጀ አልቦ ማ/ቤት፥ 1959 ዓ.ም.

መጽሐፈ ቅዳሴ፥ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 1988 ዓ.ም.

መጽሐፈ ቅዳሴ፥ ብርሃንና ሰላም፥ አ.አ. 1964 ዓ.ም.

መጽሐፍ ቅዱስ፥ ብርሃንና ሰላም፥ አዲስ አበባ፥ 1964 ዓ.ም.

ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት፥ አልቦ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1983 ዓ.ም.

ምስጢረ ሥላሴ፥ ብርሃንና ሰላም፥ 1903 ዓ.ም.

ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍት በምላ

ስይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፥ (መጋቤ ብሉይ) የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1982 ዓ.ም.

## አንድ እርኛ፥ አንድ መንጋ የተጠቀሱ መጻሕፍት

ስንክሳር (የእጅ ጽሑፍ)
ቅዱሳት መጻሕፍት
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፥ 4ኛ ዓመት በዓለ ሢመት፥ አልቦ ማ/ቤት፥ ሐምሌ 5 1988 ዓ.ም.
በአየሊቃውንት እጅ የሚገኘው ምዕሳድ።
የሰባልዮሳውያን ክታባት አንድኛና ሁለተኛ
ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፥ (ቄስ)፥
ሀ/ መለኮታዊ ኀይል፥ አዲስ አበባ፥ ሐምሌ 20 1961 ዓ.ም. አልቦ ማ/ቤት
ለ/ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስተማሪያ፥ አልቦ ማ/ቤት ወይም ቦታ፥ 1974።
ሐ/ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፊልጉ፥ አልቦ ማ/ቤት ወኢ ዓ.ም.
መ/ አንድ መንጋ፥ አልቦ ማ/ቤት ወኢ ዓ.ም.
ሠ/ ጥያቄዎቻችሁና መልሶቻችሁ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ፤ 1974 ዓ.ም. አልቦ ማ/ቤት።
ተወልደ ብርሃን መድኅን (መምህር) የክርስትና ትምህርት ሁለተኛ መጽሐፍ ንግድ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ 1985።
ቴዎፍሎስ (አባ፥ ሊቀ ጳጳሳት ዘ ሐረር መዘክሩ አድያሚሃ) መዝሙረ ዳዊት፥ ንባቡ ከነትሩጓሜው፥ አርቲስቲክ ማ/ቤት፥ 1955 ዓ.ም.
ኅሩይ ወልደ ሥላሴ (ብላታ) መጽሐፈ ቅኔ፥ ብርሃንና ሰላም፥ 1901 ዓ.ም.
አየለ ተክለ ሃይማኖት (አባ! ዶክተር) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት፥ አልቦ ማ/ቤት፥ አሥመራ፥ 1951።
አያሌው ታምሩ (አለቃ)
ሀ/ ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ፥ አልቦ ማ/ቤት፥ አ.አ. ሐምሌ 1979 ዓ.ም.
ለ/ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት አልቦ ማ/ቤት 1953 ዓ.ም.
አዲስ ልደት፤ ንግድ ማ/ቤት፥ አዲስ አበባ፥ ጥር 20 1967 ዓ.ም.
አድማሱ ጀምበሬ (መሳእከ ብርሃን) መድሎተ አሚን፥ አልቦ ማ/ቤት፥ ነሐሴ 1:1954 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ 21፡ ደራሲያን፣ አልቦ ማ/ቤት፣ ጥር:1988 January 1995.
ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ሃይማኖተ አበው ዘቀደምት ወዘደኃርት ቁ.1890፤ በዶር ሽብሩ የተሰጠ፣ የኢ.ጥ.ተቋም።
ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፤
በአንድምታ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1943 ዓ.ም.
ዓስማየሁ ሞገስ (ቀደስ) ሁሉም ሁሉን ይወቅ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1987 ዓ.ም.
ዐሥራት ገብር ማርያም፣ ትምህርተ መስኮት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም.
ዐሥራት ገብረ ማርያም፣ ፍኖተ ብርሃን፣ ብርሃንና ሰላም፣ አዲስ አበባ፣ 1986 ዓ.ም.
ድርሳነ ሚካኤል፣ የሠኔ
ጋዜጦች፣ ዜና ቤተ ክርስቲያን መጋቢት 17:1988 ዓ.ም. እና ጦማር መጋቢት 18:1988 ዓ.ም.
የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ማስተማሪያ፤ (ከዐረብኛ ተተርጉሞ) 1948።
ጎርጎርዮስ (አባ ሊቀ ጳጳስ ዘሸዋ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ክፍል፣ አዲስ አበባ 1974።

In Foreing Languages

Adventists Affirm,, Vol.8., No.3 A Publication Affirming Seventh-Day Adventist Beliefs, Year-end 1994.
Adventists Affirm, Vol.802, A Publication Affirming, Seventh-Day Adventist Beliefs, Fall 1994.
Aeschlimann, Carlos H., the Faith of Jesus, Tr. Berry, Vermone. Central American Union.
The Anglican Tradition, Holloway (ED) Mowbray, London & Oxford, 1984.

In Foreign Languages

The Augsburg Confession. A Confession of Faith Presented in Augsburg by Certain Prences and Cities to his Imperial Majesty Charles V in the year 1530.

Ayala Takla Haymanote, Dr. Abba, The Ethiopian Church and its Christological Doctrine. Graphic Printers Addis Ababa, Ethiopia, 1982.

The Book of Common Prayer and Administration of the Sacraments and other Rites and Ceremonies of the Church According to the use of the Church of England, Oxford University Press, No Printing date or Year.

Bulgakov, Sergius, The Oxthodox Church. St. Vladimir's Seminary Press, Crestwood, New youk, 1988.

Orthodoxy and other Christian Confession PP.187-192.

The Virgin and the Saints PP. 116-128.

The Catechism of the Catholic Church. Paulines Publication Africa, Nairobi Kenya, 1994.

Cayr'e, F,A. A Manual of Patrology and History of Theology. Sociology OE Gohn' The Evangelist, Paris, Tournai, Roma, 1936.

Catechism of the Cathloic Church. Paulines Publications Africe, 1994.

Comparative Theology Text Book for Coptic Theological Schools 1948.

Confession of Faith. in a Mennonite Perspective, Herald Press, Waterloo, Ontario, 1996.

Crichton, J.D., Christian Celebration: The Sacraments, (Hapman, London,) 1973.

The Christian Faith Ed. Neuners, J,2nd Edition, the Merciers Press, Dublin and Corks, 1976.

The Christian Faith, in the Doctrinal Documents of the Catholic Church, ED, Neuner, J.E Dupuis, J.S.J. The

Mercier Press, Dublin and Cork, 1976. PP. 135-190.
A Dictionary for Beleivers and Unbeleivers. Progress Publishers, Moscow, 1989.
Elmasry, Iris, H. Introduction to the Coptic Church, Dar Elalam Elarabi.
Emmanuel Abraham, Reminiscences of my life Lunde Balag Oslo, Norway, 1995 PP. 250-1
McGavran, Donald, A. Understanding Church Groth. William B. EER Dman, Publisbing Company, Michigan, 1970.
Gordon, A.J. D.D., The Ministry of the Spirit, Bethany Fellowship. Inc U.S.A. 1964.
IL Grande Libro Della Mitologia Greca E Romana, Michael Stapleton E Elizabeth Servan-Schrei Eer, Armondo Mandatori Editore, S.P.A. Milano 1979.
Hammono, T.C. IN Understanding Be men, A Hadbook of Christian Doctrine, Inter-Varsity Press, London, 1971.
Hardon, John A Modern Catholic Dictionary Robert Hale, London, 1971.
Haynes, Carlyle, Seventh-Day Adventists, Their Work and Teachings, Review and Herald Publication Association, Torma Park, Washington, D.C.1940.
Hermann Pesch, Otto, Breve Catechismo Cattloico, Tr. Sivestri, Geovani, Que reniana, Berscia, 1976.
The Identity of Jesus Christ, Thomas Nelson, INC. Publisher, Printed in United Sates of America, 1982.
Kevin D'Mahoney, M.Afr., The Spirit and the Bride, A Manual Church History, Book One, Unite Printers, Addis Ababa, Ethiopia 1994. PP. 57-130.
Malaty, Todrag. Y, (Fr) St. Mary, In the Orthodox Concept, St. Mark Church, Allen Street Kensington, London, W.S. U.K.

## 1N Foreign Languages


Messale Dell Assemblea Cristiana, Feriale, Ed. Elle Di Ci-Esprienze, 1979.

The Second Volume also of the same Author and Title,

Sheed, P.J. Theology and Sanity, New England Editioo with a oew Preface, 33 Years after, Sheed and Ward, London, 1978.

Spicer, William A. Sigos of Christ's Coming Foretold in Mathew 24.

Review aod Herald Publishing Association, Washington D.C. 1941.

Stephanidou, Basiliou, Professor of Athene University, Church History, from the Beginning to the Present, (in Greek) Astir, Athene 1947. PP. Christogical Dogma. 149-227.

Sykes, Stephen, Unashamed Anglicanism, Darton, Long man, London, 1995.

Tecle Mariam Gezahegne (Priest) The Identity of Jesus Christ, Word Alame press, U.S.A. 1989.

Ruth Tucker, Straoge Gospels, Marshal Pickering, 1991.

The Vienna Dialogue, Five Pro Orient Coosultations with Oriental Orthodoxy, Ferdioand Berger, Austria, (PP. throughout)

Ware, Kallistos, Bishop, the Orthodox Way, St. Vladimir's Seminary Press, Crestwood, Ny,1993 PP.88-117 Incarnation,

Wort und Wahrheit Revue for Religion and Culture Supplementary Issue Nember 5, 1989. PP. 49-50.